★ ሁለት ክንፎች በክፍት ስብሰባ ደቀመዝሙር የማድረግ ዘዴ ★

1. የወንጌል ስብከት

1) የክፍት ስብሰባ ራእይ

ክፍት ስብሰባ ከ3-4 ሰዎችን በአንድ ቡድን በማድረግ አዳድስ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያን የመምጣት ሥራ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ የክፍት ስብሰባ ራእይ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው፡፡

2) ክፍት ስብሰባ 1

ክፍት ስብሰባ ለ12 ሳምንታት በትንሽ ቡድን(3-4 ሰዎች) የሚድረግ የወንጌል ስብከት ነው፡፡ አዳድስ ሰዎችን አግኝቶ ወደ ክፍት ስብሰባ ቦታ (ወደ ቤተክርስቲያን) የማምጣት ሥራ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ስለ ክፍት ስብሰባ የሚገልጥ መጽሐፍ ነው፡፡

3) ክፍት ስብሰባ 2

ክፍት ስብሰባ ጌታ ኢየሱስና ሐዋርያ ጳውሎስ የወንጌል ስብከት ዘዴ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ክፍት ስብሰባን መቀጠል እንደ ክፈት መርዳት ማድረግ መጽሐፍ ነው፡፡

4) ክፍት ስብሰባን የማሳዳደግያ መጽሐፍ ነው

ስለ 12 ሳምንት ክፍት ስብሰባ ዕቅድ ገለፀ ማድረግ፡፡

2. አዲስ ሰውን ወደ ቤተክርስቲያን መምጣትና መመስረት

1) አዲስ ሰውን የአገልግሎት ትምህርት መስጣት

ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጣው ሰዎችን(ቤተሰብን) በቤተክርስቲያን በጽናት እንድኖሩ መርዳት

2) ስለ አዲስ ቤተሰብ አገልግሎት የሚገልጥ መጽሐፍ ነው

ይህ መጽሐፍ ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጣውን አዲስ ሰው በጽናት እንዲኖሩ ማስተማሪያ ዘዴን የሚገልጥ መጽሐፍ ነው፡፡

3. ልምምድ ማድረግ

1) *ሥጋና መንፈስን የሚፈውስ ህብረት*

ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ፀጋ መቀበል ብቻ ሳይሆን የልብን ሥቃይ፡ ኃጢአትና ኃይለኛ ችግሮችን በቃሉ ይመረምረል የቃል የመንፈስ ቅዱስን የማዳን ኃይል የሚያሳይ መጽሐፍ ነው፡፡

2) የልምምድ ደስታ

ይህ መጽሐፍ እምናታችን እንድታድግ የሚረዳ መጽሐፍ ነው፡፡

3) የልምምድ ደስታ የሚገለጥ መጽሐፍ

ይህ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያኖችን በአንደኛ እምነት እንዲለወጥ መርዳት ዝርዝር ዘዴን የሚገልጥ መጽሐፍ ነው፡፡

4) በአንተ የፀጋ ስጦታ መስራት

ክርስቲያኖችን በፀጋ ስጦታ ለጌታ ሥራ የሚያዘጋጅ መጽሐፍ ነው፡፡

5) ስለ ፀጋ ስጦታ የሚገልጥ ነገር ግን የፀጋ ስጠታቸውን ለይቶ የማይጠቀሙ ብቻ ቤተ ክርስቲያን አሉ **መጽሐፍ ነው**
ጤናማ ቤተ ክርስቲያን የራሱን የፀጋ ስጦታ አወቆ ይጠቀማል:: ስለ ፀጋ ስጦታ አገልግሎት መጽሐፍ ነው::

4. የደቀ መዝሙር ማሰልጠን ደረጃ 1

1) የደቀ መዝሙር ሕይወት

የኢሱስ ደቀ መዝሙር ጠርቶ የታዘዥነትን የተማኝነት መለማመጅ መጽሐፍ ነው፡፡ ክፍት ስብሰባ የመረ ደቀ መዝሙር ደረጃ 1 የልምምድ መጽሐፍ ነው፡፡

2) የደቀ መዝሙርን ሕይወት የሚገልጥ መጽሐፍ

ታማኝ ሰው እንደወለድ ብቻ ሳይሆን እንዲያድግ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በደቀ መዝሙር ጠርቶ ማወቅና መታዘዝ መንፈስ ቅዱስ በዛ የደቀ መዝሙር ሕይወት እንደኖር መረዳትና የደቀ መዝሙር ሕይወት ማድረግ መገለጥ መጽሐፍ ነው፡፡

3) ስለ ሌሎች ሰዎች መፀልይ

ስለ ሌሎች ሰዎች እንዲመስክሩና እንዲፀልይ የሚረዳ መጽሐፍ ነው፡፡

4) ስለ ሌሎች ሰዎች መፀልይ

ጤናማ ቤተክርስቲያን የፀሎት ማዕከል ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ሰዎች ስለ ፀሎት መለኸ እግዚአብሔር የሚያለማምድ መጽሐፍ ነው፡፡

5. የጭፍራ ማሰልጠን ደረጃ 2

1) የጭፍራ ሕይወት 1

ታማኝ የኢየሱስ ጭፍራ ማሰልጠን ቀደ መዝሙር ዩኒቨርሲቲ 2 ደረጃ ልምምድ መጽሐፍ ነው፡፡

2) የጭፍራ ሕይወት 2

በመንፈስ ቅዱስ መርናት ሌሎችን እንደረዳ ማሰልጠን ደረጃ 2 ልምምድ መጽሐፍ ነው::

3) የአበለትን ሕይወት የሚገልጥ መጽሐፍ

የሕይወት ምስክርነት በማስፈል ምሰልጣን የሚያስችል መጽሐፍ ነው፡፡

4) የቡድን መሪ

የእግዚአብሔር ጥሪ ሸክም ሳይሆን በረከት ነው፡፡ የቡድኑ መሪ ጥሪውን እንዲያወቅና እንዲታዘዝ የሚረዳ መጽሐፍ ነው፡፡

6 ሌሎችን እንደገና ደቀ መዝሙር ማድረግ ደረጃ 3

1) ሌሎችን እንደገና ደቀ መዝሙር የማድረግ ሕይወት 1

"አህዛብን ሁሉ ደቀ መዝሙር አድጋቸው" ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ የሰጠውን ትዕዛዝ በቆረጥናትና በዓለም ይዞ ሌሎችን ደቀ መዝሙር ማድረግያ መጽሐፍ ነው፡፡

2) ሌሎችን እንደገና ደቀ መዝሙር የማድረግ ሕይወት 2

የቡድኑ እወናተኛ ፍሬ ሌላ ቡድንን እንደገና ማፍረት ስችል ነው፡፡ ለአድሱ ቡድን ሌላ መሪ መሰጣት።
ይህ መጽሐፍ ደቀ መዝሙር ደረጃ 3 መጽሐፍ ነው፡፡

3) ሌሎችን እንደገና ደቀ መዝሙር የማድረግ ሕይወት መገለጥ መጽሐፍ

እንደ አዲስ ኪዳን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ሥራና ሕይወት እንደኖር በማሰልጠን እንደገና ሌሎችን ደቀ መዝሙር የማድረግ ሕይወት መግለጥ መጽሐፍ ነው፡፡

4) የሚስዮን ራእይ

የሚስዮን ራእይ ለሰዎች የወንጌልን ስብከው ወደ ቤተክርስቲያን በማምጠት እንደገና ሌሎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ ነው፡፡ ወደ ዓለም ሁሉ ደቀ መዝሙርን እንደላከ ነው፡፡

5) ስለ የሚስዮን ራእይ የሚገልጥ መጽሐፍ

በዓለም የሚስዮነውያንን አስፈላጊነጉ፤ ተልዕኮና ዕቅድ የሚገልጥ እንዲሁም ራእያቸውን የሚያስተለስፉበት ቀለል ዘዴ የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

ባለ ሁለት ክንፍ የደቀመዛሙር ስልጠና 2
(Two Wings Disciple Training 2)

★ መጽሐፍ አንድ

የመፅሐፍ መውጫ

መግለጫ . . . . . ገጽ
1. የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ 1 - እኛ ቤተ ክርስቲያን ደስታ ቦታ ነው……. 4
2. የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ 2 - እኛ ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ቦታ ነው……. 6
3. የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ 3 - እኛ ቤተክርስቲያን መክበር የጌታ ቤተክርስቲያን ነው……. 8
4. የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ 4 - እኛ ቤተክርስቲያን በባለ ሁለት ክንፍ ቤተክርስቲያን ነው……. 9

★ መጽሐፍ ሁለት

1. ምዕራፍ አንድ - ዕድልን ለመቀየር ምቹ ጊዜ …….. 10
2. ምዕራፍ ሁለት - ኃጢአትን መስቀል …….. 14
3. ምዕራፍ ሶስት - ጠንካራ ግንብ መደምሰስ …….. 21
4. ምዕራፍ አራት - የመንፈስ ቅዱስ ቅባት መቀበል …….. 25

★ መጽሐፍ ሶስት

1. ምዕራፍ አንድ - እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት የደስታ ስሜትን መግለፅ …….. 38
2. ምዕራፍ ሁለት - የደህንና ፅኑ እምነት …….. 40
3. ምዕራፍ ሶስት - ኃጢአትን ለማስወገድ ፅኑ እምነት …….. 45
4. ምዕራፍ አራት - የፀሎት ምላሽ ፅኑ እምነት …….. 49
5. ምዕራፍ አምስት - ምሪትን በመቀበል የማሸነፍ ፅኑ እምነት …….. 53
6. ምዕራፍ ስድስት - መንፈስ ቅዱስ የተትረፈረፈ ክርስቲያኖች …….. 58
7. ምዕራፍ ሰባት - እምነታችን እንደ መኪና ቸርክ አይነት ነው …….. 61
8. ምዕራፍ ስምንት - የጥልቅ ሀሳብ (የጥሞና ጊዜ) …….. 70
9. ምዕራፍ ዘጠኝ - ክፍት ስብስባ ማለት ምን ማለት ነው? …….. 76
10. ምዕራፍ አሥር - እግዚአብሔርን ዕቅድ የምትሠራ ቤተክርስቲያን …….. 81

★ መጽሐፍ አራት

1. ምዕራፍ አንድ - የንጉሥ ካህን ነኝ …….. 84
2. ምዕራፍ ሁለት - የሥራ ሰው ታርክ …….. 86
3. ምዕራፍ ሦስት - የሚያሳስብ ነገር ማግኘት …….. 88
4. ምዕራፍ አራት - ሥጦታ መቀበል …….. 90
5. ምዕራፍ አምስት- ፀባይን መቀበል …….. 110
6. ምዕራፍ ስድስት- የሥራ ሰው የሕይወት ታርክ እንዴት እንደሚጻፍ …….. 120
7. ምዕራፍ ሰባት- ፀጋ ሥጦታ ማስተካከልና ማጽናናት …….. 126

★ መጽሐፍ መግለጫ …….. 128



የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ

የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ 1

1. እኛ ቤተ ክርስቲያን ደስታ ቦታ ነው፡፡

ማንኛውም ሰው በዚህ ምድር ሲኖር ደስታን ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ያንን ፈልጎ ሳያገኙ በመከራ፣ በህመም፣ በቤተሰብ ችግር፣ በጤና ችግር፣ በኢኮኖሚ ችግር፣ ስለወደፊት ኑሮ በማሰብ ችግርና በአዕምሮ ህመም ችግር ይወድቃሉ፡፡ ከዚያም በኋላ ጊዜያዊ ደስታ ሊያገኙ ይችላሉ፤ ነገር ግን ዘላቂ የሆነ ደስታን አያገኙም፡፡ ለምን አያገኙም? እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ትተው ኃጢአት ስለሚሠሩ ነው፡፡

1. ሰው እግዚአብሔርን ትተው ኃጢአት ሠርተው ከወደቀ በኋላ ምን እንደሚሰራ ተናገር፡፡

1) እግዚአብሔር ሰውን እንደ ራሱ ምስል አድርጎ ሲፈጥር እንዲደሰቱና በሕይወት እንዲኖሩ ሁሉንም ነገር ሰጠ፡(ዘፍ.1÷27-28)
2) ነገር ግን ሰው ኃጢአት ከሰራ በኋላ እግዚአብሔርን ተወው። (ዘፍ.3÷1-5)
3) የእግዚአብሔርን ክብር ማጣት። (ሮሜ.3÷23)
4) በሰው ሕይወት ላይ ችግሮችና ህመሞች ቀጠሉ፡፡ ወንድ በድካሙ ምግብ እንደምበላና ሴት እንደምትወልድ መከራ መጣ። (ዘፍ.3÷16-19)

2. ሰው እግዚአብሔርን ሲተው በህመምና በሀዘን ይኖራል::

1) እውነተኛ ሰላምና ዕረፍት ስለሌለ። (ዮሐ.10÷10)
2) በባዶነትና በትርጉም አልባ ሕይወት ስለሚኖር (ማቴ.11÷28)
3) የአዕምሮ ህመምተኛና የስጋ ደዌ ህመምተኛ በመሆን ይኖራል፡፡(ማቴ.9÷36)
4) በተረገመ አካባቢ ይኖራል፡፡ ይህ ማለት መከራና አደጋ ገንዘብ ማጣት ይከሰታል ማለት ነው፡፡(ማቴ.8÷1-8)
5) በሞት ፍርሃት ውስጥ ይኖራል። (ዕብ.9÷27)
6) የዚህ ሁሉ ምክንያት መንፈሳዊውን ነገር አላማወቀ ነው፡፡ (ኤፌ.3÷1)

3. እግዚአብሔርን የሚተው ሰዎች ለህመማቸውና ለስቃያቸው መፍትሄ የሚሰጥ ጠንቃይና ሌሎችን ጣኦታት ይፈልጋሉ የዚህ ነገር ውጤት ምንድን ነው?

1) ሠርቶ ጥቅም አልባ ይሆናሉ፡፡ (ማቴ.12÷43-44)
2) ለራሳቸው መፍተሄ ያጣሉ፡፡ (ማቴ. 12÷28-29)
3) በሃይማኖታቸው ደስተኞ አይሆኑም፡፡ (ማቴ.11÷28)
4) ተጨመረ ህመም በራሳቸው ላይ ይጨምራሉ፡፡ ሰይጣንን ማገልገል ህመም መጨመር እንጂ ሌላ ትርፍ የለም፡፡(ማቴ.12÷45 45)
5) እግዚአብሔርን እስካላገኙ ድረስ እውነተኛ ደስታ የላቸውም፡፡ (ኢሳይያስ. 44÷3-4)

4. ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መፍትሄ ይሰጣል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው?

1) ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ እውነተኛ መንገድ ነው፡፡ (ዮሐ.14÷6)
2) ከችግሮች ሁሉ ነፃ የሚያወጣ ስለሆነ ለችግሮችን ሁሉ መፍትሔ ይሰጣል:: (ሐዋ.10÷38)
3) ኢየሱስ ወደ እኛ የመጣበት ዋና ምክንያት የተትረፈረፈ ሕይወትንና ደስታን ለመስጠት ነው፡፡ (ዮሐ.10÷10)
4) ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝና ጌታ አድርገን በልባችን እንቀበለዋለን። (ዮሐ.1÷12-13)
5) አሁን አንተ ዛሬን ለክብሩ ለመኖር ወሰን። (ምሳሌ 27፡1)

★ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚቀበል ሰው ፀሎት፡-

ውድ እግዚአብሔር ሆይ፡ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን አሁን ወደ ልቤ እንድገባ ፈቅጀአለሁ፤ የእኔን ኃጢአት ሁሉ በመስቀል ላይ ባፈሰሰከው በደምህ በኩል እጠብልኝ ኃጢያትንም ይቅር በል፤ የዘላለምን ህይወት ስጠኝ፤ አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንተን የሕይወቴ ጌታና አዳኝ አድርገ ተቀብየዋለሁ፤ እግዚአብሔር አባቴ ሁንልኝ እኔ ያንተ ልጅ እሆናለሁ፤አሁን እኔን ስላዳንክ፡

ከኃጢአቴም ስላነፃኸኝ ስሜንም በሕይት መጻሐፍ ስለጻፍክልኝ አመሰግናለሁ፡፡ ከአሁን ጀምሮ ካንተ ጋር ለዘላለም አኑረኝ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን፡፡

5. ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበልህ በኃላ ልዩ ስልጣን ምንድን ነው?

1) የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፡፡ አሁን እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፡፡(ዮሐ.1÷12)
2) ኃጢአታችንና እርግማናችን ወዲያውኑ ተወግደዋል፤ የመጀመሪያው ኃጢአት፣የአሁኑና የወደፊቱ ሁሉም ተወግደዋል፡፡(ሮሜ.8÷2)

በክርስቶስ ኢየሱስ የሚገኘውን ሕይወት የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶኛል፡፡

3) ስንፀልይ መላሽ እንቀበላለን፡፡
ከአሁን ጀምሮ በኢየሱስ ስም ብንፀልይ እግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣል፡፡(ዮሐ.16÷24)
4) ኢየሱስ ክርስቶስን በማመናችን ሰላም፣ ደስታና ዕረፍት ይበዛልናል፡፡ (ማቴ.11÷28)
5) የኢየሱስ የስሙ ሥልጣን በየቀኑ አሸናፊዎች ያደርገናል፡፡(ሐዋ.3÷6-8)

6. ኢየሱስን ያመነ ሰው ምን ያድርግ?

1) በየእሑድ ቀን ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት::
2) በየቀን ወደ እግዚአብሔር መፀለይ፡፡
3) በየቀን የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ፡፡
4) ክፍት ስብሰባ ማሳለፍ፡፡

✿ በእኛ ቤተክርስቲያን ጥሩ ሶስት ሰዎች ማስተዋወቅ፡፡

1	
2	
3	

የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ 2

2. የእኛ ቤተክርስቲያን ጤናማ ቦታ ነው።

1. እኛ ቤተክርስቲያንን ማስተዋወቅ::

ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያኖችን እንደዚህ እንነግራለን፡፡

1) እግዚአብሔርን ሰዎች እውነት መውደድ ያለበት ቤተክርስቲያን ነው፡፡
2) ለጌታ ኢየሱስና ለመጋቢ(ለመሪ) የሚታዘዝ ቤተክርስቲያን ነው፡
3) የጌታ ኢየሱስን መከተል ትምህርትና ልምምድ ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡

4) ተልዕኮና ራዕይ ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡
5) አገልግሎት ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡
6) ንጹሕ ልብ ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡
7) እርግጠኛ ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡
8) የጌታ ኢየሱስ ሥራ ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡
9) መዝሙር ሁልጊዜ ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡
10) ማመስገን ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡

2. እኛ መጋቢንና መሪን ማስተዋወቅ፡፡

የቤተ ክርስቲያናችን መጋቢ (መሪ)ን እንደዚህ እንነግራለን፡፡
1) ጌታ ኢየሱስን የሚወድ ሰው ነው፡፡
2) በሕይወት ውስጥ ጥሩ ሥራን የሚያደርግ ሰው ነው፡፡
3) ሰዎች ሁሉን እንደጌታ ኢየሱስ የሚወድ ሰው ነው፡፡
4) ቤተክርስቲያንን የሚያማክርና መፍትሔን የሚሰጥ ሰው ነው፡፡
5) እስክጨርስ ድረስ እምነትና ተዕግስተኛ ሰው ነው፡፡
6) እንደ ቃል የሚኖር ሰው ነው፡፡
7) የጌታ ኢየሱስ ማረጋገጥ ግብና ራዕይ ያለው ሰው ነው፡፡
8) ሥልጣንና ጥበብ ያለው ሰው ነው፡፡
9) ሰፊ ልብ ያለው ሰው ነው፡፡
10) ቤተክርስቲያን እንዳደግ አይቶ የሚደሰት ሰው ነው፡፡

3. የእኛ ቤተክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ ማስተዋወቅ፡፡

4. የእኛ ክፍት ስብሰባ ማስተዋወቅ፡፡

ክፍት ስብሰባ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትን፤ ሥልጣንን፤ ግብን መለማመድ፤ ወንጌል ስብከት፤ የማድረግ ልምምድ፤ መመስረት፤ ማሰልጠን በብዛት የተትረፈረፈ ስብሰባ ነው፡፡

5. የአግዚአብሔር መደስቻ ቤተክርስቲያን፡፡

መዝሙር ምዕራፍ 1 ላይ እኛን ጥሩ ቦታ ተክል፡፡ እኛ ብዙ ፍሬንና በረከት እንዲኖር ያደርገናል፡፡

1) በቤተክርስቲያን መካከል ሕይወትን መኖር ያስፈልጋል፡፡ሀዘን እና ችግር ሲደርስ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄደውን ሰው እግዚአብሔር ደስታና በረከት ይሰጣል፡፡
ማቴ 6÷33 "ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅን ፈልጉ እነዚህ ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡ ብሎ ይናገራል፡፡ ቤተክርስቲያን መካከል ሕይወት ማለት የእግዚአብሔር መንግሥትና ጽድቁ ነው፡፡ እነዚህን በሰራን ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ ሁሉን ይሰጣል፡፡

2) በእሑድ ቀን አምልኮ ጊዜ መምጣት ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ዮሐ 4÷24 ላይ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባቸዋል፡፡ ብሎ ይናገራል፡፡
በአምልኮ በኩል እኛ ከእግዚአብሔር ሥልጣንን እንቀበላለን፡፡ የአምልኮ መከናወን ማለት የሕይወት መከናወን ነው፡፡
3) ፀሎትም ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
ፀሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ንግግር ነው፡፡ የምንፈልገውን መቀበያ መንገድ ነው፡፡ ፀሎት ማለት የሕይወታችን ችግሮችን መክፈቻ ቁልፍ ነው፡፡
4) የእግዚአብሔር ቃል ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ ቃል (በመንፈስ ቅዱስ) ማለት የመንፈስ እንጀራ ነው፡፡ የመንፈስን እንጀራ (ቃል) በየቀን ስንበላ እምነታችን ጤናማ እናደርጋለን፡፡
5) ንብረትን ለቤተክርስቲያን መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ንብረትን(ገንዘብን) ለእግዚአብሔር ለንሰጥ የሕይወታችን ጌታ መሆንን እንደተስማማ ነው፡፡ ንብረትን ስንሰጥ እግዚአብሔር ለእኛ ብዙ በረከትን ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ 30 እጥፍ÷ 60 እጥፍ÷ 100 እጥፍ በረከትን ይሰጣል፡፡ (ማርቆስ 4÷20)

6. ማስተዋወቅ ….ወዘተ

1) በቤተክርስቲያን ውስጥ ችግር ባለ ጊዜ ለመጋቢ ለመሪና አገልጋይ ሰው ይነገራል፡፡

2) የመጋቢው ስልክ ቁጥር፡ ስም:

የወንጌላዊ ስልክ ቁጥር፡ ስም:

መሪ 1 ስልክ ቁጥር፡ ስም:

መሪ 2 ስልክ ቁጥር፡ ስም:

በሃዘንና በደስታ ያለው ጊዜ ለመጋቢ (ለወንጌላዊ) ና ለመሪ ይነገራል፡፡
በእኛ ቤተክርስቲያን አንተን (አንቺን) ያስተዋውቃሉ፡፡

✿ በእኛ ቤተክርስቲያን ጥሩ ሶስት ሰዎች ማስተዋወቅ፡፡

1	
2	
3	

የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ 3

3. የእኛ ቤተክርስቲያን መክበር የጌታ መክበር ነው፡፡

መጸሐፍ ቅዱስ የቤተክርስቲያን መሪ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ይነግረናል። (ኤፌ 5÷23) ኢየሱስ ሕይወት እስኪሰጥ ድረስ ቤተክርስቲያንን መውደድ ይነገረናል፡፡ ስለዚህ እኛ ደግሞ ጌታን እንደምንወድድ ቤተክርስቲያን እኛም መውደድ ያስፈልጋናል፡፡

1. ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚመጣበት ቅዱስ ቦታ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን በድንኳን የእግዚአብሔር መምጣት አለ፡፡ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ከሰራ በኋላ በቤተ መቅደስ እግዚአብሔር መገናኘት ቻሉ፡፡ አሁን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቦታ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ክብርንና ፀጋን መለማመጃ ቦታ ነው፡፡

1) ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሚያደርግበት ቦታ ነው፡፡
2) ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት ሰማይ ምስል ነው
3) ቤተ ክርስቲያን የተመረጡ የእግዚአብሔር ሰዎች መሰብሰቢያ ነው፡፡
4) በቤተክርስቲያን የመንግሥት ሰማይ ቁልፍ አለ፡፡
5) የቤተክርስቲያኖች በረከት ቤተ ክርስቲያን በኩል ይሆናል፡፡

2. ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን አምልኮ ቦታ ነው፡፡

1) አምልኮ ማለት መልካምን እንደ ዋና መስጠት ነው፡፡
አንተ አካልን፤ ሰዓትንና ንብረትን መስጠት ማለት ነው፡፡
2) አምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሚያደርግበት ቦታ ነው፡፡
ምሳሌ፡- እሁድ ቀን አምልኮና ክፍት ስብሰባ አለ፡፡

3. እግዚአብሔር እውነተኛ የአምልኮ ለውን ማግኘት ይፈልጋል፡፡

በአምልኮ መከናወን ሰው ታላቅ በረከትን ይኖራል፡፡

1) አምልኮ 10 ደቂቃ በፊት መምጣት መፀለይ መዘጋጀት ያስፈልል፡፡
2) ንፁህ ልብስ መልበስ አለማውራትና ትኩረትን ለአምልኮ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
3) ስልክ መዝጋት ያስፈልጋል፡፡
4) ልብና አይምሮ መሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡

4. እግዚአብሔር በእሑድ ቀን ጊዜ አምልኮን መቅዱስ መጠበቅ አዘዘ፡፡

1) እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ከፈጠረ በኋላ አረፈ፡፡
2) እሑድ ቀን የጌታ እግዚአብሔር ነው::
3) ሐዋርያት በአዲስ ኪዳን ጊዜ ጀምሮ እሑድ ቀንን በጌታ ቀን ይጠብቃል፡፡
   (ሐዋ 20÷7 1ቆሮ 16÷2. ራእይ 1÷10)
4) በእሑድ ቀን በጌታ ውስጥ የመቅደስ ዕረፍት ቀን ነው፡፡

5. እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የሚሰጥበት መንገድ አለ፡፡

1) ከመጋቢ ወንጌላውያን ጋር ህብረት ማድረግ መጋቢ (ወንጌላዊ) ማለት የእግዚአብሔርን ተልዕኮ በውስጡ ይዞ የሚፈጽም ለእኛ የተላከ ቅዱስ ሰው ነው፡፡
   ቤተክርስቲያኖች ከመጋቢ (ወንጌላዊ) ስብሰባ በሚደረግበት ጊዜ እንደ ጌታ ማክበርና መታዘዝ ያስፈልጋል፡፡
2) ከክፍል መሪ ጋር ሕብረት ክፍል መሪና መሪ ጌታ ማድረግ ለእኛ እንደ መንፈስ አባት ነው፡፡ ችግር በሚያጋጥም ጊዜ አብሮ በመነጋገርና መፀለይ ያስፈልጋል
3) ከቤተክርስቲያኖች ጋር እብረት በሚደረግበትና ስብሰባ በሚደረግበት ጊዜ "እርስ በርሳችሁ በወንድማማችነት ፍቅር ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ለመከባበርም ተሽቀዳደሙ፤ (ሮሜ 12÷10)" ይናገራል፡፡ እርስ በርሳችሁ መዋደድ በቃል ውስጥ ህብረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እርስ በርሳችሁ መረዳዳት በቃል ክርክር እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ የተለየ ገንዘብን መስጠትና መቀበል እንዳይኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

✿ በእኛ ቤተክርስቲያን ጥሩ ሶስት ሰዎች ማስተዋወቅ፡፡

1	
2	
3	

የአዲስ ቤተሰብ ደስታ ማስተዋወቅ 4

4. እኛ ቤተክርስቲያን በባለ ሁለት ክንፍ ቤተክርስቲያን ነው፡፡

የእኛ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ቅርጽ ዓለም ራዕይ የዞ በሁለት ክንፍ የምትበር ቤተክርስቲያን ነው፡፡
1ኛ ክንፍ ታላቅ አምልኮ ነው፡፡ እሑድ ቀን የአምልኮ ጊዜ ነው
2ኛ ክንፍ ትንሽ አምልኮ ነው፡፡ በትንሽ ቡድን 3-4 ሰዎች ስብሰባ ነው

1. የእኛ ቤተክርስቲያን ራዕይ

የእኛ ቤተክርስቲያን ሰዎችን በዓለም ላይ የወንጌልን መልዕክተኛ (ሚስዮናዊ ሰው) ይልካል፡፡
የእኛ ቤተክርስቲያን የክፍት ስብሰባ መሪ ለማድረግ ወደ ኢትዮጲያ ሌላ መሪ ይልካል፡፡

2. የእኛ ቤተክርስቲያን ተልዕኮ

1) ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ደቀ መዝሙር ለማድረግ ሚስዮናዊ ሰው ይልካል፡፡ የክፍት ስብሰባ መሪ ሰዎችን ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ ይልካል፡፡
2) የሳምንቱ ዋና ዋና ነገሮች፣
   ① የወንጌል ስብከት
   ② ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አምልኮ
   ③ ጥሩ ሕብረት
   ④ ክፍት ቤተሰብ ስብሰባ
   ⑤ የመንፈስ ቅዱስ ፍቅር
   ⑥ ሰዎችን መሪ የማድረግ ልምምድ
   ⑦ የፀጋ ሥጦታ አተኰረ ሥራ

⑧ በዓለም ላይ ሚስዮናዊ ሰውን ይልካል፡፡

3. በሁለት ክንፍ የምትበር ቤተ ክርስቲያን

1) 1ኛ ታላቅ ክንፍ በእሁድ ቀን፤ አምልኮ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ በዓል ነው፡፡ እኛ በአምልኮ በኩል የእግዚአብሔር ሥልጣንንና ኀይልን እንቀበላለን፡፡ አምልኮ መከናወን ማለት የሕይወት መከናወን ነው፡፡
2) 2ኛ ትንሽ ክንፍ ክፍል ቤተሰብ ስብሰባ ክፍል ቤተሰብ ስብሰባ ማለት በኢየሱስ ሕይወት አንድ መሆን መንፈስ ቤተሰብ ስብሰባ ነው፡፡ ይህም በቦታ ውስጥ ጥሩ ህብረት ፍቅር አለ፡፡ እኛ የእግዚአብሔር መንግሥት አንድ ቤተሰብ ነው፡፡ ቤተሰብ ስብሰባ መምጣት እርስ በርሳችሁ መዋደድ ያስፈልጋል፡፡ ወደ ኢየሱስ ውስጥ አንድ ቤተሰብ ሲመጣ ዓለምን ማሸነፍ ይቻላል፡፡ እኛ በኢየሱስ ፍቅር ዓለምን ማሸነፍ እንችላለን፡፡ ክፍት ቤተሰብ ስብሰባ መምጣት ማለት የመንፈስ ሕይወት ጀምሪ ማለት ነው፡፡

4. ለእኛ ማደግ ግዴታና ልዩ መብት ነው፡፡

ሕይወት ከቶ ማደግ ያስፈልጋል፡፡ ማሰሀሳቡ፤ አንተ ልጅ ከወለድክ በኋላ የማያደወግ ከሆነ ልብህ ምን የሆናል? የእግዚአብሔር ልብ ደግሞ እንዲህ አይነት ነው፡፡ በአንተ ልብ ውስጥ ሕይወት አለ፡፡ ሕይወትህ ከቶ ማደግ ያስፈልጋል፡፡ ጥሩ ሲያድግ በረከትን መኖር ይችላል፡፡ማደግ ማለት በልምምድና በስልጠና ይቻላል፡፡ ልምምድ ክፍል ሄዶ በእምነት ማደግ በረከትን ይሆናል፡፡

5. እንዴት በልምምድ ትምህርት ውስጥ መግባት ይቻላል?

1) ቤተክርስቲያን በማመልከቻ ወረቀት መጻፍ ለመጋቢና ለመሪ መስጠት፡፡
2) ልምምድ ማመልከቻ ወረቀት ዝርዝር መጻፍ ለመጋቢና መሪ ይሰጣል፡፡
3) መጋቢ መሪ ለአንተ ልምምድ ክፍል ቦታንና ሰዓትን ይነገራል፡፡
4) ልምምድ ክፍል 12 ሳምንት አለ፡፡ ከልምምድ ክፍል በፊት ሥጋና መንፈስ መፈወስ ህብረት አለ፡፡
5) ሥጋና መንፈስ መፈወስ ህብረት ከልምምድ በፊት ልዩ ትምህርት ነው፡፡
6) ሥጋና መንፈስ መፈወስ ህብረት ጊዜ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ልብን ይፈውሳል፡፡ በአንተ ውስጥ ያለውን ጠንካራ ስፍራ አፍርሶ የእግዚአብሔርን ፍቅር ልምምድ ታደርጋለህ፡፡

ባለ ሁለት ክንፍ የደቀመዛሙር ስልጠና 3
(Two Wings Disciple Training 3)



ሥጋንና መንፈስን የሚፈውስ ህብረት

ማውጫ **ገፅ**

1. ምዕራፍ አንድ - ዕድልን ለመቀየር ምቹ ጊዜ ……
2. ምዕራፍ ሁለት - ኃጢአትን መስቀል ……
3. ምዕራፍ ሶስት - ጠንካራ ግንብ መደምሰስ ……
4. ምዕራፍ አራት - የመንፈስ ቅዱስ ቅባት መቀበል ……

መቅድም

እምነት በጣም የሚታዘዘው ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ ለፀኑት ሰዎች ነው፡፡ሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን አሉ፡፡ 1ኛ ዓይነት በክርስትና እምነት እየኖሩ ነገር ግን በዓለም ውስጥ ኃጢአት የሚሠሩ ሰዎች፣ 2ኛ ዓይነት በደንብ የተሰጡ የሆኑ ነገር ግን እምነታቸው ያላደጉ ሰዎች ናቸው፡፡
ለምንድን ነው የተሰጡ ሆኖ ያላደጉት?

ያለማደጋቸው ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስን እያመኑ ነገር ግን በልባቸው ውስጥ ካለው ከክፉ ነገር ስላልተፈወሱ ነው፡፡ በልባቸው ክፉ ነገር ሲኖር በቤተሰብ ሕይወት ችግሮች ይኖራሉ፡፡ በአካባቢ ላሉት ሰዎችም ጉዳት ይሆናል፤ በተጨማሪም የበረከት በሮች ይዘጋል፡፡ ለተከታታይ ክፉ ሥራ በሕይወታቸው ይከሰታል፡፡

ከዚህ ሁኔታ የሚያወጣው ሥጋንና መንፈስን የሚፈውስ ህብረት መከታተልና የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፈውስን መቀበል ነው፡፡ ይህ ህብረት ከክፉ ነገር ነፃ የሚወጡበት፣የማያዩ የሚያዩበት፤ በሰይጣን እስራት ውስጥ ያሉ ሰዎች ነፃ የሚወጡበት ህብረት ነው፡፡ እግዚአብሔር አብና ጌታ ኢየሱስ አሁን እኛን ለመገናኘት ይፈልጋል፡፡ በዚህ ህብረት የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ህይወት ተገልጦ ሕይወታችንን ቀይሮ አዲስ ሰው እንዲያደርግ ራሳችንን ሊንፈቅድ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ አንድ

1. ዕድልን ለመቀየር ምቹ ጊዜ (ሉቃ.19÷1-10)

● ሉቃ.19÷1-10

1. ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ ከተማ ገብቶ በዚያ በኩል አልፎ እየሄደ ነበር፡፡
2. ስሙ ዘኬዎስ የተባለ አንድ ሰው በዚያ ነበረ፤ዋና ቀረጥ ሰብሳቢና ሀብታም ነበረ፡፡
3. ዘኬዎስ ኢየሱስ የቱ እንደ ሆነ ለማየት ይፈልግ ነበር፣ ነገር ግን ቁመቱ አጭር በመሆኑ ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ሊያየው አልቻለም፡፡
4. ኢየሱስ በዚያ በኩል ያልፍ ስለ ነበር ዘኬዎስ እርሱን ለማየት ብሎ ከሕዝቡ ፊት ቀድሞ ሮጠና በአንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ፡፡
5. ኢየሱስም ወደዚያ ስፍራ በደረሰ ጊዜ ቀና ብሎ ተመለከተና ዘኬዎስን፣ "ዘኬዎስ ሆይ! ዛሬ በአንተ ቤት መዋል ይገባኛልና ፈጥነህ ከዛፉ ውረድ!" አለው፡፡
6. ዘኬዎስም ቶሎ ብሎ ወረደና፣ በደስታ ኢየሱስን በቤቱ ተቀበለው፡፡
7. ይህን የተመለከቱ ሰዎች ሁሉ፣ "ይህ ሰው ወደ ኃጢአተኛ ቤት ሊጋበዝ ገባ!" ብለው በኢየሱስ ላይ አጕረመረሙ፡፡
8. ዘኬዎስ ቆሞ ጌታ ኢየሱስን እንዲህ አለው፣ "ጌታ ሆይ! እነሆ፣ ካለኝ ሀብት ሁሉ እኩሌታውን ለድኾች እሰጣለሁ፣ በማታለል ከሰው ላይ የወሰድኩትም ገንዘብ ቢኖር፣ አራት እጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ፡፡"
9. ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "ይህ ሰው ደግሞ የአብርሃም ዘር ነውና ዛሬ መዳን ለዚህ ቤት መጥቶአል፤
10. የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው፡፡"

ምቹ ጊዜ ምንድን ነው?

ይህ ሀብረት 98% የሰውን ዕድል ይቀይራል፡፡

1. **አሁን ለአንተ ምቹ ጊዜ መጣ፡፡ ይህን ምቹ ጊዜ ልትጠቅም ይገባሃል፡፡**
   1) ለሁሉም ሰዎች ምቹ ጊዜ አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ሕይወት ልምምድ ስላልሆነ አሁን ምቹ ጊዜህን ተጠቀም፡፡
   2) ምቹ ጊዜ እንደ ነፋስ ይሄዳል፡፡ ምቹ ጊዜ በጊዜ የተወሰነ ስለሆነ በሰዓት ይመጣል፡፡
   3) ይህን ምቹ ጊዜ ለመጠቀም "እኔ እጠቀማለሁ" በል፡፡
   4) ምቹ ጊዜን ተጠቀም፤ በሁሉም ምቹ ጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ አለው፡፡ ዛሬ ለእኔ ሕይወት ለሁላችንም ሕይወት መፍትሔ ልንቀበል ያስፈልጋል፡፡

2. **አንድ ባለጠጋ ወጣት ሐዘንን ወሰነ፡፡ (ማቴ.19÷21-22)**
   1) አንድ ባለጠጋ የሆነ ወጣት ወደ ኢየሱስ መጥቶ አንድ ጥያቄ ጠየቀ፡፡ ለባለጠጋው ጥያቄውን የሚጠይቅበት ጊዜ ምቹ ጊዜ ነበር፡፡ነገር ግን ባለጠጋው ወጣት የሀብቱን ብዛት አይቶ ኢየሱስ ክርስቶስን አልተከተለም፡፡
   2) ይህ ባለጠጋ ወጣት ገንዘብን ፈልጎ ከተሰጠው ምቹ ጊዜ ጠፋ፡፡ የጌታንም ጥሪ እምቢ አለ፡፡
   3) ከዚህ ቃል እኛ የሚገማረው መንፈሳዊ ትምህርት ምንድን ነው?
      የገንዘብና የንብረት ምኞት እንዳይወስድ ኢየሱስ ክርስቶስን ከገንዘባችንና ከንብረታችን እንዲሁም ከምኞታችን አስበልጠን መከተል እንዳለብንና የተሰጠንን ምቹ ጊዜ መጠቀም እንዳለብን ተምረናል፡፡

   ● ማቴ.19÷21-22

   21. ኢየሱስም "ፍጹም መሆን ብትፈልግ ሂድና ያለህን ሸጠህ ገንዘቡን ለድኻ ስጥ፣ በሰማይ ሀብት ታገኛለህ፣ መጥተህም ተከተለኝ!" አለው፡፡
   22. ወጣቱ ግን ብዙ ሀብት ስለ ነበረው ይህን በሰማ ጊዜ እያዘነ ሄደ፡፡

3. **ሁለት ዕድሎች**
   በመስቀል ላይ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተሰቀሉ ሁለት ወንበዶች የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ መታዘዝ ያስፈልጋቸው፡፡

   1) በመስቀል ከተሰቀሉት መካከል አንዱ ክፉ ዕድል ያለው ሰው ነው፡፡
   2) አንደኛው ሰው ይህን ምቹ ጊዜ ተጠቀመ፤ ሌላኛው ሰው ግን አልተጠቀመም፡፡
   3) የአንደኛው ውሳኔ የዘላለም ሕይወት ነው፡፡

   ● ሉቃ.23÷41-43

   41. እኛ ባደረግነው በደል ምክንያት የሚገባንን ቅጣት እግኝተናል፣ ይህ ሰው ግን ምንም ክፋት አላደረገም፡፡"
   42. እርሱም ኢየሱስን፣ "ኢየሱስ ሆይ፣ በመንግሥትህ ስትመጣ አስበኝ!" አለው፡፡
   43. ኢየሱስም፣ "እኔ እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" አለው፡፡

4. **ዕድሉን የቀየረው ዕውሩ ለማኝ በርጤሜዎስ ዕድሜው በግምት 40 ዓመት ሲሆን፤**

1) ዕውሩ በርጤሜዎስ የሳንቲም ለማኝ ነበር፡፡ ዓይኑ ማየት የማይችል ነበር፣ ነገር ግን ጆሮው ለመስማት ክፍት ነበር
2) በርጤሜዎስ የኢየሱስ የምስራች ቃል ማለትም ኢየሱስ እንደሚፈውስ ሰማ፡፡ በርጤሜዎስ ይዞ የነበረው ተስፋ ኢየሱስን ባገኝ እርሱ ዓይኖቼን ይከፍታል የሚል ነበር፡፡ ኢየሱስ በአጠገቡ ሲያልፍ በርጤሜዎስ "የዳዊት ልጅ ሆይ እኔን ማረኝ" በማለት ጮኸ፡፡ ኢየሱስም ጩኸቱን ሰምቶ የበርጤሜዎስን ዓይኖች ከፈተ፡፡
3) ከሕይወቱ ችግሮች የሚወገዱበት ምቹ ጊዜ ሆነ፡፡ ምቹ ጊዜ ለችግሮቹ መጣ፡፡
4) በርጤሜዎስ ምቹ ጊዜ ሲመጣ ተጠቀመ፡፡ ይህ ምቹ ጊዜ ለመጠቀም በርጤሜዎስ ውሳኔ አደረገ፡፡
በርጤሜዎስ ኢየሱስ ምቹ ጊዜ እንደሚሰጥ ተስፋ ተጠቀመ፡፡

- ማር.10÷46-52

46. ከዚህ በኋላ ወደ ኢያሪኮ መጡ፡፡ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ ሲወጡ ዐይነ ሰውሩ የጤሜዎስ ልጅ በርጤሜዎስ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን ነበር፡፡
47. እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ መሆኑን በሰማ ጊዜ፣ "የዳዊት ልጅ፣ ኢየሱስ ሆይ፣ ማረኝ!" እያለ ይጮኽ ጀመር፡፡
48. ብዙዎቹ፣ "ዝም በል!" ብለው ገሠጹት፣ እርሱ ግን "የዳዊት ልጅ ሆይ! ማረኝ!" እያለ ይበልጥ ጮኸ፡፡
49. ኢየሱስም ቆም ብሎ "ጥሩት" አላቸው፡፡ እነርሱም ዐይነ ስውሩን፣ "አይዞህ፣ ተነሥ፣ ይጠራሃል!" አሉት፡፡
50. እርሱም ሸማውን ጣለና ዘሎ ተነሥቶ ወደ ኢየሱስ መጣ፡፡
51. ኢየሱስም፣ "ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?" ሲል ጠየቀው፡፡ ዐይነ ስውሩም፣ "መምህር ሆይ፣ እንዳይ እፈልጋለሁ" አለው፡፡
52. ኢየሱስም፣ "ሂድ፣ እምነትህ አድኖሃል" አለው፣ ወዲያውም ዐይኑ ማየት ቻለ፣ በመንገድም ኢየሱስን ተከትሎት ሄደ፡፡

5. ዕድሉን ለመቀየር ምቹ ጊዜ የወሰነው ቀራጩ ዘኬዎስ፤ ዕድሜው በግምት በ50 ዓመት መካከል

1) ዘኬዎስ ምን ዓይነት ሰው ነው?
የቀረጥ ሰብሳቢ፣ ቁመቱ አጭር የሆነ፣ በኢያሪኮ ከተማ የሚኖር ባለጠጋ (ሀብታም) የሆነ ሰው ነው፡፡
2) በአይሁዶች ዓይን ዘኬዎስ እንደ ምን ታየ?
ሮማውያን በሚገዙበት ጊዜ ዘኬዎስ ከአይሁዶች ቀረጥ የሚሰበስብ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ለሮማውያን ከሚገባው በላይ ከህዝቡ ለራሱ ጥቅም ቀረጥ ስለምሰበስብ በአይሁዶች ዐይን እንደ ዘራፊ ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር ዝሙት እንደሚፈፅም ሰው ነው፡፡
3) ኢየሱስ ዘኬዎስን አይቶ ምን አለ?
ከጠፉት በጎች እንደ አንዱ የሆነ፣ መዳን የሚገባ ሰው ነው አለ፡፡
4) ዘኬዎስ የጠፋና እግዚአብሔርን ለመቀበል የሚፈልግ ሰው ነው፡፡
5) የጠፋ ሰው ማለት ምን ማለት ነው?
- በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የወደቀ ሰው
ለምሳሌ፡- የጊዜ መቆጣጠሪያ ሰዓት ሲቆም እንደማይሰራ ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥበቃና ከመንፈስ ቅዱስ እንክብካቤ የወጣ ማለት ነው፡፡

- ሉቃ.19÷1-4

1. ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ ከተማ ገብቶ በዚያ በኩል አልፎ እየሄደ ነበር፡፡
2. ስሙ ዘኬዎስ የተባለ አንድ ሰው በዚያ ነበረ፤ዋና ቀረጥ ሰብሳቢና ሀብታም ነበረ፡፡
3. ዘኬዎስ ኢየሱስ የቱ እንደ ሆነ ለማየት ይፈልግ ነበር፣ ነገር ግን ቁመቱ አጭር በመሆኑ ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ሊያየው አልቻለም፡፡
4. ኢየሱስ በዚያ በኩል ያልፍ ስለ ነበር ዘኬዎስ እርሱን ለማየት ብሎ ከሕዝቡ ፊት ቀድሞ ሮጠና በአንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ፡፡

6) ኢየሱስን ያገኘ ዘኬዎስ
① ከኢየሱስ ጋር እንዳይገናኝ የሚከለክል የዘኬዎስ ችግሮች ምንድን ናቸው? የቁመቱ ማጠር (አጭር ሰው መሆን)
② ከኢየሱስ ጋር ዘኬዎስ እንዳይገናኝ የሚከለክሉ የአካባቢ ችግሮች ምንድን ናቸው? የሮማውያን የቀረጥ ሰብሳቢና ባለጠጋ ስለሆነ በህዝቡ ዘንድ መጠላት ነው፡፡
③ ዘኬዎስ ይህንን ምቹ ጊዜ ለመጠቀም ከኢየሱስ ጋር ለመገናኘት በሾላ ዛፍ ላይ ወጣ፡፡ ዘኬዎስ ክብሩን ትቶ ኢየሱስን ለማየት በሾላ ዛፍ ላይ ወጣ፤ ከዚያም በኋላ ኢየሱስ የዘኬዎስን የልቡን ሀሳብ አውቆ ቀረጥ ሰብሳቢውንና ዝሙት ፈፃሚውን ከሰዎች አልለየውም፤ ምክንያቱም ዘኬዎስ በሰዎች (በአይሁዶች) ዘንድ የተጠላና ብቸኛም መሆኑን አውቆ ነበርና፡፡ ዛሬ እናንተ በሾላ ላይ ወጥታችሁ ኢየሱስን የሚትገናኙበት ምቹ ጊዜ ነው፡፡
④ ምቹ ጊዜን ተጠቅሞ ኢየሱስን ያገኘ ዘኬዎስ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን በረከት ተቀበለ (ዮሐ.1÷12)

7) ዘኬዎስ ኢየሱስን ከተቀበለ በኋላ ውጤቱ ምንድን ነው?

① የሕይወት ዕቅድና አስተሳሰብ ተቀየረ፡፡ የሕይወት ደስታና የሰዎቹን ህብረት አገኘ

② የጠፋውን ራሱን አገኘ

③ ከጎረቤቶቹ ጋር የነበረውን የጠፋውን ህብረት መማረክ፡፡

★ በሥራ ላይ የምናውልና የምንከፋፈል:- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸው ነገር ጽፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተነጋገር፡፡

ጥያቄ፡- 1. ዛሬ አንተ ቢትሞት (ከዚህ ዓለም በሞት ቢትለይ) ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደምትገባ እርግጠኛ ነህ?

2. ለሕይወትህ በጣም ምቹ ጊዜ የትኛው ጊዜ ነው?

3. አሁን ኢየሱስን ስትቀበል በአካባቢ ላይ ያለው ችግር ምንድን ናቸው?

4. በዚህ ህብረት በኩል አንተ ሊትፈወስ የምትፈልገው ነገር ምንድን ነው?

ፀሎት፡- ይህ ኮንፍራንስ ኢየሱስን ለመቀበልና ለመባረክ ምቹ ጊዜ እንዲሆን በደንብ መፀለይ፡፡

ምዕራፍ ሁለት

2. ኃጢአትን መስቀል (ሮሜ.3÷10-12)

- ሮሜ.3÷10-12

10. እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ “ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤
11. አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ አንድም የለም፡፡
12. ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፤ በአንድነት ሆነው ተሳስተዋል፡፡ ደግ ሥራ የሚሠራ አንድ ሰው እንኳ የለም፡፡

- ያዕ.1÷13-15

13. ማንም ሲፈተን፣ “እግዚአብሔር ፈተነኝ” አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም፤
14. ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በገዛ ራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው፡፡
15. ከዚህ በኋላ ምኞት ስትፀንስ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአት ሰታድግ ሞትን ትወልዳለች፡፡

እንዲህ ተብሎ ተፃፈ፡፡ “ፃድቅ ማንም የለም አንድም እንኳ አስተዋይ የለም፡፡ እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም፡፡ ሁሉም ተሳስተዋል፤ በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ በጎ የሚያደርግ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፡፡” አ/መ/ት

ኃጢአት ምንድን ነው? የኃጢአት ውጤት ምንድን ነው?

ኃጢአት ካደገ በኋላ ሞትን ያመጣል፡፡ (ያዕ.1÷13-15) ስለኃጢአት ችግሮች መፍትሔ የተቀበለ ሰው በነፃነት ይኖራል፡፡

1. የአዳም ልጆች የዚህ ዓለም ሰዎች ሁሉም ከአዳም ኃጢአት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

1) አዳም ባለመታዘዝ ኃጢአት እስከ ልጆች መጣ፡፡ ይህ ምንጭ የኃጢአት መጀመሪያ ነው፡፡

- መዝ.51÷5

5. እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።

2) አዳም ኃጢአት ሲጀምር በእግዚአብሔር ፊት ትምክህተኛ (ትዕቢተኛ) ሆነ፡፡ ሰዎች ኢየሱስን ያለማመናቸው ምክንያት ትምክህተኞች ስለሆኑ ነው፡፡ በዓለም ላይ ታላቅ ኃጢአት ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና እንደሚያድን አለማመን ነው፡፡

- ዘፍ.3÷5-7

5. እግዚአብሔር ይህን ያዘዛችሁ ከዚያ ዛፍ ፍሬ በበላችሁ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑና ደጉን ከክፉ ለይታችሁ እንደምታውቁ ስለሚያውቅ ነው፤”
6. ሴቲቱም ዛፉ የሚያምር፣ ፍሬውም ለመብላት የሚያስጐመጅና ጥበብን የማያስገኝ እንደ ሆነ ባየች ጊዜ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ለባሏም ከፍሬው ሰጠችው፤ እርሱም በላ፡፡
7. የሁለቱም ዐይኖች ተከፍተው እራቁታቸውን እንደ ሆኑ ተገነዘቡ፤ ስለዚህ የበለስ ቅጠሎችን አገናኝተው ሰፋና በማገልደም እርቃናቸውን ሸፈኑ፡፡

3) ሰዎች ለተከታታይ እግዚአብሔርን የሚቃወሙት ለራሳቸው (ጥቅም) ፍላጎት የባቢሎን ግንብ መስራታቸው ነው፡፡

- 2ጢሞ.3÷1-4

1. በመጨረሻዎቹ ቀኖች የሚያስጨንቅ ጊዜ እንደሚመጣ ዕወቅ፤
2. ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፣ ለገንዘብ የሚስገበገቡ፣ ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ ውለታቢሶች፣ ቅድና የሌላቸው፣
3. ፍቅር የሌላቸው፣ ይቅርታ የማያደርጉ፣ የሰው ስም የሚያጠፉ፣ ራሳቸውን የማይቈጣጠሩ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን ነገር የሚጠሉ፣
4. ከዳተኞች፣ ጥንቃቄ የሌላቸው፣ በትዕቢት የተነፉ፣ እግዚአብሔርን ከመውደድ ይልቅ ሥጋዊ ደስታን የሚወዱ ይሆናሉ፡፡

2. ከአያት እስከ ልጆች እስከ ልጅ ልጆች ድረስ ያመጣው የኃጢአት ውጤት ስቃይና ጥፋት ነው፡፡

1) ጣኦትን በማምለክ ርግማን እስከ ልጆች መጣ፡፡

- ዘፀ.20÷5

5. አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ

2) የአያት አምልኮ ሲል ጣኦትን ማምለክ፤ የአያት አምልኮ ሲል ከሰይጣን ጋር ህብረትን ማድረግ ማለት ነው፡፡

- 1ቆሮ.10÷20

20. አይደለም! አሕዛብ መሥዋዕት የሚያቀርቡት ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለአጋንንት ነው፤ ስለዚህ እናንተ ከአጋንንት ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ አልፈልግም፤

3) በቤተሰብ ርግማንና ስቃይ መቀበል፡፡

ምሳሌ፡- በ19ኛ ምዕተ ዓመት በእንግሊዝ አገር በሚኖሩ ሁለት ቤተሰብ ላይ ምርምር ተደርጓል፡፡ የመጀመሪያ ቤተሰብ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምኑ እስከ 7ኛ ትውልድ ድረስ ያለው ቤተሰብ እግዚአብሔር እንዴት እንደባረከ የሚገልጽ ነው፡፡

- ዘፍ.9÷24-25

  24. ኖኅ ስካሩ አልፎለት ሲነቃ፣ ትንሹ ልጁ ያደረገበትን ዐወቀ፤

  25. እንዲህም አለ፤ "ከነዓን የተረገመ ይሁን! ለወንድሞቹ የአገልጋዮች አገልጋይ ይሁን፤ እንደገናም እንዲህ አለ፤

<u>★ የጀናዳን ኤድዋርድ በረከቶችን</u>

የቤተሰብ ብዛት ጠቅላላ 1394 አባላት አሉ፡፡ እያንዳንዱን እግዚአብሔር ባርኮዋል፡፡

1. ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር. . . 1
2. የከተማ መሪ 3
3. የመንግሥት ሠራተኞች . . . 88
4. የጦር ሠራዊት መሪ 75
5. ዶክተር 56
6. ጠበቃ 100
7. የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን 295
8. የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት 13
9. ፕሮፌሰር 65
10. የፖለቲካ መሪዎች 3
11. የቀበሌ መሪ 3
12. ሚሽኔሪ . . . . . ብዙ
13. ዳኛ 30

<u>እነዚህ ቤተሰብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የሚቀበሉ እስከ 1,000 ትውልድ ድረስ ይባረካሉ እንደሚለው እንደ እግዚአብሔር ቃል የተባረኩ ናቸው፡፡ (ዘዳ.5÷10)</u>

<u>★ ኢየሱስ ክርስቶስን ያላመነ</u>

መስቹኩ እስከ 7ኛ ትውልድ ድረስ ሲመረመር ከእግዚአብሔር በረከት ያመለጠና በርግማን ውስጥ ያለ ቤተሰብ ነው፡፡

1. ጠጭዎች (መጠጥ የሚጠጡ) . . . 560 ሰዎች
2. ለማኞች . . . . .260 ሰዎች
3. እስረኞች (የህግ ታራሚዎች) . . . 160 ሰዎች
4. ነፍሰ ገዳዮች (በወህኒ ቤት ታስረው ያሉ) . . . . 7 ሰዎች
5. በመጠጥ የተሸነፉ . . . . . .100 ሰዎች
6. ዝሙት አዳሪዎች ወንድና ሴት. . . 50%

<u>እነዚህ ቤተሰብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስላላመኑ ከ3ኛ-4ኛ ትውልድ ድረስ የተረገሙ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ቃል የተረገሙ ቤተሰብ ናቸው፡፡</u>

- ዘፀ.20÷5

  5. አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ

<u>4) ኃጢአት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ከአያቶች የተላለፈ ውርስ ነው፡፡</u>

- ማቴ.2÷1-3

  1. በንጉሥ ሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተልሔም ይሁዳ ምድር በተወለደ ጊዜ፣ ከምሥራቅ አንዳንድ ጠቢባን ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።

  2. እነርሱ እንዲህ በሉ ጠየቁ፥ "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? በምሥራቅ ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና"

  3. ንጉሡ ሄሮድስ ይህን በሰማ ጊዜ ታወከ፣ የኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ ከእርሱ ጋር ታወኩ።

<u>5) ጥላቻና መጥፎ ነገሮችን ወረሱ</u>

- ዕብ.12÷15-17

  15. ከእናንተ ማንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይጐድልበት ተጠንቀቁ፤ እንዲሁም ምንም ራራ ፍሬ የሚያፈራ ሥር በመካከላችሁ እንዳይበቅልና እንዳያስቸግራችሁ ብዙዎችንም እንዳያረክስ ተጠንቀቁ፡፡

  16. ሴሰኛ የሆነ ወይም ለአንድ ጊዜ ምግብ ብሎ ብኩርናውን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ነውረኛ የሆነ ሰው እንዳይገኝ ተጠንቀቁ፡፡

  17. በኋላም ዔሳው በረከትን እንደ ገና ለመቀበል በፈለገ ጊዜ ይህን በረከት እንደ ተከለከለ ታውቃላችሁ፤ እያለቀሰ እንኳ ያንን በረከት ተግቶ ቢፈልግ ሊያገኘው አልቻለም፡፡ ለንስሓ ምንም ዕድል አላገኘም፡፡

ስለዚህ ጥላቻን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡

① ጥላቻን ምግብ ተብላልቶ እንደ ምንሽራሽር ከራሳችን ማስወገድ አለብን

② ከልብ መውደድ ያስፈልጋል

③ መስቀሉን ብቻ ማየት ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ፡- ምግብ ከቤተሰብ ጋር በሚበሉበት ጊዜ መልካም ቃል መነጋገር ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ልጆች የአባታቸውን ፈለግ ይከተላሉና መልካም ትምህርት ለልጆች ማስተማርና ማሰማት አለብን፡፡

6) የምድርን ርግማን ወረሱ.

- ዘፍ.3÷17

17. አዳምንም እንዲህ አለው፣ "የሚስትህን ቃል ሰምተህ 'አትብላ' ያልኩህን ፍሬ ከዛፉ ወስደህ ስለ በላህ፣ አንተ በፈጸምከው ክፊ ሥራ ምክንያት ምድር የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ምግብህን ከእርስዋ የምትበላው በብርቱ ድካም ነው፡፡

3. እንደገና ኃጢአት የሚሠራ ሰው የእግዚአብሔርን እርግማን ይቀበላል፡፡

የሚደጋግም ኃጢአት ምንድን ነው?

ኃጢአት ባለበት ስፍራ ሁል ጊዜ ሰይጣን አለ፡፡ ሰይጣን ባለበት ስፍራ ሁል ጊዜ ኃጢአት ደግሞ አለ፡፡ ኃጢአት የሚያደርጉ ሰዎች የሰይጣን ባሪያዎች ይሆናሉ፡፡

- ገላ.5÷19-21

19. የሥጋ ሥራዎች የታወቁ ናቸው፤ እነርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ ስድነት፤
20. ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጠላትነት፣ ንትርክ፣ ቅናት፣ ቍጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት፣
21. ምቀኝነት፣ ስካር፣ ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው፤ ከዚህ በፊት እንዳስጠነቀቅኋችሁ አሁንም ደግማ አስጠነቅቃችኋለሁ፤ እንደ እነዚህ ያሉትን ነገሮች የሚያደርጉ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡

1) ምኞት እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡

① ዝሙት: - እግዚአብሔር የሰጠውን በጋብቻ ፍቅር በቀር በዝሙት ያስረክሳሉ፡፡ እግዚአብሔር የጋብቻን ፍቅርና ሥጋውን ያስረከሰውን ሰው ያጠፋል፡፡

- 1ቆሮ.3÷16-17

16. እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን?
17. ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፤ ይህም ቤተ መቅደስ እናንተ ናችሁ፡፡

② መጥፎ: - የቴልብሺን ፕሮግራም፣ ዘፈን፣ የተቀረፀ ፊልም፣ በኢንተርኔት በተለያዩ በምታዩት ዘዴዎች ኃጢአት እንዲያደርጉ የሚገፋፉ፣ በዓይን የሚታዩ ሕይወታቸውን የሚያጠፉ ናቸው፡፡ ያንን እንዲመለከቱ ሰይጣን ያደርጋል፡፡

- ሮሜ.1÷24

24. ስለዚህ እግዚአብሔር በኀጢአት በተሞላው የልባቸው ምኞት እርስ በርሳቸው የገዛ አካላቸውን እንዲያስነውሩ ቅድስና ለሌለው ሩካቤ ሥጋ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡

③ ዓለማዊ: - የምኞት ባሪያ ሆኖ ገንዘብን፣ ጊዜንና ሥጋን የሚያባክኑ ሁሉ የሚያጠፉ ናቸው፡፡

- ገላ.5÷19

19. የሥጋ ሥራዎች የታወቁ ናቸው፤ እነርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ ስድነት፤

④ ሳምሶን በምኞት ምክንያት የጠፋ ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰጠውን ተልዕኮና ገንዘብን በመመኘት፣ ዕቃዎችን በመመኘት በእነዚህ ነገሮች ላይ ዓይኑን በማድረግ ወደቀ፡፡

- መሳ.16÷21-31

21. ፍልስጥኤማውያንም ከማረኩት በኋላ ሁለቱን ዐይኖቹን አውጡ፤ ወደ ጋዛም ወስደው በነሐስ ሰንሰለት በማሰር በታሰረበት ቤት እህል እንዲፈጭ አደረጉት፤
22. የተቈረጠውም የራሱ ጠጒር እንደገና ማደግ ጀመረ፡፡
23. "በጠላታችን በሶምሶን ላይ ድልን እንድንቀዳጅ አድርጎናል" ብለው የደስታ በዓል ለማዘጋጀትና ለአምላካቸውም ለዳጎን ታላቅ መሥዋዕት ለማቅረብ የፍልስጥኤማውያንገዢዎች በአንድነት ተሰበሰቡ፤
24. "በጠላታችን በሶምሶን ላይ ድልን እንድንቀዳጅ አድርጎናል" ብለው የደስታ በዓል ለማዘጋጀትና ለአምላካቸውም ለዳጎን ታላቅ መሥዋዕት ለማቅረብ የፍልስጥኤማውያንገዢዎች በአንድነት ተሰበሰቡ፤

25. ልባቸውንም ደስ ባለው ጊዜ እንዲጫወትልን ሶምሶንን ጥሩት አሉ ሶምሶንንም ከግዞት ቤት ጠሩት፤ በፊታቸውም ተጫወተ፤ በምሰሶና በምሰሶ መካከል አቆሙት፡፡
26. ሶምሶንም እጁን ይዞ የሚመራውን ልጅ፣ "ሕንጻውን ደግፈው የያዙትን ምሰሶዎች አስጨብጠኝና እነርሱን ተደግፌ ልቁም" አለው፡፡
27. በሕንጻውም ውስጥ ብዙ ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም የፍልስጥኤም ገዢዎች ሁሉ ነበሩ፤ በሰገነት ላይ ሆነው ሶምሶን ሲያጫውታቸው የሚመለከቱ ሦስት ሺህ ወንዶችና ሴቶች ነበሩ፡፡
28. ከዚህ በኋላ ሶምሶን "ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! እባክህ አስበኝ፤ አምላኬ ሆይ! እባክህ ጎይል ስጠኝና ፍልስጥኤማውያን ዐይኖቼን ስላወጡ አንድ ጊዜ ብቻ እንድበቀላቸው አድርገኝ!" ብሎ ጸለየ፡፡
29. ስለዚህ ሶምሶን ሕንጻውን ደግፈው የያዙትን ሁለቱን መካከለኛ ምሰሶዎች ጨበጠ፤ በቀኝ እጁ አንድን ምሰሶ፣ በግራ እጁም ሌላውን ምሰሶ ይዞ ተጠጋ፤
30. "ሕይወቴ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ትለፍ!" ብሎ ጮኸ፤ በሙሉ ጎይሉም በገፋቸው ጊዜ ሕንጻው በፍልስጥኤም ገዢዎቹና እዚያ ባሉት ሁሉ ላይ ተደረመሰ፤ ሶምሶንም በሕይወቱ ሳለ ከገደላቸው ይልቅ በሞተበት ጊዜ የገደላቸው በዙ፡፡
31. ወንድሞቹና የቀሩት ቤተሰቡ ሁሉ መጥተው አስከሬኑን ወሰዱት፤ ወስደውም በጾርዓና በአሽታኦል መካከል በሚገኘው በአባቱ በማኑሄ መቃብር ቀበሩት፤ ሶምሶን ኻያ ዓመት ሙሉ እስራኤልን መራ፡፡

⑤ የሥጋ ምኞት እንደ ደልላ እየጣፈጠ ይፈትናል፡፡ እኛ ሁሉንም ነገሮች ተመኝተን እንዳንጠፋ ጥንቃቄ ልንደርግ ያስፈልጋል፡፡

- መሳ.16÷19

19. ደሊላ ሶምሶንን በጭንዋ ላይ አስተኝታ፤ እንቅልፈ እነዲወስደው አደረገች፡፡ አንድ ሰውም ጠርታ ሰባቱን የጠጒሩን ቁንዳላዎች እንዲቈረጡ አደረገች፤ ጎይሉም ከእርሱ ተለይቶት ሰለ ነበር በማዋረድ ታስጨንቀው ነበር፤

2) ሰይጣን ጣአትን እንዲያመልኩ ያደርጋል፡፡

① ጣአትን ማምለክ: - እግዚአብሔር በጣም ይፀየፋል፡፡

- ዘፀ.20÷3-5

3. ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።
4. በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ።
5. አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ

② ሴራ:- ጣአት በማምለክና በጠንቋይ ክታብ መውሰድ

- ገላ.5÷20

20. ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጠላትነት፣ ንትርክ፣ ቅናት፣ ቊጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት

3) ክፉ ስሜት:- ጠላትነት፣ ጥላቻ፣ እንደ ጠላት መተያየት፣ቁጣ

እነዚህ ሁሉ የሰይጣን መሣሪያ ስለሆኑ በቁጣና በክፉ ስሜት እንዲናወራ አድርጎ የእኛ ነፍስ ያጠፋል፡፡

- ገላ.5÷20

20. ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጠላትነት፣ ንትርክ፣ ቅናት፣ ቊጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት

4) አንድ ላይ ሆኖ ጥፋትን መነጋገር (ማጉረምረም):- ሐሜት ማለትም ከሚወዱት ጋር የጌታን ቃል መከፋፈል ሌላው ጊዜ ግን የማይወዱአቸው ሰዎች ሲመጡ መጥላት ማማት ጥርጣሬ ወዘተ . . . በቤተክርስቲያን ልዩነትን ያመጣሉ፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ እነዚህ ነገሮች ሲኖሩ የክርስቶስ አካል የሆኑትንና የራሳችን ሕይወት ሁሉ ያጠፋሉ፡፡

- ገላ.5÷20

20. ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጠላትነት፣ ንትርክ፣ ቅናት፣ ቊጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት

5) ሰካራም: - ሌሎች ሰዎች በደንብ ሲሠሩ በቅንአት ያያል፡፡ መቅናትና ብዙ መጠጦችን መጠጣት አባካኝና ሰነፍ ነው፡፡

- ኤፌ.5÷18

18. ወደ ጥፋት የሚመራችሁ ስለ ሆነ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይልቅስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡፡

- ምሳሌ 12÷11

11. ምድሩን የሚሠራ ሰው እንጀራ ይጠግባል ለከንቱ ነገር የሚሮጥ ግን አእምሮ የጐደለው ነው።

- ምሳሌ 12÷27

27. ታካች ሰው አደን ምንም አያድንም ለሰው የከበረ ሀብት ትጋት ነው።

6) ከንቱ የማይጠቅም:- የማይታዘዝ ሰው ምቹ ጊዜን የሚጠፋ ነው፤ መልካም ሥራ አለማድረግ ኃጢአት ነው፡፡

- ያዕ.4÷17

17. እንግዲህ መልካም ነገር ማድረግን እያወቀ የማያደርግ ሰው አለማድረጉ ኃጢአት ይሆንበታል፡፡

7) ስድብ ኃጢአት:-ርግማን፣ስድብ፣መቃወም፣ማታለል፣ውሸታም፣ወሬኛ መሆን፣ክፉ ቃል መናገር፣ትችት የሚያበዛ፣ስህተቱን የሚናገር

- ኤፌ.4÷29

29. ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፤ ነገር ግን ለሚሰሙት ደስ የሚያሰኝና ለማነጽ የሚጠቅም ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ፡፡

8) የልብ አስተሳሰብና የድርጊት ኃጢአት

- ማር.7÷20-23

20. ቀጥሎም፣ እንዲህ አለ፣ "ከሰው የሚወጣ ያ ሰውን የረክሰዋል፣
21. ከውስጥ፣ ከሰው ልብ የሚወጡት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፣ ስርቆት፣ ሰው መግደል፣ ዝሙት፣
22. አመንዝራነት፣ ስግብግብነት፣ ክፋት፣ አታላይነት፣ ስድነት፣ ምቀኝነት፣ ሐሜተኛነት፣ ትዕቢት፣ ግዴለሽነት ናቸው፡፡
23. ይህ ሁሉ ክፉ ነገር ከሰው ልብ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል፡፡"

4. የኃጢአት ውጤት ምንድን ነው?

ታላቅ ኃጢአትና ትንሽ ኃጢአት ሁሉ ኃጢአት ናቸው፡፡

1) ኃጢአት ከእግዚአብሔር ይለያል፡፡ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ህብረት ያበላሻል፡፡

- ኢሳ.59÷2

2. ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።

2) ከሰዎች ጋር ያለውን ህብረት ያጠፋል፡፡ በኃጢአት ምክንያት ከሰዎች ጋር ያለው ህብረት ይቋረጣል፡፡

- ዘፍ.4÷5-8

5. ለቃየልና ለመሥዋዕቱ ግን ግምት አልሰጣቸውም፤ በዚህ ምክንያት ቃየል በጣም ተቈጣ፤ ፊቱም በቀኣጣ ተኮሳተረ፤
6. በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ቃየልን እንዲህ አለው፤ "የተቈጣኸውና ፊትህም በቀኣጣ የተኰሳተረው ለምንድን ነው?
7. መልካም ነገር አድርገህ ቢሆን ኖሮ ተቀባይነት አይኖርህም ነበርን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በበርህ ላይ ያደባል፤ በቀኣጥጥሩ ሥር ሊያደርግህም ይፈልጋል፤ ሆኖም አንተ ልታሸንፈው ይገባል፡፡"
8. ከዚህ በኋላ ቃየል ወንድሙን አቤልን "ና ወደ ሜዳ እንሂድ" አለው፤ ወደ ሜዳም በሄዱ ጊዜ ቃየል በጠላትነት ተነሥቶ ወንድሙን አቤልን ገደለው፡፡

3) ኃጢአት ሲያደርጉ ዕብድ ሰው ይሆናሉ፡፡ የልብ ሰላምና ደስታ ይጠፋል፡፡

- መዝ.32÷3-4

3. ሁልጊዜ ከመጮኼ የተነሣ ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቶቼ ተበላሹ
4. በቀንና በሌሊት እጅህ ከብዳብኛለችና፥ እርጥበቴም ለበጋ ትከሳት ተለወጠ።

4) ኃጢአት ትክክለኛውን ያጣምማል፡፡

- ኤፌ.4÷18

18. የእነርሱ አእምሮ ጨልሞአል፤ ባለማወቃቸውና በእልኸኛነታቸው ምክንያት እግዚአብሔር ከሚሰጠው ሕይወት ተለይተዋል፡፡

5) የዚህ መጨረሻ ሞት ነው፡፡

- ያዕ.1÷14-15

14. ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል።
15. ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።

6) ማንኛውም ሰው ከሞተ በኋላ በፈራጁ ፊት ይቆማል፡፡

- ዕብ.9÷27

27. ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥

7) ኃጢአትን የሚያደርግ ሰው የዘላለም እርግማን ይቀበላል፤ በ2ኛ ሞት ይፈረዳል፤ ወደ ዘላለም እቶን እሳት ውስጥ ይወረወራል፡፡

- ራዕ.21÷8

8. ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኞዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።

5. ከኃጢአት መውጣት የሚችልበትና የእግዚአብሔርን ክብር የምናገኝበት መንገድ አለ? ይህ መንገድ ማን ነው?

1) ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን ስላፈሰሰ የኃጢአት ይቅርታን ይሰጣል፡፡

- ዕብ.9÷14, 22

14. ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?

22. እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።

2) ኢየሱስ ስለእኛ ኃጢአት ራሱን አሳልፎ ሰጥቶ እኛን ከኃጢአታችን አነፃ፡፡

- ዮሐ.19÷30

30. ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ። ተፈጸመ አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።

3) ኃጢአቱ ይቅር የተባለ ሰው ከጌታ ጋር ተስማምቶ የሚኖርበትን የደንነትን ስጦታ ይቀበላል፡፡ እግዚአብሔር ይህንን ስጦታ በነፃ ይሰጣል፡፡

- ዮሐ.1÷12

12. ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤

6. ኢየሱስ የእኛን ኃጢአት እንዴት አስወገደ?

1) በጾ ላጠስ ግቢ ተመትቶና ተሰቃይቶ ኃጢአታችንን አስወገደ፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቶ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር አለ፡፡

2) ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቃይቶ፣ በሚስማርም ተቸንክሮና ደሙንም አፍስሶ አዳነን፡፡ ኢየሱስ ኃጢአቻችንን ሊያስወግድ እንደ ሞተ ማስታወስ ይገባናል፡፡

3) በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስ የሁሉንም ኃጢአት ይቅር በማለት ፍቅሩን አሳይቶ ኃጢአትን አሸነፈ፡፡

- ኢሳ.53÷5-7

5. እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።

6. እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።

7. ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም።

★ በሥራ ላይ የምናውልና የሚንከፈለው:- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸው ነገር ጽፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተነጋገር።

ጥያቄ፡- 1. በህይወታችሁ ላይ ኃጢአት ያመጣው ችግሮች ሁከቶች አሉ? እነዚህ ሁከቶችና ችግሮች እንዴት አሸነፋችሁ?

2. ፈተናን በደንብ የተቀበላችሁ ስፍራዎች የትኞች ናቸው?

3. ይህንን ፈተና ለማሸነፍ ያደረጋችሁ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ፀሎት፡- ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያሳየውን ፍቅርና ኃጢአታችንንም ይቅር ያለውን በደንብ ልንለማመድና በዚያው ይቅርታ ሌሎችንም ይቅር እንድንል ልንፀልይ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሶስት

3. ጠንካራ ግንብ መደምሰስ (2ቆሮ.10÷4)

- 2ቆሮ.10÷4

4. የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤

ሰይጣን መንፈስ ነው፡፡ መላእክት እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ፍጡር ናቸው፡፡ ነገር ግን ሰይጣን ስለታበየ የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ፡፡ ሰይጣን ብዙ ሴራ በማድረግ ብዙዎችን አታልሎ ማርኮ አጠፋ፤ ደግሞም ገደለ፡፡ የእግዚአብሔር ሰዎችን ለማጥፋት፣ የራሱ ባሪያ አድርጎ ለመውሰድና የዘላለምን ጥፋት እንዲቀበሉ ብዙ ሴራ ያደርጋል፡፡ ክርስቲያኖች ሁል ጊዜ ከሰይጣን ጋር መንፈሳዊ ውጊያ አላቸው፡፡ ኃጢአት ሰይጣን የሚገባበት መንገድ ነው፡፡ ሰይጣን በኃጢአት በኩል ወደ ክርስቲያኖች ገብቶ ጠንካራ ግንብ ይገነባል፡፡

የእግዚአብሔር ታላቅ ዕቅድ ጠላት ራሱን ከፍ ከፍ ያደረገውንና የገነባውን ግንብ ማፍረስ ነው፡፡ ሰይጣን ይህንን ጠንካራ ግንብ መኖሩን ይሸሽጋል፡፡ ሰይጣን በገነባው በጠንካራ ግንብ በብርቱ ክርስቲያኖች ላይ የህይወት ችግሮችን በማምጣት እነርሱን ይጥላል፡፡ ሰይጣን የገነባው ጠንካራ ግንብ የእግዚአብሔር በረከት ወደ እኛ እንዳይመጣ ይዘጋል፡፡

1. ሰይጣን ጠንካራ ግንብ እንዴት መገንባት ይጀምራል?

1) መንፈስንና ነፍስን በማሰር

- 1ቆሮ.6÷15-18

15. ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም።
16. ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ ተብሎአልና።
17. ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው።
18. ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።

2) ጣኦትን እንዲያመልኩ በማድረግ:- ጣኦትን ማምለክ ከእግዚአብሔር ፍቅር መለየት ማለት ነው፡፡

- ዘፀ.20÷3-5

3. ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።
4. በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ።
5. አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ

3) ምድራዊ ምኞት እንዲመኙ በማድረግ (ትምክህተኞች) እንዲሆኑ በማድረግ:-
የመንግስተ ሰማይ ተስፋ ወደፊት ሄደን የምንወርሰውን እንዳንጠባበቅ ቸልተኞች እንዲንሆን ያደርጋል፡፡

- 1ዮሐ.2÷16

15-16 ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።

4) የልምድ ኃጢአቶችን እንዲያደርጉ በማድረግ:-
መጠጥ በማጠጣት፣ ሲጋራ በማስጨስ፣ ጫት በማስቃም፣ ዝሙት እንዲፈጽሙ በማድረግ፣ ቁማር በማስጫወት፣ ያለማቋረጥ እነዚህን ነገሮች በማስደረግ ጠንካራ ግንብ ይገነባል፡፡

- ኤፌ.4÷22

22. ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥

5) ይቅርታ የማያደርግ ልብ እንዲኖር በማድረግ:-

- ማቴ.18÷21-35

21. በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው።

35. ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።
መንፈስ ቅዱስ ሲበዛ ይቅር ሊንል ያስፈልጋል፡፡

6) ተችዎች በማድረግ:-

ሰውን መተቸት አያስፈልግም፡፡በዓይንህ ውስጥ ያለውን ትልቅ ግንድ (ምሰሶ) ሳታይ በወንድምህ ዓይን ውስጥ ያለውን ትንሹን ጉድፍ ለምን ትመለከታለህ? አስቀድመህ የራስህን ግንድ አውጣ ከ=ላ የወንድምህን አጠርተህ ትመለከታለህ ይላል፡፡

- ማቴ.7÷1-5

1-2 እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል።
3. በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፥ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም?
4. ወይም ወንድምህን። ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም፥ በዓይንህ ምሰሶ አለ።
5. አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ፥ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።

7) በትኩረት እንዳይታዘዙ በማድረግ፡፡

- ሉቃ.6÷46

46. ስለ ምን። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም?

8) የልብ ሀዘን (ነቀርሳ) በመስጠት

- ዕብ.12÷15

15. የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥ ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ፥ ሴሰኛም የሚሆን እንዳይገኝ፥
በሣንባ ነቀርሳ ምክንያት ሞት ያመጣል፡፡ የልብ ነቀርሳ ሕይወታችንን ያጠፋል፡፡

2. ሰይጣን እንዴት በሕይወታችን ውስጥ ጠንካራ ግንብ ይገነባል?

1) ወግ በማጥበቅ
2) በደለኛውን (ስህተት የሠራውን) ሰው በሕግ በማስጨቆን በአስተሳሰብ፣በምኞት፣በሀዘን በእነዚህ ነገሮች አዕምሮአቸውን በማሙላት የጌታን መንገድ እርግፍ አድርገው እንድንተው ያደርጋል፡፡
3) ተከታታይ ሀዘን በማምጣት
4) በመጨረሻ እንድንተው በማድረግ

3. ሰይጣንና ክፉ መናፍስት የሚሠሩት ምንድን ነው?

1) የበረከት በሮችን ይዘጋሉ፡፡

- ዮሐ.10÷10

10. ዛሬ እነዚያን ሌባዎች (ሰይጣንና ክፉ መናፍስትን) ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡

2) ጥርጣሬን ይሰጣሉ፡፡

- ራዕ.12÷9

9. ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።

3) ኃጢአትን እንዲያደርጉ ይፈትናሉ፡፡

- 1ዮሐ.2÷15-17

15-16 ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።
17. ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።

4) በጉልበታቸውና በኃይላቸው እንድመኩ ያደርጋሉ፡፡

- 1ዜና.21÷1, 8

1. ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሣ፥ እስራኤልንም ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው።

8. ዳዊትም እግዚአብሔርን፦ ይህን በማድረግ እጅግ በድያለሁ አሁን ግን ታላቅ ስንፍና አድርጌአለሁና የባሪያህን ኃጢአት ታስወግድ ዘንድ እለምንሃለሁ አለው።

5) በትዕቢት መንፈስ እንዲሞሉ ያደርጋሉ፡፡ በመጀመርያ ሉስኤል ቅዱስ መላአክ ነበር ፤ነገር ግን ሉስፈሮር ከታበየ በኋላ ሰይጣን ሆነ፡፡

● 1ጢሞ.3÷6

6. በትዕቢት ተነፍቶ በዲያቢሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን።

6) እንዲታወኩ እንድያዝኑ ያደርጋሉ፡፡

● ገላ.6÷9

9. ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት።

7) እንድጠሉና እንድጨነቁ ያደርጋሉ፡፡ ጌታን ማመንህ በቂ ነው ብዙ መድከም ጥሩ አይደለም በማለት ያዘናጋሉ፡፡

● ራዕ.2÷10

10. ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ

8) አገልግሎትን እንድያቆሙ ያደርጋሉ፡፡

● 1ተሰ.2÷18

18. ወደ እናንተ ልንመጣ ወደን ነበርና፥ እኔ ጳውሎስም አንድና ሁለት ጊዜ፥ ሰይጣን ግን አዘገየን።

9) ቤተክርስቲያንን እንዲያከፋፈሉ (እንዲያለያዩ) ያደርጋሉ፡፡

● 1ቆሮ.1÷11-13

11. ወንድሞቼ ሆይ፥ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና።

12. ይህንም እላለሁ። እያንዳንዳችሁ። እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፥ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ።

13. ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን? በፀናች ቤተክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል የለም፡፡

10) የወንጌል ብርሃን እንዲጠፋ ያደርጋሉ፡፡

● 2ቆሮ.4÷4

4. ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።

11) የብርሃን መላአክ በመምሰል

● 2ቆሮ.11÷14

14. ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና።

4. የሰይጣንን ጠንካራ ግንብ ለመደምሰስ (ለማሸነፍ) መንፈሳዊ የጦር መሳሪያ (ዕቃ) ምንድን ነው?

1) በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በኩል የሰይጣንን ጠንካራ ግንብ መደምሰስ (ማሸነፍ) ይቻላል፡፡

● ቆላ.2÷15

15. አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።

2) ኢየሱስ የሰይጣንን ሥራ በመጀመሪያ አሸነፈ፡፡

● 1ዮሐ.3÷8

8. ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና።

3) በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማመን ማሸነፍ ይቻላል፡፡

● ዮሐ.1÷12

12. እኛ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመጀመሪያ አሸናፊዎች ነን፡፡

4) የወንጌልን ሥልጣን በማመን፡፡

● ሉቃ.4÷18-19

17-19 የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ። የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ።

5) በእግዚአብሔር ቃል፡፡

● ኤፌ.6÷17

17. የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።

6) በኢየሱስ ደም በመመካት፡፡ የኢየሱስ ደም ሥልጣን አለው፡፡

● ራዕ.12÷11

11. እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።

7) በፀሎት ኃይል ሁልጊዜ የሚነሳውን ጠላት ሰይጣንን ማሸነፍ እንችላለን፡፡

የውሳኔ ፀሎት፡-

ጌታ ኢየሱስ አንተ ስለ እኔ ኃጢአት ፋንታ በመስቀል ላይ በሚስማር ተቸንክረህ ሞተህ ከሞት እንደተነሳህ አምናለሁ፤ አሁን በዚህን ጊዜ ዝሙትን፣ ጣኦት አምልኮን፣ ምኞትን ሁሉ፣ ትዕቢትን፣ ባለመታዘዝን፣ ትችትን፣ የልምድ ኃጢአትንና፣ ይቅርታ የማያደርግ ልብ በመስቀል ላይ በሚስማር በተቸነከርከው ይቅር ብለህ ምህረትን ስጥ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ በመስቀል ላይ ስለ እኔ ተሰቅለህ ለእኔ የአሸናፊነትን ሕይወት በነፃ ስለሰጠህ፤ የኃጢአቴን ዋጋ ስለከፈልህ እኔን ከኃጢአት ስላነፃህና ስለዳንህ አመሰግንሃለሁ፡፡ አሁን በኢየሱስ ሥልጣን ሰይጣን በውስጤ የገነባውን ጠንካራውን ግንብ አፍርስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን፡፡

ውሳኔ፡- የሰይጣንን ጠንካራ ግንብ በእኔ ህይወት ላይ የሠራውን ሁሉ እያፈረሰሁት አሰርሁት፡፡

በኢየሱስ ስም ለመታዘዝ ሰይጣንና የሥጋ ፈቃድን ሁሉ ትቸዋለሁ፡፡ አሁን በእምነት አሸናፊ ሆኝዋለው ከዛሬ ጀምሮ የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅ ነኝ ይህንን ዕድል የሰጠኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡

● 1ጴጥ.5÷8-9

8. በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤

9. በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።

በፀሎት ጠንካራ ወታደር መሆን ያስፈልጋል፡፡

★ በሥራ ላይ የምናውልና የምንከፋፈል:- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸው ነገር ጽፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተነጋገር፡፡

ጥያቄ፡ 1. በውስጥህ ያለው አንድ ጠንካራ ግንብ ምንድን ነው?

2. በዚህ ሰዓት ከሰማኸው ነገሮች በጣም አስቸጋሪ (ጠንካራ) ችግሮች ምንድን ናቸው?

3. ይህን ለማድረግ ያሰብከው ዝርዝር የፀሎት ርዕስ ምንድን ነው?

★ ፀሎት፡- በውስጣችን ያለውን ሰይጣን የገነባውን ጠንካራ ግንቦችን ለማፍረስ በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡ ጥያቄ ወረቀቶችን በመስጠት ማለትም ሰይጣን የገነባውን ጠንካራ ግንቦች በኃጢአት ውስጥ እንድንገባ ያደረገውን የኃጢአት ዝርዝሮችን በሙሉ በወረቀት ላይ በመፃፍ ወረቀቱን በእሳት ማቃጠል፡፡ በዚህን ጊዜ ሰይጥን የገነባው ጠንካራ ግንቦች አፈረስን እያለን ደጋግመን መጮኽ ያስፈልጋል፤ እንደገና መጮኽ ማለት ሰይጣን የገነባውን ጠንካራ ግንቦችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማፍረስ ማለት ነው፡፡ እኛ በኢየሱስ ስም አሸናፊዎች ሆነናል፡፡

ምዕራፍ አራት

4. የመንፈስ ቅዱስ ቅባት መቀበል (ሐዋ.2÷1-4)

● ሐዋ.2÷1-4

1. በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥

2. ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።

3. እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።

4. በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።

● ዮሐ.7÷38-39

38. በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ።

39. ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ አድርገው ለተቀበሉት ነፍስ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለውጥን ያደርጋል፡፡ ይህ በሕይወታችን ውስጥ የዘላለም ሕይወት ምንጭ ያፈስሳል፡፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወታችን ስለተላከ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ነው፡፡

ዮሐ.7÷38-39 ኢየሱስ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ **"የሕይወት ውሃ ምንጭ ከሆዱ ይፈልቃል"** ብሎ ተናገረ::ሆድ ማለት በሔላዊያን ቋንቋ የሰው ጥልቅ ቦታ ማለት ሲሆን ይህ ደግሞ ሕይወት (ነፍስ) ማለት ነው፡፡

ሕይወት ጉዞ ናት፡፡ ኢየሱስን የተቀበሉት የሕይወት ጥም ይረካሉ፡፡ ምክንያቱም ከሆዱ የሕይወት ውሃ ምንጭ ይፈልቃል፡፡ ዝርዝር ኃጢአቶችን ንስሐ ለመግባት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብዙ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ንፁህ ሲሆን እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በብዛት ይሰጣል፡፡ እኔ በመጀመሪያ በሕይወት ኖሮ ሌሎች ሰዎች በሕይወት እንዲኖሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሕይወቴንና ሥጋዬን በመንፈስ ቅዱስ ማብዛት ያስፈልጋል፡፡

1. መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

1) እግዚአብሔር ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በውሃ ላይ ሰፍሮ ነበር፡፡

- ዘፍ.1÷2

2. ምድርም ባዶ ነበረች፥ አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።

2) ማንነት ያለው ነው፡፡

- 1ቆሮ.2÷10-11

10. መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።
11. በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም

3) አፅናኝ ነው፡፡ አፅናኝ ማለት እኛን የሚረዳ የሚያበረታታ ማለት ነው፡፡

- ዮሐ.14÷16

15-16 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤

- ዮሐ.16÷13

13. ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።

2. በዓለ ኀምሳ (50) ቀን ላይ የመጣው መንፈስ ቅዱስ ትርጉም ምንድን ነው?

1) የብሉይ ኪዳን ነቢያት ትንቢት መፈፀሙን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የመምጣቱን ትንቢት ይናገራል፡፡

- ኢዮ.2÷28-32

28. ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ
29. ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ
30. በላይ በሰማይ ድንቆችን አሳያለሁ፥ በታች በምድርም ደምና እሳት የጢስም ጭጋግ።
31. ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ፥ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣል።
32. እንዲህም ይሆናል የእግዚአብሔር ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ፥ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኃኒት ይገኛል። ደግሞም እግዚአብሔር የጠራቸው፥ የምስራች የሚሰበክላቸው ይገኛሉ።

2) የአዲስ ኪዳን ትንቢት መፈፀሙን፤ ኢየሱስ የመንፈስ እሳት መስጠቱን ይገልፃል፡፡

- ማቴ.3÷11

11. እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፤

3) በዓለ ኀምሳ (50) ቀን፤ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ የተከፋፈለ ልሳኖችን በአፋቸው ላይ መንፈስ ቅዱስ የሰጠበት ቀን ነው።

- ሐዋ.2÷1-4

1. በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥
2. ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።
3. እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።
4. በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።

4) በበዓለ ኀምሳ (50) ቀን ኢየሱስ ስለሚመጣበት ቀን ማዘጋጀት

① ወደ ሁሉም ሀገሮች በመሄድ ደቀመዛሙርት ማድረግ

② የሲኦልን ሥልጣን በማሸነፍ ቤተክርስቲያንን ለመገንባት

● ማቴ.28÷18-20

18. ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።

19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

3. መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው ሥራ ምንድን ነው?

1) ስለኃጢአት፣ ስለፅድቅና ስለፍርድ ዓለምን ይወቅሳል፡፡

● ዮሐ.16÷8-11

8. በሚስያም አጠገብ አልፈው ወደ ጢሮአዳ ወረዱ።

9. ራእይም ለጳውሎስ በሌሊት ታየው፤ አንድ የመቄዶንያ ሰው። ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን እያለ ቆሞ ሲለምነው ነበር።

10. ራእዩንም ካየ በኋላ ወዲያው ወደ መቄዶንያ ልንወጣ ፈለግን፥ ወንጌልን እንሰብክላቸው ዘንድ እግዚአብሔር እንደ ጠራን መስሎናልና።

11. ከጢሮአዳም ተነሥተን በቀጥታ ወደ ሳሞትራቄ በነገውም ወደ ናጹሌ በመርከብ ሄድን፤

2) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይመራል፡፡

● ዮሐ.16÷13

13. በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ስፍራ በዚያ መሆኑን ስላሰብን ወደ ወንዝ አጠገብ ወጣን፤ ተቀምጠንም ለተሰበሰቡት ሴቶች ተናገርን።

3) ኢየሱስ ጌታ እንደሆን እንዲቀበሉ ያደርጋል፡፡

● 1ቆሮ.12÷3

3. ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር። ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ፥ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር። ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።

4) ስለ ወደፊት ራዕይ ይሰጣል፡፡

● ዮሐ.16÷13

13. በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ስፍራ በዚያ መሆኑን ስላሰብን ወደ ወንዝ አጠገብ ወጣን፤ ተቀምጠንም ለተሰበሰቡት ሴቶች ተናገርን።

5) ክርስቲያኖችን ያፅናናል፡፡

● ሐዋ.9÷31

31. በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።

6) ክርስቲያኖችን ይመራል ያስተምራል፡፡

● ሐዋ.10÷19

19. ጴጥሮስም ስለ ራእዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ፥ መንፈስ። እነሆ፥ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል፤

7) ወንጌልን እንድንሰብክ ይረዳል፡፡

● ሐዋ.8÷26

26. የጌታም መልአክ ፊልጶስን። ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው።

8) ክርስቲያኖችን ይቀድሳል፡፡

● ሮሜ.15÷16

15-16 ነገር ግን አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው የተወደደ መሥዋዕት ሊሆኑ፥ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልሁ፥ ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ እሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ ምክንያት ተመልሼ ላሳስባችሁ ብዬ በአንዳንድ ቦታ በድፍረት ጻፍሁላችሁ።

9) ዳግም ልደትን ይሰጣል፡፡

● ዮሐ.3÷5

5. እርሱም አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ ወደ እነርሱ ተመለከተ።

10) በክርስቲያኖች መካከል ይኖራል

● ዮሐ.8÷11

11. ከብዙ ዘመንም ጀምሮ በጥንቁላ ስላስገረማቸው ያደምጡት ነበር።

11) የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ቅባትን ይሰጣል፡፡
በእኛ ሕይወታችን በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ምንድን ነው?
መልስ፡- እግዚአብሔር ቅባት መኖር ነው፡፡
● ዮሐ.2÷20
20. ስለዚህ አይሁድ። ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት።

12) ሥልጣን በመስጠት መስካሪዎች እንድንሆን ያደርጋል፡፡
● ሐዋ.1÷8
8. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።
13) ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጅ ሆነው ምስክር እንዲሆኑ ይረዳል፡፡
● ሮሜ.8÷16
16. የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።
14) የቃሉን ትርጉም እንድንረዳ ያደርጋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያስረዳል (ይገልፅልናል)
● ዮሐ.14÷26
26. አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።

15) ለፃድቃን ሰላምንና ደስታን ይሰጣል፡፡
● ሮሜ.14÷17
17. የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና።
16) መናፍስት እንዲለይ ያደርጋል፡፡ ዕውቀትን ይሰጣል፡፡ ለመሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር መጥፎንና መልካሙን መለየት ነው፡፡ ይህን ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ለመሪዎች ይሰጣል፡፡
● 1ቆሮ.2÷10
10. መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።

17) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ይሰጣል፡፡
● 1ቆሮ.12÷4-7
4. የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤
5. አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤
6. አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።
7. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።
18) ደቀመዛሙርት የሆኑት ሌሎች ሰዎችን ደቀመዛሙርት እንዲያደርጉና ወንጌልን ለዓለም እንዲሰብኩ ኃይልን ይሰጣል፡፡
● ማቴ.28÷20
19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

4. የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ምንድን ነው?
1) የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ማለት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲንኖርና እንዲንሠራ የሚገልፅ የመንፈስ ልምምድ ነው፡፡
① ሐዋ.2÷1:- 120 ሰዎች ለ10 ቀን ከፀለዩ በኋላ በሚፀልዩበት ቤት በመካከላቸው የመንፈስ ቅዱስ እሳት ወረደ
② ሐዋ.8:- ከአንድ አመት በኋላ እስጢፋኖስ ፊልጵዮስ የወንጌወልን ሥራ እንዲሠራ አደረገ፡፡
③ ሐዋ.2÷4፡- ከአሥር ዓመት በኋላ ለቆርስቴዎስ ቤተሰብ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲወድዱ አደረገ፡፡ ጴጥሮስ ቃሉን ከሰበከ በኋላ የቆርስቴዎስ ጌተሰብ እግዚአብሔርን እንዲቀበሉ መንፈስ ቅዱስ ረዳቸው፡፡
④ ሐዋ.19:- ከ23 ዓመት በኋላ ሐዋ.ጳውሎስ ለአጵሎስ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት እንዲቀበል ፀለየ፡፡ መንፈስ ቅዱስ የተቀበለ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ጀምሮ እስከዚህ በዓለም ያሉት ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን ያመኑ ሰዎች ድረስ መንፈስ ቅዱስ መጣ፡፡

2) ዳግመኛ የተወለደ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ተቀብሎ በተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራል፡፡
3) የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለመስጠት እግዚአብሔር ተስፋ ይሰጣል፡፡
4) የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ሁሉም ክርስቲያኖች ይቀበላሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስን ቅባት ተቀበል!

5. የልሳን ቋንቋ ምንድን ነው? (1ቆሮ.14÷1-40)
1) በመንፈስ መፀለይ ማለት ነው፡፡

2) ልሳን ለሰው የሚነገር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገር ቋንቋ ነው፡፡
3) የመንፈስ ቅዱስ ቅባት መቀበሉን የሚያረጋግጥ በሰው ላይ የወረደ ምስክርነት ነው፡፡
4) ልሳንን መተርጎም ይቻላል፡፡ ልሳን ትርጉም ያለው ነው፤ አዲስ ልሳን አለ፡፡
5) ልሳን የፀሎት ስጦታ ነው፡፡

- 1ቆሮ.14÷1-40

1. ፍቅርን ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ።

40. ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።

6. ልሳን እንዴት መነጋገር ይቻላል?

1) በአፋችን ድምፅ አውጥተን እንድንነጋገር መንፈስ ቅዱስ ይረዳል፡፡
2) ልሳን በምንናገርበት ጊዜ በውስጣችን ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ይሰጣል፡፡
3) መንፈስ ቅዱስ ቋንቋ እንደሚመራ ልሳን እንዲናገር ያደርጋል፡፡
ክርስትና የፀሎት ሃይማኖት ነው፡፡ በአውሮፓና በአሜሪካ ክርስትና የጠፋበት ምክንያት የፀሎት መጥፋት ነው፡፡

- ወንጌላዊና መጋቢ ከ3 ሰዓት በላይ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡
- የክፍል መሪዎች ከ2 ሰዓት በላይ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡
- ክርስቲያኖች ከ1 ሰዓት በላይ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

7. በልሳን የመፀለይ ጥቅሙ ምንድን ነው?

1) በልሳን መፀለይ ራሱን ለማነፅና በጎነት እንዲበዛ ይጠቅማል፡፡

- 1ቆሮ.14÷4

4. በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል።

2) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያሳድጋል፡፡

- ሐዋ.2÷14-41

14. ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ፥ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፡፡ አይሁድ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፥ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሎቼንም አድምጡ።

41. ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤

3) የፀሎት ርዳታ ይሰጣል፡፡

- ሮሜ.8÷26-27

26. እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤
27. ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።

4) ኢየሱስ ክርስቶስ ክብርን እንዲቀበል ያደርጋል፡፡

- ዮሐ.16÷13-14

13. ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።
14. እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና።

5) የመንፈስ ዕረፍት ይሰጣል ሕይወትን ያሳድሳል፡፡

- ዮሐ.7÷38-39

38. በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ።
39. ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።

6) በእምነት እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡

- ይሁዳ.1÷20-21

20. እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፥
21. ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።

7) የመንፈስን መሪነት ይሰጣል፡፡

- 1ቆሮ.14÷13-14

13. ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ።
14. በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።

8) ታላቅ በረከትን ይሰጣል፡፡

● 1ቆሮ.14÷15

15. እንግዲህ ምንድር ነው? በመንፈስ እጸልያለሁ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ።

9) ታላቅ ደስታ፣ ሰላምና ተስፋን ይሰጣል፡፡

● ኢሳ.28÷11-13

11. በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል እርሱም፡- ዕረፍት ይህች ናት፥
12. የደከመውን አሳርፉ ይህችም ማረፊያ ናት አላቸው እነርሱ ግን መስማትን እንቢ አሉ።
13. ስለዚህ ሄደው ወደ ኋላ እንዲወድቁ እንዲሰበሩም ተጠምደውም እንዲያዙ የእግዚአብሔር ቃል ትእዛዝ በትእዛዝ፥ ትእዛዝ በትእዛዝ፥ ሥርዓት በሥርዓት፥ ሥርዓት በሥርዓት፥ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ይሆንላቸዋል።

10) ለሚያምኑ ሰዎች ምልክት ነው፡፡

● ማር.16÷17

17. ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ

11) በብዙ ጥልቅ ፀሎት በመዝሙር መሳሪያ ይሆናል፡፡

ልሳን በፍፁም ልብ በእግዚአብሔር እንዲመካ ያደርጋል፡፡ መዝሙር ሥጋችንና መንፈሳችንን የሚያረካ ዕረፍት የሚሰጥ ዝማሬ ነው፡፡

● 1ቆሮ.14÷15

15. እንግዲህ ምንድር ነው? በመንፈስ እጸልያለሁ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ።

8. የመንፈስ ቅዱስ ቅባትና የተትረፈረፈ ሕይወት በሥልጣን የሚንቀበልበት መንገድ ምንድን ነው?

1) በቃሉ በኩል መንፈስ ቅዱስ እንዲገባ በሩን መክፈት ያስፈልጋል፡፡

● ሐዋ.10÷43-44

43. በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።
44. ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ።

2) ሁሉንም ሁከት በማስወገድ አንድ ላይ መስበክ፡፡

● ሐዋ.1÷13-14

13. በገቡም ጊዜ ወደሚኖሩበት ሰገነት ወጡ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስም፥ ያዕቆብም፥ እንድርያስም፥ ፊልጶስም፥ ቶማስም፥ በርተሎሜዎስም፥ ማቴዎስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም፥ ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም፥ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳም።
14. እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።

3) እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ መጠባበቅ

● ሐዋ.1÷4

4. ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፥ ነገር ግን። ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤

4) የመንግስት ሰማይ ሥልጣን በደንብ በመውደድ

● ሐዋ.1÷14

14. እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።

5) ኃጢአትን ንሥሐ መግባት መፀለይ

● ሐዋ.2÷38

38. ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

6) በይቅርታና በአስታራቂ ልብ መፀለይ

● ሐዋ.1÷14

14. እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።

★ የመንፈስ ቅዱስ ቅባትና መርዳትን የመቀበል መንገድ።

1. ሁሉንም ሁከቶችን ማስወገድ የቀድሞ ክፉ ሥራዎችን በልባችን ውስጥ ያሉ የማይጠቅሙ ሀሳቦችን ሁሉ ማስወገድ፡፡
2. መጥራት መንፈስ ቅዱስ ቅባት እግዚአብሔር እንዲሰጥ መጥራት
3. በእምነት መቀበል፡፡
4. ለመንፈስ ቅዱስ ሕይወትን ማስረከብ

★ በሥራ ላይ የምናውል:- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸው ነገር ጽፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተነጋገር

የመንፈስ ቅዱስ ቅባት የሚያልቅ ሳይሆን የሚቀጥል ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ቅባት ተቀበለን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ልንኖር ያስፈልጋል፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት የመንፈስ ቅዱስ ቅባት መኖር ወሳኝ ነው፤ ይህ ሳይኖር በራሳችን ልምምድ መሥራት ጥሩ አይሆንም፡፡ ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በዝቶ በምስክርነት ሕይወት መኖር ያስፈልጋል፡፡

★ ፀሎት፡- በየቀኑ የመንፈስ ቅዱስ የበዛ ሕይወት እንዲኖር በደንብ ተግተን ልንፀልይ ያስፈልጋል፡፡

★ በሕይወታችን ሰይጣን የገነባውን ጠንካራ ግንብ ለመደምሰስ የሚጠቅም ዘዴ

በዚህ ጥያቄ ላይ በአንተ ሕይወት ውስጥ የሚገኙ ስህተቶችን በመርመር ፃፍ፡፡ ይህ ጥያቄ ወረቀት በአንተና በጌታ ፊት አስቀምጥ! የትኛውን ዓለም አየኸው? የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ስትጨርስ በዚህ ወረቀት ላይ የዘረዘርካቸውን ኃጢአቶችን አቃጥል፡፡

★ የግል ጥያቄዎች

ጥያቄዎችን በምትፅፍበት ጊዜ በእውነት ልትመልስ ይገባሃል፡፡ የምትመልሳቸው መልሶችም ብዙ ናቸው፡፡

1. ከሚቀጥሉት ልምድ ያንተን ድካም (ችግሮች) የሚያሳይ የትኞቹ ናቸው?

①ፀሎት ( ) ②ፆም ( ) ③የጥሞና ጊዜ ( ) ④መጠን (ልከኛ) ( )

⑤እምነት ( ) ⑥ባለስልጣንን መታዘዝ ( ) ⑦ሕብረት ( ) ⑧አስራት መስጠት ( )

⑨ደቀመዝሙር ማድረግና ማሰልጠን ( ) ⑩የመንፈስ ቅዱስ ታምራት ስራ ( )

2. ከሚቀጥለው ጥያቄዎች ውስጥ በየትኛው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ውስጥ አለህ?

①ሴሰኛ መሆን ( ) ②ዝሙት (አመንዝራ)( ) ③ግብረ ሰዶም መፈፀም ( )

④ከዘመድ ጋር ግንኙነት ማድረግ ( ) ⑤ራስ በራስ ግንኙነት ማድረግ ( ) ⑥ፍትወት ( )

⑦ከእንስሳት ጋር ዝሙት መፈፀም ( ) ⑧በስልክ በኢንተርኔት ግንኙነት መፈፀም ( )

⑨ራቆት የመሄድ ኃጢአት ( ) ⑩በሃሳብ ዝሙትን መፈፀም ( )

⑪ሌሎች ሰዎች ራቆታቸውን ዝሙት የሚያደርጉትን በዓይን በማየት ኃጢአት ( )

⑫የግንኙነት ፊልም ማየት ( )

3. ሕይወትህን እንደገና የሚመርዝ (የሚጎዳ) ልምድ የተኛው ነው?

①የማያቋርጥ እንቅልፍ ( ) ②የሌላ ሀብት መስረቅ ( ) ③መርሳት ( )

④ብዙ መጠጥ መጠጣት ( ) ⑤ጫት መቃም ( ) ⑥ግፈኛ መሆን ( ) ⑦ማጨስ ( )

⑧ቅንዓት ( ) ⑨አደንዛዥ እፅዎችን መጠቀም ( ) ⑩መዋሸት ( ) ⑪ሆዳምነት ( )

⑫ስንፍና ( ) ⑬ብዙ የኮምፒተር ውጤቶች ጌሞችን መጫወት ( ) ⑭ስንፍና ( )

⑮ትችት ( ) (16)ተስፋ መቁረጥ ( ) (17)ቁማርተኛ ( ) (18)ምኞት ( )

(19)ጥላቻ ( ) (20)የቪዲዮ ጨዋታ እየተጫወቱ ጊዜ ማባከን ( )

(21)የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያሳይ ፊልም ማየት ( ) (22)የቴሌቭዥን ሱስ መያዝ ( )

(23)ክፉ መሳደብ(ስምፍና ቃል መናገር ( ) (24)መፈተን(ክፉ ስራ ለመስራት ( )

4. ከሚቀጥለው አንተ የተለማመድከው የስሜት ኃጢአት የትኞቹ ናቸው?

①መጨነቅና ፍርሃት ( ) ②የልብ ክፋት ( ) ③ቁጣ ( ) ④መደናገር ( )

⑤ራስ ወዳድነት ( ) ⑥መወዳደር ( ) ⑦ቸልተኛ ( )

⑧ሁል ጊዜ ልክ ነኝ ማለት ( ) ⑨ትዕቢተኛ (ትምክህተኛ)( ) ⑩ሀዘን (ማዘን) ( )

⑪ምክር መፈለግ ( ) ⑫ልዩነት ማምጣት(ሰውን መለየት) ( )

⑬ሌሎች ሰዎችን ሁል ጊዜ መተቸት ( ) ⑭ሌሎች መጥላትና ቂም መያዝ ( )

⑮አለመታገስ (ትዕግስት ማጣት) ( )

5. አንተ በሕይወትህ የተለማመድካቸው መንፈሳዊ ኃጢአቶች የትኞቹ ናቸው?

①ክፉ ህልም ( ) ②በእንቅልፍ መሰቃየት (ቅዠት) ( )

③ፍርሀትና ክፉ ሀሳብ ( ) ④ሰይጣንና ጭፍራዎችን ማየት ( )

6. አንተ በሰውነትህ ጤና እንዳይኖር ያወኩ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

①ብዙ ህልም ( ) ②የሆድ ህመም ( ) ③የአካል ህመም ( )

④ድካም (አቅም ማጣት) ( ) ⑤የሥራ ብዛት ሕመም ( )

★ የቤተሰብ ጥያቄዎች

7. በአንተ ቤተሰብ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምን ማን ነው?

8. በቤተሰቦችህ መካከል ከሚቀጥለው ጋር ሕብረት የሚያደርግ አለ?

①ከኃጢያን ሐይማኖት ጋር ( ) ②ከእስልምና ሐይማኖት ጋር ( )

③ሙታን ከሚያምኑ ጋር ( ) ④የይሐዋ ምስክሮች ጋር ( )

⑤ከቡዲዝም ሐይማኖት ጋር ( ) ⑥ከሞርሞን ጋር ( ) ⑦ጣኦትን ከሚያመልኩ ጋር ( )

⑧ሌሎችን ከሚጠራጠሩ ጋር ( ) ⑨ከክርስቲያኖች ጋር ( )

9. በአንተ ቤተሰብ መካከል ከሚቀጥለው ጋር ህብረት የሚያደርግ ሰው አለህ?

①ጥንቆላ ከሚያደርግ ጋር ( ) ②ከዕድል ነጋሪዎች ጋር ( )

③የሰውን ፊት አይቶ ከሚናገሩት ጋር ( ) ④የጣኦት መስመማን በማየት ከሚናገሩት ጋር ( )

⑤የዕድሜና የልደት ወረቀት በማየት ሰውን ከሚያነሳሳው ሰው ጋር ( )

⑥ከሚጠራጠሩት ጋር ( ) ⑦ከቡዲዝም መሪዎች ጋር ( )

⑧የወደፊቱን ህይወት ከሚናገሩት ጋር ( ) ⑨ጥሞና ከሚያደርጉ ጋር ( )

⑩ክታብ ከሚከትቡ ጋር ( ) ⑪አስማትና መተት ከሚያደርጉ ጋር ( )

⑫ከዮጋ (ከሰይጣን) ጋር ህብረት ከሚያደርግ ሰው ጋር ( )

⑬የቀን መቁጠሪያ በማየት ዕድል በወረቀት ከሚያይ ሰው ጋር ( )

4. የአንተ ቤተሰብ በዳግመኛ ሐዘን ውስጥ አሉ?

①በህመም ( ) ②መግደል ( ) ③በእሳት ቃጠሎ ( ) ④ፍቺ ( )

⑤ገንዘብ ማጣት ( ) ⑥ድህነት ( ) ⑦መቅሰፍት ( ) ⑧አስገድዶ መስፈር ( )

⑨ጥላቻ ( ) ⑩የመጠጥ ሱስ ( ) ⑪የአዕምሮ ህመም ( )

⑫ከዘመድ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ( ) ⑬አደንዛዥ ዕፆችን መጠቀምና ጫት መቃም ( )

5. አንተ የምታውቀው የአያት ኃጢአት የትኞቹ ናቸው?

①ግፍ መስራት ( ) ②ማመንዘር ( ) ③የመጠጥ ሱስ ( )

④ቁማርተኛ ( ) ⑤ድህነት ( ) ⑥ነቀርሳ ( ) ⑦ስቃይ ( )

⑧የአዕምሮ ህመም ( ) ⑨ዝሙት መፈፀም ( ) ⑩መቅሰፍት (በደል)( )

⑪ ጫት መቃም አደንዛዥ ነገሮችን መጠቀም ( ) ⑫ፍቺ (ትዳር መፍታት) ( )

6. አንተ ከቤተሰቦችህና ከሌሎች ሰዎች ጋር በህፃንነት ስትኖር ከሚቀጥለው ሀሳቦች የተጎዳኸው በየተኛው ነው?

①በየጊዜው ማስፈራራት ( ) ②በዝሙት ግፍ መስራት ( )

③በስድብ ግፍ መስራት ( ) ④መጣል ( )

⑤መደብደብ (መመታት)( ) ⑥መቃወም ( )

★ የህብረት ጥያቄ

ለጥያቄው እውነተኛ መልስ ፃፍ፡፡ መልሶቹም ብዙ ናቸው፡፡

13. ከአባትህ ጋር ህብረት አለህ?

14. ከእናትህ ጋር ህብረት አለህ?

15. ከሚስትህ ጋር ህብረት አለህ?

16. ከልጆችህ ጋር ህብረት አለህ?

17. ከምትወደው ከወዳጅህ (ከቅርብ ሰው) ጋር ህብረት አለህ?

18. ከማህበረሰብህ ጋር ህብረት አለህ?

19. ከዚህ ጥያቄ ወረቀት በጣም ያልተረዳኸው ጥያቄ ምንድን ነው?

20. ቀድሞና አሁን የአንተን ሕይወት የያዘው የእርግማን ቃል አለህ?
ለምሳሌ፡- የአንተ ቤተሰብ ሁልጊዜ የሚረግሙት ርግማን ቃል

21. ቀድሞና አሁን በሕይወትህ ውስጥ የያዝከው መሀላና ተስፋ ቃል አለህ?

22. በለፈው ዓመታትና ዘንድሮ በህይወትህ ውስጥ የሰማከው የፍርድ ቃል አለህ?
ለምሳሌ፡- አንተ ሰነፍ ነህ! ፉንጋ ነህ! የማትረባ ነህ ተባለህ የተሰደብከው ቃላት በውስጥህ አሉህ?

★ መንፈስና ሥጋን የሚፈውስ ህብረት

1. በህብረት ሰዓት ወደ ህብረት ግቢ ከገባ በኃላ ኮንፍራንሱ ሳያልቅ ወደ ውጭ መውጣትና ወደ ቤት መሄድ ክልክል ነው፡፡
2. የቤተሰብህንና የሥራህን ሁሉ ጭንቀት ለእግዚአብሔር ስጥ! እግዚአብሔር የሁሉም ዳኛ ነው፡፡
3. ስልክህ አጥፋ
4. አንዱ አንዱን ያገልግል

5. የሚትጠቀመውን ስፍራ ንፁህ አድርግ
6. በምትታመምበት ጊዜ የወንጌላዊና የመጋቢያንን እርዳታ ጠይቅ
7. ለሚያስተምረው አስተማሪ (ወንጌላዊ) ፀልይ
8. እግዚአብሔር የሚሰጠውን ፀጋ ውደድ

★ <u>የሚሠራበት ቦታ (የሚትቀረጽበት)</u>

1. በስብከት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አብርሆነት እንዲሰማህ በናፍቆት ጥራ፡፡
2. የተሠራህበትን ጉዳይ ከሌሎች ጋር ተከፋፈል፡፡ ለራስ የሚመች ንፁህ አየር ተጠቀም
3. እንድትሠራ ለሚረዳው አስተማሪ ልብህን ክፈት
4. የራስህን ታሪክ ለረጅም ሰዓት አታውራ (አትናገር)
5. የሚሠራ (የሚቀርጽ) መሪ መልስ የሚሰጥ ሳይሆን የሚመራ ነው፡፡
6. የሚሠራ ሰው በሚያስተምርበት ጊዜ ችግሮችና መከራዎች ለእርሱ ሲኖሩ አንድ ላይ በመሆን ፀልይ
7. ችግሮች በሚያገጥሙ ጊዜ ለመጋቢዎችና ለወንጌላዊያን እንዲሁም ለቤተ/ያን መሪዎች ተናገር፡፡

★ <u>ከቤተክርስቲያን ውጭ ህብረት በሚሰራበት ጊዜ</u>

መግቢያ	ሰዓት	የት/ርት ሰዓት	አስተማሪ	ማነፃፀር (ማወዳደር)
የፕሮግራሙ ጅማሬ	2፡00	1 ሰዓት		
ዝማሬ	3፡00-3፡15	15 ደቂቃ	የመዝሙር መሪ	
መግቢያ የሚሰጥ	3፡15-3፡20	5 ደቂቃ	የሚሰራ ቡድን መሪ	የፕሮግራም ቅደም ተከተል ማን እንደሚያስተምር መግለፅ
ዝማሬ	3፡20-3፡30	10 ደቂቃ	የመዝመር ቡድን	

1. አስተማሪ	3፡30-5፡00	90 ደቂቃ	አስተማሪ/ወንጌላዊ/መጋቢ	
የሚሰለጥኑበት ቦታ ስኬት	5፡00-5፡50	50 ደቂቃ	የሚያሰለጥን ቡድን	የክፍል ስብስባ መከፋፈል
የምሳ ሰዓት	5፡50-6፡50	1 ሰዓት	የሚሰለጥኑ ቡድን	
ዝማሬ	6፡50-7፡00	10 ደቂቃ	የመዝሙር አምልኮ መሪዎች	
2. አስተማሪ	7፡00-8፡10	70 ደቂቃ	አስተማሪ	
ቴሌቨዥን	8፡00-8፡20	10 ደቂቃ	የቴሌቨዥን ቡድን	
የሚሰለጥኑበት ቦታ ስኬት	8፡20-9፡10	50 ደቂቃ	የሚሰለጥኑ ቡድን	የቡድን ስብስባ መከፋፈል
የዕረፍት ጊዜ	9፡10-9፡20	10 ደቂቃ	የሚሰለጥኑ ቡድን	
የዝማሬ	9፡20-9፡30	10 ደቂቃ	የአምልኮ የዝማሬ ቡድን	
3. አስተማሪ	9፡30-10፡40	70 ደቂቃ	አስተማሪ/ወንጌላዊ/መጋቢ	
የሚሰለጥኑበት ቦታ ስኬት	10፡40-11፡30	50 ደቂቃ	የሚሰለጥኑ ቡድን	የቡድን ስብስባ መከፋፈል
ጠንካራ ግንብ በወረቀት በእሳት ላይ ማቃጠል	11፡30-12፡00	30 ደቂቃ	የሚሰለጥኑ ቡድን	
የእራት ጊዜ	12፡00-1፡00	1 ሰዓት	የሚሰለጥኑ ቡድን	ወረቀተን በእሳት ላይ መጣል
ዝማሬ	1፡00-1፡20	20 ደቂቃ	የዝማሬ ቡድን	
4. አስተማሪ	1፡20-2፡30	70 ደቂቃ	አስተማሪ/ወንጌላዊ/መጋቢ	
የአስተማሪና የዝማሬ ቡድን መሪ	2፡30-3፡00	30 ደቂቃ	የአስተማሪና የአምልኮ (ዝማሬ ቡድን)	
ፀጋ ስጦታ የሚፃፍበት ወረቀት መቀበል	3፡00-3፡10	10 ደቂቃ	የሚሰለጥኑ ቡድን	
ፀጋውን መከፋፈል	3፡10-3፡40	30 ደቂቃ	የሚሰለጥኑ ቡድን	የክፍል ሰባኪ መምረጥ
ማጠቃለያና የመኝታ ጊዜ	3፡10-			

ይህንን ትምህርት የሚሰለጥኑ ሰዎች ለራሳቸው መኝታ ልብስና ፊታቸውን የሚታጠቡበት ሳሙና ይዞ ይመጣሉ፡፡
የቤተክርስቲያን መሪዎች ደግሞ ለእያንዳንዱ ስልጣኝ የቁርስ፣የምሳ፣የዕራት የሚሆን መስተንግዶ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

★ ጠንካራ ግንብ ለማፍረስ ወረቀቱን በእሳት ውስጥ የማቃጠል ዘዴ

1. ነፍስ መንፈስንና ስጋን የሚፈውስ ህብረት ስልጠና የሰለጠንከውን ትምህርት በሥራ ላይ ልታውል የወሰንከውን ከጓደኞችህ ጋር ከተከፋፈልክ በኃላ አንድ ላይ በመፀለይ በመጨረሻ የክፍሉ መሪ ሊፀልይ ያስፈልጋል፡፡
2. ጠንካራ ግንብ ለማፍረስ የተጠቀመውን ጥያቄ ወረቀት ከመጀመሪያ ገፅ ጀምሮ እስከ መጨረሻ ገፅ ድረስ ያሉትን ጥያቄዎችን በማንበብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡
3. የጥያቄ ወረቀቱን ከመመርመርክ በኃላ ከጓደኞችህ ጋር ሳትከፋፈል ወደ ሚቃጠልበት ወደ እሳት ቦታ ሄደህ ወረቀትህን በእሳት ላይ ከጣልክ በኃላ ለአንድ ደቂቃ ያህል ጮኽ መፀለይ አለብህ፤ በመጨረሻ የሚያሰለጥንህ የክፍል መሪ ሰው ልፀልይ ያስፈልጋል፡፡
4. የክፍል መሪ ሰይጣን የገነባው ጠንካራ ግንብና ሌሎች ችግሮች ሁሉ ወድቁ ተደመሰሰ በማለት 3ጊዜ መጮኽ አለበት፡፡ ደግሞም ሌሎቹም አንድ ላይ አሸነፍን በማለት 3ጊዜ መጮኽ አለባቸው፡፡
5. ከሚሰለጥኑ ሰዎች ጋር (ከክፍሉ ሰዎች ጋር ምግብ ከበሉ በኃላ የእግዚአብሔርን ፀጋ ተከፋፈሉ፡፡ ይህ ጊዜ የዕራት ጊዜ ይሆናል፡፡)

★ በእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ሥራዎቻቸውን በደንብ እንዲያደርጉና እንዲፀልዩ መግለፅ፡፡

- አዲስ ቤተሰብ ለመስበክ 4 ሳምንታትን ተጠቀም፡፡
- ሥጋንና መንፈስን የሚፈውስ ህብረት አንድ ቀን አድርግ፡፡

- ልምምድ የሚደረግ ትምህርት 12 ሳምንት ተጠቀም፡፡
- ደረጃ 1 የደቀመዛሙርት ዩንቨርሲቲ 12 ሳምንት ተጠቀም፡፡
- ደረጃ 2 የደቀመዛሙርት ዩንቨርሲቲ 12 ሳምንት ተጠቀም፡፡
- ደረጃ 3 የደቀመዛሙርት ዩንቨርሲቲ 12 ሳምንት ተጠቀም፡፡



ልምምድ ሲደረግ የሚገኘው ደስታ

መግቢያ

በዚህ ምድር ብዙ ቤተክርስቲያናትና ክርስቲያኖች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መኖር የሚያስብ ሳይኖር ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣትና በመመለስ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን ዝም ብለው ይጨርሳሉ፡፡ የራሳቸው መንፈሳዊ ሁኔታ ህፃን በመሆ እንደ ልጆች ባለማወቅ የሌሎችን እርዳታ በመቃወም ፍላጎታቸውን ለማገልገል ይፈልጋሉ፡፡ ብዙዎች ለምን የራሳቸውን መንፈሳዊ ህይወታቸው እንዲያድግ አያስቡም? መልሱ የዕውድ አምልኮን ዘወትር ቢንመጣ ራሳችንን እናሳድጋለን በማለት የተሳሳተ አመለካከት ስላላቸው ነው፡፡ የእሁድ አምልኮ ብቻ መጥቶ ስብከት መስማት እምነትን በመጠኑ ያሳድጋል፡፡ ነገር ግን እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ማደግ የሚመጣው በሥርዓት ትምህርት ሲማሩና ልምምድ ሲያደርግ ነው፡፡

ክርስትናን የመገንባት ሥራ ታላቅ ጥረትና ልቅሶ ይጠይቃል፡፡ (ተስ.2÷7-8) ልምምድ ለምድረግ የሚረዳ ቃል ነው ቃሉም እናት ልጆቹን እንደምትንከባከብ በየዋህነት ያዘናችሁ ብሎ ሐዋሪያ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ይናገራል፡፡ ልክ እንደዚህ ህፃንን እናት እንደሚትከባከብ ክርስትናን ለመገባት ጥረት ይጠይቃል፡፡

በወላጅነት ልብ የሰውን መንፈሳዊ ሕይወት ለመገንባት ልምምድ ልናደርግ ያስፈልጋል፡፡ ህፃን ተወልዶ ልጅ ሆኖ እስኪያድግ ድረስ የወላጆች ርዳታ ያስፈልጋል፡፡ ደግሞም ልምምድን የሚያደርግ በመንፈሳዊ ሕይወት የወለዱአቸውን ልጆችን እስከ ክርስቶስ ድረስ እንዲደርሱ እንዲያደርጉ መርዳት አለበት፡፡ ይህ የእርዳታ ለማግኘት የልምምድን ትምህርት) ብትማር አንተ በመንፈሳዊ ሕይወትህ ታድጋለህ በዚህ መጽሐፍ በኩል እግዚአብሔር የሚሰጠውን ልዩ ስሜትና ደስታ ለብዙ ቤተክርስቲያን ታካፍላለህ፡፡

ከፀሐፊው!

ማውጫ **ገፅ**

1. ምዕራፍ አንድ - እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት የደስታ ስሜትን መግለፅ .....
2. ምዕራፍ ሁለት - የደህንና ፅኑ እምነት .....
3. ምዕራፍ ሶስት - ኃጢአትን ለማስወገድ ፅኑ እምነት .....
4. ምዕራፍ አራት - የፀሎት ምላሽ ፅኑ እምነት .....
5. ምዕራፍ አምስት - ምሪትን በመቀበል የማሸነፍ ፅኑ እምነት .....
6. ምዕራፍ ስድስት - መንፈስ ቅዱስ የተትረፈረፈ ክርስቲያኖች .....
7. ምዕራፍ ሰባት - እምነታችን እንደ መኪና ቸርክ አይነት ነው .....
8. ምዕራፍ ስምንት - የጥልቅ ሀሳብ (የጥምና ጊዜ) .....
9. ምዕራፍ ዘጠኝ - ክፍት ስብስባ ማለት ምን ማለት ነው? .....
10. ምዕራፍ አሥር - እግዚአብሔርን ዕቅድ የምትሠራ ቤተክርስቲያን .....

ምዕራፍ አንድ
1. እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት የደስታ ስሜትን ግለፅ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ክርስቶስ ኢየሱስን እንዲቀበሉና ልምምድ ልታደርግ ከምታገኛቸው ሰዎች ጋር እየተነጋገርክ የምትከፋፈልበት የፀሎት ርዕሶችን ተቀበል፡፡

1) የሕይወት ታሪክ ፃፍ

ስም	
የቤተሰብ አባላት	
ሥራ	
ዕድሜ	

2) ኢየሱስ ክርስቶስን መቼ ተቀበልክ?
3) አሁን ኢየሱስ ክርስቶስን ካልተቀበልክ እርሱ እንደ ሰው ነው ብለህ አስበሃል?
4) አንተ ኢየሱስ ክርስቶስን እንድትቀበል የረዱ የመጀመሪያ ሰዎች አሉ? የአስተዳደግ ሁኔታ የሚገልፅ ደጀን የሆኑ ሰዎች አሉ?
5) በአንተ ሕይወት ውስጥ የምትደሰትበት ጊዜ የትኛው ነው?
6) በሕይወትህ ላይ ችግሮች የበዙበት መቼ ነው?
7) የሕይወትህ ግብና ዓላማ ምንድን ነው?
8) ልምምድ የምታደርገውን ቃል እንዴት ሰማኸው?
9) የፀሎት ርዕሶች ምንድን ናቸው?
10) በዚህ ልምምድ በምናደርገው ትምህርት በኩል ልትቀይር የምትፈልገው ክፍል ምንድን ነው?

2. የጥያቄ ዝርዝር
1) ልምምድ ልታደርግ ስለመጣህ እናመሰግናለን፡፡

2) ልምምድ የምታደርግበትን ዕቅድ (ግብ) ልታውቅ ያስፈልጋል፡፡
አንተ(አንቺ) የእግዚአብሔር ልጅ(ሴት) ነው። ቃልና መንፈስ ቅዱስ ስብዛ የጌታ ደቀ መዝሙር ይሆናል::
3) ለልምምድ የሚያስተምረውን አስተማሪ ልትወድ ያስፈልጋል፡፡ ስለ እርሱ ስትፀልይ የሚጠቅም ይሆናል፡፡
4) መቅረትና ማርፈድ እንዳታደርግ ልትጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡
3 ጊዜ በተከታታይ መቅረት አያስመርቅም፡፡
3 ጊዜ ማርፈድ የ1 ቀን ቀሪነትን ያመለክታል፡፡
5) ልምምድ የሚያደርጉ ተማሪዎችን ተስፋ ልናደርግ ያስፈልጋል፡፡
- የልምምድ ትምህርት ዓይነቶችን በደንብ ተስፋ ልናደርግ ያስፈልጋል፡፡
- በየቀኑ መፅሐፍ ቅዱስን የማንበብና የመፀለይ ተስፋ ልንይዝ ያስፈልጋል፡፡
- በየዕሁድ ወደ አምልኮ አዳራሽ መምጣት፣ አምልኮ ማካሄድ፣ አስራት፣መባ፣ምፅዋትና የመሳሰሉትን ለጌታ ቤት ሥራ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
6) በየሳምንቱ የሚመረመሩት ዝርዝሮች
- ይህን የዝግጅት መፅሐፍ በቅድሚያ መማር
- በእምነት መፅሐፍ ቅዱስን አንብብ
- ሁሉንም የአምልኮ ጊዜያት ለመምጣት መሞከር

7) ሥጋንና መንፈስን የሚፈውስ ሥልጠና መካፈል (መሠለጠን)
- በዕውቀትና በፀሎት መሞከር
እኛ በፍቅር ልብ እግዚአብሔርን እያገለግልን ሰዎችን ልንገነባ እንፈልጋለን፡፡
8) የልምምድን ትምህርት ከተቀበልክ በኋላ ይህን ትምህርት በአንደኛ ደረጃ ላይ አስቀምጥ፡፡
9) አብሮ የሚለማመዱ (የሚሰለጥኑ) ሰዎችን በፍቅር አገልግል፡፡

★ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድግበት አጭር መንገድ

ለክርስቲያኖች ታላቅ በረከት መንፈሳዊ ህይወት ማደጉ ነው፡፡ የዓለም ሰዎች ታላቅ በረከት ገንዘብ ነው፡፡ ነገር ግን ለክርስቲያኖች ታላቅ በረከት እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም ሙላት ልክ መድረስ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ጠንካራ ልምምድ (ሥልጠና) መውሰድ አለብን፡፡ ልምምድ የሚያደርጉ (ሥልጠና የሚቀበሉ) ሰዎች አሸናፊዎች ማለትም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አሸናፊዎች ይሆናሉ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመኑ ሰዎች ከ1-3 ደረጃ ይኖራሉ፡፡

ኢሱስን ያመነ ነገር ግን በ3ኛ ደረጃ ላይ ያለ ሰው አንድ እግር በዓለም ሌላው እግር በቤተክርስቲያን ውስጥ አለ፡፡ ይህ ሰው በየዕሁድ አምልኮ ሥራ ሲበዛ አምልኮን የማይመጣ ሥራ በሌለበት ጊዜ ደግሞ ጌታን ለማምለክ ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጣ ነው፡፡ ያመነው በ2ኛ ደረጃ ላይ ያለው ሰው በመንፈሳዊ ሕይወት በደንብ የጠነከረ ነው፡፡ ነገር ግን ሁል ጊዜ በራሱ ስሜት ይሠራል፡፡ በራሱ ስሜት ሲሠራ ይደክምና ይወድቃል፡፡ ያመነ በ1ኛ ደረጃ ላይ ያለ ሰው በየቀኑ ይፀልያል፣ ይደሰታል፣ በአፉም የምስጋና ቃል ይሞላል፣ ዓለምን የሚቀይርና ለሰዎች የክርስቶስ ውጤት በሥልጣን የሚናገር ሰው ነው፡፡

እኛ በእምነት 1ኛ ለመሆን ልምምድ የሚያደርጉ (ሥልጠና የሚቀበሉ) ሰዎች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ 12 ሳምንት ልምምድ አድርጎ በኋላ አንተ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ይችላል።

ምዕራፍ ሁለት
2. የደህንነት ፅኑ እምነት (ኤፌ.2÷8-10)

- ኤፌ.2÷8-10

8. ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤
9. ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።
10. እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።

ደህንነት፣ የዘላለም ሕይወት፣ የእግዚአብሔር መንግስትና መንግስተ ሰማይ እንዚህ ሁሉ አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው፡፡ መንግስተ ሰማይ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምንና ዳግመኛ የተወለዱ ሰዎች የሚኖሩበት ስፍራ ነው፡፡ ዳግመኛ መወለድ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወቴ ጌታና አዳኝ ነው ብሎ በአፉ መመስከር ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው አዳኝ ነው ብሎ ለተቀበለው ሰው እግዚአብሔር አዲስ ሕይወትና የዘላለም ሕይወት ይሰጣል፡፡

የእግዚአብሔር ልጅና ከሴት መወለዱን የሚገልፅ ሁኔታ ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት ዓይን ያላየውን እጅ ያልዳሰሰው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ የሕይወቴ ጌታና አዳኝ ነው ብሎ በተቀበለበት ጊዜ ዳግመኛ ተወለደ፡፡

★ በእምነት ማደግ ለምን ይጠፋል?

1. አዳኙን (ደህንነትን) ያለመቀበል ምክንያት ነው፡፡ መንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋል፡፡
2. ስለ እምነት ነገር እንዳናስብና እንዳንኖር ካደረገው ርግማን ለመውጣት የልምምድ ትምህርት (ስልጠና) ያለመውሰድ ነው፡፡ ስለራሱ መንፈሳዊ ህይወት ለማሳደግ የማያስብ (ጥረት የማያደርግ) ማለት ነው፡፡
3. ለእግዚአብሔር ቃል ያለመታዘዝ ውጤት፡፡ እምነት ከመስማት ይመጣል፤ መስማት መንፈሳዊ ሕይወትን ያሳድጋል፡፡

★ መንፈሳዊ ሁኔታ የሚገልፅ ጥያቄዎች

1. አንተ አሁን ዛሬ ብትሞት ወደ መንግስተ ሰማይ ትገባለህ?
2. ኢየሱስ አሁን የት ነው ያለው?
   በልቤ ውስጥ ይኖራል
3. የአንተ ኃጢአት ምን ሆነ?
   ሁሉም ኃጢአቶች በኢየሱስ በኩል መፍትሔ አግኝተዋል፡፡

1. ደህንነትን ያልተቀበለውን ሰው ምን ሆነ?

1) በመንፈስ ምን ሆነ?

- ኤፌ.2÷1

1-2 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።

2) የማን ልጅ ነህ?

ያላመነ ሰው የሰይጣን ልጅ ነው፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመነ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ (ዮሐ.1÷12)

- ዮሐ.8÷44

44. እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።

3) የማን ባሪያ ነህ?

ያላመነ ሰው የሰይጣን ባሪያ(ኤፌ.2÷2)

ኢየሱስ ክርስቶስን ያመነ ሰው ከኩነኔና ከኃጢአት ነፃ ወጥተዋል፡፡(ሮሜ.8÷1-2)

- ኤፌ.2÷2

1-2 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።

- ሮሜ.8÷1-2

1. እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም።
2. በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና።

4) በማን እርግማን (ቁጣ) ውስጥ አለህ? ኢየሱስ ክርስቶስን ያላመኑ በእግዚአብሔር ቁጣና እርግማን ውስጥ አለ፡፡ (ገላ.3÷13-14) አሁን እኛ ያመንን ሰዎች በእግዚአብሔር በረከቶች ተባርከናል፡፡

- ኤፌ.2÷3

3. በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።

5) በልብህ ውስጥ ምን አለህ? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያላመኑ ሰዎች ልብ ውስጥ እውነተኛ ሰላምና ዕረፍት የላቸውም፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ባመኑት ሰዎች ልብ እውነተኛ ሰላምና ዕረፍት ይበዛል፡፡

- ማቴ.11÷28

28. እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።

6) ከሞት በኋላ ሥራህ እንዴት ይገለጣል? ኢየሱስን ያላመኑ ሰዎች ከሞት በኋላ ወዲያውኑ ወደ ሲኦል ይሄዳሉ፡፡ (ፊልጵ.3÷20) ኢየሱስ ያመኑት ሰዎች ሲሞቱ ወደ መንግስተ ሰማይ ይሄዳሉ፡፡

- ራዕ.20÷10

10. ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።

7) መንፈሳዊ ርስት ምንድን ነው ያለው? (ዘፀ.20÷4-5) ያላመኑ ሰዎች ጣኦትን ስለሚያመልኩ ልጆች ሁሉ ይጠፋሉ፡፡ (ከ3ኛ-4ኛ ትውልድ ይጠፋሉ) ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምኑ ሰዎች እስከ 1,000 ትውልድ ድረስ የእግዚአብሔርን ፀጋ ይወርሳሉ፡፡

- ዘፀ.20÷4-5

4. በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ።
5. አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ

- ዘዳ.5÷10

9-10 በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውም።

2. ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምን ሰዎች ምን ይለውጣል?

1) አዲስ ሕይወት መቀበልህን

- ሮሜ.6÷4

4. እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።

2) የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን ወደ ወንድሞችና ወደ እህቶች ህብረት በመምጣት፡፡

- ዮሐ.1÷12

12. ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ በምድር ላይ በህብረት ክርስቲያኖች መኖራቸው የሚገልጸው በመንግስተ ሰማይም ክርስቲያኖች አንድ ላይመኖራቸውን ይገልሃል

3) አዲስ ፍጥረት መሆንህን

- 2ቆሮ.5÷17

17. ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

4) አዲስ ልብ ማግኘትህን

- ሕዝ.11÷19

19-20 በትእዛዜም ይሄዱ ዘንድ ፍርዴንም ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ፥ በውስጣቸውም አዲስ መንፈስ እሰጣለሁ፥ ከሥጋቸውም ውስጥ የድንጋዩን ልብ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ።

5) የቀድሞ ችግሮችን፣ የአዳም ኃጢአት፣ የእንደገና ኃጢአትና የአያት ኃጢአት ሁሉ መፍትሔ ማግኘትህን

- ኤፌ.2÷1

1-2 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።

6) ለአሁኑ ችግሮችም መፍትሔ ማግኘትህን ግለጽ፡፡

- ኤፌ.2÷2

1-2 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።

7) ከሞት በኋላ ወደ መንግሥተ ሰማይ ይሄዳል።

- ኤፌ.2÷6

6-7 በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ፥ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።

3. እንዴት ደህንነትን ልትቀበል ቻልክ?

1) በመከራ የተገኘ ሳይሆን እግዚአብሔር የሚሰጠው ስጦታ ነው፡፡

- ኤፌ.2÷8-9

8. ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤
9. ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።

2) ስለዚህ መከራትና መተበት የለብንም፡፡

- ኤፌ.2÷9

9. ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።

3) ደህንነትን መቀበል ማለት በመንፈስ ዳግም መወለድ ማለት ነው፡፡

- ዮሐ.3÷5-7

5. ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።
6. ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።
7. ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ።

በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አማካይነት ዳግመኛ የተወለደ ብቻ ወደ መንግሥተ ሰማይ ይሄዳል፡፡

ክርስትና ከእግዚአብሔር ፀጋ የተነሣ የሚገኝ ደህንነት ነው፡፡ ነገር ግን ሌሎች ሃይማኖቶች በሙከራና በመልካም ሥራ ደህንነት እንደሚቀበሉ ያስባሉ፡፡ የቡድሀይም ሃይማኖት ምኞትን በመተው ደህንነትን መቀበል ይቻላል ይላሉ፡፡ እስልምና ደግሞ ብዙ በመፀለይ፣ መልካም ሥራ በመሥራትና ወደ መካ በመሄድ ደህንነት እንደሚቀበሉ ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስን ሲናምን እግዚአብሔር ደህንነትን እንደሚሰጥ ያስባሉ፡፡

4) የእግዚአብሔርን ፍቅር የተቀበለ ሰው አይነጫነጭም አይፈርድም፡፡

- ዮሐ.3÷16

16. በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

5) ፍቅሩን የገለጠውን ኢየሱስን ያመሰግናል

- ሮሜ.5÷8

8. ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።

6) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያምናል፡፡የእግዚአብሔር ፈቃድ እኔና አንተን ማዳን ነው፡፡

- ዮሐ.20÷30-31

30. ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤
31. ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።

7) ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ አምኖ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል፡፡

- ዮሐ.1÷12

12. ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤

8) የሰው ውሳኔ አስፈላጊ እንደሆነ ይገነዘባል፡፡

- ሮሜ.10÷8-9

8. ነገር ግን ምን ይላል? በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው።
9. ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤

★ በመንፈስ ዳግመኛ የተወለደ ሰው ምስክርነት

1. ክርስቲያኖችን (አማኞችን) በወደድ ይጀምራል፡፡
2. የጌታን ህግ በደስታ ይጠይቃል፡፡
3. የእግዚአብሔርን ቃል በደስታ ይታዘዛል፡፡
4. በጌታ ፅኑ እምነት ያድጋል፡፡
5. የፀሎት ምላሽ የሚቀበልበት ፅኑ እምነት ይኖረዋል፡፡
6. በንፁህ ሕይወት ይኖራል፡፡
7. በየቀኑ የራሱን ሕይወት ለጌታ ይሰጣል፡፡
8. ጌታ ኢየሱስን የሕይወቱ መጀመሪያ ያደርጋል፡፡

4. ኢየሱስን እንዲቀበሉ ፀልይ

5. ኢየሱስን ለሚያምን ሰው እግዚአብሔር የሚሰጠው በረከት ምንድን ነው?

1) የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን በረከት

- ዮሐ.1÷12

12. ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ አሁን እኛ ከሰይጣን ባሪያነት ወደ እግዚአብሔር ልጅ መሆን ተቀይረናል፡፡

2) ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የመኖርን በረከት

እኛ ብቻችን አንኖርም ደግሞም አንጠማም፡፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ይኖራልና፡፡

- ዮሐ.14÷16-17

15-16 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤
17. እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።

3) የፀሎት ምላሽ የማግኘት በረከት

የእግዚአብሔር መኖር ምስክር የፀሎት መልስ በመስጠቱ ነው፡፡ እኛ በኢየሱስ ስም ሲንፀልይ እግዚአብሔር መልስ ይሰጣል፡፡

- ዮሐ.16÷24

24. እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።

4) የሰይጣንን ሥልጣን የማፍረስ በረከት፤ የሲኦል ሥልጣን ከቶ ቤተክርስቲያን ሊያሸንፍ አይችልም፡፡ ፀሎት የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሳይንስ ስለሆነ ፍፁም መልስን ትቀበላለች፡፡ ፅኑ እምነት አላችሁ?

- ማቴ.16÷18

18. እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።

5) የመላእክት እርዳታ የመቀበል በረከት

- ዕብ.1÷14

14. ከቶ ለማን ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን? መላእክት መጥቶ እኛን ይረዱልናል፡፡

6) የመንግስተ ሰማይ ዜጋ የመሆን በረከት፤ የእኛ መዝገብ በመንግስተ ሰማይ አለ፡፡ (ኢየሱስ ክርስቶስን ሲናምን በመንግስተ ሰማይ ስምን ተፅፏል፡፡

● ፊልጵ.3÷20
20. እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤

7) የመንግስተ ሰማይ አንባሳደሪዎች (እንደራሴዎች) የመሆን በረከት

● ዘፍ.1÷28
28. እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፡- ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።

8) የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የመሆን በረከት

● ማቴ.16÷18-20
18. እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።
19. የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።
20. ያን ጊዜም እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለማንም እንዳይነግሩ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው።

9) የአብርሃምን በረከት የመቀበል

① እያንዳንዱ ሰው ② ቤተሰብ
③ ነገድ ④ አገር ⑤ ዓለም

● ገላ.3÷13-14
13. በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤
14. የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።

10) ዓለምን የማሸነፍ በረከት፤ በወንጌል ዓለምን እናሸንፋለን፡፡

● ማቴ.28÷18-20
18. ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።
19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

★ በሥራ ላይ የምናውል፡-ከዚህ ምዕራፍ አዲስ ያወቅኸውን (በሥራ ላይ ልታውል የፈለግከውን) ፅፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት፡- የደህንነት ፅኑ እምነትንና ኢየሱስ ክርስቶስን ያመነ ሰው የሚባረክበትን በረከትን ለመቀበል በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሶስት
3. ኃጢአትን ለማስወገድ ፅኑ እምነት (1ዮሐ.1÷9)

● 1ዮሐ.1÷9
9. በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።

አሜሪካ አገር ውስጥ የተደረገ እውነተኛ ታሪክ

አንድን ሰው የገደለውን ሰው ይዞ ወደ ዳኛው ፊት ሲያቀርቡ ዳኛው የሞት ፍርድ በየነው፡፡ የገዳዩ ወንድም ከፍተኛ ባለስልጣንና ለአገሩ ጥሩ የሚሠራ ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው ታናሹ ወንድም ሰውን መግደሉን ሰምተው በልቡ በጣም አዘነ፡፡ ስለዚህ ወንድም ወደ ፕሬዝዳንቱ ቢሮ ሄዶ ስለታናሽ ወንድሙ ፕሬዝዳንቱ ይቅርታ እንዲያደርግለት ጠየቀ፤ ፕሬዝዳንቱ የገዳዩ ወንድም ለአገሩ ጥሩ ሥራ የሚሠራና ባለስልጣንም እንደሆነ ሰምተው የሞት ፍርድ ለተፈረደው ለታናሹ ወንድም ከባለ ሥልጣኑ ልመና የተነሣ ይቅርታ አደረገለት፡፡

ባለስልጣኑ የፈቃድ ወረቀት ተቀብሎ ወደ ወህኒ ቤት ሄዶ ነፍሰ ገዳዩን ወንድም እንዲህ ሲል ጠየቀው፡፡ የኃጢአትህን ይቅርታ ብትቀበልና ነፃ ብትወጣ ወደፊት ምን ትሠራለህ? ታናሽ ወንድሙ ሲመልስ ለእኔ ሞት የፈረደውን ዳኛና መስካሪዎችን

ሁሉ እገድለላለሁ አለ፡፡ ነፃ መልቀቂያ ፈቃድ ከፕሬዝዳንቱ ቢሮ የተቀበለው ባለስልጣኑ ወንድም በጣም በልቡ አዝኖ የነፃ መልቀቂያ ወረቀት ለታሰረው ወንድም ሳያሳይ የልቡን ክፋት ተመልክቶ በፊቱ ቀደደ፡፡

ሁሉም ሰው ኃጢአተኛ ነው፡፡ የራሱን ኃጢአት የሚያውቅ ሰው አለ፤ የማያውቅ አለ፡፡ ኃጢአትን የሚያውቅ ሰው ስለ ኃጢአቱ በእግዚአብሔር ፊት ንሰሐ ቢገባ ኃጢአቱ ይቅር ይባላል፡፡ ነገር ግን ስለ ኃጢአቱ ንሰሐ ባይገባ በስቃይና በመከራ ውስጥ ይኖራል፡፡ ደግሞ የኃጢአትና የሰይጣን ባሪያ ሆኖ ይኖራል፡፡

1. እግዚአብሔርን የተውው ሰዎች ምን ሆነ?

1) መፅሐፍ ቅዱስ የሰውን ሁኔታ እንዴት ይገልፃል?
በዓለም ውሸታምና የተበላሸ ልብ የሰው ልብ ነው፡፡ በማለት ይገልፃል፡፡

- ኤር.17÷9

9. የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?

2) የሰው ፅድቅ ሥራ ምን ይመስላል? የሰው ፅድቅ እንደ መርገም ጨርቅ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

- ኢሳ.64÷6

6. ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፥ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፥ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል።

3) ሰዎችን አይተው መልካም ሥራ የሚሠሩት ሰዎች እግዚአብሔርን አይተዋል?
እግዚአብሔርን አላዩትም የእነርሱ መጨረሻ የሞት መንገድ ነው፡፡

- ምሳሌ 14÷12

12. ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።

4) በዓለም ላይ መልካም ሥራ የሚሠሩ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን ኃጢአትን የማይሠራ ፃድቅ ሰው በዓለም አለ?
ፍፁም ኃጢአትን ሳይሰራ የሚኖር የለም፡፡

- መክ.7÷20

20. በምድር ላይ መልካምን የሚሠራ ኃጢአትንም የማያደርግ ጻድቅ አይገኝምና።

5) የኃጢአት ውጤት ምን ያመጣል? ሞት ያመጣል ከዚያም ፍርድ፡፡

- ዕብ.9÷27

27. ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥

2. ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበት ግብ ምንድን ነው?

1) ስለ ሰዎች ኃጢአት የራሱን ደም አፍስሶ ይቅርታን ለመስጠት፤

- ዮሐ.1÷29

29. በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፦ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።

2) ኃጢአታችን በራሱ ላይ ለመሸከም መጣ፡፡

- 1ዮሐ.3÷5

5. እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፥ በእርሱም ኃጢአት የለም።

3) የሰይጣንን ሥራ ለማፍረስ መጣ፡፡

- 1ዮሐ.3÷8

8. ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና።

4) በእኛ ፋንታ ሞቶ ኃጢአታችንን ሊያስወግድ

- ሮሜ.5÷8

8. ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም? እንዲሁ ይሰድቡናልና አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና። የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው።

3. ኢየሱስ ኃጢአታችንን እንዴት አስወገደ?

1) በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ኃጢአታችንን አስወገደ፤ ኢየሱስ በእኛ ፋንታ በመገረፉ

- 1ጴጥ.2÷24

24. ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ *ፍ1*

2) የእኛ እርግማን በራሱ ላይ በመውሰድ ኃጢአታችንን አስወገደ፡፡

- ገላ.3÷13

13. በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤

3) ስለ መተላለፋችን በመወጋት ስለ በደላችን በመድቀቅ ኃጢአታችንን አስወገደ፡፡

- ኢሳ.53÷5-6

5. እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።
6. እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።

4. ኢየሱስ ኃጢአታችንን የማስወገድ ውጤት ምንድን ነው?

1) የአብርሃም በረከት እንዲንቀበልና የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ እንዲንቀበል አደረገ፡፡

- ገላ.3÷14

14. የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።

2) የቀድሞ የአሁኑና የወደፊቱ ከሞት በኋላ ላለው ሁሉ መፍትሔን አስገኘ፡፡

- ኤፌ.2÷3-7

3. በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።
4. ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥
5. ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥
6-7 በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ፥ ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።

3) ለድሆችንና ለዓይነ ስውራን ለአዕምሮ ሕመምተኞች ሁሉ ነፃነትን ሰጠ

- ሉቃ.4÷18-19

17-19 የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ። የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ።

4) ከጨለማ ሥልጣን ነፃ አውጥቶ እርግማነውን ወደ በረከት ለወጠ፡፡ ከሲኦል ወደ መንግስተ ሰማይ አሸጋገረን፡፡

- ቆላ.1÷13

13-14 እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።

5. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምኑ ሰዎች ኃጢአትን ቢሠሩ ምን ይሆናሉ?

1) የደህንነት ተስፋ ይጠፋል፡፡

- መዝ.51÷12

12. የማዳንህን ደስታ ስጠኝ፥ በእሽታ መንፈስም ደግፈኝ።

2) የፀሎት መልስን አያገኙም፡፡ የመንግስተ ሰማይ በር ዝግ ይሆናል፡፡ ደግሞም የበረከትም በሮች ዝግ ይሆናሉ፡፡

- ኢሳ.59÷1-2

1. እነሆ፥ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፥ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም
2. ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።

3) ስጦታቸው (ፀጋ ስጦታቸው) ይጠፋል፡፡

- 1ቆሮ.3÷13-15

13. በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፥ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል።
14. ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፤
15. የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፥ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።

4) ስቃይና ህመም ይበዛል፡፡

- ዮሐ.5÷14

14. ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና። እነሆ፥ ድነሃል፤ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ አለው።

5) በታላቅ ፈተና ውስጥ ይወድቃሉ፡፡

- 1ጴጥ.5÷8

8. በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤

6. በእኛ ላይ የእግዚአብሔር ጥሪ ምንድን ነው?

1) ተከታታይ የእግዚአብሔር ጥሪ ምንድን ነው? መልስ፡- ከኃጢአት ነፃ እንዲንወጣ ነው፡፡

- ሕዝ.33÷11

11. እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ተመለሱ፥ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ ስለ ምንስ ትሞታላችሁ? በላቸው።

2) የትኛው ሰው ነው ከእግዚአብሔር ምህረት የሚቀበለው? መልስ፡- ኃጢአትን የሚናዘዝና የሚተወው ሰው፡፡

- ምሳሌ 28÷13

13. ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።

3) ኃጢአትን የሚናዘዙ ሰዎችን እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?
መልስ፡- ከኃጢአታቸው አንጽተው እንደ በረዶና እንደ በግ ፀጉር ነጭ ያደርጋል፡፡

- ኢሳ.1÷18

18. ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።

4) እግዚአብሔር የሚሰጠው የኃጢአት ይቅርታ በረከትና ሰው ይቅር ከሚለው ይቅርታ ጋር ስታወዳድር ልዩነት ምንድን ነው?
መልስ፡- እግዚአብሔር ኃጢአታችንን እንደገና አያስብም፡፡ ነገር ግን ሰው ኃጢአታችንን እንደገና ያስታውሳል፡፡

- ዕብ.8÷12

12. ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም።

5) የኃጢአትን ጦርነት እንዴት ታደርጋለህ? መልስ፡- ደም እስከ መፍሰስ ድረስ የኃጢአት ውጊያ ሊገጥም ይገባል፡፡

- ዕብ.12÷4

4. ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም፤

7. አሁን የኃጢአት ይቅርታ አግኝተህ ፅኑ እምነት ለመገንባት ቁም

1) የኃጢአት ይቅርታ ባይኖር ምን ትሆናለህ? መልስ፡- በፍርሃትና በጭንቀት ውስጥ እኖራለሁ፡፡

- 2ጢሞ.1÷7

7. እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።

2) የኃጢአት ይቅርታን ሲታገኝ ምን ትሆናለህ? መልስ፡- በፅኑ እምነት ያለፍርሃት እኖራለሁ፡፡

- 2ጴጥ.1÷3-9

2-3 የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።

4. ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።

5. ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥

6. በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥

7. እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።

8. እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና፤

3) የእግዚአብሔር አብ ፍቅር ምንድን ነው?
መልስ፡- እስከ መጨረሻ ድረስ ታግሶ የሚቆይ ፍቅር ነው፡፡(እስከ ሚንመለስ ድረስ መታገስ)

- ሉቃ.15÷22-24

22. አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ። ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፤

23. የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፥ እንብላም ደስም ይበለን፤

24. ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር።

ውጤት፡- ኃጢአትን ደም እስከሚፈስስ ድረስ ተዋግተህ ልታሸንፍ ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔርን ብትወድድ የእግዚአብሔርን ህግ ጠብቅ አሁን እግዚአብሔርን ከወደድክ ኃጢአት አትስራ የኃጢአትን ልምድ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡

★ በሥራ ላይ የምናውል ከዚህ ምዕራፍ አዲስ ያወቅከውን በስራ ላይ የምታውለውን ፅፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት፡- የኃጢአት ይቅርታ አግኝተህ በፅኑ እምነት ለመኖር በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ አራት
4. የፀሎት ምላሽ ፅኑ እምነት (ዮሐ.16÷24)

- ዮሐ.16÷24

24. እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።

ፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና በመንፈስ ቅዱስ መተንፈስ ነው፡፡ እኛ በፀሎት በኩል ፍላጎታችንን ከእግዚአብሔር የምንቀበልበትና አስፈላጊውን የእግዚአብሔርን ሥራ የምንሠራበት ነው፡፡ እግዚአብሔር መልካም ስለሆነ የእኛን ፀሎት በመመለስ ይደሰታል፡፡ ሁል ጊዜ 50ሺህ ጊዜ ፀልዮ የፀሎት መልስ የተቀበለ ጆርጅ ሚላር 1,500 ወላጅ አልባ ልጆችን በመውሰድ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን እርሱ ለሌሎች ገንዘብን አይፈልጋቸውም።

አንድ ቀን አንድ ሰው ምሳውን ጆርጅ ሚላር በሌላ ሥፍራ እንዲበላ ጋበዘው፡፡ በግባዣ ሥፍራ እያለ ጆርጅ ሚላር ሰውየውን አሁን ስንት ሰዓት ነው? ብሎ ሲጠይቅ ሰውየውም ሰዓቱ አሁን አምስት ሰዓት ነው ብሎ መለሰ፡፡ ጆርጅ ሚላር ስድስት ሰዓት እስከሚሞላ ታገሰ በማለት ተናገረ፡፡ ጆርጅ ሚላር ወዲያውኑ ወደ ክፍሉ ገብተው የልጆች ምሳ (ወላጅ አልባ) ልጆች የሚበሉበት ምሳ እግዚአብሔር እንዲሰጥ ፀለየ፡፡ እውነት ስድስት ሰዓት ሲሞላ ዳቦ የሞላበት ጋሪ ህፃናት የሚኖሩበት ቦታ ገባ፡፡ ሰዎቹ ጋሪውን የሞላ ዳቦ ወደዚህ ስፍራ እንዴት ሊመጣ ቻለ ብሎ ሲጠየቁ ዳቦ የሚጋገርበት ስፍራ በእሳት ስለሚቃጠል ከዚያም ዳቦ የሞላ ጋሪ ወላጅ አልባ ህፃናት ወደ ሚኖሩበት ሥፍራ ሊመጣ ቻለ ብሎ መለሰ፡፡

ጆርጅ ሚላር በሙሉ ሕይወት 50ሺህ ጊዜ ፀልዮ እነዚያን ፀሎቶችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ምላሽ ተቀበለ፡፡ እንደዚሁ እግዚአብሔር ፀሎታችንን ይመልሳል፡፡ እግዚአብሔር የመኖሩ ምስክር የፀሎታችን መልስ በመስጠቱ ነው፡፡ እኛ ደግሞ እንደ ጆርጅ ሚላር በየቀኑ በሙሉ ሕይወት ወደ እግዚአብሔር በፅኑ እምነት በመፀለይ የፀሎትን ምላሽ ተቀብለን በተትረፈረፈ ሕይወት ሊንኖር ያስፈልጋል፡፡

1. እግዚአብሔር ፀሎታችንን እንዴት እንደሚመልስ አግኝ።

1) የፀሎት መልስ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆኑት የሚሰጥ ልዩ ሥልጣን ነው፡፡

- ዮሐ.1÷12

12. ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤

2) እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ እኛን ከመውደዱ የተነሳ የሚሰጥ ነው፡፡
እግዚአብሔር ለእኛ የተትረፈረፈ ሕይወት ይሰጣል፡፡

- ዮሐ.10÷10

10. ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ፡፡

3) እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ የሚመልስ ነገር ነው፡፡

- መዝ.91÷15

15. ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፥ በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ አድነዋለሁ አከብረውማለሁ።

4) እግዚአብሔር ፍፁም ሥልጣን ስለያዘ የሚሰጥ ነው፡፡
እግዚአብሔር እኛ ስንፀልይ ሰምቶ መልስ ይሰጣል፡፡

- ኢሳ.65÷24

24. እንዲህም ይሆናል ሳይጠሩ አመልስላቸዋለሁ፥ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ።

5) የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ስለሚበዛ የሚመጣ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ስለ እኛ ይማልድልናል፡፡

- ሮሜ.8÷26-27

26. እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤
27. ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።

2. በምንፀልይበት ጊዜ ልናደርጋቸው የሚገቡ ሥራዎች ምንድን ናቸው?

1) የፀሎት ሥራ ማን ይሠራል? መንፈስ ቅዱስ ይሠራል፡፡

- ሉቃ.11÷13

13. እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?

2) መንፈስ ቅዱስ ምን ዓይነት ሥራዎችን ይሠራል?

በእግዚአብሔር ኃይል መላእክት መጥቶ የጌታን ሥራ እንዲሠሩ ያደርጋል፡፡

- ዕብ.1÷14

14. ከቶ ለማን ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?

3) አካባቢያችን የሚቀይር ነገሮች ምንድን ናቸው?

አካባቢያችን በሙሉ መቀየር የሚችለው ፀሎት ነው፡፡

- ሉቃ.18÷1-7

1. ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፥
2. እንዲህ ሲል፦ በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ።
3. በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፥ ወደ እርሱም እየመጣች። ከባላጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር።
4. አያሌ ቀንም አልወደደም፤ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ። ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር፥
5. ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜም እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ።
6. ጌታም አለ። ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ።
7. እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን?

- አስቴ.4÷16

16. ሄደህ በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ ሰብስብ፥ ለእኔም ጹሙ ሦስት ቀን ሌሊቱንና ቀኑን አትብሉም፥ አትጠጡም እኔና ደንገጥሮቼ ደግሞ እንዲሁ እንጾማለን ምንም እንኳ ያለ ሕግ ቢሆን ወደ ንጉሡ እገባለሁ ብጠፋም እጠፋለሁ።

- አስቴ.5÷8

8. በንጉሡ ዘንድ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፥ ልመናዬንም ይፈጽም ዘንድና የምሻውን ያደርግ ዘንድ ንጉሡ ደስ ቢያሰኘው፥ ንጉሡና ሐማ ወደማዘጋጅላቸው ግብዣ ይምጡ እንደ ንጉሡም ነገር ነገ አደርጋለሁ አለች።

4) ሐዋ.10÷1-19 እንደሚገልፀው የፀሎት መልስ ምልክት ምንድን ነው?

የፀሎትን መልስ ከሰዎች ጋር ተካፈለ፡፡ ለቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ሐዋሪያ ጴጥሮስን ልከዋል፡፡

- ሐዋ.10÷1-19

1. በቂሣርያም ኢጣሊቄ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ።
19. ጴጥሮስም ስለ ራእዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ፥ መንፈስ። እነሆ፥ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል፤

3. የፀሎታችን መልስ እግዚአብሔር በሶስት አቅጣጫ ይመልሳል፡፡

1) በምንፀልየውበት ጊዜ ወዲያውኑ ይመልሳል፡፡

2) የእኛን ህይወት ሊያበላሹ የሚችሉና የማይፈለጉ ፀሎቶችን እግዚአብሔር አይመልስም፡፡

3) የሚበልጠውን መልካም ነገሮችንና ሌሎችን የተሻለ ነገሮችን ለመስጠት ዘግይቶ ይመልሳል፡፡

4) እግዚአብሔር ፀሎታችን በፍፁም የሚመልሰው ለአዕምሮአችን ለአሳባችንና ለልባችን ሰላምንና ጥበብን በመስጠት መልስ መስጠት ይጀምራል፡፡

4. የፀሎት መልስ ለምን ሳይመለስ ይቀራል? ስህተቱስ የቱ ጋ ነው?

ለእኛ የፀሎት መልስ ያለመምጣት ምክንያት እግዚአብሔር የምንፀልየውን ፀሎት የመስማት ሥልጣን ስለሌለ ሳይሆን የፀሎት መልስ እንዳይመጣ መንገዱ ስለተዘጋ ነው፡፡ ይህ የተዘጋበት ምክንያት ምን እንደሆነ በቃሉ በኩል አግኝ፡፡

1) ያለ ማወቅና ያለ መፈለግ

- ያዕ.4÷2

2. ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም፤ ትገድላላችሁ በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ ትዋጉማላችሁ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤

2) ምኞታችንን ለማርካት የተሳሳተ ፀሎት ስለ ምንፀልይ

- ያዕ.4÷3

3. ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም።

3) ባለማመንና በመጠራጠር

- ያዕ.1÷6-7

6. ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና።
7-8 ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው።

በጥርጣሬ ሕይወት መፀለይ ለፀሎት መልስ እንቅፋት ነው፡፡

4) ያልተናዘዘ ኃጢአት በውስጣችን በመኖር

- መዝ.66÷18

18. በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር።

5) በሰይጣን ተቃውሞና በሁከት ስለሚንኖር

- ዳን.10÷12-14

12. እርሱም እንዲህ አለኝ። ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ።
13. የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሀያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ እነሆም፥ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት።
14. ራእዩም ገና ለብዙ ዘመን ነውና በኋለኛው ዘመን ለሕዝብህ የሚሆነውን አስታውቅህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ

6) በዓለም ሀሳብ ውስጥ ስለሚንኖር

ክርስትና ማለት የፀሎት ሃይማኖት ነው፡፡ ፀሎት ለሁሉም ችግሮች መፍትሔ የሚሰጥ ነው፡፡ እኔ መታዘዝ የሚገባ ነገር ፀሎት ነው፡፡ ፀሎት ሲኖር ማደግ አለ፡፡

- 2ጢሞ 3÷1-7

1. ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ።
2. ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥
3. ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥
4. ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤
5. የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ።
6-7 ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፥ ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትንም የሚወሰዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ፥ ከእነዚህ ዘንድ ናቸውና።

5. ጥሩ የፀሎት ዘዴና አቋም ምንድን ነው?

1) በኢየሱስ ስም መፀለይ ነው፡ ፡እንደ ፈቃዳችን ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መፀለይ አስፈላጊ ነው፡ ፡

- ዮሐ.16÷24

24. እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።

2) ከእግዚአብሔር እኛን ያለያየውን ኃጢአት በማጥፋት፤ ኃጢአትን በመናዘዝ መጸለይ፡ ፡

- ኢሳ.59÷1-2

1. እነሆ፥ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፥ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም
2. ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፥ እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።

3) እንደ ዕቅዳችን ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር እቅድ መፀለይ

- ምሳሌ 19÷21

21. በሰው ልብ ብዙ አሳብ አለ የእግዚአብሔር ምክር ግን እርሱ ይጸናል።

4) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመታዘዝ ልብ መፀለይ

- ዮሐ.15÷10

10. እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ።

5) እስከ መጨረሻ በእምነት በመታገስ መፀለይ

- ሉቃ.18÷1-8

1. ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፥
2. እንዲህ ሲል፦ በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ።
3. በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፥ ወደ እርሱም እየመጣች። ከባላጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር።
4. አያሌ ቀንም አልወደደም፤ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ። ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር፥
5. ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜም እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ።

6. ጌታም አለ። ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ።
7. እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን?
8. እላችኋለሁ፥ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል። ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?

6) ያለጥርጣሬ መፀለይ

- ያዕ.1÷6

6. ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና።

7) የእግዚአብሔርን ቃል በመጠበቅ መፀለይ

- 1ጴጥ.2÷2

2-3 ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ እንደ ሃሳባችን ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

8) የመልስ ምልክት እስከምናይ ድረስ መፀለይ፤

ኤልያስ ትንሽ እጅ የምታህል ደመና እስከ ሚገለጥ ድረስ ፀለየ፡፡

- 1ነገ.18÷44

44. በሰባተኛውም ጊዜ። እነሆ፥ የሰው እጅ የምታህል ታናሽ ደመና ከባሕር ወጥች አለ። እርሱም፡- ወጥተህ አክዓብን፡- ዝናብ እንዳይከለክልህ ሰረገላን ጭነህ ውረድ በለው አለ።

6. የፀሎት መልስ እግዚአብሔር የመኖርና እኛን የመውደዱ ምስክር ነው፡፡

1) ሥጋችንና መንፈሳችን እንዲጠናከር የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡

- 3ዮሐ.1÷2

2. ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።

2) ሕይወታችን የተትረፈረፈ ሕይወት እንድኖር ያደርጋል፡፡

- ዮሐ.10÷10

10. ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።

3) እግዚአብሔር የተትረፈረፈ ኑሮ ይሰጣል፡፡

- ሮሜ.8÷32

32. ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?

4) ሳንጠራጠር የምንፀልየውን ጌታ ይመልስልናል፡፡

- ፊልጵ.4÷6

6. ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።

5) ጌታ ብዙ ፍሬ እንድናፈራ ያደርጋል፡፡ጌታ የወይኑ ግንድ ሲሆን እኛ ደግሞ የወይኑ ቅርንጫፎቹ ነን፡፡

- ዮሐ.15÷4-5

4. በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም።

5. እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።

★ በሥራ ላይ የምናውል፡- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸውንና በሥራ ላይ ልታውል የፈለግኸውን ዕፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት፡- የፀሎት ምላሽና ፅኑ የእምነት በረከትን ለመቀበል በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ አምስት

5. ምሪትን በመቀበል የማሸነፍ ፅኑ እምነት (ኤፌ.6÷10-13)

- ኤፌ.6÷10-13

10. በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።
11. የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።
12. መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።
13. ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።

ሕይወት ትግል ናት፡፡ አንተ ብትፈልግ ባትፈልግም ሕይወት ትግል ነው፡፡ ትግልን የሚያሸንፍ ሰው አለ፡፡ደግሞም በትግሉ የሚወድቅ የሚጎዳ የሚሞት ሰው አለ፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ምሪት የሚቀበሉ ሰዎች በፍፁም ያሸንፋሉ፡፡ እግዚአብሔር ለራሱ ልጆች ከሰጠው ተስፋዎች ውስጥ አንዱ ሕይወታችንን በበጎነት ወደ ፅድቅ መንገድ መምራት ነው፡፡ ስለዚህ የሚያምኑ ሰዎች በስቃይና በመከራ ቢኖሩም ወድቀው አይሸፉም፡፡ ምክንያቱም በመጨረሻ አሸናፊዎች ስለሆኑ ነው፡፡ ይህንን ተስፋ አምነሃል?

★ እግዚአብሔር አሁን ስለ እኛ ምን ይሠራል?

1. እግዚአብሔር እኛን ከማንኛውም ችግሮች ረድቶ አሸናፊዎች ያደርጋል፡፡
   - 1ቆሮ.10÷13

   13. ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።
2. እኛን ያበረታታናልና ይጠበቃልም፡፡
   - 1ተሰ.3÷3

   3. በዚህ መከራ ማንም እንዳይናወጥ፥ ለዚህ እንደ ተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና።
3. ድካማችንን አይቶ አይንቅም ይራራልናል፡፡
   - ዕብ.4÷15

   15. ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።
4. በፈተና ሁሉ ይረዳናል፡፡
   - ዕብ.2÷18

   18. እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።
5. ስለ እኛ ይማልዳል
   - ሮሜ.8÷34

   34. የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።
6. መንፈስ ቅዱስ ድካማችንን እንዲያግዝ ያደርጋል፡፡
   - ሮሜ.8÷26

   26. እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤

ውጤት፡- እግዚአብሔር እኛን ስለሚመራ አሸናፊዎች ነን፡፡

1. ሕይወት ትግል ነው፡፡ በየትኛው ትግል ውስጥ እንዳለህ ከሚቀጥለው መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ውስጥ አግኝ፡፡

1) ሐዋ.8÷4-8 የስጋ ጦርነት (ትግል) በምኞት በህልም ውስጥ ትግል አለ፡፡
- ሐዋ.8÷4-8

4. የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።
5. ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው።
6. ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ።
7. ርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤
8. በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።

2) ኤፌ.2÷3 የአዕምሮ ህመም ትግል ማለትም ሐዘንና ስቃይ መቀበል፡፡
- ኤፌ.2÷3

3. በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።

3) ኤር.17÷9 የእርስ በእረስ ትግል (ጦርነት)
ራሱን በራሱ የሚገድል 47%
ፍቺ(የጋብቻ መፍታት) 46%
- ኤር.17÷9

9. የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?

4) ዘፍ.3÷17 የኢኮኖሚ ጦርነት
- ዘፍ.3÷17

17. አዳምንም አለው። የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ

5) ኤፌ.6÷12 የመንፈስ ጦርነት (ትግል)
- ኤፌ.6÷12

12. መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

2. ለምን ብዙ ሰዎች በሥጋዊ ጦርነት ይወድቃሉ?

1) በቃሉ ስለ ማይመኩ

- ሮሜ.10÷17

17. እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።

2) የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስለማያውቁ

- ሮሜ.8÷13-14

13. እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ።
14. በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።

3) የሰይጣንን የውጊያ ስልት ስለማያውቁ

- ኤፌ.6÷10-12

10. በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።
11. የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።
12. መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

4) የተልዕኮ ሕይወት ስለጠፋ

ስለ ወደፊት ቀን አለመረዳት በፍፁም ያስወድቃል፤ ይህ ደግሞ ሞኝነት ባዶ ከንቱ ያለማወቅ ሕይወት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ፍፁም አሸናፊ ለመሆን የእግዚአብሔርን ምሪት መቀበል ያስፈልጋል፡፡

- ዮሐ.21÷3-4

3. ስምዖን ጴጥሮስ፦ ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ አላቸው። እርሱም፦ እኛም ከአንተ ጋር እንመጣለን አሉት። ወጥተውም ወደ ታንኳይቱ ገቡ በዚያችም ሌሊት ምንም እላጠመዱም።
4. በነጋም ጊዜ ኢየሱስ በባሕር ዳር ቆመ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም።

3. ሥጋዊ ጦርነት በሚንዋጋበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመራ ከመፅሐፍ ቅዱስ ፈልገህ አግኝ

1) እስራኤላውያንን በምድረ በዳ እንዴት መራ?

እግዚአብሔር ከፈታቸው እየቀደመ መራቸው፡፡

- ዘፀ.13÷21-22

21. በቀንና በሌሊትም ይሄዱ ዘንድ፥ መንገድ ሊያሳያቸው ቀን በደመና ዓምድ፥ ሊያበራላቸውም ሌሊት በእሳት ዓምድ እግዚአብሔር በፊታቸው ሄደ።
22. የደመና ዓምድ በቀን፥ የእሳት ዓምድ በሌሊት ከሕዝቡ ፊት ከቶ ፈቀቅ አላለም።

2) ከጠላቶቻችን እንዴት ይረዳል? እግዚአብሔር በአራቱ አቅጣጫ ሁሉ በመጠበቅ ከጠላቶቻችን ይጠብቀናል፡፡

- 2ዜና.32÷22

22. እንዲሁም እግዚአብሔር ሕዝቅያስንና በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ከአሦር ንጉሥ ከሰናክሬም እጅ ከሁሉም እጅ አዳናቸው በዙሪያቸውም ካለው ሁሉ አሳረፋቸው።

3) እንዴት ነው እግዚአብሔር እኛን የሚመራው?

እግዚአብሔር እንደ ዓይኑ ብለን በመጠበቅ ይመራል፡፡

- መዝ.32÷8

8. አስተምርሃለሁ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጠናለሁ።

4) እስራኤላዊያን ቀይ ባህርን ከፍሎ እንዲሻገሩ እንዴት ነበር የመራቸው?

በሰላም እየመራቸው ያለምንም ጉዳት ቀይ ባህርና በማሻገር መራቸው፡፡

- መዝ.78÷52-53

52. ሕዝቡን ግን እንደ በጎች አሰማራቸው፥ እንደ መንጋም በምድረ በዳ መራቸው።
53. በተስፋም መራቸው አልፈሩምም፥ ጠላቶቻቸውንም ባሕር ደፈናቸው።

5) እኛን እስከ መቼ ይመራል?

① ዘወትር

② እስከ መንግሥተ ሰማይ ድረስ

③ በየቀኑ በጌታ ዕውቀት እንዲንሄድና እንድናድግ፡፡

- መዝ.121÷3-8

3. እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም የሚጠብቅህም አይተኛም።

4. እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም።
5. እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፥ እግዚአብሔርም በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል።
6. ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም ጨረቃም በሌሊት።
7. እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፥ ነፍስህንም ይጠብቃታል።
8. ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህና መግባትህን ይጠብቃል።

- መዝ.73÷24

24. በአንተ ምክር መራኸኝ ከክብር ጋር ተቀበልኸኝ።

4. የእግዚአብሔርን ምሪት ስንቀበል ምን እንሆናለን?

1) ለፀሎት ሕይወታችንን እንሰጣለን

የእኛን የመቃተታችን ድምፅ ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን

- መዝ.37÷5

5. መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፥ በእርሱም ታመን፥ እርሱም ያደርግልሃል።

2) እግዚአብሔርን ብቻ እናምናለን፡፡

ሰላም እስከምንቀበል ድረስ በእምነት መፀለይ አለብን፡፡

- ፊልጵ.4÷6-7

6. ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።
7. አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።

3) እንታዘዛለን

አብርሃም እንደ ታዘዘ ከአብርሃም ሕይወት መታዘዝን እንማራለን በክፉ ቀን የሚረዳና የሚጠቅም ሰው ሲጠፋም በእምነት መታዘዝ ያስፈልጋል፡፡

- ዕብ.11÷8-10

8. አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፥ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ።
9. ለእንግዶች እንደሚሆን በተሰፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ፥ ያን የተስፋ ቃል አብረውት ከሚወርሱ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር፥ እንደ መጻተኛ በእምነት ተቀመጠ፤
10. መሠረት ያላትን፥ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና።

5. ምሪትን በመቀበልና በማሸነፍ ፅኑ እምነት ኑር፡፡

1) እግዚአብሔር ለልጆቹ ምን ይሰጣል?

የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ሥልጣን ይሰጣል፡፡

- ዮሐ.1÷12

12. ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤

2) ፈተናንና ችግሮችን እንድናሸንፍ እግዚአብሔር ለእኛ ምን ይሰጣል?

ፈተናንና ችግሮችን እንድናሸንፍ መሸሸጊያ መንገድን ይሰጣል፡፡ የእግዚአብሔርን ተስፋ ልናምን ያስፈልጋል፡፡

- 1ቆሮ.10÷13

13. ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።

3) ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ምንድን ነው ያሸነፈው?

አለቆችንና ባለስልጣናትን ሁሉ አሸነፈ፡፡

- ቆላ.2÷13-15

13. እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ። በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ።
14. በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው። እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል።
15. አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።

4) በጌታ በኢየሱስ ስም ድፍረትን ማግኘት እንችላለን?

በኢየሱስ ስም ስናምንና ስንታዘዝ ማግኘት እንችላለን፡፡

- ሉቃ.10÷17-19

17. ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።
18. እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።
19. እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።

5) መንፈስ ቅዱስን በብዙ ሲንቀበል ምንድነው የምንገልፀው?
መንፈስ ቅዱስ ሲበዛ ሥልጣኑን ይገልፃል
- ሐዋ.1÷8

8. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

6) ለክርስቲያኖች መከራ አላቸው፤ ነገር ግን ውድቀት የላቸውም፤ የእናንተ ውሳኔ ምንድን ነው?
የእኔ ውሳኔ አሸናፊ ሰው ሆኜ መኖር ነው፡፡
- ፊልጵ.4÷13

13. ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።

★ በሕይወቱ አሸናፊ የሆነ ሰው ምን ያደርጋል?

1. በማንኛውም ውጊያ ውስጥ መንፈሳዊ ጦርነት እንዳለ ያውቃል
   - ኤፌ.6÷12

   12. መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።
2. አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ሰዎች የሚገስፅበት ሁኔታ እንዳለ ያውቃል
   - ዕብ.12÷5-6

   5-6 እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር። ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል።
3. በመከራ ጊዜ ጽኑ እምነት እንደሚኖር ያውቃል፡፡
   - ኢዮብ.13÷5

   5. ምነው ዝም ብላችሁ ብትኖሩ! ይህ ጥበብ በሆነላችሁ ነበር።
4. መከራ ስደርስበት በምስጋና በእግዚአብሔር ፊት መቅረብን ያውቃል፡፡
   - 1ጴጥ.4÷13

   13. ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ፥ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ።
5. መከራ ሲመጣ በእምነታችን ፍፁማን እንዲንሆን ስለሚያደርግ ይታገሳል፡፡
   - ያዕ.1÷2-4

   2-3 ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት

   4. ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።
6. መከራ ሲኖር እግዚአብሔር በሕይወቱ ላይ ሥልጣን እንደሆነ ይረዳል
   - ኤፌ.6÷10

   10. በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።

★ በሥራ ላይ የምናውል፡- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸውንና በሥራ ላይ ልታውል የፈለግከውን ፅፈህ ከጓደኞችህ ጋር ህብረት አድርግ፡፡

★ ፀሎት፡- ምሪትን በመቀበል የአሸናፊነት ፅኑ እምነት ለማግኘት በውሳኔ ልትፀልይ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ስድስት
6. የመንፈስ ቅዱስ ቅባት የተትረፈረፈ ክርስቲያን (ኤፌ.5÷18)

● ኤፌ.5÷18
18. መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤

በሁሉም ሰው ልብ ውስጥ እግዚአብሔርን የመፈለግ ሀሳብ አለው፡፡ ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች ጥልቅ እምነት ለማገኘት ይፈልጋሉ ነገር ግን ሳያገኙ ይባዝናሉ፡፡ የዛሬ ቀን የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ የሚበዛበት ቀን ነው፡፡ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ምንም አያውቁም፡፡

ደግሞም የፅድቅ ሕይወት የላቸው፤ ስለዚህ የክርስትና ሕይወትና ደስታ አይሰማቸውም፡፡ በክርስትና ሕይወት ብዙ ፍሬ ቢያፈሩ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጥሩ ህብረትን ማድረግ ይቻላል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? በመንፈስ ቅዱስ ፀጋ መትረፍረፍስ ምንድን ነው? የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተቀብለህ ትታዘዛለህ? ይህ መንፈስ ቅዱስ ሲበዛ ከባለስልጣናትና ከአለቅነት እንዲሁም ከተራ ሃይማኖተኝነት ለመውጣት ድፍረትን ይሰጣል፡፡

★ የመንፈስ ቅዱስ መብዛት ግብ

1. የደህንነትን ፈቃድ ያስገኛል
   ● ሮሜ.8÷16
   16. የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።
2. መንፈስ ቅዱስ የሕይወታችን ጌታ ነው፡፡
   ● 1ቆሮ.3÷16-17
   16. የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?
   17. ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።
3. ስለ ኢየሱስ እንዲንመሰክር ያደርጋል፡፡
   ● ሐዋ.1÷8
   8. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።
4. ለሚመሰክሩ ሰዎች ሥልጣን ይሰጣል፡፡
   ● ሉቃ.24÷48-49
   48. እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ።
   49. እነሆም፥ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።

   ● ሐዋ.1÷8
   8. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

1. መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

1) መንፈስ ቅዱስ ከስላሴ አንዱ ነው፡፡

እግዚአብሔር አብ ፣ እግዚአብሔር ወልድ(ኢየሱስ) ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ።

- ማቴ.28÷18-20

18. ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።

19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

2) መንፈስ ቅዱስ ችሎታ(ዕውቀት)፣ስሜት፣ፈቃድ ያለው ነው፡፡

① ዕውቀት አለው ሲንል

መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገር ያውቃል ይችላል፡፡

- 1ቆሮ.2÷10

10. መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሰንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።

- ሮሜ.8÷27

27. ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።

② ስሜት አለው ሲንል

መንፈስ ቅዱስ ይደሰታል ያዝናል

- ኤፌ.4÷30

30. ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።

③ ፈቃድ አለው ሲንል

- 1ቆሮ.12÷11

11. ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።

መንፈስ ቅዱስ ይፈቅዳል፤ ይወስናል፤ በሌላ ቋንቋ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድና ውሳኔ አለው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሳይቀበል ወደ ጥልቅ ክርስትና ዓለም ውስጥ መግባት አይቻልም፡፡

④ መንፈስ ቅዱስ ይረዳናል፡፡

- ዮሐ.14÷16-17

15-16 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤

17. እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።

2. ሐዋ.1÷4 የአብ ተስፋ ተብሎ የተነገረው ነገር ምንድን ነው? መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

- ሐዋ.1÷4

4. በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።

3. ኢየሱስ ክርስቶስን ያመኑ ሰዎች ደህንነትን ይቀበላሉ፡፡ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ካልተቀበሉ እምነታቸው ሥልጣን የላቸውም፡፡ እንዴት ነው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት መቀበል የሚቻለው?

1) አስቀድሞ የመንፈስ ቅዱስን ምንነት በማወቅ፡፡ በቁጥር አንድ ላይ መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ የተሰጠውን መልሶችን ተመልከት

2) እውነተኛ ንስሐ በመግባት፡፡

- ሐዋ.2÷38

38. ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

3) እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ቅባት እንደሚሰጥ በተስፋ በማመን፡፡

- ሐዋ.2÷39

39. የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።

4) የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በመፈለግ ልብ መፀለይ፡፡

- ሐዋ.1÷14

14. እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።

- ሐዋ.2÷1-14

1. በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥

14. ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ፥ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው። አይሁድ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፥ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሎቼንም አድምጡ።

4. የመንፈስ ቅዱስ ቅባት የመቀበል ውጤት ምንድ ነው?

1) የደህንነትን ሥራ እንዲሠራ ያደርጋል፡፡

- ሐዋ.16÷33

33. በሌሊትም በዚያች ሰዓት ወስዶ ቍስላቸውን አጠበላቸው፥ ያን ጊዜውንም እርሱ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ተጠመቀ፤ የወህኒ ቤት መሪና ቤተሰቡ ደህንነትን እንዲቀበሉ አደረገ፡፡

2) በክርስትና ሕይወት ድፍረትን ይሰጣል፡፡

- 1ቆሮ.14÷18

18. ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤

3) የእግዚአብሔርን ሥልጣን በስጦታችን እንዲንገልጽ ይረዳል፡፡

- ሐዋ.3÷1-8

1. ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር።
2. ወደ መቅደስም ከሚገቡት ምጽዋት ይለምን ዘንድ፥ ሰዎች ተሸክመው መልካም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ በየቀኑ ያስቀምጡት የነበሩ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነ አንድ ሰው ነበረ።
3. እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቅደስ ሊገቡ እንዳላቸው ባየ ጊዜ፥ ምጽዋትን ለመናቸው።
4. ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ትኵር ብሎ ወደ እርሱ ተመልክቶ። ወደ እኛ ተመልከት አለው።
5. እርሱም አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ ወደ እነርሱ ተመለከተ።
6 ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።
7. በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና፥
8. ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፥ ይመላለስም ጀመር፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ።

4) የልብ ደስታ ያበዛል፡፡

- ሮሜ.14÷17

17. የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና።

5) የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሕይወታችን በዝቶ ሕይወታችንን እንዲቀይር ያደርጋል፡፡
በእውነተኛ እምነት ውስጥ መልካም ፍሬዎች ያድጋሉ፡፡

- ገላ.5÷22-23

22. የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።
23. እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።

6) ለዓለም ብርሃን ለምድር ደግሞ ጨው እንዲሆን ያደርጋል፡፡

- ኤፌ.5÷8

8. ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤

7) በሥልጣን ወንጌልን እንዲንመሰክር ያደርጋል፡፡
ለእግዚአብሔር ክብር በድፍረት ወንጌል እንዲሰበክ ያደርጋል፡፡

- ሐዋ.1÷8

8. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

5. መንፈስ ቅዱስ ቅባት አንድ ጊዜ ከተቀበልን በኋላ የሚቀጥል ሁኔታ ስለሆነ ይህ እንዴት እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል?

1) በየቀኑ በመፀለይ፡፡

2) በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና እንዲቃሉ በመኖር፡፡

3) ከኃጢአት በመራቅና ኃጢአትን በመናዘዝ፡፡ ኃጢአትን እስከደም ማፍሰስ ድረስ መዋጋት ያስፈልጋል፡፡

4) ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመኖርና መንፈስ ቅዱስን በመስማት፡፡

5) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወንጌልን በመስበክ ፡፡

6) የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ በሕይወታችን በማፍራት፤ ልባችንን እንድንለውጥ በመፀለይና የፀሎት ሕይወት ልምምድ በማድረግ፡፡

★ በሥራ ላይ የምናውል፡- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸው ነገርና በሥራ ላይ ልታውል የፈለግከውን ነገር ፅፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት፡- ገና የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ያልተለማመደ ሰው ስኖር ለዚያ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት እንዲለማመድ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሰባት

7. እምነታችን እንደ መኪና ቸርኬ ዓይነት ነው፡፡ (ኤፌ.4÷13)

● ኤፌ.4÷13

12-13 ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።

<u>የሂሳብ ጥያቄ መልስ የሚመጣበትን መንገድ ካወቅከው በደንብ መፍትሔን ማግኘት ትችላለህ፡፡ ደግሞም ለክርስትና ህይወት መሠረታዊውን ምንጭ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በዓለም ሲንኖር መሠረታዊ ምንጮችን አውቀን ወደ ሚቀጥለው ምዕራፍ መሸጋገር አለብን፡፡</u>

<u>ቤት የሚሠራ ሰው መሠረቱን በዓለት ላይ እንደሚመሥርት የክርስቲያኖች መሠረት ምንድን ነው? ይህን በቀላሉ ሊገልፀው የሚችለው የመኪና ቸርክ ነው፡፡ የመኪና ቸርክ በእኛ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስን የልባችን ማዕከል ማድረግ በቃል፣ በፀሎት፣ በአምልዕኮ፣ በአገልግሎት፣ በምስክርነት፣ በህብረት አምልኮ ለእግዚአብሔር የመታዘዝ ሕይወት ይገልጻል፡፡ እኛ በሥጋዊ ውጊያ መካከል በየቀኑ አሸናፊዎች መሆን አለብን፤ እግዚአብሔር በሚሰጠው ፀጋ የተትረፈረፈ ህይወት መኖር እንችላለን፡፡</u>



<u>1. ማዕከል ላይ ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ</u>

● ማቴ.6÷33

33. ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።

● ገላ.2÷20

20. ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።

● ዮሐ.15÷5
5. እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።
● 2ቆሮ.5÷17
17. ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

<u>የመኪና ቸርከ ውስጥ ያሉትን የማሽከረከር ሥልጣን ያለው ኢየሱስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ተትረፍርፎ የሚመጣው ባለሥልጣንና ማዕከል ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወታችን ማዕከል ልናደርግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ኢየሱስ ጌታችንና የሕይወታችን ንጉሥ እንደ ሆነ መስማማት አለብን፡፡</u>

<u>1) ሮሜ.11÷36 እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ ፈጣሪና ንጉሥ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ንጉሥነት ብንስማማ የሕይወታችን አቋም እንዴት ይለወጣል?
መልስ፡- እግዚአብሔር ሁሉን ፈጠረ። ሁሉም ለእግዚአብሔር ይመለሳል።</u>
● ሮሜ.11÷36
36. ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

<u>2) እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሁሉ ነገሮች ምንጭና ሁሉንም ነገር የሚያውቅ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለ እኛ ሁሉን ነገር ያውቃል፡፡ ይህ ታሪክ በሕይወታችን ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ምን ዓይነት ትርጉም ይሰጣል? መልስ፡-በሕይወታችን ላይ ጌታ ነው።</u>

● ኢሳ.40÷12-14
12. ውኖችን በእፍኙ የሰፈረ፥ ሰማይንም በስንዝር የለካ፥ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ፥ ተራሮችን በሚዛን ኮረብቶችንም በሚዛኖች የመዘነ ማን ነው?
13. የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ፥ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው?
14. ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረው? የፍርድንም መንገድ ማን አስተማረው? እውቀትንስ ማን አስተማረው? የማስተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?
● 1ዮሐ.3÷20
20. ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም።
● ማቴ.10÷29-31
29. ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም።
30. የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል።
31. እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ።

<u>3) እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ ባለሥልጣን ነው፡፡ የፍጥረታት መሪና ጠባቂ እርሱ ነው፡፡ ስቃይና ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜ ይህ ታሪክ ለእኛ ምን ትርጉም ይሰጣል?
መልስ፡-ፍፁም እምነትን ይሰጣል እግዚአብሔር የተትረፈረፈ ስጦታ እንደሚሰጥ ያስተምረናል፡፡</u>
● መዝ.147÷5
5. ጌታችን ታላቅ ነው፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፥ ለጥበቡም ቍጥር የለውም።
● ኤፌ.3÷20
20. እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥
<u>4) እግዚአብሔር የማይለወጥና ተስፋ ቃሉን ፍፁም የሚያደርግ ነው፡፡
የእግዚአብሔርን ዕቅድ ባናስተውልእግዚአብሔርን ብናምን ምን ጥቅም አለ?
መልስ፡- አገልግሎትና ጥሩ ስራ ይችላል።</u>
● መዝ.102÷27
27. አንተ ግን ያው አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።
● ያዕ.1÷17
17. በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።

<u>2. ቃል፡-</u>
<u>መፅሐፍ ቅዱስ የተፃፈበት ግብ የእግዚአብሔር አዳኝነት ለማሳወቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንድንኖርና የምንፈልጋቸውን ነገሮች የምንቀበልበትን መንገድ ለማሳየት (ለማመልከት) ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስን ሲማሩ በሕይወታቸው ልተገብሩና አቋም ያለው ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡</u>

★ የእግዚአብሔርን ቃል የሚንቀበልበት 5 መንገዶች

1. በመስማት
   - ሮሜ.10÷17

   17. እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።
2. በማንበብ

   ቃሉን በማንበብ ጠቅላላ የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማወቅ ይቻላል፡፡
   - ራዕ.1÷3

   3. ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።
3. በመማር (በመፃፍ)

   በግልና በትናንሽ ቡድን የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርትን በመማር ይቻላል፡፡
   - 2ጢሞ.2÷15

   15. የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።
4. መንገዱን መጠበቅ

   ቃልን የምንጠብቅበት መንገድ ነው፡፡
   - መዝ.119÷9, 11

   9. ጕልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው።

   11. አንተ እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።
5. የጥሞና ጊዜ በመውሰድ (በማሰላሰል)

   እኛ ዕውቀትን በመውሰድ የቃልን ጥልቅ ሚስጢር ማወቅ ይቻላል፡፡ ይህንን ቃል በሕይወታችን ልንተገብር ያስፈልጋል፡፡ በጥልቀት ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ቃሉን በጥልቀት ማወቅ እንድናድግና እንድንቀይር ይረዳናል፡፡
   - መዝ.1÷1-2

   1. ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ።
   2. ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል።

3. ፀሎት፡ -

ፀሎት የመንፈስ እስትንፋስና ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው፡፡ እግዚአብሔር በፀሎት በኩል የራሱን ፈቃድ ለእኛ ይገልፃል፡፡ እኛ ስንፀልይ እግዚአብሔር መልስ ይሰጣል፡፡ ወደ እግዚአብሔር በመፀለይ ፍላጎቶችን እንናገራለን፡፡ ከዚያም የልባችንን ሀሳብ ይካፈላል፡፡ ፀሎት የእግዚአብሔርን ሥልጣን የምንገልፅበት መንገድ ነው፡፡ ስንፀልይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ እናደርጋለን፡፡

- ፊልጵ.4÷6-7

6. ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።
7. አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።

- ዮሐ.15÷7

7. በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።

- ዮሐ.16÷24

24. እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።

1) ዕብ.4÷14-16 ላይ ያለውን ቃል በማንበብ የፀሎት ምንነት በራስህ ቋንቋ ፃፍ፡፡

መልስ፡- ስንፀልይ የሚረዳ ፀጋን ስለ ምንቀበል ወደ ፀጋ ዙፋን በእምነት እንሄዳለን፡፡

- ዕብ.4÷14-16

14. እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።
15. ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንምና።
16. እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።

2) ወደ ማን እንፀልይ?

መልስ፡ -ወደ እግዚአብሔር አብ

ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ባስተማረው ፀሎት በኩል እግዚአብሔር አብን የምናስደስትበት ጥሩ መንገድ እናገኛለን፡፡

- ማቴ.6÷9-13

9. እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ። በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥
10. ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤
11. የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤
12. እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤
13. ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

★ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ሲፀልይ

1. ወደ እግዚአብሔር አብ ፀለየ
2. ለአባቱ ስም ክብር ሰጠ
3. ስለ እግዚአብሔር መንግሥተ ፀለየ
4. የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድሆን ፀለየ
5. ወደ እግዚአብሔር በየቀኑ የሚያስፈልገውን እንዲሰጥ ፀለየ
6. ሌሎችን ይቅር በማለት ልብ እግዚአብሔርን ይቅር እንዲንል ፀለየ
7. ከፈተና እንዲጠብቅ ፀለየ
8. ከክፉ እንድጠብቅ ፀለየ
9. የእግዚአብሔር መንግስት ከፍ እንዲትል ፀለየ

4. አምልኮ፡-

አምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት በዓል ነው፡፡ እግዚአብሔርን እንደዚህ ባለ ሁኔታ በእውነት የሚያመልከውን ሰው ሲያገኝ በአምልኮ በሰላም በረከት ውስጥ ያኖራል፡፡

- ዮሐ.4÷23-24

23. ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤
24. እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።

1) የአምልኮ ትርጉም ፍቺ ፈልገህ አግኝ፡፡

- አምልኮ ማለት እግዚአብሔርን ማክበር ማለት ነው፡፡
- አምልኮ ማለት እግዚአብሔር ለእኛ የሚሰጠውን ታላቅ ፀጋና የእግዚአብሔር ሰፊ ልብ በመውደድ በምስጋና ለእግዚአብሔር በዝማሬ ክብርን መስጠት ማለት ነው፡፡

- ዘፍ.22÷1-5

1. ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፥ እንዲህም አለው፡- አብርሃም ሆይ፡- አብርሃምም፡- እነሆ፥ አለሁ አለ።
2. የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።
3. አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ፥ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፥ እንጨትንም ለመሥዋዕት ሰነጠቀ ተነሥቶም እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ።
4. በሦስተኛውም ቀን አብርሃም ዓይኑን አነሣና ቦታውን ከሩቅ አየ።
5. አብርሃምም ሎሌዎቹን አላቸው፡- አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን፥ ወደ እናንተም እንመለሳለን።

1 ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፥ እንዲህም አለው፡- አብርሃም ሆይ፡- አብርሃምም፡- እነሆ፥ አለሁ አለ።

2) ዮሐ.4÷24

በመንፈስና በእውነት ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው?

እግዚአብሔርን በእውነት ማምለክ ማለት ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስና በኢየሱስ ክርስቶስ እርዳታ ማምለክ ማለት ነው፡፡ አምልኮ የሰው ጥልቅ ሀሳብ የሚመጣበት ነገር ነው፡፡

- ዮሐ.4÷24

24. እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።

3) ሮሜ.12÷1

ሰውነታችንን ሕያውና ቅዱስ መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ ትርጉም ምንድን ነው?

በየቀኑ በሕይወታችን እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ነው፡፡

- ሮሜ.12÷1

1. እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራሄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።

4) ዕብ.13÷15-16

እግዚአብሔርን የሚያስደስት የአምልኮ አቋም ምንድን ነው?

እግዚአብሔርን የሚያምን እምነት፤ ንስሐና መልካም ሥራ ማድረግ እነዚህ ነገሮች እግዚያብሔርን ደስ ያሰኛሉ፡፡

● ዕብ.13÷15-16
15. እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ እናቅርብለት።
16. ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።

5. አገልግሎት፡ -

አገልግሎት ማለት በሥራ ላይ ማሳየት (መተግበር) ማለት ነው፡፡ እኛ ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያንን ስናገለግል ወደ አንድ አካል እስከሚንሆን ድረስ ሊናድግ ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ብዙ ስጦታ ሰጥቷል፡፡ በስጦታችን በኩል ስናገለግል ቤተክርስቲያን ትታነፃለች፤ ክርስቲያኖችም እርስ በርስ ይደሰታሉ፡፡ የአገልግሎት ሕይወት ማሳየት ማለት ፍቅርን ማሳየት ማለት ነው፡፡

● ኤፌ.2÷20-22
20. በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤
21. በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤
22. በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።

1) 1ጴጥ.2÷9 ሁሉም ክርስቲያኖች እንደ ካህናት ናቸው፡፡ ሲል ትርጉሙ ምንድን ነው?
አገልጋዮች ናቸው ማለት ነው፡፡

● 1ጴጥ.2÷9
9. እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤

2) ገላ.5÷13 እያንዳንዱ ምን እንዲያደርጉ ተጠርተዋል?
በፍቅር አንዱን ሌላውን እንደ አገልጋይ እንዲያገለግሉ ነው፡፡

● ገላ.5÷13
13. ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።

3) ኤፌ.4÷12 ክርስቲያኖች እንዴት ያገለግላሉ?
ክርስቲያኖች በቅድስና የክርስቶስ አካል (ቤተክርስቲያንን) በመገንባት ሊያገለግሉ ያስፈልጋል፡፡

● ኤፌ.4÷12
12-13 ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።

4) ስጦታ የሚገኝበት ትምህርት ከወሰድክ ያንተ ስጦታ ምንድን ነው?
በዚህስ ስጦታ እንዴትስ እያገለገልክ ነህ?

6. ምስክርነት (ወንጌል መስበክ)

እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ ለሰው ልጆች ታላቅ ሚስዮን (ተልዕኮ) ሰጥተዋል፡፡
የሰው ልጆች ወደ ዓለም ሄደው ዓለምን በወንጌል እንዲገዙ (እንዲቆጣጠሩ) ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡ ይህ ክፍል ሄደን ምድርን በወንጌል እንድንወርስ (እንድንገዛ) ወይም እንድንቆጣጠር ይናገራል፡፡ ይህ ምድርን ለመግዛት (ለመቆጣጠር) የሚረዳ እውነተኛ መንገድ ወንጌልን መስበክ ነው፡፡ እግዚአብሔር በጣም የሚደሰትበት ሥራና የበረከት መንገድ ነው፡፡ እግዚአብሔር ወንጌልን የሚሰብከው ሰው ታማኝ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

● 2ጢሞ.4÷2
2. ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም።
● ማቴ.4÷19
19. እርሱም፦ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።
● ሮሜ.1÷16
16. በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።
● 1ጴጥ.3÷15
15. ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን።

1) የወንጌል ምስክርነት ምን ማለት እንደሆነ ፃፍ፡፡
ወንጌል መመስከር በወንጌል የተትረፈረፈ ህይወት እንዲኖር መርዳት ማለት ነው፡፡

● ዮሐ.10÷14

14-15 መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ።

2) ሐዋ.16÷1 ጠቅላላ ቁጥሮችን አንብብ የወንጌል ምስክርነት የእግዚአብሔር ሥራ መሥራትና የተዘጋጁ ሰዎችን እንድንወርስ ማስተዋወቅ ማለት ነው፡፡

① ሐዋ.16÷1-15 ሊዲያና ቤተሰቦቹዋ በጌታ ድነዋል፡፡

- ሐዋ.16÷1-15

1. ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራንም ደረሰ። እነሆም፥ በዚያ የአንዲት ያመነች አይሁዳዊት ልጅ ጢሞቴዎስ የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ፤ አባቱ ግን የግሪክ ሰው ነበረ።

15. እርስዋም ከቤተ ሰዎችዋ ጋር ከተጠመቀች በኋላ። በጌታ የማምን እንድሆን ከፈረዳችሁልኝ፥ ወደ ቤቴ ገብታችሁ ኑሩ ብላ ለመነችን፤ በግድም አለችን።

② ሐዋ.16÷19-34 የእስር ቤት አዛዥና ቤተሰቦቹ በጌታ ዳኑ::

ሐዋ.16 ፊልጵዮስ ቤተክርስቲያን እንደገነባ (እንዳነፀ) ይናገራል፡፡

- ሐዋ.16÷19-34

19. ጌቶችዋም የትርፋቸው ተስፋ እንደ ወጣ ባዩ ጊዜ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው ወደ ገበያ በሹማምት ፊት ጐተቱአቸው፤

34. ወደ ቤቱም አውጥቶ ማዕድ አቀረበላቸው፥ በእግዚአብሔርም ስላመነ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ሐሤት አደረገ።

3) ወንጌልን ለሚሰብከው ስጦታው ምንድን ነው? በምድር መቶ እጥፍ በረከት ከሞት በኋላ በመንግሥተ ሰማይ አክሊል አለ፡፡

4) ፍፁም ደህንነት ለመቀበል የሚፈልጉት የሶስት ሰዎች ስም ፃፍ፡፡

①_____

②_____

③_____

ለቤተክርስቲያን ወይም ለመሪዎች (ለወንጌላውያን) እንዲሁም ለመጋቢያን የእነዚህን ሰዎች ስም የተፃፈውን የወረቀቱ ኮፒ በመስጠት ዘወትር ስለሚድኑ ነፍሳት በጌታ ፊት እንዲያስቀምጡና እንዲፀልዩ መስጠት፡፡ ሌላውን ከእነዚያ ሰዎች ጋር የሚገናኘው አገልጋዩ ዘንድ ይቀርና ሁል ጊዜ አገልጋዩም ስለ እነርሱ ይፀልያል፡፡

7. ሕብረት፡-

የክርስቲያኖች ህብረት በእግዚአብሔር እጅ ብቻ ስለተያዘ ልዩ ሥልጣን ነው፡፡ የህብረቱ ማዕከል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ተካፈል ደግሞ በክርስቲያኖች ህብረት እርስ በርስ ተገላገሉ፡፡ እውነተኛውን የክርስቲያኖች ህብረት ክርስቲያኖች ማድረግና የክርስቶስን አካል መገንባት ዋና ጉዳይ ነው፡፡

- ሮሜ.12÷4-5

4. በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥

5. እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።

- ዕብ.10÷24-25

24. ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤

25. በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።

- ዮሐ.13÷34-35

34. እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

35. እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።

1) 1ቆሮ.12÷14-26 አንብበህ የክርስቲያኖች ህብረት የሚፈልጋቸውንና ወሳኝ የሆኑ ነገሮችን ፃፍ፡፡
በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል አንድ ቤተሰብ መሆን ከእያንዳንዳችን ይህ ህብረት ይጠበቃል፡፡

- 1ቆሮ.12÷14-26

14. አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና።

26. አንድም ብልት ቢሣቀይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሣቀያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል።

2) ክርስቲያኖች ፍቅርን ሳይናገሩ እንዴት ይገልፃሉ?
የበሰሉ ሰዎች በመሆናቸውና በአገልግሎታቸው እየበዙ በመሄዳቸው ነው፡፡

3) የክፍሉ ቡድን ስለ ህብረት እርስ በርስ እንዲነጋገሩ አድርግ፡፡ የክፍል ቤተሰብ እያንዳንዱ አምኖ ይሠራሉ፤ በህብረት ባይሆን ሰዎች ይተዋል፤ የትንሽ ቡድን(3-4 ሰዎች) ህብረትና የትልቅ ቡድን ህብረት (ቤተክርስቲያን አምልኮ) ወሳኝ ነው፡፡

8. ለኢየሱስ መታዘዝ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች እንደሚገልጹ መታዘዝ ያለብን እንደ ኢየሱስ እስከ ሞት ድረስ መታዘዝ ነው፡፡
የመኪና ቸርከው ስድስቱን ጠቅላላ አቅፎ የያዘው የክርስቲያኖችን የመታዘዝ ሕይወት ነው፡፡ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለመጠበቅ፣ ለጌታ ለመሥራትና ለመታዘዝ አቋም ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

- ዮሐ.14÷21

21. ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ።

- ሮሜ.12÷1-2

1. እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራሄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።
2. የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።

- ሉቃ.9÷23

23. ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።

- ዮሐ.8÷31-32

31. ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ። እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤
32. እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።

- ዕብ.5÷8

8. ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤

★ መታዘዛችንን በፐርሰንት ሲንገልጽ
ለእግዚአብሔር 100% ብንታዘዝ እምነታችን 100% ያድጋል
ለእግዚአብሔር 50% ብንታዘዝ እምነታችን 50% ያድጋል

1) ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ምን እንዲክዱ ተናገራቸው?
ራሳቸውን ከደው በየቀኑ የራሳቸውን መስቀል ተሸክመው እንዲከተሉ ተናገራቸው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ላይ ጌታ ነው፡፡ በየቀኑ ኢየሱስ ክርስቶስን ስንታዘዝ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ እየገለፅን ነው፡፡ ብናውቅም ባናውቅም ብንረዳም ባንረዳም ብንጠቅምም ባንጠቀምም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልንታዘዝ ያስፈልጋል፡፡

- ሉቃ.9÷23

23. ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።

★ ለማን እንታዘዛለን?
የምንታዘዘው ለእግዚአብሔር፣ ለቤተክርስቲያን ለመጋቢያን ለወንጌላውያን ወዘተ…
የሚንታዘዝበት ምክንያት እግዚአብሔር ሥልጣኑን ስለሰጠ ነው፡፡

2) መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚገልፀው በእምነት የታዘዘ ታላቅ አያት (አባት) አብርሃም ነው፡፡ አብርሃም በምን ሁኔታ እግዚአብሔርን ታዘዘ?
አብርሃም ሳያገባም ጥቅምም ሳያገኝ በእምነት እግዚአብሔርን ታዘዘ፡፡ ስለዚህ ከአብራሃም ሕይወት መታዘዝን ወዲያውኑ ተምረን ልንከተል ያስፈልጋል፡፡

- ዘፍ.22÷1-3 ቁ.9-12

1. ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፥ እንዲህም አለው፡- አብርሃም ሆይ፡- አብርሃምም፡- እነሆ፥ አለሁ አለ።
2. የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።

3. አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ፥ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፥ እንጨትንም ለመሥዋዕት ሰነጠቀ ተነሥቶም እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ።

9. እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ፥ እንጨትንም ረበረበ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው።
10. አብርሃምም እጁን ዘረጋ፥ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ።
11. የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ ጠራና። አብርሃም አብርሃም አለው
12. እርሱም፦ እነሆኝ አለ። እርሱም፦ በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ።
13. አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።

3) የዓለም ታሪክ የሚቀየረው በመታዘዝና ባለመታዘዝ ነው፡፡ የአዳም ያለመታዘዝ ውጤት ምንድን ነው?
አዳም የእግዚአብሔርን ቃል ስላልታዘዘ ሁሉም ሰዎች ከአዳም አለመታዘዝ የተነሳ ኃጢአተኞች ሆኑ፡፡

- ሮሜ.5÷19

19. በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።

4) ኢየሱስ እንዴት ታዘዘ ውጤቱስ ምንድን ነው?
ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን አባት እስከ ሞት ድረስ ታዘዘ፡፡ ኢየሱስ ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የዘላለም ደህንነት ምንጭ ሆነ፡፡

- ዕብ.5÷8-10

8. ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤
9-10 ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ፥ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።

5) ስለ ሚታዘዙ ሰዎች በረከት ምንድን ነው?
በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ መኖር ነው፡፡ እግዚአብሔርን ስንታዘዝ ባልንጀራችን እንደራሳችን እንወደዋለን፡፡ (ዮሐ.14÷23) የሚታዘዝ ሰው የሚወደድ ሰው ነው፡፡

- ዮሐ.15÷10

10. እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ።

- ዮሐ.15÷14

14. እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ።

- ዮሐ.14÷23

23. ኢየሱስም መለሰ አለውም። የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።

- 1ዮሐ.2÷5

5. ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል። በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን፤

★ በሥራ ላይ የምናውል

1. **ከዚህ ምዕራፍ ከመኪና ቸርክ ሕይወት በደንብ ሊትሠራው የፈለግኸውን ነገር ምንድን ነው?**

2. **ለአንተ ጎዶሎ የሆነው የማትሠራበት ሥፍራ የቱ ነው?**

3. **ለአንተ በጣም ጎዶሎ የሆነውን ሥፍራ ለማሟላት የተዘረዘሩ ነገሮች ምንድን ናቸው?**

★ ፀሎት፡- የመኪና ቸርክ ሕይወት ዓይነት ያንተ ሕይወትህ በሚዛን እንደሆን ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወትህ ማዕከል ሆኖ እርሱ እንዲቆጣጠር በደንብ መፀለይ አለበት፡፡

ምዕራፍ ስምንት
8. የጥሞና ጊዜ (quiet time) (መዝ.1÷1-3)

- መዝ.1÷1-3

1. ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ።
2. ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል።

3. እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።

ኢየሱስ ክርስቶስን ስናምን የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን፡፡ ለእግዚአብሔር ልጆች የተሰጠው ልዩ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ጋር የፍቅር ህብረት የመከፋፈል በረከት ነው፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ በኩል የሰው ልጅ ሆኖ ወደ እኛ መጣ፡፡ (ዮሐ.1÷14) ስለዚህ ሁሉም ክርስቲያኖች በቃሉ በኩል የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ መፀለይና ህብረት ማድረግ ይችላል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን በጥልቀትና በመልካም ሁኔታ ማድረግ አለብን፡፡ በቃልና በፀሎት ከጌታ ጋር ተገናኝቶ ህብረት ማድረግ የጥሞና ጊዜ ይባላል (quiet time)

በጠንካራ አለት ላይ የሚኖሩ ሰዎች የጥሞና ጊዜ የምጠቀሙ ሰዎች ናቸው፡፡ በየቀኑ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የጥሞና ጊዜ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ የጥሞና ጊዜ ማለት የመንፈስ ቅዱስ ሙያ ማለት ነው፡፡ ህብረት እያደርግን ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ማለት ነው፡፡ በጥሞና ጊዜ እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ይናገራል፡፡ ለእኔ በፀሎትና ቃሉን በማንበብ ህብረት ሳደርግ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ይናገራል፡፡ ለእኔ የጥሞና ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ወዲያውኑ የሚገናኝበት ጊዜ ነው፡፡

1. የጥሞና ጊዜ ለምን አስፈለገ?

1) የእግዚአብሔርን ድምፅ የሚንሰማበት ጊዜ ስለሆነ

- መዝ.143÷8

8. አንተን ታምኛለሁና በማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ አቤቱ፥ ነፍሴን ወደ አንተ አንሥቻለሁና የምሄድበትን መንገድ አስታውቀኝ።

2) ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚናደርግበት ጊዜ ስለሆነ

- ሉቃ.15÷11-32

11. እንዲህም አለ፦ አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት።

32. ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ ሕያው ስለ ሆነ ጠፍቶም ነበር ስለ ተገኘ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ ይገባናል አለው።

3) በመንፈሳዊና በሥጋዊ ነገር ስለሚያሳድግ

- 2ጢሞ.3÷17

16-17 የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

4) እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም ሙላት ድረስ የሚያሳድግበት መንገድ ስለሆነ
እምነታችንን ልናሳድግ የምንችልበት አጭር መንገድ የጥሞና ጊዜ ነው፡፡

- ፊልጵ.2÷12

12. ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ሁልጊዜ እንደ ታዘዛችሁ፥ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ፥ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤

5) ጠንክረን እንድንቆም ስለሚያደርገን፡፡

- ሐዋ.20÷32

32. አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።

2. ከእግዚአብሔር የቅርብ ህብረት እንዲናደርግ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድን ነው?

1) ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ከአባቱ ጋር ስላስታረቀ የዕርቁን (የመታረቁን) ቃል ስለወሰድን ነው፡፡
የኢየሱስ ደም እኛን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀን፡፡

- ዕብ.10÷19-20

19-20 እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፥

2) እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ህብረት እንድናደርግ ስለፈለገ
በጠዋትና በማታ የጥሞና ጊዜ የሚወስድ ሰው በረከትን የሚቀበል ሰው፡፡

- መዝ.1÷2

2. ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል።

3) የጌታን ድምፅ ለመስማት ስለሚረዳ
ጥሞና ማለት ከእግዚአብሔር ጋር በህብረት መነጋገር ማለት ነው፡፡

- መዝ.95÷7

7. እርሱ አምላካችን ነውና፥ እኛ የማሰማርያው ሕዝብ የእጁም በጎች ነንና።

4) በጥቂት ቃል እግዚአብሔርን ስንገናኝ ዕረፍት ሰላምና ድነት ስለሚገኝ

ጥሞና ጊዜ፤ በጥቂት ጊዜ እግዚአብሔርን በቃሉ በኩል ማየት ማለት ነው፡፡ ጥሞና ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝተን ቃሉን የምንሰማበት ጊዜ ነው፡፡

- መዝ.62÷1, 5

1. ነፍሴ ለእግዚአብሔር የምትገዛ አይደለችምን? መድኃኒቴ ከእርሱ ዘንድ ናትና።
5. ነገር ግን፥ ነፍሴ ሆይ፥ አንቺ ለእግዚአብሔር ተገዢ፥ ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ናትና።

3. የጥሞና ጊዜ የሚስማማ ስለ መሆኑ የተዘረዘሩ ሀሳቦች

1) የጥሞና ጊዜ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የምናደርግበት ነው፡፡ በቃሉ በኩል የእግዚአብሔርን ድምፅ የምንሰማበት ጊዜ ነው፡፡

2) በየቀኑ ከምዕራፍ ከ10-15 ቁጥሮችን ማሰላሰል መልካም ነው፡፡

3) በየቀኑ ከ15 ደቂቃ እስከ 30 ደቂቃ በጥሞና ጊዜ ማሳለፍ ጥሩ ነው፡፡ ብዙ ደቂቃዎችን ለጥሞና ጊዜ መውሰድ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ለጥሞና ጊዜ ቢበዛ 30 ደቂቃ ብቻ በቂ ነው፡፡ በጥሞና ጊዜ እነዚያን የመረጥካቸውን ቁጥሮች ለ15-30 ደቂቃ ደጋግሞ ማንበብ ጥሩ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ድምፅ ሰምተህ መታዘዝ ያስፈልጋል፡፡

4) የጥሞና ጊዜ በትክክል አድርግ (በየቀኑ) የጥሞና ጊዜ ተለማመድ(ልምድ ጥሩ ነው)

5) ለጥሞና ጊዜ ሰዓትን ምረጥ

6) ጠዋት የጥሞና ጊዜ ብትወስድ ይሻላል፡፡

7) የጥሞና ጊዜ መፃፍን አትርሳ፡፡ በየቀኑ የምታሰላስለውን ሁልጊዜ ፃፍ ምክንያቱም ስለምትረሳ ነው፡፡

1882 ዓመተ ምህረት በእንግዚዝ በካምበረጅ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል ሁፋና ደርቶን ወዘተ . . . ከጓደኞቻቸው ጋር የጥሞና ጊዜ ጀመሩ፤ እነዚህ የጥሞና ጊዜ የተጠቀሙ ጓደኞች በሚሲዮናዊነት ወደ ቻይና ሄደው የቻይና ሰዎችን በወንጌል ቀይረዋል፡፡ አሁን ጥሞና ለሚያደርጉ ክርስቲያኞች የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ለተከታታይ ይገለጣል፡፡

4. እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ህብረት መካፈል እንደምንችልና የጥሞና ጊዜ ሳባት ደረጃዎችን እንደምናገኝ ፈልግ?

1) በመጀመሪያ መፅሐፍ ቅዱስ በማንበብ የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት፡፡ በየቀኑ ከ10-15 ቁጥሮች በማቀናጀት ማሰላሰል መፅሐፍ ቅዱስ ስታነብ የእግዚአብሔርን ድምፅ ትሰማለህ፡፡

① በመጀመሪያ ጊዜ ጠቅላላውን በፍጥነት አንብብ፤ ከዚህም ዋና ሰባቦችን ታገኛለህ

② በቀስታ (በዝግታ) ሁለተኛ ጊዜ አንብብ፤ ከዚያም እግዚአሔር የሚናገረውን ቃል ታገኛለህ

③ በሶስተኛ ጊዜ ከሁለተኛውም ቀስ በማድረግ በርጋታ አንብብ፤ የተሻለውን መልእክት ከእግዚአብሔር ለአንተ የሚሰጠውን ቃል ከክፍሉ ትቀበለዋለህ፡፡

2) እግዚአብሔር ምን እንደሚናገር በደንብ አጣርተህ ስማ እግዚአብሔር የሚለውን ማወቅ በጣም ወሳኝ ነው፡፡

3) ከዛሬ ፅሁፍ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ምስጋና፣ ፀሎት፣ የሰጠው ፀጋ ምንድን ነው?

4) እግዚአብሔር ለእኛ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ በመስማትና በመታዘዝ ማግኘት አለብን፡፡ የክፍሉን ሀሳብ ስንታዘዝ የምንቀበለው መፅናናት፣ (ማበረታታት) ተስፋ፣ ማስጠንቀቂያ፣ ወቀሳ፣ የምንከተለውና የማንከተለውን ነገሮች ልናገኝ እንችላለን፡፡

5) ራሳችንን አይተን ሊቀይር የሚፈልግበትን ዝርዝር ነገሮችን ተመልክተን በሥራ ላይ ማዋል አለብን፡፡
ምሳሌ፡- የወላጅ አልባ ህፃናትንና መበለቶችን እንጠብቅ (እንከባከብ) ካለ አቅም በፈቀደ መጠን ሊናደርግ ያስፈልጋል፤

6) የሚገዙ ነገሮችን (የክፍሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን) (ርዕሶችን) በራስ ሀሳብ መፃፍ

7) ዛሬ ያወቅከውን በሥራ ላይ ለማዋል መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

5. በጥሞና ጊዜ የተቀበልከውን የእግዚአብሔርን ቃል በሥራ ላይ እንዴት ማዋል እንዳለብህ የሚረዱ ማስጠንቀቂያዎች፡፡

1) በየቀኑ የምትፈልገውን ቃል ይሰጣል።

2) ለአንተ እስከምገባህ ድረስ እግዚአብሔር እርሱን እንደገና የታውቅበትን ምቹ ጊዜ ያመቻቻል፡፡
ለምሳሌ፡- በጭንቀት አታሰላስል መልዕክቱን ደጋግመህ በቀስታ አንብብ

3) ሌሎች ሰዎች ሳይሆኑ በጥሞና ጊዜ እግዚአብሔር ላንተ(ለእኔ) የተናገረውን መተግበር አለብህ፡፡

4) በጣም ክፉ የሆኑ ነገሮች በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ የተፃፉት እነዚያን ድርጊቶችን አታደርግ፤
ለምሳሌ፡- ግደል ካለ የእግዚአብሔርን ነፍስ መግደል ጥሩ አይደለም፤ እነዚያ ገደሉ እኛም ዛሬ መግደል አለብን ማለት ጥሩ አይሆንም፡፡

5) መፅሐፍ ቅዱስ በምታነብበት ጊዜ ራስህን ፃድቅ አታድርግ በሚታነብበት ጊዜ ኃጢአተኛ እንደሆንክ በማወቅ አንብብ፡፡

6) ከሌሎች ሰዎች ጋር በምትከፋፈልበት ጊዜ አንድ ላይ ሁን! ማስጠንቀቂያዎችን የሚቀበል አስተዋይ ከበደሉ ይነፃል፡፡
እግዚአብሔር በሚሰጠው በሌሎች ፀጋዎች (ስጦታዎች) ይባረካሉ፡፡

★ የጥሞና ጊዜ የማድረግ 8 ጥቅሞች

1. እያንዳንዱን በሥራ ላይ ለማዋልና ለመለማመድ ምቹ ጊዜ ይሰጣል፡፡
2. የራሱን ችግሮች የትኞች እንደሆነ ለይቶ እንዲያውቅ ይረዳል፡፡

3. ከእምነት ድህነት እንዲወጣ ያደርጋል፡፡
4. የሌሎችን ችግሮች በማየት በትዕግስት (በትህትና) እንዲለወጥ ያደርጋል፡፡
5. የማይጠነቀቁና በህይወታቸው ችግሮች የበዛባቸው ሰዎች መሆናቸውን በማወቅ በጌታ ብቻ መታመን እንዳለበት ያስገነዘባል፡፡
6. እውነተኛ የፍቅር ህብረትን ይገልጣል፡፡
7. ህብረተሰቡን ያሳድጋል
8. የጥሞና ጊዜ አብሮ መጸለይ ያስፈልጋል፡፡

6. የጥሞና ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ የሚናገረውን የምንሰማበት ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ በጥሞና ሰዓት የሚሰማውን ቃል በፀሎት መጀመር ያስፈልጋል፡፡

1) 2ሳሙ.7÷18-29 ነቢዩ ናታን የእግዚአብሔርን ቃል (ድምፅ) ሰምቶ ወደ ዳዊት መጥቶ ዳዊትን ለእግዚአሔር እንዴት መፀለይ አለብህ? ብሎ ሲጠይቅ፡፡ ዳዊትም ሲመልስ በንስሐና በመታዘዝ መፀለይ እንዳለበት ተናገር፡፡

- 2ሳሙ.7÷18-29

18. ንጉሡ ዳዊትም ገባ፥ በእግዚአብሔርም ፊት ተቀምጦ እንዲህ አለ፡- ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ፥ እስከዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ?

29. ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ፥ አንተ ተናግረሃልና አሁን እንግዲህ ለዘላለም በፊትህ ይሆን ዘንድ የባሪያህን ቤት፥ እባክህ፥ ባርክ በበረከትህም የባሪያህ ቤት ለዘላለም ይባረክ።

2) ዘፍ.15÷1-9 የእግዚአብሔር እርግጠኝነት ሳያውቅ አብርሃም እግዚአብሔርን በፀሎት እንዴት ታዘዘ? አብርሃም የታዘዘውን እንደገና እግዚአብሔርን ጠይቆ ምላሽ በማግኘት ነው፡፡ የጌታን ቃል በሕይወትህ እንዴት መተግበር እንዳለብህ የሚረዳ ጥሩ ምሳሌ ግለፅ፡፡ ስትታዘዝ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በ5 ዳቦና በ2 ዓሣ አምስት ሺህ ሰዎችን መግቦ 12 መሶብ እንዳተረፈ አንተም በሕይወትህ ታአምራት ማየት ትጀምራለህ፡፡

- ዘፍ.15÷1-9

1. ከዚህ ነገር በኋላም የእግዚአብሔር ቃል በራእይ ወደ አብራም መጣ፥ እንዲህ ሲል፡- አብራም ሆይ፥ አትፍራ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው።
2. አብራምም፡- አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፥ ምንን ትሰጠኛለህ? እኔም ያለ ልጅ እሄዳለሁ የቤቴም መጋቢ የደማስቆ ሰው ይህ ኤሊዔዘር ነው አለ።
3. አብራምም፡- ለእኔ ዘር አልሰጠኸኝም እነሆም፥ በቤቴ የተወለደ ሰው ይወርሰኛል አለ።
4. እነሆም፥ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል መጣለት፡- ይህ አይወርስህም ነገር ግን ከጉልበትህ የሚወጣው ይወርስሃል።
5. ወደ ሜዳም አወጣውና፡- ወደ ሰማይ ተመልከት፥ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸው ትችል እንደ ሆነ ቍጠር አለው። ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል አለው።
6. አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።
7. ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ እንድሰጥህ ከከለዳውያን ዑር ያወጣሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለው።
8. አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንድወርሳት በምን አውቃለሁ? አለ።
9. እርሱም፡- የሦስት ዓመት ጊደር፥ የሦስት ዓመት ፍየልም፥ የሦስት ዓመት በግም፥ ዋኖስም፥ ርግብም ያዝልኝ አለው።

3) በጥሞና ጊዜ በኩል ኃጢአቶችን ካወቅህ በኋላ የኃጢአት ዓይነቶችን በመግለፅ ንስሐ ልትገባ ያስፈልጋል፡፡ ለሕይወትህ የእግዚአብሔርን ቃል የሚለውን ጠቅላላውን መተግበር አለብህ፡፡

- ማቴ.14÷13-21

13. ኢየሱስም በሰማ ጊዜ ከዚያ ብቻውን ወደ ምድረ በዳ በታንኳ ፈቀቅ አለ፤ ሕዝቡም ሰምተው ከከተማዎቹ በእግር ተከተሉት።
14. ወጥቶም ብዙ ሕዝብ አየና አዘነላቸው ድውዮቻቸውንም ፈወሰ።
15. በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው። ቦታው ምድረ በዳ ነው አሁንም ሰዓቱ አልፎአል፤ ወደ መንደሮች ሄደው ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት አሉት።
16. ኢየሱስም፡- እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው እንጂ ሊሄዱ አያስፈልግም አላቸው።
17. እርሱም፡- ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር በዚህ የለንም አሉት።
18. እርሱም፡- እነዚያን ወደዚህ አምጡልኝ አላቸው።
19. ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፥ አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፥ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ።
20. ሁሉም በልተው ጠገቡ፥ የተረፈውንም ቁርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ።
21. ከሴቶችና ከልጆችም በቀር የበሉት አምስት ሺህ ወንዶች ያህሉ ነበር።

4) ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን ለተከታታይ ማድረግ መንፈሳዊ ሕይወታችን በፍፁም እንዲያድግ ያደርጋል፡፡ የጥሞና ጊዜ አስተካክለህ ከያዝክ መንፈሳዊ ህይወትህ ያድጋል፡፡ ነገር ግን ካለደገ ያለማደጉ ምክንያት ምንድን ነው? ምሳሌ፡- የእግዚአብሔር ቃል በሥራ ያለማዋል (ያለመተግበር) ነው፡፡

- ማር.10÷35-45

35. የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ወደ እርሱ ቀርበው። መምህር ሆይ፥ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንወዳለን አሉት።

45. እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።

5) ቃሉን ለመተግበር እኛ የእግዚአብሔርን እርዳታ መፈለግ ያስፈልጋል፡፡ በእኛ ሥልጣን የእግዚአብሔርን ቃል ፍፁም መጠበቅ አንችልም፡፡ ይህ ደግሞ አስቸጋሪ ነው፡፡

በምንናገረው ቃል መሰረት ስለ ፀሎታችን ምን ዓይነት አቋም ይነግረናል?

ምሳሌ፡- በእምነት መፀለይ እንዳለብን ይገልፅልናል፡፡ ደግሞም የሥጋ ምኞታችን እንዳይወስደን መፀለይ ያስፈልጋል፡፡

- ዕብ.11÷6

6. ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።

7. የጥሞና ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን የምናደርግበትና ማንነቱን የምናይበት ጊዜ ነው፡፡

እኛ ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ግንኙነት በኩል እኛ መንፈሳዊና ሥጋዊ ዕድገቶችን የምናይበት ነው፡፡

★ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ሲናደርግ የሚኖሩ እድገቶች

1) የዕውቀት ዕድገት፡- የተፃፈውንና የምንሰማውን ዋና ቃል ሀሳብ ለይተን እናውቃለን የእግዚአብሔርን ማንነት ደግሞ እንረዳለን፡፡

2) የስሜት ዕድገት፡- የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ የሚገልፀው ስሜት ስለተቀበልነው ፀጋ እግዚአብሔርን በፀሎት በምስጋና፣ በአምልኮና በምስክርነት እንዲናመሰግን ያደርጋል፡፡

3) የፈቃድ ዕድገት:- የሚናደርገውንና የማናደርገውን ለይተን እንዲናውቅ ያደርጋል፡፡ ከእነዚህ ነገሮች ዕድገት ያገኛል፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የጥሞና ጊዜ የሚያሳልፍ ሰው 60% ስሜትን ያስባል፡፡

25% ዕውቀትን ያስባል፡፡

15% ፈቃድን ያስባል፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል (ድምፅ) ለመስጣት የጥሞና ጊዜ ተጠቀም

የጥሞና ጊዜ ሲያድግ

ስሜት 40% ከቃሉ የተሰማው

ዕውቀት 30%

ፈቃድ 30%

የጥሞና ጊዜ የተስተካከለ ሲሆን ሁሉም ነገሮች እኩል ሚዛኑን የጠበቁ ይሆናሉ፡፡

8. የጥሞና ጊዜ ለሁሉም ሕይወት ውጤት እንዲኖረው እንዴት ልንለማመድ እንችላለን?

1) የሕፃንነት ህይወት ማለትም በእምነት ሊጋ የመሆንን ሕይወት በማስወገድ

- ዕብ.6÷1

1-2 ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ መሠረትን ደግመን አንመሥርት፥ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት፥ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን ስለ ሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው።

2) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ

- ሮሜ.12÷2

2. የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።

3) ራዕይን በመጠበቅ

- ምሳሌ29÷18

18. ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል ሕግን የሚጠብቅ ግን የተመሰገነ ነው።

4) ከእግዚአብሔር ጋር በመኖር

- ዘፍ.5÷21-24

21. ሄኖክም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ኖረ፥ ማቱሳላንም ወለደ

22. ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ ማቱሳላንም ከወለደ በኋላ የኖረው ሁለት መቶ ዓመት ሆነ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ።

23. ሄኖክም የኖረበት ዘመን ሁሉ ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ሆነ።

24. ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና።

5) ለሕይወት ዘመናችን የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅና ለመፈለግ የጥሞና ጊዜ በማድረግና ጥበብን ወደ ሚሰጠው መንገድ በመሄድ፡፡

● ማቴ.7÷14
14. ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።
6) ያለማቋረጥ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ልምምድ ማድረግ
● ዕብ.5÷13-14
13. ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤
14. ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።

★ የጥሞናን ጊዜን የምትለማመድበት መንገድ

1. የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል መምረጥ =>(ዘዳ.6÷1-9)
   ● ዘዳ.6÷1-9
   1-2 አንተ ልጅህም የልጅ ልጅህም በዕድሜአችሁ ሁሉ ልትወርሱአት በምትገቡባት ምድር ታደርጉአት ዘንድ፥ አምላክህን እግዚአብሔርን ፈርተህ እኔ ለአንተ ያዘዝሁትን ሥርዓቱንና ትእዛዙን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ፥ ዕድሜህም ይረዝም ዘንድ፥ አምላካችሁ እግዚአብሔር እንዳስተምራችሁ ያዘዛት ትእዛዝና ሥርዓት ፍርድም ይህች ናት።
   3. እንግዲህ፥ እስራኤል ሆይ፥ ስማ መልካምም እንዲሆንልህ፥ የአባቶችህም አምላክ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ ወተትና ማር በምታፈስሰው ምድር እጅግ እንድትበዛ፥ ታደርጋት ዘንድ ጠብቅ።
   4. እስራኤል ሆይ፥ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው
   5. አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።
   6. እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ።
   7. ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው።
   8. በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው በዓይኖችህም መካከል እንደክታብ ይሁንልህ።
   9. በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው።

2. ዋና ሀሳብ ፈልጎ ማግኘት
3. የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ስታነብብ የተሰማ ስሜትን መፃፍ
4. እግዚአብሔር ምን አለ? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት
5. የተቀበልከው የፀጋና የምስጋና ቃል ከክፍሉ ለይቶ ማውጣት
6. ለሕይወትህ የተቀበልከው ትምህርት መፃፍ
7. ከክፍሉ ሀሳብ ልብህን የነካውን ሊትተገብር የወሰንከውን ፈፅሞ ያንኑ በማስታወሻ ላይ ፃፍ፡፡
8. ፀሎት - ከክፍሉ ስለ ፀሎት የተማርከው ነገር

★ ምሳሌ -ልምምድ

1. የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል፡- (ዘዳ.6÷1-9)
2. ዋና ሀሳብ፡- እግዚአብሔርን የመውደድ መንገድ
3. ከመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል የተሰማውን ስሜት፡- እስራኤላዊያንና እኛ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተን ብናድግ እንባረካለን፡፡
4. እግዚአብሔር ምን አለ? እግዚአብሔር አንድ አምለክ መሆኑን በመግለፅ እኔን ብቻ አምልኩ አለ፡፡
5. የተቀበልከው ፀጋና ምስጋና፡- በልቤ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብዬ ለልጆች ማስተማር
6. ትምህርት፡- ከፍፁም ፈቃድና ከፍፁም ሥልጣን እግዚአብሔርን መውደድ ነው፡፡
7. ትግበራ (በስራ ላይ ማዋል)፡- በማንኛው ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል መስበክን ነው፡፡
8. ፀሎት፡- በፍፁም ልብ በፍፁም ፈቃድ በፍፁም ስሜት እግዚአብሔርን እንዲንወድና የእግዚአብሔርን ቃል በኃይል የሚሰብክ ሰው እንዲያደርገኝ እፀልያለሁ፡፡

★ በሥራ ላይ የምናውል፡- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸውን ነገር በሥራ ላይ ሊታውል የፈለግኸውን ፅፈህ ከጓደኞችህ ጋር ከተፋፈል፡፡

★ ፀሎት፡- ከእግዚአብሔር ጋር ይበልጥ ጥልቅ ህብረት ለማድረግ የጥሞና ጊዜ እንድታደርግ በደንብ ፀልይ፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ

9. ክፍት ስብስባ ማለት ምን ማለት ነው? (ሐዋ.16÷25-34)

● ሐዋ.16÷25-34

25. በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር፥ እስረኞቹም ያደምጡአቸው ነበር
34. ወደ ቤቱም አውጥቶ ማዕድ አቀረበላቸው፥ በእግዚአብሔርም ስላመነ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ሐሤት አደረገ።

የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን አገልጋዮች ሮማዊያንን እንዴት በወንጌል አሸነፉ? ቻይና 400,000-500,000 ክርስቲያኖች በኮምንስት ዘመን በጣም በጭንቅ ጊዜ ወደ 100,000,000 ክርስቲያኖች ማደግ እንዴት ቻሉ? ጌታ ኢየሱስ እንደተናገረው እንደ ትንሽ እርሾና እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ወንጌልን በመመስከር በትንሽ ቡድን ማለት በክፍት ስብከት በኩል መስፋፋት ቻሉ፡፡ ክፍት ስብከት በአንድ ቦታ እንደ እርሾና እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት በቀላሉ አንድ አካባቢን በወንጌል መማረክ ማለት ነው፡፡ ክፍት ስብከት ወደ ሥፍራቸው በመሄድ የምሰበክ ስብከት ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስና ሐዋ.ጳውሎስ ወንጌልን ለመስበክ የተጠቀሙበት ዘዴ ነው፡፡ እኛ አሁን መፅሐፍ ቅዱሳችን እንደሚገልፀው ወደ አዲስ ኪዳን ዘመን የወንጌል ስብከት ዘዴ ልንመለስ ያስፈልጋል፡፡

1. ወንጌልን መመስከር ማለት ምን ማለት ነው?

1) በወንጌል የተትረፈረፈ ሕይወት ሰዎች እንዲኖሩ መርዳት ማለት ነው

● ዮሐ.10÷10

10. ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።

2) በሕይወታቸው ብዙ ፍሬ እንዲያፈሩ የማድረግ ሥራ ነው፡፡

① ማቴ.10÷6 የጠፋውን ሰው ፈልጎ የማግኘት ሥራ

● ማቴ.10÷6

6. ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ።

② ሐዋ.16÷1-3 የተሰወረውን የተልዕኮ ሰው ፈልጎ የማግኘት ሥራ

● ሐዋ.16÷1-3

1. ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራንም ደረሰ። እነሆም፥ በዚያ የአንዲት ያመነች አይሁዳዊት ልጅ ጢሞቴዎስ የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ፤ አባቱ ግን የግሪክ ሰው ነበረ።
2. ለእርሱም በልስጥራንና በኢቆንዮን ያሉ ወንድሞች መሰከሩለት።
3. ጳውሎስ ይህ ከእርሱ ጋር ይወጣ ዘንድ ወደደ፥ በእነዚያም ስፍራዎች ስለ ነበሩ አይሁድ ይዞ ገረዘው፤ አባቱ የግሪክ ሰው እንደ ሆነ ሁሉ ያውቁ ነበርና።

③ ሐዋ.18÷10-13 እግዚአብሔር የሚልከውን ሰው ፈልጎ የማግኘት ሥራ

● ሐዋ.18÷10-13

9-10 ጌታም ሌሊት በራእይ ጳውሎስን። እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፥ ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፤ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና አለው።

11. በመካከላቸውም የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ ዓመት ከስድስት ወር ተቀመጠ።
12. ጋልዮስም በአካይያ አገረ ገዥ በነበረ ጊዜ፥ አይሁድ በአንድ ልብ ሆነው በጳውሎስ ላይ ተነሡ፥ ወደ ፍርድ ወንበርም አምጥተው።
13. ይህ ሕግን ተቃውሞ እግዚአብሔርን ያመልኩት ዘንድ ሰዎችን ያባብላል አሉ።

④ ሐዋ.19÷1-10 የተዘጋጀን ሰው ፈልጎ የማግኘት ሥራ

● ሐዋ.19÷1-10

1. አጵሎስም በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፥

10. በእስያም የኖሩት ሁሉ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ሁለት ዓመት ያህል እንዲህ ሆነ።

3) የወንጌል ምስክርነት እውነተኛ ቅርፅ ምንድን ነው?

① 1ዮሐ.5÷11-13 ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የዘላለም ሕይወትን ሰጠ።

● 1ዮሐ.5÷11-13

11. እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው።
12. ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።

13. የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።

② ሉቃ.10÷17-19 የኢየሱስ ሥልጣን

- ሉቃ.10÷17-19

17. ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።
18. እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።
19. እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።

③ ዮሐ.16÷24 የእግዚአብሔር አብ የመኖር ምስክርነት(የጸሎት ሥልጣን)

- ዮሐ.16÷24

24. እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።

4) ወንጌልን መመስከር ማለት ወንጌልን ከሚቀበለው ሰው ጋር በረከትን መካፈል ማለት ነው፡፡

① ማቴ.16÷18 የራሱን ሕይወት በዓለት ላይ መመስረት

- ማቴ.16÷18

18. እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።

② ማቴ.28÷18 የሰማይና የምድርን ሥልጣን ይዞ መለማመድ

- ማቴ.28÷18

18. ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።

③ ማቴ.24÷14 ወንጌልን ሰብኮ በዓለም መጨረሻ ላይ በረከትን መቀበል ነው፡፡

- ማቴ.24÷14

14. ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።

5) ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ክርስቲያኖች በአንድነት መስራት ነው፡፡

- ሐዋ.1÷8

8. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

- ሐዋ.2÷37-38

37. ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት። ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉአቸው።
38. ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

- ሐዋ.2÷43

43. ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።

6) በመንግሥተ ሰማይ ስጦታ መቀበል

- ዳን.12÷3

3. ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፥ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።
እንደ ከዋክብት ለዘላለም የመድመቅ ስጦታቸው ነው፡፡

2. ስለ ወንጌል ምስክርነት አስተሳሰባችንን መቀየር ያስፈልጋል፡፡

1) ብቻውን መሥራት ሳይሆን በቡድን ከሌሎች ጋር መረብ የመዘርጋት ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡
2) በህብረት ወንጌልን መመስከር ወሳኝ ነው፡፡ ህብረት ማለት ወንጌልን ይዘን የምንሸጋገርበት ድልድይ ነው፡፡
3) ወንጌልን ለመቀበል ለተዘጋጀው ሰው ለመስጠት መዘጋጀት
4) ቤተሰብ ወንጌል የሚሠራበት ቦታ ነው፡፡ ቤት ውስጥ፣ ትምህርት ቤት፣ ሐኪም ቤት፣ መዝናኛ ስፍራ ወዘተ . . . ወንጌልን ሲንሠራ ያስፈልጋል፡፡

3. ክፍት ስብከት በመኖሪያ አካባቢ የሚሠራ የወንጌል ሥራ ነው፡፡

1) ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ ወደ ቤት ከሄዱ በኋላ የሚሠሩበት ሥራ ነው፡፡

- ሐዋ.11÷19-21

19. በእስጢፋኖስም ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ ዞሩ፥ ቃሉንም ለአይሁድ ብቻ እንጂ ለአንድ ስንኳ አይናገሩም ነበር።
20. ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ።
21. የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ።

2) ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበሉ ሁሉ የሚያደርጉት ሥራ ነው፡፡

- ዮሐ.1÷12

12 ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤

● ራዕ.3÷20

20. እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።

3) የኢየሱስ ክርስቶስን ሥልጣን የተከፋፈሉት የሚሠሩበት ሥራ ነው፡፡

● 1ዮሐ.3÷8

8. ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና።

● ማቴ.12÷28-29

28. እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።

29. ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።

4) ታማኞችን የምናገኝበት ሥራ

በእኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ ታማኝ የሆነ ሰው ማን ነው? ለእምነቱ ምሳሌ የሆኑ ሰዎችን ማየት አለብን፡፡

● 2ጢሞ.2÷2

2. ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።

4. ክፍት ስብከት የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰብክበት ዘዴ ነው፡፡

1) በትንሽ ቡድን ወንጌልን መስበክ ነው፡፡

● ሐዋ.19÷8-10

8. ስለዚህ ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እግጅ ፈራ፤

9. ተመልሶም ወደ ገዡ ግቢ ገባና ኢየሱስን። አንተ ከወዴት ነህ? አለው። ኢየሱስ ግን አንድ እንኳ አልመለሰለትም።

10. ስለዚህ ጲላጦስ። አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው።

2) በትንሽ ቡድን በፀሎት ወንጌልን መስበክ ነው፡፡

ሁለትና ሶስት ሆነው በስሜ በሚፀልዩበት ስፍራ እግዚአብሔር በመካከላቸው እገኛለሁ አለ፡፡

● ማቴ.18÷18-20

18. እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።

19. ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።

20. ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።

3) በትንሽ ቡድን ከሕይወቱ ወንጌል መስበክ ነው

ለጓደኛህ ለዘመድ ለጎረቤቶችህ በፍቅር ወንጌልን መስበክ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዘዴ ወንጌልን ስትሰብክ ከ80% በላይ ሰዎች ጌታን ይቀበላሉ፡፡

● ዮሐ.1÷39-42

39. እርሱም፦ ረቢ፥ ወዴት ትኖራለህ? አሉት፤ ትርጓሜው መምህር ሆይ ማለት ነው።

40. መጥታችሁ እዩ አላቸው። መጥተው የሚኖርበትን አዩ፥ በዚያም ቀን በእርሱ ዘንድ ዋሉ፤ አሥር ሰዓት ያህል ነበረ።

41. ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ።

42. እርሱ አስቀድሞ የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና። መሢሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው።

4) ክፍት ስብከት አንዱ ከአንዱ ጋር በመያያዝ መብዛት ነው (እንደ አብዝሮ ዛፍ) መሥራት ነው፡፡

● ዘፍ.1÷28

28. እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።

5. ክፍት ስብስባ ዋጋ ከትንሽ ጀምሮ እንደ እርሾና እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ዓለምን የሚያሰራጭ የሚያስፋፉ ነው፡፡ ይህ ምን እንደሆነ አግኝ፡፡

1) እንደ ዘር መዝራት ነው፡፡

በእምባ ዘርን ዘርተው በደስታ ለቀሙ፡፡ አንድ መቶ ፍሬ በማባዛት ወሰዱ፡፡

● ማቴ.13÷2-9

2. እርሱም በታንኳ ገብቶ እስኪቀመጥ ድረስ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፥ ሕዝቡም ሁሉ በወደቡ ቆመው ነበር።

3. በምሳሌም ብዙ ነገራቸው እንዲህም አላቸው፦ እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ።

4. እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፥ ወፎችም መጥተው በሉት።

5. ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፥
6. ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ።
7. ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው።
8. ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ።
9. የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።

2) መልካም ዘር እንደ መዝራት ነው፡፡
የመንግሥትን ወንጌል የማስፋፋት ሥራ ነው
- ማቴ.13÷14-30

14. መስማት ትሰማላችሁና አታስተውሉም፥ ማየትም ታያላችሁና አትመለከቱም።

30. ተዉአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜም አጫጆችን። እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ፥ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ።

3) እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ዓይነት ነው፡፡
አንተ በትንሹ ጀምር ፍፃሜህ ታላቅ ይሆናል፡፡
- ማቴ.13÷31-32

31. ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፡- መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤
32. እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፥ በአደገች ጊዜ ግን፥ ከአታክልቶች ትበልጣለች የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች።
- ኢዮብ.8÷7

7. ጅማሬህ ታናሽ ቢሆንም እንኳ ፍጻሜህ እጅግ ይበዛል።

4) እንደ እርሾ ዓይነት ነው፡፡
እርሻ ያለው ሥራ መሥራት አለብህ፡፡
- ማቴ.13÷33

33. ሌላ ምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ፡- መንግሥተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች።

5) የተወረሰ መዝገብ እንደሚፈልግ ዓይነት ነው፤
- ማቴ.13÷44

44. ደግሞ መንግሥተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረውን መዝገብ ትመስላለች፤ ሰውም አግኝቶ ሰወረው፥ ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ።

6) ጥሩ ሉልን እንደሚፈልግ ነጋዴ ዓይነት ነው፤
ተልዕኮ ያለው ሰው የሚገኝበት ሥራ ጥሩ ሉልና ወንጌል አንድ ዓይነት እንደሆኑ ዘውትር ያከብራል፡፡
- ማቴ.13÷45

45. ደግሞ መንግሥተ ሰማያት መልካምን ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች፤

7) ብዙ ክፍት ስብከቶችን መክፈት፡፡ ብዙ መረቦችን መዘርጋት፡፡
በዚህን ጊዜ ከብዙ መረቦች የተመረጡ ሰዎች ኢየሱስን ያምናሉ፡፡
- ማቴ.13÷48-50

48. በሞላችም ጊዜ ወደ ወደቡ አወጡአት፥ ተቀምጠውም መልካሙን ለቅመው በዕቃዎች ውስጥ አከማቹ ክፉውን ግን ወደ ውጭ ጣሉት።
49. በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፤ መላእክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል፥ ወደ እቶነ እሳትም ይጥሉአቸዋል፤
50. በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

6. የክፍት ስብስባ ለሚያከናነው አገልጋይ ድርሻ ምንድን ነው?

1) ክፍት ስብስባን በአንድ ቦታ ለአንድ ሰዓት ማድረግ
- ሐዋ.19÷8-10

8. ወደ ምኵራብም ገብቶ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያስረዳቸው ሦስት ወር ያህል በግልጥ ይናገር ነበር።
9. አንዳንዶች ግን እልከኞች ሆነው በሕዝብ ፊት መንገዱን እየሰደቡ ባላመኑ ጊዜ፥ ከእነርሱ ርቆ ደቀ መዛሙርትን ለየ፥ ጢራኖስም በሚሉት በትምህርት ቤት ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር።
10. በእስያም የኖሩት ሁሉ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ሁለት ዓመት ያህል እንዲህ ሆነ።
ቃል የተሰበከላቸው ሰዎች ልብ ሊለወጥ ይችላል፡፡ በየሳምንቱ አንድ ጊዜ ለአንድ ሰዓት ክፍት ስብከት ማድረግ፡፡

2) በተስፋ ልብና በፍፁም ነፍስ መዘጋጀት

ምሳሌ:- ሊዲያና የእስር ቤት አዛዥ የተዘጋጁ ሰዎች ነበሩ፡፡(ጳውሎስ)

- ሐዋ.16÷14-15

14. ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት።
15. እርስዋም ከቤተ ሰዎችዋ ጋር ከተጠመቀች በኋላ። በጌታ የማምን እንድሆን ከፈረዳችሁልኝ፥ ወደ ቤቴ ገብታችሁ ኑሩ ብላ ለመነችን፤ በግድም አለችን።

3) እግዚአብሔር ወንጌልን ለሚሰበከው ሰው በምድር መቶ እጥፍ እንደሚባርከና በመንግስተ ሰማይ ደግሞ አክሊል እንደሚሰጠው ተስፋ ማድረግ፡፡

- ማር.10÷30

30. አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።

★ በሥራ ላይ የምናውል - ከዚህ ምዕራፍ አዲስ ያወቅከውን ልትተገብር የፈለግከውን ከፃፍክ በኋላ ከእያንዳንዱ ሰው ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት፡- በእኔ ወንጌል እንዲስፋፋና የክፍት ስብከት ሥራ እንዲከናወን በደንብ እፀልያለሁ፡፡

ምዕራፍ አሥር

10. የእግዚአብሔርን ዕቅድ የምትሠራ ቤተክርስቲያን (ሐዋ.2÷43-47)

- ሐዋ.2÷43-47

43. ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።
44. ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤
45. ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።
46. በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤
47. እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

መንፈስ ቅዱስ ያላት ቤተክርስቲያን ሁለት ክንፍ ያላት ቤተክርስቲያን ናት፡፡
1ኛው ክንፍ፡- የትልቅ ቡድን ክንፍ (የቤተክርስቲያን ህብረት አምልኮ ነው፡፡)
2ኛው ክንፍ፡- የትንሽ ቡድን ክፍት ስብስባ ነው፡፡
ሁለት ክንፎችን እኩል በመያዝ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሊትሠራ ይገባታል፡፡

1. የእግዚአብሔርን ዕቅድ የምትሠራ ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሁለት ክንፎችን የያዘች ቤተክርስቲያን ናት፡፡

1ኛው ክንፍ የትልቅ ቡድን የቤተክርስቲያን አምልኮ ነው፡፡
2ኛው ክንፍ የትንሽ ቡድን ክፍት ስብስባ ነው፡፡

1) ትልቅ ቡድን ክፍት ስብከት በቤተክርስቲያን አምልኮ በኩል መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ላይ ይወርዳል፡፡
እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ የሚኖርና ሁሉን ቻይ እንደሆነ ሊለማመዱ ይችላሉ፡፡
2) በትንሽ ቡድን ክንፍ ክፍት ስብስባና ክፍል ቡድን ሲያደርጉ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚወርድ ተነጋገሩ፡፡
እግዚአብሔር በመካከላችን እንደሚኖር ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

★ አምስት ዓይነት ሥርዓት

1. ህብረት
   በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ መኖር (ዮሐ.15 ምዕራፍ በሙሉ)
2. ልምምድ ማድረግ
3. አንዱ ከአንዱ ጋር መስራት፣ መንፈስ ቅዱስ ያግዘናል (ይረዳናል)
   ● ዮሐ.14÷16
   14. ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።
   15-16 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤
4. የማገልገል ሥልጣን
5. የወንጌል ምስክርነት

2. ስትቪን ኮቢ (አሜሪካዊ) ሰዎች ተለማምዶ (ሠልጥነው) እንዲያከናውኑ ካዘጋጀው ከ7ቱ ነገሮች አንዱ በራሳቸው አስተሳሰብ ማንኛውም ሰው አይተው የቤተክርስቲያንን ሥራ እንዲያምኑ ማድረግ ነው፡፡

1) ስለ ቤተክርስቲያን ሥራ የራሳችሁ አሳብ ምንድን ነው?
   ቤተክርስቲያን፡- ቤተክርስቲያን ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምኑ ሰዎች በአንድ ላይ የሚሰበሰቡበት አዳራሽ ነው፡፡
   ቤተክርስቲያን ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን ያመኑ ሰዎች በአንድ ላይ ቤተክርስቲያን ይባላሉ፡፡
2) እሁድ እግዚአብሔርን የምናመልክበት ቦታ በራሳችን አሳብ ምን ማለት ነው?
   አምልኮ ወይም ማምለክ ወሳኝ ስለሆነ አንድ ላይ ጌታን መስማት፣ ማክበር፣ ማወደስ ከፍ ከፍ ማድረግና ክብር መስጠት ወዘተ . . . ማለት ነው፡፡
3) የገዥዎች አስተሳሰብ ምንድን ነው?
   ገዥዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲኖሩ ቤተክርስቲያን አታድግም ከክርስቲያኖች መካከል ከ80-90% የማይሠሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን የእሁድ ደቦኞች ብቻ ናቸው፡፡ በሥራ የሚተጉ ገበሬዎች ናቸው፡፡
4) ስለ በቆሎ ምን አሳብ አላችሁ?
   ሁሉም በአንድ ላይ ተሰብስቦ በእሁድ አምልኮ ያደርጋሉ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ሲበተን ምንም ዓይነት ሥራ የማይሠሩ ማለት ነው፡፡ በቆሎ በወፍጮ ከተፈጨ ለምግብነት ያገለግላል፡፡ እንደዚሁም ክርስቲያኖች አንድ ላይ ተሰብስቦ እንደ እግዚአብሔር ቃል ከተሠሩ የጌታን ቤት ሥራ መሥራት ይችላሉ፡፡

3. ሐዋ.2÷43-47 የአዲስ ኪዳን ዘመን ቤተክርስቲያን ቅርፅ ሁለት ክንፎችን ይዛ እንደሠራች አሳይ፡፡

1) በእግዚአብሔር አብርሆትንና ሥልጣንን ሠራች፡፡
   ● ቁ.43
   43. ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።

2) እያንዳንዱ ክርስቲያን ይሠራል፡፡ እኛ አንድ ቤተሰብ ነን፡፡
   ● ቁ.44
   44. ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤

3) በህብረት እየተከፋፈሉ ያገለግላሉ፡፡
   ● ቁ.45
   45. ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።

4) በፍቅር እርስ በርስ ምግብን ይበላሉ፡፡
   ● ቁ.46
   46. በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤

5) ቁጥራቸውን ይጨምራሉ (ይበዛሉ)
   ● ቁ.47
   47. እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

4. ለቤተክርስቲያን ሌላኛው ክንፍ መሆን የክርስቲያኖች መሠረት በህብረተሰብ ክፍል ቡድን ውስጥ መሆን ምን ማለት ነው?

1) ክፍል ቡድን ማለት በክርስትና ኑሮ የሚኖር የቤተሰብ ስብስባ ነው፡፡
2) ቤተሰብን እንደሚረዳ ሳይሆን ልክ ቤተሰብ መሆን ነው፡፡ ነገር ግን ፍፁም ቤተሰብ አይደለም

3) እያንዳንዱ በትዕግስት መስራት
4) የቤተሰባዊ ፍቅር፤ ከልጆች፤ ከባል፤ ከሚስት፤ ከሠራተኛ => እርስ በርስ መዋደድ ያስፈልጋል፡፡

5. ክፍል ቡድን የኢየሱስን መምጣት፣ ሥልጣንና ግብ ሊገልፅ ያስፈልጋል፡፡

1) መምጣት ሲንል ምን ማለት ነው?
በሚናከብርበት ጊዜ በሚንዘምርበት ጊዜ ቅባት ይመጣልናል፤ ይህ ለእኛ የሚያሳየው በሥልጣን ውስጥ መኖራችንን ነው፡፡
2) ሥልጣን ምንድን ነው?
በቃል በኩል መዳንን ማግኘት ነው፡፡
3) ግብ ምንድን ነው?
በወንጌል ምስክርነት በኩል ማብዛት ያስፈልጋል፡፡
4) የክፍል ቡድን ምንጩ ምንድን ነው?
ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የክፍል ሕይወትና ሥልጣን ኢየሱስ ነው፡፡

6. የክፍል ቡድን ኑሮውንና ሥልጣን በየቀኑ አዲስ ሕይወት መውለድ ነው፡፡ ክፍል ቡድን የማብዛት ራዕይ ሊኖር ያስፈልጋል፡፡

1) የክፍል እውነተኛ ፍሬ ሌሎች ክፍል ቡድን ማድረግ ነው፡፡
ምሳሌ፡- የአፕል ተክል እውነተኛ ፍሬ ሌሎች አፕሎች መሆን ነው፡፡
የቤተክርስቲያን እውነተኛ ፍሬ ሌሎች ቤተክርስቲያንን መገንባት ነው፡፡
2) የማያበዛ ክፍል ቡድን የሞተ ክፍል ነው፡፡
3) 12 ሰዎችን የክፍል መሪ አድርግ (D12 ራዕይ) እንደገና ክፍል ቡድኖችን መሥራት ማለት ነው፡፡
4) ህልምን (ራዕይህን) ፍፁም አድርግ።
5) የዓለም መሪ ራዕይ ያለው አንተ መሆንህን አምነሃል?

★ በሥራ ላይ የምናውል - ከዚህ ምዕራፍ አዲስ ያወቅኸውንና በሥራ ላይ ልታውል የፈለከውን ነገር ፅፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተከፋፈል፡፡

★ ፀሎት፡- የእኛ ቤተክርስቲያን የእግዚአሔርን ዕቅድ የምትሠራ እንድትሆን በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡



የመንፈስ ጸጋ ሥጦታ ምጦታ ማገልገል
(ክርስቲያኖች በሥጦታቸው እንዲያገለግሉ የማስተካከል ሥራ)

ማውጫ

ማውጫ **ገጽ**

1. ምዕራፍ አንድ - የንጉሥ ካህን ነኝ ……
2. ምዕራፍ ሁለት - የሥራ ሰው ታርክ ……
3. ምዕራፍ ሦስት - የሚያሳስብ ነገር ማግኘት ……..
4. ምዕራፍ አራት - የመንፈስ ጸጋ ሥጦታ ማግኘት ……..
5. ምዕራፍ አምስት- ፀባይን ማግኘት ……..
6. ምዕራፍ ስድስት- የሥራ ሰው የሕይወት ታርክ እንዴት እንደሚጻፍ …….
7. ምዕራፍ ሰባት- ፀጋ ሥጦታ ማስተካከልና ማጽናናት ……..

★ ተጨማሪ - ምስክርነት

1. የሥራ ዝርዝር ……
   1) የሥራ ማመልከቻ …….
   2) የሥጦታ ማስተካከያ ማጽናናት መግለጫ ወረቀት (አስተማሪ)……
   3) የሥጦታ ምርመራ ……
   4) የፀባይ ምርመራ …….

መግቢያ

የንጉሥ ካህን ነህ? የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ለመጋቢያንና ለወንጌላዊያን ብቻ መሆኑ ቀርቶ የክርስትና ተሃድሶ ቢደረግ ሁሉም ሰዎች የንጉሥ ካህናት መሆናቸውን ያውቃሉ፡፡ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮች መጋቢያንና ወንጌላዊያን ሥጦታ የማስተካከል ሥራ በክርስቲያኖች ላይ ቢሠሩ ሁሉም ክርስቲያኖች የንጉሥ ካህናት ሆነው ጌታን እንዲያገለግሉ ይህ መጽሐፍ ሥር መሠረት ያስቀምጣል፡፡

የእግዚአብሔርን ጥሪ የተቀበሉ ክርስቲያኖች ሁሉ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ክርስቲያኖች በየሥጦታቸው እንደ ካህናት ቤተ ክርስቲያንን፣ ሌሎች ክርስቲያኖችን፣ ቤተሰብንና ጓደኞችን ሁሉ ለማገልገል ጥሪውን ተቀበለዋል፡፡ ነገር ግን ከክርስቲያኖች መካከል የራሳቸውን ሥጦታ ያወቁ በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ በብዙ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ ሲናገሩ የመዝሙር ቡድንና የሕፃናት ትምህርት ቤት ብቻ እንዳለ ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን ብዙ የፀጋ ሥጦታዎች መኖራቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልፃል፡፡

የቤተ ክርስቲያን የምሥራች ቃል መዳንን በአጭር መንገድ ለማሳየት ነው፡፡ የፀጋ ሥጦታቸውን ሳያውቁ የሚኖሩ ብዙ ክርስቲያኖች የራሳቸውን ስጦታ የቤተክርስቲያን ሙሉ ጊዜ አገልጋዮች እንዲረዱ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ መጋቢያንና ወንጌላዊያን የሰዎችን የፀጋ ሥጦታ በመለየት በየሥጦታቸው ማሰማራት ያስፈልጋል፡፡

next

የሥጦታ ማስተካከል ሥራ ክርስቲያኖች ሁሉ ባሉበት ሆነው እንዲያገለግሉ የሚረዳ ፕሮግራም ነው፡፡ አሁን ክርስቲያኖች የራሳቸውን የፀጋ ሥጦታና ፀባይ በማስተዋል አግኝቶ በመልካም ሥራ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ማገልገል

ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ባሉበት ሆነው የምሥራቹን ቃል (ወንጌል) የተቀበለችና የዳነች ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የምታገለግል ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች፡፡ እግዚአብሔር አሁን እኛን የንጉሥ ካህናት እንዲንሆን ይጠራል፡፡

ምዕራፍ አንድ

1. እኔ የንጉሥ ካህን ነኝ

ምሳሌ፡- ለፀጋ ሥጦታ ዕውቀት እንድረዳ አራዊትን እንደ ምሳሌ እንጠቀም፡፡ ዳክዬ፣ጥንቸል፣እንዳሴቁኒ፣ንስር እነዚህ ነገሮች የየራሳቸው ልምድ አላቸው፡፡ ነገር ግን እነርሱን ስንፈትናቸው፡፡

የፈተናው ዓይነት

- መዋኘት
- መሮጥ
- በእንጨት ላይ መውጣትና
- በአየር ላይ መብረር

በመጀመሪያ ፈተና ማለት በመዋኘት ፈተና እነዚህን አራቱን አራዊትን ብንፈትናቸው በፈተናው የሚያልፈውን አንድ ዳክዬ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች የራሳቸው ሥጦታ ስላልሆነ ይወድቃሉ፡፡ በሁለተኛ ፈተና የመሮጥ ፈተና ብንሰጣቸው ጥንቸል ሩጫ ስለምትችል በፈተና ታልፋለች ሌሎቹ 3ቱ ይወድቃሉ፡፡

በሦስተኛ ፈተና በእንጨት በዛፍ ላይ መውጣት ፈተና ብንሠጣቸው እደሰቁኒ ያልፍናሌሎቹ 3ቱ ይወድቃሉ፡፡ በአራተኛ ፈተና በአየር ላይ የመብረር ፈተና ብንሰጣቸው ንሥር መብረር ሰለሚችል በፈተናው ያልፋል ሌሎቹ 3ቱ ይወድቃሉ፡፡

እንደዚሁም በቤተክርስቲያን ለእያንዳንዱ የተሠጠ ፀጋ ሥጦታ ስላላቸው በፀጋ ሥጦታቸው ቤተክርስቲያንን ቢያገለግሉ ውጤታማ ይሆናሉ፤ አለበለዚያ ያለ ሥጦታቸው ገብተው በሚሰሩበት ጊዜ ውጤት አልባ ሆኖ እንደ አራዊቶች መውደቅ ይሆናሉ፡፡

ፍልፈል ወደ እንስሳት ትምህርት ቤት በምትገባበት ጊዜ የትምህርት ዓይነት እንደማይኖራት ሁሉ ያለ ፀጋ ሥጦታ በሚያገለግልበት ጊዜ በሰዓት ለመጀመርና በብዙ ስንፍና ውስጥ ገብቶ የቤተክርስቲያንን ሥራ ያስተጓጉላሉ፡፡ ወይም የቤተክርስቲያን ስሜት እንዲጠፋ ምክንያት ይሆናል፡፡ (1ጴጥ.4÷10) ‘‘እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው ጸጋ ሥጦታ ሌላውን ያገልግል፡፡''

እነዚህ ሁሉ ክርስቲያኖች በጸጋ ስጦታ በኩል እንዲያገለግሉ የሚያደርግ አጽንኦት ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔር ለሁሉ ክርስቲያኖች ልዩ ልዩ ፀጋ ስጦታ ሰጠ፡፡ ልዩ ልዩ ጸጋ ስጦታ የተቀበለ በተሰጠው ፀጋ ስጦታ በሚያገለግልበት ጊዜ ታላቅ ሥልጣን መግለጽ ይችላል፡፡

አሁን እግዚአብሔር ለአንተ የሰጠው ልዩ ፀጋ ስጦታ አግኝ ይህ መጽሐፍ ያንተ ልዩ ፀጋ ስጦታ የምታገኝበትን መንገድ የሚረዳ መጽሐፍ ነው፡፡ ደግሞም በፀጋ ስጦታ በኩል በቤተክርስቲያን ውስጥ መልካም ሥራ እንዲተሠራ ያደርጋል፡፡ አንተ በምታደርገው ፀጋ ሥጦታ ደስተኛ ስትሆን ቤተክርስቲያን እንድትታነጽና እንድታድግ ምክንያት ይሆናል፡፡

ምዕራፍ ሁለት
2. የሥራ ሰው ታሪክ

1. የሥራ ሰው ታሪክ ምንድን ነው?

ምን ዓይነት ሰውና ምን ዓይነት ሥራ በደንብ እንደምችል የሚያስረዳ ነው፡፡

1) እግዚአብሔር ብቻውን እያንዳንዱን ሰውን ልዩ አድርጎ ፈጠረ

- መዝ.139÷14-16

14. ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች።
15. እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፥ አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም።
16. ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።

እኖን እግዚአብሔር ውብ አድርጎ ፈጠረ፡፡ እኔ የእግዚአብሔር ውብ ሰው ነኝ

2) የሥራ ሰው ታሪክ እኔ ራሴን እንዲያስታውስ የሚረዳ ነው

- ኢሳ.43÷1

1. አሁንም ያዕቆብ ሆይ፥ የፈጠረህ፥ እስራኤልም ሆይ፥ የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ በስምህም ጠርቼሃለሁ፥ አንተ የእኔ ነህ።

3) የሥራ ሰው ታሪክ እኔ የተቀበልኩት ፀጋ ሥጦታ የትኛው እንደሆነ የሚያሳውቅ ነው፡፡

- 1ጴጥ.4÷10

10. ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤

2. የሥራ ሰው ታሪክ ባህሪይ



1) የሚያስብ

- እኔ የት ቦታ ማገልገል እችላለሁ? የሚያስብ ሰው በየትኛው ቦታና በየትኛው አቅጣጫ ደግሞም በየተኛው ፀጋ ሥጦታ ቢያገለግል ውጤታማ (ፍርያማ) እሆናለሁ የሚለውን ያስባል፡፡
- የሚያስብ ሰው በየተኛው ቦታና ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚያገለግል የሚያውቅ ነው፡፡

- ፊልጵ.2÷13

13. ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።

2) የፀጋ ስጦታ

መንፈሳዊ ፀጋ ስጦታ ለቤተክርስቲያን ጥቅም መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚሰጥ ልዩ ስጦታ ነው፡፡
በየትኛው ፀጋ ስጦታ ለማገልገል ትፈልጋለህ? የእግዚአብሔር ዕቅድ በእኛ ላይ ነው፡፡

- 1ቆሮ፣7÷7

7. ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ።

3) ፀባይ

የእኖን ሥራዎች የሚገልጥ ፀባይ ነው፡፡ በፀባይ እንዴት ማገልገል ይቻላል?
አገልጋይ በፀጋ ስጦታ በኩል ሲሠራ ደስተኛና ምርኮን የሚማርክ ሰው ወይም በቤተክርስቲያን ውስጥ መልካም ፍሬ የሚያፈራ ነው፡፡

- 1ቆሮ.2÷11

11 በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።

★ የፀጋ ስጦታ የማስተካከል ሴሜናሪ (ትምህርት)

ደረጃ 1 አንተ የምታስበውን፣የፀጋ ሥጦታና ፀባይ የምታገኝበት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለአንተ የሰጠውን ቅርጽ ለማየት ይጠቅማል፡፡

ደረጃ 2 ማጽናናት ለአንተ ጥሩ የአገልግሎት ልምድ እንዲትወስድ የሚረዳ ነው፡፡

ደረጃ 3 የፀጋ ስጦታ ማስተካከያ ግብ ማግኘት ማጽናናት ብቻ ሳይሆን የምታከናውንበት አገልግሎት ነው፡፡

ወንድሞቼ ሆይ ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል ነጻነታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታድርጉ፤ ይልቁንም አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል፡፡

● ገላ.5÷13

13. ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።

★ የፀጋ ስጦታ ማስተካከያ ሥራ አስታውስ

1. እግዚአብሔር አንተን ምን ዓይነት ሰው እንዳደረገ በደንብ አስታውስ
2. አንተ በፀጋ ስጦታህ ስታገለግል የእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚስፋፋ አስታውስ
3. ቤተክርስቲያንና እግዚአብሔር አንተን እንደሚፈልጉ አስታውስ፤ አንተ በቤተክርስቲያን በኩል ይህን አገልግሎት ቢታገለግል እግዚአብሔር ይደሰታል፡፡

ምዕራፍ ሦስት
3. የሚያሳስብ ነገር ማግኘት

1. የሚያሳስብ ነገር ምንድን ነው?

1) የሚያሳስብ ነገር እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ የሰጠውን ተስፋ ነው፡፡ እግዚአብሔር እኛን ሲፈጥር በእኛ ውስጥ የተኛውን ዓይነት ሥራ መሥራት እንዳለብን የሚያስብ ልብ ስለሰጠን በዚህ በኩል ለእግዚአብሔር ክብርን እንድንሰጥ ያደርጋል፡፡

የሚያሳስብ ነገር ማለት በተለያዩ ሥራ ቦታዎች ታላቅ ሥራ እንዲንሠራ እኛን ለማሰልጠን እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ነው፡፡

አንተን የሚያሳስብ በየትኛው ቦታ በበጎ ፈቃድህ ለማገልገል ነው?

● ፊልጵ.2÷13
13. ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።
● መዝ.37÷4
4. በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፥ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል።

2) የሚያሳስብ ማለት የምትሰራበት ቦታ እንድታገኝ አንተን መረዳት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ለመጥቀም አስቀድሞ ልዩ የሆነውን ቦታ እንዲያስብ ካደረገ በኋላ በዚያ አገልግሎት እንዲያገለግል ያደርጋል፡፡ የሚያሳስብ ነገር እኛ የት ቦታ ማገልገል እንዳለብን የተሻለ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

① እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤርምያስ ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መገንባት የሚያሳስብ ነገር ሰጠ፡፡ የሚያሳስብ ነገር የልብ ተስፋ ነው፡፡

● ኤር.1÷2-4
2. በይሁዳ ንጉሥ በአሞጽ ልጅ በኢዮስያስ ዘመን በመንግሥቱ በአሥራ ሦስተኛው ዓመት የእግዚአብሔር ቃል መጣለት።
3. በይሁዳም ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም ዘመን፥ እስከ ይሁዳ ንጉሥ እስከ ኢዮስያስ ልጅ እስከ ሴዴቅያስ እስከ አሥራ አንደኛው ዓመት ፍጻሜ፥ ኢየሩሳሌም እስከ ተማረከችበት እስከ አምስተኛው ወር ድረስ መጣ።
4. የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ።
● ኤር.2÷12
12. ሰማያት ሆይ፥ በዚህ ተደነቁ፥ እጅግም ደንግጡና ተንጥቀጡ ይላል እግዚአብሔር፡-

② እግዚአብሔር ለሐዋሪያ ጳውሎስ ወንጌልን እንዲሰብክ የሚያሳስብ ነገር ሰጠ፡፡

● ሮሜ.9÷1-3
1-2 ብዙ ጎዘን የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል።
3. በሥጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና።
● ገላ.1÷15-16
15-16 ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥

3) የሚያሳስብ ነገር ተስፋ፣ሕልም፣ራዕይ፣ተልዕኮ፣ታላቅ ስሜት የሚሰጥና የሰውን ልብ መቀየር የሚችል ነው፡፡

★ የሚያሳስብ ነገር

① እግዚአብሔር በልቤ ውስጥ የሰጠው ልዩ ተስፋ ነው
② በየትኛው ቦታ እንድሚሰራ ህልምና ራዕይ የሚሰጥ ነው
③ በየትኛው ቦታ ተልዕኮንና ፍላጎትን እንደሚሠራ የሚገልጽ ነው
④ ከሌሎች ሥራዎች ይህ ታላቅ ስሜት እንዴት እንደሚሰጥ የሚያስብበት ነው፡፡

4) የሚያሳስብ ነገር እግዚአብሔር የሰጠው ነገር ለእያንዳንዱ ሰው የተለያየ እንደሆነ ሁሉ እውነትንና በደልን ለይተው እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡
5) የሚያሳስብ ነገር ሲበዛ ብዙ ደስታን ይሰጣል፡፡
● 1ኤር.2÷17-18
17. ይህ ሁሉ የሆነብሽ እኔን ስለ ተውሽ አይደለምን? ይላል እግዚአብሔር አምላክሽ።
18. አሁንስ የሺሖርን ውኃ ትጠጪ ዘንድ በግብጽ መንገድ ምን ጉዳይ አለሽ? የኤፍራጥስንም ውኃ ትጠጪ ዘንድ በአሦር መንገድ ምን ጉዳይ አለሽ?
6) የሚያሳስብ ነገር ተመሳሳይ ሰዎች እርስ በርስ አንድ ላይ ወንጌልን እየሰብኩ በአንድ ማህበረሰብ በአንድ ቦታ ላይ ተስማምተው ተሰብስበው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙና እንዲያገለግሉ የሚያደርግ ነገር ነው፡፡ የከተማውን ቅጥር የመገነባት ተስፋ የያዙ ሰዎች የነቢዩን ኤርምያስ የከተማውን ቅጥር የመገንባት ስብከት ሰምተው ልባቸውን በአንድ ላይ በማድረግ በሥልጣን ሠሩ፡፡

2. የሚያሳስብ ነገር መመርመር

ከዚህ በታች ባሉት ጥያቄዎች መሠረት አንተን የሚያሳስብ ነገር የትኛው እንደሆነ የሚታገኝበት ዝርዝር ሁኔታ ይሰጣል፡፡ የትኛውን ሥራ ለመሥራት እንደምትፈልግ እስከምትመልስ የሚያሳስብ ነገር ከባድ አይደለም፡፡ በቤተ ክርስቲያን፣ በቤተሰብ፣ በሥራ ቦታ የቀድሞ ልምምድ ወዘተ… የሕይወታችን ሥፍራዎች መልስ የምናገኝበት ነው፡፡ በሚያሳስብ ነገር ለማገልገል ውሳኔ ማድረግ አለብን፡፡

1) እኔን ከሚያሳስብ ነገር አንደኛው የትኛው ሀሳብ ነው?
2) ጎረቤቶች ጓደኞች እኔ ምን ዓይነት ሥራ በደንብ እንድሠራ ይናገራሉ?
3) ቀድሞ ከሚያሸንፉ ሥራዎች መካከል በጣም የሚከብደው ሥራ የትኛው ነው?

4) በራስ አስተሳሰብ በጣም በደንብ የምትሠራው ሥራ የትኛው ነው?
5) የሥራ ሰዓት ማለፉን ሳታውቅ በደንብ የምትወደው ሥራ ምንድን ነው?
6) ሕይወትህ ሁሉ ልታደርግ የምትፈልገው የፀሎት ዓይነት ምንድን ነው
7) ጊዜህን ሁሉ ለሌሎች ሰዎች ሰጥተህ ለመስራት የሚትፈልገው የትኛውን ሥራ ነው?
8) የትኛውን ስብከት በምትሰብክበት ጊዜ ጎረቤቶችህ ይሰማሉ?

3. የሚያሳስብ ነገር አግኝ

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ተመልክተህ በጣም በልብህ የሚትወድደውን ወስደህ ከዚህ በታች ባሉት ጥያቄ መሠረት ጻፍ፡፡የሚያሳስብ ነገር ዝርዝር ጻፍ፡፡

ምሳሌ፡-

① በልቤ ውስጥ ስለ ሕፃናትና የደቀመዝሙርት ሥልጠና ለመስጠት ያሳስበኛል፡፡
② ለሕመምተኞች ርዳታ ለማድረግ ያሳስበኛል፡፡
③ ወጣቶች በሚያገቡበት ጊዜ ማበረታታት ያሳስበኛል ወዘተ…

የግል ጥያቄ

እኔ ስለ _____ የሚያሳስብ ነገር አለኝ፡፡

ከላይ የተገለጸውን ዐረፍተ ነገር ቀስ በቀስ አንብብ፡፡ ይህ ዐረፍተ ነገር በሚታነብበት ጊዜ በአንተ ልብ ውስጥ የሚሰማው ታላቅ ስሜት እግዚአብሔር ላንተ የሰጠው ትክክለኛው የሚያሳስብ ነገር እንደሆነ ትረደዋለህ፡፡

እግዚአብሔር በውስጥ ባስቀመጠው በሚያሳስብ ነገር ፈቃዱን እንዲታገልግል ይፈልጋል፡፡አሁን ያገኘኸው የሚያሳስብ ነገር አንተን እንዲያሸንፍ ተስፋ አድርግ፡፡

ምዕራፍ አራት
4. ሥጦታ መቀበል

★ የሚያሳስብ ነገር

1. በመጀመሪያ የሚያሳስብ ነገር እግዚአብሔር የሰጠው ነገር ነው፤
2. እውነት ወይም ውሸት የሚባል ነገር የለም፤
3. የሚያሳስብ ቦታ የተኛው እንደሆነ በሚጠይቅበት ጊዜ መልስ ይሰጣል፤
4. የሚያሳስብ ነገር ትርጉም እግዚአብሔር የሰጠው በልባችን ውስጥ የሚሞላ ተስፋ ነው፤ ደግሞም እኛ በተለያየ ፀጋ ሥጦታ እንዲናገለግ የሚረዳ ነው፡፡ገጽ 72 ላይ ያለውን ተመልከት፡፡

1. ፀጋ ሥጦታ ምንድን ነው?

1) ፀጋ ሥጦታ መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚያድለው ልዩ ፀጋ ነው፡፡

- 1ቆሮ.12÷11

11. ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።

2) ፀጋ ሥጦታ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም የሚሰጥ ነው፡፡መንፈስ ቅዱስ ፀጋ ሥጦታ የሚሰጥበት ምክንያት ሁሉ ቤተክርስቲያኖች እንዲጠቀሙና እንዲያዲጉ ፈልጎ ነው፡፡
እኔ ምን እየሠራሁ ነኝ? ይህ ማለት በምን ፀጋ ሥጦታ ቤተ ክርስቲያንን እያገለግልሁ ነኝ? ማለት ነው፡፡የሚያሳስብ ነገር ወዴት ሄደህ መሥራት እንዳለብህ የሚገልጽ ነው፡፡ሥጦታ አንተ የተኛውን ሥራ መሥራት እንደምትችል የሚገልጽ ነው፡፡

- 1ቆሮ.12÷7

7. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።

3) ፀጋ ሥጦታ ለክርስቲያኖች በብዙ ዓይነት የሚሰጥ ነው፤እግዚአብሔር ፀጋ ሥጦታ የሰጠው ቤተ ክርስቲያን እንዲገነባና እንዲያዲግ ነው፡፡

- 1ቆሮ.12÷8-10

8. ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፥
9. ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፥
10. ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤

4) በፀጋ ሥጦታ ውስጥ ትልቅና ትንሽ የሚባል ነገር የለም፤ ሁሉም ሥጦታዎች እኩል ናቸው፡፡እግዚአብሔር ፀጋ ሥጦታ የሰጠበት ዋና ነገሩ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ወይም ቤተ ክርስቲያን እንዲታነጽ ነው፡፡

- 1ቆሮ.12÷20-21

20. ዳሩ ግን አሁን ብልቶች ብዙዎች ናቸው አካል ግን አንድ ነው።
21. ዓይን እጅን። አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም፥ ወይም ራስ ደግሞ እግሮችን። አታስፈልጉኝም ሊላቸው አይችልም።

5) ሁሉም ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ፀጋ ሥጦታ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያንጹና እንዲጠቅሙም እግዚአብሔርንም እንዲያገለግሉ ይፈለጋል፤መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው ፀጋ ሥጦታ የክርስቶስን አካል ማነጽ አለብን፡፡

- 1ጴጥ.4÷10

10. ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤

6) ዳግመኛ የተወለዱ ክርስቲያኖች ማንኛውም ሰው ከእግዚአብሔር አንድና ከአንድ በላይ የሆነ ሥጦታ ተቀብለዋል፡፡

- 1ቆሮ.12÷11

11. ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።

★ በመንፈሳዊ ፀጋ ሥጦታ አንተ በየተኛው ሊታገለግል ትፈልጋለህ? አንተ በዚያው ሥጦታ እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ቢታገለግል የተሻሌ ነገር ትሠራለህ፡ ፡

① መንፈሳዊ ፀጋ ሥጦታ እግዚአብሔር የምሰጥ ነው፤
② በመንፈሳዊ ፀጋ ሥጦታ እውነትና ውሸት የሚባል ነገር የለም፤
③ በየተኛው ለማገልገል እንደሚትፈልግ ለጥያቄው መልስ ስጥ፤ አንተ በምን ዓይነት አገልግሎት ሊታገልግል ትወዳለህ?

★ የመንፈሳዊ ሥጦታ ትርጉም

1. መንፈሳዊ ሥጦታ ልዩ የሆነ ሥጦታ ነው፤

- 1ቆሮ.12÷7

7. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።

2. መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ሰው እንደፈቀደ የሚያድለው ነገር ነው፤

- 1ቆሮ.12÷11

11. ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።

3. ለሁሉም ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚሰጥ ነው፤

- 1ጴጥ.4÷10

10. ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤

4. ለክርስቶስ አካል ለማነጽ የሚሰጥ ነው፤

- 1ቆሮ.12÷7

7. ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል።

2. የፀጋ ሥጦታ ዓይነት

1) 1ቆሮ.12÷8-10 ቁ.28 የሚገልጸው የፀጋ ሥጦታ ዓይነቶች 13 ናቸው እነርሱም፡- የጥበብን ቃል መናገር፤የዕውቀትን ቃል መናገር፤እምነት፤ፈውስ፤ሥልጣን፤ትንቢት መናገር፤መናፍስትን መለየት፤ታምራት ማድረግ፤ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፤ በልዩ ልዩ ልሳን የተነገረውን የመተረጎም ሥጦታ፤ሐዋሪያነት፤ ማስተማር፤ ርዳታና መሪነት ናቸው፡ ፡

- 1ቆሮ.12÷8-10 ቁ.28

8. ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፥
9. ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፥
10. ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤

28. እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል።

2) ሮሜ12÷6-8 የሚገልጸው የፀጋ ሥጦታ ዓይነቶች ከላይ በ1ቆሮ.12 ላይ ከተገለጹት ሌላ ሦስት የፀጋ ሥጦታዎች በዚህ ምዕራፍ ተጨምሮ ይገኛሉ፡ ፡እነርሱም፡- ማስተዳደር፣ ድኻ ሰዎችን መርዳትና ማገልገል (በሽምግልና) ወይም በመጋቢነት አገልግሎት ናቸው፤

- ሮሜ12÷6-8

6. እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤
7. አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤
8. የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር

3) ኤፌ.4÷11 የሚገልጸው ፀጋ ሥጦታ ከላይ የተጠቀሱትን የፀጋ ሥጦታ ሁሉ እንዳለ ሆኖ የሚጨምራቸው ሁለቱ ፀጋ ሥጦታዎች ወንጌል ምስክርነትና መጋቢነት ናቸው፡ ፡

- ኤፌ.4÷11

11. እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤

4) 1ጴጥ.4÷9-10 የሚገልጸው ፀጋ ሥጦታ ድኾችን መርዳት ነው፡ ፡

- 1ጴጥ.4÷9-10

9. ያለ ማንጐራጐር እርስ በርሳችሁ እንግድነትን ተቀባበሉ፤
10. ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤

5) ዘጸ.31÷3 የሚገልጸው የፀጋ ሥጦታ በሁሉም ዓይነት የእጅ ጥበብ ችሎታ መኖር ነው፡ ፡

- ዘጸ.31÷3

3. በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም በማስተዋልም በእውቀትም የእዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት

6) 1ጢሞ.2÷1-2 የሚገልጸው የፀጋ ሥጦታ ልመና፣ጸሎት፣ምልጃና ማመስገን ናቸው፡ ፡

- 1ጢሞ.2÷1-2

1-2 እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።

7) መዝ.150÷3-5 የሚገልጸው የፀጋ ሥጦታ ድምፅ ባለው ዕቃዎች (መሣሪዎች) በሙያቸው እግዚአብሔርን ማመስገን

- መዝ.150÷3-5

3. በመለከት ድምፅ አመስግኑት በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት።
4. በከበሮና በዘፈን አመስግኑት በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት።
5. ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት።

3. የፀጋ ሥጦታ መመርመር

★ መመሪያ

1) የፀጋ ሥጦታ መመርመሪያ ጥያቄ ካነበብህ በኋላ ያንተ ፀጋ ሥጦታ የሚያድግበት ሁኔታ የሚያሳይ ነጥብ ስጥ፡ ፡

- ሁልጊዜ በትክክል የሚታደርገውን (4) ቁጥር ጻፍ፡ ፡
- ከግማሽ በላይ በትክክል እሠራለሁ የሚትል ከሆነ (2) ቁጥር ጻፍ፡ ፡
- አንዳንድ ጊዜ በትክክል እሠራለሁ የሚትል ከሆነ (1) ቁጥር ጻፍ፡ ፡
- ፍጹም አልሠራሁትም የሚትል ከሆነ (0) ቁጥር ጻፍ፡ ፡

2) ወደፊት በሚል በተስፋ እምነት መልስ የሚሆኑ ቁጥሮችን አትጻፍ፤ አሁን አንተ እያደርግህ ያለውን የሚታውቀውን ጻፍ፡ ፡

3) ዐረፍተ ነገሩን አንብበህ በ2 ሰከንድ ልዩነት ቁጥሮች ጻፍ፡ ፡

★ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡ ፡

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሰዎች ባህሪያቸውን በጥልቀት እንዲያስተካክሉ መስበክ ( )
2. የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በማስተማር ብዙ ደስታ ማግኘት ( )
3. የእግዚአብሔርን ቃል በሕይወት በፍጹም እምነት ወደ ግብ ማድረስ ( )
4. በፀሎት ሕመምተኞችን መፈወስ ( )
5. የእግዚአብሔር መኖር በታምራት ማሳየት ( )
6. የእያንዳንዱ የሰዎች ሁኔታ በማወቅ በመልካም ፈቃድ ማስተናገድ ( )
7. የሰዎችን ጥሩና መጥፎ ጎኖች ሰምቶ መለየት ( )
8. በፀሎት ጊዜ በልሳን እየፀለዩ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ( )
9. የልሳን አውድ ወዲያውኑ በመረዳት ትርጉም መስጠት ( )
10. ቤተ ክርስቲያን በለሌበት ቦታ ሄዶ አዲስ ቤተ ክርስቲያን መትከል ( )
11.መጽሐፍ ቅዱስን በቀላሉ ተረድቶ ለሰዎች መተረጎም ( )
12. ሰዎች ምን እንደሚፈልጉ በመረዳት ትክክለኛውን ርዳታ መስጠት ( )
13. ዕቅድን ወደ ግብ እንዲያደርሱ ለሰዎች ማስተላለፍ ( )
14. ሰዎችን የሚያጽናና፣የሚመክርና የሚያድን ቃል መናገር ( )
15. በዕውድ አምልኮ ከመቶ አስር እጅ በላይ ምጽዋት፣ መባ በመስጠት ደስተኛ መሆን ( )
16. ከብዙ ሰዎች ጋር በተመሳሳይ ፍቅርና ልብ መነጋገር ( )
17. ድኾች በማየት ከልቡ ራርቶ መርዳት ( )
18. ኢየሱስ ክርስቶስን ያላመኑ ሰዎችን ሰምቶና አይቶ በታላቅ ፍቅር መውደድ ( )
19. ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ እንዲከተሉ በማሰልጠን ደስተኛ መሆን ( )
20. አዲስ ሰዎችን በፍቅር በመቀበል ደስተኛ መሆን ( )
21. ብዙ ዓይነት ዕቃዎችን በችሎታ ሠርቶ መጠቀም ( )
22. በየቀኑ ከ3 ሰዓት በላይ በሥልጣን መፀለይ ( )
23. በመዝሙርና በድራማ በተለያዩ በሙዝቃ መሣሪያዎች በሽብሸባ በክነ-ጥበብ ወዘተ… በመጠቀም ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ( )
24. መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ሕይወቱን በዝርዝር ተመልክቶ ሕወቱን ማስተካከል ( )
25. የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ክርስቲያኖች ከሀሳባቸው ጋር እንዲያዋህዱ በሥልጣን መተረጎም ( )
26. እግዚአብሔርን ፍጽም ተስፋ በማድረግ ሁልጊዜ በድፍረት መኖር ( )
27. እግዚአብሔር ሁሉንም ሕመም እንደሚፈውስ ተስፋ ማድረግ ( )
28. የእግዚአብሔርን ታላቅነት ታምራት በማድረግ በአካባቢ ማስመሰከር ( )
29. ከእግዚአብሔር ወዲያውኑ በሚቀበለው ቃል ሌሎችን መርዳት ( )
30. የሰዎች ቃል ጥሩ ይሁን መጥፎ ማታለል ይሁን እውነተኛ ለይቶ መቆጣጠር ( )
31. ባልተማረ (በማያውቅ) ቋንቋ ደንብ መፀለይ ( )
32. በልሳን የተነገረውን ለሌሎች ሰዎች መተረጎም ( )
33. የቤተ ክርስቲያን የምሥራች ቃል በሥልጣን ማስተማር ( )
34. ለሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በደንብ ለመግለጽ መታዘዝ ( )
35. ሌሎች ሰዎችን በደንብ መርዳት ( )
36. ሥራን በሥርዓት በደንብ መሥራት ( )
37. አንዳንድ ሰዎችን በችሎታቸው ለመያዝ መጣር ( )
38. ለእግዚአብሔር ንብረትንና ገንዘብን ያለ ስስት መስጠት ( )
39. ሥራን በሥርዓቱ በደንብ ለውጤት እንዲሰሩ ማህበረሰቡን ማነሳሳት ( )
40. የሌሎችን ስቃይ እንደራሱ አድርጎ በማየት መራራት ( )

41. ኢየሱስ ክርስቶስን ካላመኑ ሰዎች ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ዘውትር ለእነርሱ ወንጌልን በመመስከርና አቅጣጫ በማሳየት ደስተኛ መሆን ( )
42. በእምነት ደካማ የሆኑ ሰዎች ቁርጥ አቋም እንዲኖራቸው በፍቅር ልብ ማሰልጠን ( )
43. እንግዶችን በመቀበል ህብረት ማድረግ ( )
44. ብዙ ዓይነት ዕቃዎችን መጠቀም ( )
45. በፀሎት ደስተኛ መሆን ( )
46. በአሁኑ ጊዜ የሚያሳስብ ባህል ቢኖርም በዚያው ባህል ኢየሱስ ክርስቶስን ለሰዎች ማሳወቅ ( )
47. በመከራና በችግር ጊዜ አስፈላጊውን መፍተሔ መስጠት ( )
48. መጽሐፍ ቅዱስን ተንትኖ ስተረጉም ስቃይና መከራ በሚደርስበት ጊዜ ደስተኛ መሆን ( )
49. ያለጥርጣሬ የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ ( )
50. ማንኛውም ህመም ስያምም ያለጥርጣሬ ስለ ፈውስ እግዚአብሔርን መለመን ( )
51. የእግዚአብሔርን ታምራት በሥለጣን ማከፋፈል ( )
52. እግዚአብሔር የሚሰጠውን ማስጠነቀቂያ በግልጽ ለሰዎች አቅጣጫ ማሳየት ( )
53. የመንፈስ ቅዱስ ሥራና የክፉ መንፈስ ሥራ መለየት ( )
54. በልሳን በሥልጣን መፀለይ ( )
55. የራሱን ልሳን አውጹን ጠብቆ መተረጎም ( )
56. በገጠርና በሌሎች አገሮች አዲስ ቤተ ክርስቲያን መትከል ( )
57. ብዙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ እውነት ባንተ በኩል እንዲረዱ መናገር ( )
58. ሰዎችን ለመርዳት በሚታስብበት ጊዜና ያሰብከውን በሚታከናውንበት ጊዜ ደስተኛ መሆን ( )
59. ራዕይን በማካፈል ከሌሎች ሰዎች ጋር በመስራት ወደ ግብ መድረስ ( )
60. ሌሎች ሰዎችን እያስጠነቀቀ አንዳንድ ጊዜ የራሱን ሕይወት ማየት ( )
61. ሌሎች ሰዎች ገንዘብ እንደሚፈልጉ ለይቶ ማወቅ ( )
62. ከሌሎች ሰዎች ጋር በጓደኝነት አብሮ በመስራት ወደ ግብ መድረስ ( )
63. በሥጋ ሕመምና በአዕምሮ ሕመም የሚሰቃዩት ሲገናኙ ጥልቅ የሀዘን ስሜት ማሰማት ( )
64. ከማይታወቁ ሰዎች ጋር በቀላሉ የመነጋገር ችሎታ መኖር ( )
65. ሰዎች ንግግርህንና አድራጎትህን በውሳኔ መከተል ( )
66. በብዙ ፍቅር ምኞትን ለሰዎች በሥልጣን መስጠት ( )
67. ከሌላ ሰው ችሎታ መቀበል ( )
68. ሌሎች ሰዎች የፀሎት ርዕስ ስሰጡ ( )
69. በብዙ ዓይነት በክነ-ጥበብ አንድ ላይ ለመጠቀም ፍላጎት ማሳደር ( )
70. ችግሮች ሲመጡ ከእግዚአብሔር ቃል ለችግሮች መፍተሔን ማግኘት ( )
71. እምነትን ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ደስተኛ መሆን ( )
72. አንድ መከራ ሲያገኝ እግዚአብሔር አብሮ መልካም ነገር እንዲያደርግ ማጽደቅ ( )
73. ለሕመምተኞች በሚፀለይበት ጊዜ ሙቀት መሰማት ( )
74. እግዚአብሔር ባንተ በኩል የሰዎችን ችግር ሲፈታ ( )
75. ወደፊት የሚሆኑ አስፈላጊ ነገሮችን እግዚአብሔር በሰጠው ማወቅ ( )
76. ሌላው ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ስተረጉም እውነቱንና ስህተቱን ወዲያውኑ ለይተው እንዲያወቅ ማስተካከል ( )
77. በልሳን ስትፀልይ ምላሽ ወዲያውኑ ማግኘት ( )
78. ላልተማሩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በሚሰሙበት ጊዜ ለእነርሱ በቋንቋቸው መተረጎም ( )
79. ስለ ድኻ ቤተ ክርስቲያን፣ስለ መጋቢ፣ ስለ ወንጌላዊ በልዩ ሁኔታ ማሰብ ( )
80. ሰዎች ራሳቸውን እንዲያስተካክሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል አጭርና ግልጽ በሆነ መንገድ ማስተማር ( )
81. በፀጋ ሥጦታህ ሌሎች ሰዎች ፀጋቸውን በደንብ እንዲያውቁ በመድረግ ( )
82. ሰዎች የራሳቸውን ፀጋ ሥጦታ አውቆ እንዲያገለግሉ በየሥጦታቸው ማስተናገድ ( )
83. የመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳብ ለሰዎች እንዲገባ በማስተዋል እንደ አውዱ ማካፈል ( )
84. የአካባቢ ድኻ ሰዎችን በደንብ መርዳት ( )
85. ሰዎችን በየሥጦታቸው መመደብ ( )
86. ርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን በመለየት በፍቅር በደንብ መርዳት ( )
87. በወንጌል ስበከት ብዙ ሰዎች ማዳን ( )
88. ሰዎች የራሳቸውን ፀጋ ሥጦታ እንዲያገኙ ርዳታ በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ማብቃት ( )
89. ለእንግዶች ምግብና ማረፍያ ሥፍራ በማዘጋጀት ( )
90. በቤትና በቤተ ክርስቲያን መልካም ሥራ መሥራት ( )
91. ብዙ ጊዜ በመፀለይ መልስ ማግኘት ( )
92. ከሌላ ሰው ብዙ ዕውቀትና ብልሃት መማር ( )
93. የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል ማጥናትና ያጠናውን በደህና ቦታ ማስቀመጥ ( )
94. ለቤተ ክርስቲያን ሰዎች ርዳታ የመስጠት ጥበብ ( )

95. ሁሉንም ፍላጎት እግዚአብሔር እንደሚሰጥ ማመን ( )
96. በፈውስ የእግዚአብሔር እጅ እንደሚትመጣ ማመን ( )
97. የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሔር የሰራውን ታምራትንና ፈውስን አይተው እንዲያምኑ ወንጌልን መመስከር ( )
98. ማንኛውንም ነገር ሳይፈራ በቃሉ መሠረት ጠንካራ ሥልጣን ማሳየት ( )
99. ሰው ያዘዘውን ለመፈጸም በእምነት ወደ ግብ መድረስ ( )
100. ባልተማረ ቋንቋ መዝሙር መዘመር ( )
101. በልሳን የተነገረውን በመተረጎም ለሰዎቹ ሁኔታቸውን ገልጾ በማነጽ ሰዎቹ ለምሥጋና እንዲደርሱ ማድረግ ( )
102. ቤተ ክርስቲያን በሌለበት ቦታ በማዘን በዚያ ቦታ ቤተ ክርስቲያን መትከል ( )
103. ሰዎችን መጽሐፍ ቅዱስ በማስተማር ደስተኛ ማድረግ ( )
104. ያልተገለጸውን ሥራ ማለትም ለሽልማት የሚያደርሰውን ብቻ ሳይሆን አነስተኛ የሆነውን ሥራ ለመስራት ፈቃደኛ መሆን ( )
105. ትክክለኛውን ድምር ማዘጋጀት ( )
106. ብዙ ሰዎችን ለማጽናናት ጥሪ መደረግ ( )
107. በየእሁዱ አምልኮ ምጽዋት መስጠትና ርዳታ ማድረግ መልካም ሕይወት ማሳየት ( )
108. አሁን በየተኛው አቅጣጫ እንዳለህና ወዴየት መሄድ እንዳለብህ ማወቅ ( )
109. የድኻ ሰዎች የኑሮ ሁኔታ በማወቅና በአዕምሮአቸው የሚታመሙትን መርዳት ( )
110. በፀሎት ሰዓት ስለ ወንጌል ሰባኪዎች ትኩረት ሰጥቶ መፀለይ ( )
111. ርዳታ ከሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ጋር አብሮ መፀለይ ( )
112. የሚመች ሕብረት ማግኘት ( )
113. ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን ዕቃዎችን በተለያዩ ዘዴ ቀርጾ የማዘጋጀት ሀሳብ መፍጠር ( )
114. የሌሎች የፀሎት ርዕሶችን በመቀበል ስለ እነርሱ በየቀኑ መፀለይ ( )
115. ወንጌልን መልካም በሆነ በብዙ መንገድና በተለያየ ሙያ መመስከር ( )

4. የመረመርከው ፀጋ ሥጦታ ውጤት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ጻፍ፡፡

1) የመጀመሪያ የጥያቄዎች መልስ ቁጥር ከ1-115 ድረስ ወደታች ጻፍ፡፡

2) ከግራ ወደ ቀኝ ከ1-5 ወደ ጎን የእያንዳንዱ ተራ ቁጥር ድምር ጻፍ፡፡

3) የጠቅላላ ድምራቸው ከፍተኛውን ነጥብ ከ1-3 ደረጃ ስጣቸው፡፡

ተራ ቁጥር	የፀጋ ሥጦታ ውጤት (ነጥብ)				ድምር	ከፍተኛከ1-3 ደረጃ	የፀጋ ሥጦታ ዝርዝር
1	1	24	47	70	93		ጥበብ
2	2	25	48	71	94		ዕውቀት
3	3	26	49	72	95		እምነት
4	4	27	50	73	96		ፈውስ
5	5	28	51	74	97		ታምራት ማድረግ
6	6	29	52	75	98		ትንቢት መናገር
7	7	30	53	76	99		መናፍስትን መለየት
8	8	31	54	77	100		በልሳን ቋንቋ መናገር
9	9	32	55	78	101		በልሳን የተነገረውን መተረጎም
10	10	33	56	79	102		ሐዋሪያ (አዲስ ቤተ/ያን መትከል)
11	11	34	57	80	103		አስተማሪ
12	12	35	58	81	104		ርዳታ (የሚያገለግሉትን)
13	13	36	59	82	105		ማስተዳደር
14	14	37	60	83	106		ማጽናናት
15	15	38	61	84	107		ድኾችን መርዳት
16	16	39	62	85	108		መሪነት
17	17	40	63	86	109		ህብረት (አንድነት)
18	18	41	64	87	110		ወንጌል መመስከር
19	19	42	65	88	111		መጋቢነት (ሥልጠና የሚሰጥ)
20	20	43	66	89	112		እንግዳ መቀበል
21	21	44	67	90	113		የተለያየ ክነ-ጥበብ ሙያ (ችሎታ)
22	22	45	68	91	114		ስለ ሌሎች በርዕስ መፀለይ
23	23	46	69	92	115		በተለያዩ መሣሪያዎች ቅርጻቅጽ መስራት

5. የፀጋ ሥጦታ የምርመራ ውጤት

በአንደኛ ላይ የተጻፈው የጥበብ ፀጋ ሥጦታ ካነጻጸርህ በኋላ ያንተ ፀጋ ሥጦታ የተኛው እንደሆነ ማወቅ ትችላለህ፡፡እኩል የሆኑ ነጥቦችን ከ1-3 ደረጃ በመስጠት የቁጥሮቹ ድምር ባለበት በመክበብ ደረጃ ስጣቸው፡፡

ያንተ የፀጋ ሥጦታ	1
	2
	3

በሚቀጥለው ገጽ የሚገልጸው የፀጋ ሥጦታ የእያንዳንዱን ይገልጻል፡፡ ከላይ የዘረዘርካቸው ያንተ የፀጋ ሥጦታ ናቸው፤ (ውጤታቸው አንድ ዓይነት የሆኑትን ሲታገኝ ከዚያ የሚበልጥ ውጤት ከሌለ በደረጃ 1 ላይ ጻፍ ሌሎችንም እንደ ውጤታቸው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ ትችላለህ፡፡

ከ1-3 ድረስ ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው የፀጋ ሥጦታ በሠንጠረዡ ውስጥ ካገኘኸው በልብህ ውስጥ ታላቅ ስሜትና ምኞት የሚሰጠው ፀጋ ሥጦታ ያ እንደሆነ በትክክል ትረዳለህ፡፡ በእነዚህ ሥጦታዎች በማስተዋል ቤተ ክርስቲያንን ቢታገለግል ቤተ ክርስቲያን ትታነጻለች፡፡

6. የፀጋ ሥጦታ ፀባይ

1. የጥበብ ፀጋ ሥጦታ

1. ትርጉም

የእውነትን ቃል ዘርዝሮና ተንትኖ ማስተካከል ነው፡፡

2.ልዩ ተግባር

① በንግግር ጊዜ የመንፈስን ፈቃድ ያሳውቃል፡፡

② በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሰዎች እንዲንመርመር ያደርጋል

③ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብክ ያስችላል፡፡

④ የመንፈስ ቅዱስ አብሮ የመኖር ስሜት እንዲሰማ ያደርጋል፡፡

⑤ ችግሮችን በጥበብ መፍታት እንዲንችል ይረዳል፡፡

⑥ ውጤት የሚያስገኘው ሥራ የተኖው እንደሆነ እንዲረዳ ያደርጋል፡፡

⑦ መልካም የሆነው መንገድ ለይተን እንድናውቅ ያግዛል፡፡

4. ጥንቃቄ

① በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል በጥሞና ማንበብ፡፡

② ሰዎችን ሊረዳ የሚችል ቃል በውስጡ ስጠፋ ዝም ማለት፡፡

③ በማዘዝ ሳይሆን በትህትና ማናገር፡፡

⑧ ጥበብ የጎደላቸውን ሰዎች ካገኘህ መታገስ፡፡

5. የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማመሳከሪያዎች

ሐዋ.6÷3፣ ቁ 10፣ 1ቆሮ.2÷1-13፣ 12÷8፣ ያዕ.1÷5-6፣ 2ጴጥ.3÷15-16

⑨ ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው፣ የክፍት ስብከት መሪ፣ የክፍል ቤተሰብ ስብከት መሪ፣ ልምምድ የሚደርግ፣ የደቀ መዛሙርት ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፣ ስለ ሌሎች ሰዎች የሚፀልይ ቡድን፣የማጽናናት ሰው፣ ለችግሮች መፍተሔ የሚሰጥ፣ የፀጋ ሥጦታ ማጽናናት የሚሰጥ አስተማሪ፣ ዕቅድ፣ማሳተም፣ወረቀት ማዘጋጀት፣ለወንጌል ምስክርነት የሚረዳ ወረቀት ማቅረብና ቢድዮ ማዘጋጀት ወዘተ…

2. የእውቀት ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

የእውነትን ቃል በደንብ ተንትኖ ትርጉምን የመስጠት ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እውነት በደንብ እንዲናስተውል ያደርጋል፡፡

② ለረጅም ጊዜ አትኩሮትን እንዲንሰጥ ይረዳል፡፡

③ ታላቅ ዕውቀት እንዲናገኝ ይጠቅማል፡፡

④ የእግዚአብሔር ልዩ ዕቅድና ወደፊት የሚሆኑ ነገሮች እንዲናውቅ ይረዳል፡፡

⑤ ራዕይን አውቀን በሥልጣን እንዲናገለግል ያደርጋል፡፡

⑥ ብዙ ሃሳቦችን በማብራራት እንዲናስተዳደር ይጠቅማል፡፡

⑦ ስለ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት አስፈላጊውን ዕውቀት እንዲሰጥ ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ

① ምስጢር የሆኑ ነገሮችን ስላወቅህ አትታበይ (ትምክህተኛ) አትሁን፤

② ያወቅኸውን ፀጋ ሥጦታ ሌሎችን በደንብ ለማስተማር ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር መገናኘት፤

③ የትዕቢት ሃሳብ አውጥተህ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለመስራት ፈቃደኛ መሆን፤

④ የእኔ ሃሳብ ይፈጸም በማለት ግትረኛ አትሁን ከሌሎች ሰዎች ጋር ሥራ፤

4. የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያዎች

ሮሜ15÷14፣ 1ቆሮ.8÷1-2፣ 2ቆሮ.11÷6፣ ቆላስ.2÷2-3

5 ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

የክፍት ስብከት መሪ፣ የክፍል ቤተሰብ ስብከት መሪ፣ ልምምድና የደቀ መዛሙርት ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፣ መምህር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ፣ስለ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሚረዳ ትምህርት ሥልጠና የሚሰጥ አስተማሪ፣ ህብረት ማዘጋጀት፣ የረጅም ዕቅድ ማነጽ፣ የማወጅ ሥራ ማከናወን፣ ሴሚናር ትምህርት መማር፣ ሐዋሪያነት፣ ማስተዳደር፣ ዳታ መሰብሰብ፣ ኮምፒዩተር ሥራ ማቀናጀት፣ገንዘብ ያዥ ማዘጋጀትና የሚጠቅሙ ወረቀት መሰብሰብ፡፡

3. የእምነት ፀጋ ሥጦታ

1. ትርጉም

የእግዚአብሔርን ሥልጣን በማመን፣ በእምነትና በተስፋ እንዲንከተል የማድረግ ሥልጣን፡፡

2. ፀባይና ልዩ ተግባር

① የእግዚአብሔር ፈቃድና ምኞት እንዲናገኝ ይረዳል፡፡

② በታምራት የእግዚአብሔርን መኖር እንድንገልጽ ይጠቅማል፡፡

③ ለችግርተኞች መጽናናት፣ ፈውስን፣ድልንና ምኞት ዕንድንሰጥ ይጠቅማል፡፡

④ የእግዚአብሔር ቃል ስለሚያደርገው ነገር በተስፋ እንዲዘጋጅ ይረዳል፡፡
⑤ የእግዚአብሔርን ቃል በፍጹም እንዲናምን ያደርጋል፡፡
⑥ የእግዚአብሔርን ቃል በማመን ችግሮች በሚደርሱበት ጊዜ ወደ ኋላ እንዳናፈገፍግ ድፍረትን ይሰጣል፡፡
⑦ በአዲስ ራዕይ እንዲናድግ ይረዳል፡፡

3. ጥንቃቄ
① የሌሎችን ፀጋ ሥጦታ መመኘት አያስፈልግም፡፡
② ግብና ራዕይ ሲጠፋ ለምን እንደጠፋ በመስማማት ምክንያቱን ማግኘት፡፡
③ የራስ ሀሳቦችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ማትለቅ አያስፈልግም፡፡
④ ለጥሩ ዕቅዶች ማስጠነቀቂያ ሲነገር የሚነገረውን ጥንቃቄ መቀበል፡፡

4. የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያዎች
ሐዋ.11÷22-24፣ 27÷21-25፣ ሮሜ4÷18-21፣ 1ቆሮ.12÷9፣ ዕብ.11

5. ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች
ስለ ሌሎች ሰዎች የፀሎት ቡድን፣ የረጅም ዕቅድ መገንባት፣ አዲስ ቤተ ክርስቲያንን መትከል፣ በገዛ አገር ወንጌል የሚመስክር ቡድን፣ ሚሽኔሪዎችን መላክ ወዘተ . . .

4. ሕመምተኞችን የሚፈውስ ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም
የእግዚአብሔርን ፈውስ ለምያምኑት በአካል ላይ ያለ ሕመም ቢሆን የአዕምሮ ሕመም ቢሆን የመንፈሳዊ ሕመም ሁሉንም የመፈወስ ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር
① ሁሉንም ሕመም ፈውሶ ምኞትና ድልን እንዲናገኝ ይረዳል፡፡
② ለሕመምተኞች በፀሎት ፈውስን እንዲሰጥ ይጠቅማል፡፡
③ በመድኃኒት ያልተፈወሰውን ሕመም በእግዚአብሔር ርዳታ ፈውስን እንደሚቀበል ይረዳል፡፡
④ በሥልጣንና በምኞት እንዲንፀልይ ያደርጋል፡፡
⑤ እግዚአብሔር ሰዎችን (አገልጋዮችን) የፈውስ ዕቃ አድርጎ እንደሚጠቅም መረዳት ያስፈልጋል፡፡
⑥ ለሕመምተኞች እንዲንፀልይ ያደርጋል፡፡
⑦ በኢየሱስ ስም በሥልጣን እንዲንፀልይ ያደርጋል፡፡

3 ጥንቃቄ
① እግዚአብሔር በመድኃኒት በኩል እንደሚፈውስ መስማማት፡፡
② የሚፈውሰው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነና አገልጋዩ ዕቃ መሆኑን በማወቅ ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት፤
③ ረጅም ጊዜ በተጸለየው ጸሎት ፈውስ ካልመጣ አለመጠራጠር፡፡
④ ለመጋቢ በመታዘዝ መልካም ሥራ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማድረግ፡፡

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማመሳከሪያዎች
ዮሐ.9÷1-12፣ ሐዋ.3÷1-10፣ 5÷12-16፣ 1ቆሮ.12÷9፣ ያዕ.5÷14-15

5 ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች
ሌሎችን በፀሎት የማጽናናት ቡድን፣ በቤተ ክርስቲያን የመመስከር ቡድን፣የፈውስ ቡድን ወዘተ . . .

5. በሥልጣን ታምራት የማድረግ ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም
ታምራት በማድረግ የእግዚአብሔርን መልዕክት በሥራ ማሳየት

2 ፀባይና ልዩ ተግባር
① እግዚአብሔር በሚያደርገው ታምራት በኩል የእግዚአብሔር መኖር በምስክርነት እንዲናሳይ ይጠቅማል፤
② የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲንስማማ ይረዳል፡፡
③ በሚከናወኑ ነገሮች እግዚአብሔርን እንዲናውቅ ያደርጋል፡፡
④ ስለ እግዚአብሔር ፍጹም እምነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡
⑤ ታምራቶችን በሕይወታችን ብዙ ጊዜ እንዲናይ ያደርጋል፡፡
⑥ የተዘጋው የወንጌል በር እንዲከፈት ይጠቅማል፡፡
⑦ ወንጌል በሚሰበክበት አካባቢዎች ታምራትን እንዲገልጽ ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ

① በራሳችን ላይ እግዚአብሔርን ከፍ ማድረግ፤
② ራሳችንን የሚያሳይ ሥራ ከቶ አለማድረግ፤
③ የእግዚአብሔር ሥራ በእኛ የሚሆንበትን ሰዓትና ሁኔታን መስማማት፤
④ እንደ ቃሉ መሠረት ትክክለኛውን ሥራ ማድረግ፤

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያዎች
ማቴ.14÷28-33፤ ሐዋ.19÷11-20፤ 9÷36-42፤ ሮሜ15÷18-19፤ 2ቆሮ.12÷12

5 ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች
የክፍት ስብከት መሪ፣ለሌሎች ሰዎች የሚፀልይ ቡድን፣ የክፍል ቤተሰብ ስብከት መሪ፣ የወንጌል ስብከት ቡድን፣ በውጭ ሚሽኔሪዎች የሚልክ ቡድን ወዘተ. . .

6. የትንቢት ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም
የእግዚአብሔርን ቃል በሕይወቱ በዝርዝር አስተካክሎ አቅጣጫ በማሳየት ስለ ወደፊት የማወቅ ሥልጣን

2 ፀባይና ልዩ ተግባር
① የእግዚአብሔርን ቃል በዝርዝር በጥልቀት አስተውለን ሕይወታችን እዲናስተካክል ይጠቅማል፡፡
② ኃጥአትን በደንብ እንዲንናዘዝ ያደርጋል፡፡
③ ማጽናናት፣ ምሪትን፣ ጥንቃቄን፣ አጽኦትን፣ መልካም ሃሳብን፣ ቅድስናን፣ ትምህርትን ይሰጣል፡፡
④ የራሳችን ህብረተሰብ የሚፈልጋቸውን ነገር እንዲናገኝ ይረዳል፡፡
⑤ የእግዚአብሔርን ድምጽ እንዲንሰማ ያግዛል፡፡
⑥ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል እንዲታዘዙና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡
⑦ የወደፊት ነገር በትንቢት እንዲናውቅ ያደርጋል፡፡

3 ጥንቃቄ
① ስለ ሌሎች ሰዎች ጥንቃቄ ማድረግ፤
② የትንቢት መልዕክት ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ቃል መፈተሽ፤
③ በፍቅር መሠረት መተነበይ፤
④ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ዕውቀት ማግኘት፤

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ
ሉቃ.7÷26፤ ሐዋ.15÷32፤ 21÷9-11፤ ሮሜ12÷6፤ 1ቆሮ.12÷10

5 ሥራውን መስራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች
የክፍት ስብከት መሪ፣ የክፍል ቤተሰብ ስብከት መሪ፣ ልምምድና የደቀ መዛሙርት ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፣ መምህር፣ በውጭ አገር የሚሽኔሪዎች ቡድን፣ የቃል ስብከት፣ ማጽናናት፣ የአምልኮ ቡድን የፀሎት ቡድን ወዘተ . . .

7. መናፍስትን የመለየት ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም
በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጥና በሰይጣን መንፈስ እውነተኛ መንፈስ የተኛው ትክክል የተኛው ውሸት እንደሆነ ለይቶ የማወቅ ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር
① የእግዚአብሔር ሥራና የሰይጣንን ሥራ ለይተን እንዲናውቅ ይጠቅማል፡፡
② ስለ ክርስቶስ የሚያደርግ ሰውና ስለ ሰይጣን የሚያደርግ ሰው የተኛው እንደሆነ እንዲንለይ ይረዳል፡፡
③ በቃልና በሥራ በአካባቢ እንዴት መሥራት እንደምቻል ዕውቀትን ይሰጠል፡፡
④ የሥጋ ሕመም የአዕምሮ ሕመም፣በዲያብሎስ እስራት የታሰረ የተኛው እንደሆነ ለይተን እንዲናውቅ ይጠቅማል፡፡
⑤ የውሸት ትምህርቶችን፣ታምራቶችንና ስብከቶችን እንዲለይ ይረዳል፡፡
⑥ ቤተ ክርስቲያን የሰይጣንን ውጊያ ለማሸነፍ እንድትዘጋጅና እንድትከላከል ያግዛል፡፡
⑦ የክፉ መናፍስት ምንጭ ከየት እንደሆነ እንዲናውቅ ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ
① ከመናገር በፊት መመርመር፤
② በትችት ሳይሆን በፍቅር መነጋገር፤
③ የራሱ ሀሳብ ፍጹም እንዳልሆነ መረዳት፤
④ በመንፈስ ቅዱስና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ፍጹም መሠረት ማድረግ፤

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ
ማቴ.16÷21-23፤ ሐዋ.5÷1-11፤ 16÷16-18፤ 1ዮሐ.4÷1-6

5 ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

ስለ ሌሎች በርዕስ የሚፀለይ ቡድን፣ የፀሎት ቡድን፣ የወንጌል ምስክርት ቡድን፣ ማህበረሰብን የሚያገለግል ቡድን፣ ዕቅድ፣ ማስተማር፣ ማወጅ፣ ማጽናናት፣ ኣጋንንትን (ዲያብሎስን) ማስወጣት፣የቤተ ክርስቲያን ህብረት መሪ፣ ማስተዳደር፣ ፀሐፊ ወዘተ. . .

8. የልሳን ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

ባልተማረ ቋንቋ መፀለይ፣መዘመርና መነጋር መቻል

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① ጥልቅ የፀሎት ልምምድ እንዲናደርግ ይጠቅማል፡፡

② በመንፈስ ኃይል እንዲንፀልይና እንዲንዘምር ያደርጋል፡፡

③ ስለ ሌሎች ሰዎች በልሳን እንዴት መፀለይ እንደምንችል ይረዳል፡፡

④ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ክርስቲያኖች በኃይል እንዲንፀልይ ያሳስባል፡፡

⑤ ወንጌል በሚሰበክበት ቦታና ሚሽኔሪዎች ባሉበት ቦታዎች ሰይጣን የሚያመጣውን አደጋ እንዲናፈርስ ይጠቅማል፤

⑥ የእግዚአብሔርን ቃል ባልተማረ ቋንቋ ለሌሎች እንድናካፍል ይጠቅማል፡፡

⑦ በልዩ ሁኔታ ከሌሎች ሰዎች ጋር ባልተማረ ቋንቋ እንድንነጋገር ያደርጋል፡፡

3 ጥንቃቄ

① የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በሚያዝዘው መሠረት ልሳን የሚናገረው ሰው በትርጉም መነጋገር፤

② ልሳን ተናጋሪው ድምጽ አውጥቶ በሚፀልይበት ጊዜ የራሱን ሕይወት ያንጻል፤ ነገር ግን ጉባኤው ስለማያጽ ስፀልይ ጉባኤውን በማያውክ ሁኔታ በመጠኑ ልፀልይ ያስፈልጋል፤

③ ልሳን ያልተቀበለና እምነት የሌለው እኩል አይደሉም፤

④ ልሳን ቀጣይነት እንዲኖረውና እንዲጠቅም ሁልጊዜ አዲስ ልሳን መፈለግ አለበት፤

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ

ማር.16÷17፤ ሐዋ.2÷1-13፤ 19÷1-7፤ 1ቆሮ.12÷10፤ 14÷4-6

5 ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

ስለ ሌሎች ሰዎች በርዕስ የሚፀልይ፣ የፀሎት ቡድን፣ የወንጌል ምስክርነት ቡድን፣ በውጭ የሚሽኔሪዎች ቡድን፣ ወዘተ. . .

9. የልሳን ቋንቋ የመተረጎም ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

በልሳን የተነገረውን ወዲያውኑ የመተረጎም ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① የልሳን ቋንቋ የሚተረጉም አብዛኛው የልሳን ቋንቋ መነጋገር ፀጋ ሥጦታ የተቀበለ ሰው ነው፡፡

② በልሳን ስፀልይ በሚተረጉምበት ጊዜ ፍጹም የፀሎት አውድ የጠበቀ ይሆናል፡፡

③ የልሳን ቋንቋ ስተረጎም ቤተ ክርስቲያን እንዲትታነጽ ይጠቅማል፡፡

④ የራሱን ልሳን ራሱ የሚተረጉም ሂደት እንዳለ እንዲናውቅ ያደርጋል፡፡

⑤ ሌሎች ሰዎች የተናገሩት ልሳን ሌላው ሰው የሚተረጉምበት ሂደት እንዳለ እንዲናውቅ ያደርጋል፡፡

⑥ የልሳን ቋንቋ የእያንዳንዱ ቃል ትርጉም ሳይሆን የጠቅላላውን ሀሳብ ትርጉም ይሰጣል፡፡

⑦ የልሳንን ቋንቋ የሚተረጉም ሰው እንደ ሌላው ትምህርት ተምሮ ሳይሆን፣ ከሥራም ሳይሆን ከዕውቀትም ሳይሆን እግዚአብሔር የሚሰጠው ፀጋ ሥጦታ ስለሆነ ከሌሎች ይለያል፡፡

3 ጥንቃቄ

① ሁልጊዜ ራሱን በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ መመርመር፤

② መጽሐፍ ቅዱስን ዘውትር በቅርበት ማንበብ፤

③ በግትርነት መተረጎም አያስፈልግም፤

④ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅምና ዕድገት መጋቢው መታዘዝ፤

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ

1ቆሮ.12÷10፣ቁ.30፤ 14÷5፤ቁ.13፣ ቁ.26-28

5 ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

ስለ ሌሎች በርእስ የሚፀልይ፣ የፀሎት ቡድን፣ የወንጌል ስበከት ቡድን፣ በውጭ ሚሽኔሪዎች ቡድን ወዘተ. . .

10. የሐዋሪያነት (አዲስ ቤተ ክርስቲያን መትከል፣ መሪነት) ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

በብዙ ቦታ አዲስ ቤተ ክርስቲያን የመትከል፣ የማስተዳደርና በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን የሥራ ቦታና የሥራ ሰዎችን የመምራት ሥልጣን፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① አዲስ ሥራ እንዲጋሠራና አዲስ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ባለው መንገድ እንዲንተክል ይተቅማል፡፡
② ቤተ ክርስቲያንን የሚተክሉ መጋቢ፣ሠራተኞች እያንዳንዱ ችግሮቻቸውን ተቆጣጥሮ መፍተሔ እንዲያገኙ ይረዳል፡፡
③ ከአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መሪዎችን በመምረጥ እንዲጋሠራ ይረዳል፡፡
④ አዲስ ቤተ ክርስቲያንን የሚገነቡ ሠራተኞችንና ሥራውን የሚመሩ መጋቢያንን እንዲናገኝ ይጠቅማል፡፡
⑤ አዲስ ቤተ ክርስቲያን በመስራት፣ እንዲንጽናና ታላቅ ሥራ እንዲንሠራ ያደርጋል፡፡
⑥ የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲስፋፋና ስለሚድኑ ነፍሳት ብዙ ሥራ እንዲንሠራና ታላቅ ጥሪ እንዲናገኝ ይጠቅማል፡፡
⑦ መሪዎች በደንብ እንዲከተሉ ለማድረግ ይቅማል፡፡

3 <u>ጥንቃቄ</u>
① ዝና ለማግኘት ብለህ ፀጋ ስጦታህን አትጠቀም፤ ምክንያቱም ተገቢ ያልሆነ አድራጎት መስራት አያስፈልግም፡፡
② በቤተ ክርስቲያንና በመጋቢ ስምምነት ያንን ፀጋ ሥጦታ ማገልገል፤
③ ብዙ ሥራዎችን ማውጣት፤
④ የራሱን የሥጋ ሀሳብ በመመጠን ታማኝ መሆን፤

4 <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ</u>
1ቆሮ.12÷28-29፤ 2ቆሮ.12÷12፤ ገላቲ.1÷1፤ ኤፌ.4÷11

5 <u>ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች</u>
አዲስ ቤተ ክርስቲያን መገንባት፣ የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣ የአብያተ ክርስቲያናት መሪ፣ የአካባቢ መሪ፣ ሚሽኔሪዎችን ወደ ሥፍራቸው የሚመራ መሪ፣ የሠራተኞች መሪ፣ የውስጥ ሚሽኔዎች አስተዳደር ቡድን፣ የውጭ ሚሽኔሪዎች አስተዳደር ቡድን፣ ዳይሬክተር፣አምስተኛ ክፍል ስብከት መሪ የአስተዳደር መሪ ወዘተ. . .

11. የማስተማር ፀጋ ሥጦታ

1 <u>ትርጉም</u>
የቃሉን እውነት በሰው አዕምሮ እንዲቀመጥ በደንብ የማስተማር ሥልጣን ነው፡፡

2 <u>ፀባይና ልዩ ተግባር</u>
① የእውነትን ቃል በቀለሉ እንዲናስታውስ ይጠቅማል፡፡
② ሌሎች ሰዎች ስለ እምነት ነገር የሚያሳስብ ቃል እንዲይዙ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡
③ በትዕግሥት ተማሪዎችን በነፃነት ጥያቄ ጠይቆ እንዲማሩ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡
④ የእግዚአብሔርን ቃል በደንብ በማስተማር ሌሎች ሰዎች ሀሳብ ተጽእኖ እንዲናደርግ ይጠቅማል፡፡
⑤ ሌላው ሰው እንዲያድግና መልካም ሥራ እንዲሠራ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡
⑥ ስለ እምነት ጉዳይ በታላቅ ፍቅር እንዲናስተምር ይረዳል፡፡
⑦ የንግግር ችሎታ እንዲናስተካክል ይጠቅማል፡፡

3 <u>ጥንቃቄ</u>
① ትምህርት በሚናዘጋጅበት ጊዜ ለቀጣይነት የሚሆን ትምህርት እንዲሆን ማስተማር፤
② ሌሎች የሚተቹትን ትችት (አስተያየት) በደንብ መቀበል፤
③ እውነተኛ አስተማሪ መንፈስ ቅዱስ ብቻ መሆኑን በማወቅ የእኛ ዕውቀት ውስን መሆኑን መረዳት፤
④ ከማስተማር በፊት ሁልጊዜ ለመማር ፈቃደኛ መሆን፤

4 <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ</u>
ሐዋ.18÷24-28፤ 20÷20-21፤ 1ቆሮ.12÷28፤ ኤፌ.4÷11-14፤ ያዕ.3÷1

5 <u>ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች</u>
ክፍት ስብከት መሪ፣ ክፍል ቤተሰብ ስብከት መሪ፣ የልምምድ አስተማሪ፣ የደቀ መዛሙርት ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፣ የልጆችና የወጣቶች አስተማሪ፣ የትንሽ ቡድን መሪ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተማረ ክፍል፣የትምህርት አስተዳደር፣ የወንጌል ስብከት ቡድን፣ የተለያዩ ትምህርቶችን የማስተማር አገልግሎት ወዘተ. . .

12. ርዳታ (የሚያገለግሉ አገልጋዮችን የማገዝ) ፀጋ ሥጦታ

1 <u>ትርጉም</u>
ሌላ የፀጋ ሥጦታ ያሉአቸውን አገልጋዮች ፍላጎት በሀሀላት እነዚያ ሰዎች በፀጋ ሥጦታቸው በደንብ እንዲያገለግሉ የመርዳት ሥልጣን ነው፡፡

2 <u>ፀባይና ልዩ ተግባር</u>
① የተቸገሩትን መርዳት ሳይሆን መንፈሳዊ ፀጋ ያላቸውን በፀጋቸው በርትተው እንዲያገለግሉ እንዲረዳ ነው፡፡
② ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥራና ስለ መሪዎች የራሳችንን ሕይወት እንዲንሰጥ ይጠቅማል፡፡
③ መሪዎች በሚያገለግሉበት ጊዜ በብዙ መንገድ እንዲረዳቸው ይጠቅማል፡፡
④ በቤተ ክርስቲያን ህብረት ሠላም እንዲኖር ለማድረግ ይጠቅማል፡፡
⑤ ራሳችንን መቼ፣ የት፣ ለማን፣ ምን፣እንዴት፣ በእነዚህ ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ ርዳታ ማድረግ እንደምንችል ለማሳወቅ ይጠቅማል፡፡
⑥ ርዳታውን ሳናያሳይ እንዲያደርግ ይጠቅማል፡፡

⑦ ለሌላው ሰው ሥልጣን እንዲናበረታታ ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ

① በሚረዳበት ጊዜ ርዳታውን ካልተቀበለ ማሳዘን የለበትም፤

② ለሌላው ሰው አነስተኛ ሥራ በሚኖርበት ጊዜ ከመጨነቅ (ከመወትወት) ነፃ መሆን፤

③ ከርዳታ ፀጋ ሥጦታ ሌላ በውስጥ ያለው ፀጋ የርዳታ ፀጋ ሥጦታ የሚጠቅም ሊሆን ያስፈልጋል፤

④ ሁልጊዜ ከመርዳት ጥሩ የርዳታ መንገዶችን ማስተማር፤

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ

ማር.15÷40-41፤ ሉቃ.8÷2-3፤ ሐዋ.9÷36፤ 19÷22፤ 1ቆሮ.12÷28፤ 16÷15

5 ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

አዲስ ቤተሰብ የሚያገለግል ሰው፣ አዲስ ቤተሰብን የሚቀበል ቡድን፣ አዲስ ቤተሰብን የሚያገኝ ቡድን፣ የፅዳት ቡድን፣ በስልክ የማጽናናት ቡድን፣ አስተያየትን የሚመረምር ቡድን፣ ፀሐፊ፣ ሕፃናትን የሚያሰለጥን ቡድን፣ በሠርግና በልቅሶ የሚያጽናና ቡድን፣ አስተማሪዎችችን የሚረዱ ቡድኖች፣ ሹፌርና ረዳት ወዘተ. . .

13. የማስተዳደርና የመምራት ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

የዝቅተኛ ግብ አሸንፎ ውጤት ለማግኘት በማስተዳደር ሰዎችን የመምራት ሥልጣን ነው፡፡ (በመጽሐፍ ቅዱስ የመምራት ፀጋ ሥጦታ በሁለት ሥፍራዎች ተጠቅሧል፡፡

① በ1ቆሮ.12÷28

② በሮሜ12÷8 ነው፡፡

በ1ቆሮ.12÷28 ላይ ያለው የመምራት ፀጋ ሥጦታ የሚገልጸው የማስተዳደር ፀጋ ሥጦታን ነው፡፡ደግሞም በሮሜ12÷8 ላይ ያለው ፀጋ ሥጦታ የሚገልጸው ራዕይን ሌሎች ሰዎች የመስጠት (የማካፈል) ነው)፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① ዝቅተኛ ራዕይን ለማሳደግ፣ ዕቅድን ለመገንባትና ሥራን ለማደራጀት ይጠቅማል፡፡

② መጋቢ በክርስቲያኖች መካከል ምሪትን በልዩ ተግባር እንዲያከናውን ይጠቅማል፡፡

③ የረጅምን ግብ ፍጹም እንዲናስታውስ ያደርጋል፡፡

④ ረጅም ዕቅድን አቅደን እንዲናከናውን ይጠቅማል፡፡

⑤ የቢሮ ሠራተኞችን ጠቅላላ ለመቆጣጠር ይጠቅማል፡፡

⑥ አንድ ሰው ሥራውን እንዴት እንደምሠራ ለመቆጣጠር ይጠቅማል፡፡

⑦ በጥሩ ሁኔታ ሥራ ፈጥረን እንዲንሠራ ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ

① ግልጽ የሆነ ግብ የተኖው እንደሆነ ሁልጊዜ መመርመር

② የቢሮ አስተዳዳሪ (ኃላፊ) መሆን ብቻ ሳይሆን ከሠራተኞች ጋር በሥራ ቦታ በመገኘት ሥራው መሥራት

③ የመምራትን ራዕይ ለማደራጀት፣ ለማስተዳደርና አስፈላጊውን ስፍራ ለማስተካከል ጥንቃቄ ማድረግ

④ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዘውትር ህብረት ማድረግ፣ ይህ ካልሆነ ለሠራተኞች ሁል ጊዜ ትዕዛዝ ብቻ ከሆነ ሠራተኞች በአደጋ ላይ ይሆናሉ፡፡

⑤ ሠራተኞችን በትህትና መቆጣጠር

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ

ዘጸ.18÷13-27፤ 1ቆሮ.12÷28፤ 1ተሰ.5÷12-13፤ 1ጢሞ.3÷1-7፤ 5÷17-22

5 ሥራውን መሥራት የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

የቡድን መሪ፣ ልምምድ ክፍል፣ የደቀ መዛሙርት ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር፣ ርዳታ፣ ሽማግሌ፣ የአምልኮ መሪ፣ የክፍል መሪ፣ የዕቅድ ፀሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ የወረቀት ሥራ፣ የወንጌል ስብከት ሥራ፣ ትንሽ ቡድን መቆጣጠር፣ፀሐፊ፣ ወረቀት ማደራጀት፣ ማስተዳደር፣ የቤተ ክርስቲያን የሥራ ዕቅድ፣ የሠራተኞች አስተዳደር ወዘተ. . .

14. የማጽናናት ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

ማጽናናትንና ማበረታታትን ለሚፈልጉ ሰዎች በፍቅር በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ማጽናናትንና ማበራታታትን መስጠት፡፡(አንድ ሰው የሚያሳስብ ነገር ሲኖር መጋቢው ከሚያስበው ነገር ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ነገር ግን የማጽናናት ፀጋ ሥጦታ ከመጋቢነት ፀጋ ሥጦታ ጋር ሲነጻጸር በአጭር ጊዜ የሚደረግ ሥራ ነው፡፡የማጽናናት አገልግሎት በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ወደ ሰዎች በመሄድ ማጽናናት ነው)፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① መከራ የደረሳቸውን ሰዎችን በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ማጽናናትንና ርዳታን እንዲንሰጥ ሥልጣን ይጨምራል፡፡
② ከሌሎች ሰዎች ጋር ጓደኝነትን እንዲንፈጥር ይረዳል፡፡
③ የሌሎች ሰዎች እምነት እንዲናበረታታና መንፈሳዊ ሕይወትን እንዲናሳድግ ይረዳል፡፡
④ ሌሎች ሰዎችን እንዴት ማጽናናት እንደምንችልና መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚንገነባበትን ነገር እንዲናውቅ ይረዳል፡፡
⑤ በየጊዜው ብዙ ማጽናናትን እንዲናደርግ ያግዛል፡፡
⑥ ሌሎች ሰዎችን በፍቅር እንዲንወቅስ ይረዳል፡፡
⑦ በሚንሰብክበት ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተስማምተን ለሌሎች ሰዎች እንዲናካፍል ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ

① የራሱን መንፈሳዊ ሕይወት በደንብ ይዞ ሌሎች ሰዎችን ለማሳደግና ለማጽናናት ሲያገኝ በፀሎት መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ መዘጋጀት አለበት፤
② አንዳንድ ጊዜ በሚታጽናና ጊዜ የሌሎችን መጥፎ ልምዶችን ለትምህርት እንዲሆን በመናገር ከደረሰበት አደጋ ተጽናንተው እንዲመለስ ማበረታታት
③ ብዙ መከራ የራሱ አድርጎ ከማሰብ መውጣት
④ ሌሎችን በሚታጽናና ጊዜ ታማኝ መሆን

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ

ሐዋ.4÷36፤ 14÷21-22፤ ሮሜ12÷6-8፤ 1ተሰ.2÷11፤ 1ጢሞ.4÷13፤ ዕብ.10÷25

5 ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

የክፍት ስብከት ቡድን፣ የአዲስ ቤተሰብ መሪ፣ የክፍል ስብከት ቡድን መሪ፣ ለማህበረሰብ ርዳታ የሚሰጥ ቡድን፣ በጋብቻና በልቅሶ ተገናኝተው የሚረዳ ቡድን፣አስተማሪ፣ ርዳታ ሥራ የማማከር ቡድን፣ ሰውን የመቀበል ቡድን፣ ትንሽ ቡድን ሥራ፣ ፀጋ ሥጦታ አማካሪ ቡድን፣ ስለ ሌሎች ሰዎች በርዕሰ የሚፀልይ ቡድን፣ በስልክ አማካሪ ቡድን፣ የወህኒ ቤት አገልግሎት፣ በሽምግልናና በሕመም ጊዜ ወደ ሐኪም ቤት እንዲሄዱ የሚያማክር ቡድን፣ወዘተ. . .

15. ድኻ ሰዎችን የመርዳትና በአምልኮ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ የመስጠት ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲስፋፋ ቤተ ክርስቲያን ለድኾች እቃዎችንና ገንዘብን እንዲሁም ጊዜዋን በልግስና የመስጠት ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① በማዋጮ ገንዘብ ከደመወዛችን ከመቶ አስር በላይ በምስጋና እንዲንሰጥ ይረዳል፡፡

② በቤተ ክርስቲያን ያሉትን የሌሎች ሰዎች ፍላጎት ምን ዓይነት እንደሆነ እንዲንረዳ ይጠቅማል፡፡

③ ዕቃዎቻችንንና ገንዘባችንን አትርፈን እንዲንቆጥብ ይጠቅማል፡፡

④ እንደተለመደው ሥርዓት ብዙዎችን በፍቅር ጊዜአችንን በመስጠት እንዲሁም ካለን ነገራችን በማካፈል እንዲናከባክብና እንዲናገለግል ይጠቅማል፡፡

⑤ በሚናካፍልበት ጊዜ የሚበልጠውን ማረጋገጫ እንዲንቀበል ይረዳል፡፡

⑥ በትክክለኛ ዕይታና ፍርድ እንዲናካፍል ይጠቅማል፡፡

⑦ ያለንን ንብረቶችን በደንብ እንዲናስተዳድር ይረዳል፡፡

3 ጥንቃቄ

① በመስጠት የሚገኘውን ታላቅ ደስታ ለማግኘት ብለህ ያለ ዕቅድ አትስጥ፡፡

② ለቤተ ክርስቲያን ባበረከትከው ነገር ያንተ ዝና (ስም) እንዲወጣ አታደርግ፡፡

③ ከሰዎች ጋር ለመስማማት ብለህ ከሚትሠራው ከእግዚአብሔር ጋር በፍቅር ማገልገል ይሻላል፡፡

④ ድኾችን የመርዳት ፀጋ ንብረትንና ገንዘብን ከመስጠት ጋር አይዛመድም፡፡

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ

ማቴ.12÷41-44፤ ሉቃ.3÷11፤ ሮሜ12÷8፤ 2ቆሮ.8÷1-7፤ 9÷2-8

5 ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

ማህበረሰቡን የሚረዳ ቡድን፣ ሚሽኔሪዎችን የሚያስተዳድር ቡድን፣ ሠራተኞችን የሚያስተዳድር ቡድን፣ ገንዘብ ሚንስተር፣ የተለያዩ ሥራዎች እንዲከናወኑ የሚረዳ ቡድን፣ ሒሳብ ሹም (ገንዘብን የሚያወራርድ) ቡድን፣ ድኾችን የሚረዳ ቡድን፣ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ በወህኒ ቤት (በማረምያ ቤት) ያሉትን ወጣቶችን የሚረዳ ቡድን፣ መብለቶችንና ወላጅ አልባ ሕፃናትን የሚረዳ ቡድን፣ ጡረታ ሚንስተር ወዘተ. . .

16. የመምራት (የመግዛት) ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ፍጹም ራዕይና ግብ ለመግለጽ በፈቃደኝነት አብሮ የመሥራት ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① እግዚአብሔር የሚፈልገውን ራዕይና ግብ እንዲንቀበል ይጠቅማል፡፡

② ሌሎች ሰዎች በፈቃደኝነት ለራዕዩና ለግቡ እንዲተባበሩ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

③ የሕንፃ ግንባታ ለውጤት በቡድን እንዲንሠራ ይጠቅማል፡፡

④ የእግዚአብሔርን ራዕይና ግብ ሰዎች እንዲይዙ ለማነሳሳት ይጠቅማል፡፡

⑤ ራሳችን የተጠቀምንበት ጥሩ ዕድል ሌሎች ሰዎችም ያንን ጥሩ ዕድል እንዲጠቀሙ በሥልጣን እንዲይዙ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

⑥ ሥልጣን የያዘው ሰው ብቻውን ሳይሠራ ከሌሎች ሰዎች ጋር በህብረት እንዲሠራ ይጠቅማል፡፡

⑦ የተኛውን ነገር ማሸነፍ እንደምችል አውቀው ሁሉንም ነገር መስራት እንደማይችል እንዲስማማ ያደርጋል፡፡

3 ጥንቃቄ

① አንተ ራስህ የማታደርገውን ሌሎች ሰዎች እንዲያደርጉ አታደርግ፡፡

② ከሰዎች ጋር ህብረት ማድረግ ወሳኝ ነገር መሆኑን በማወቅ በትህትናና በስምምነት ምራቸው፡፡

③ አንተን ከሚከተሉ ሰዎች ወደፊት ከመቅደም ይልቅ አብረሃቸው በመሆን ከእነርሱ ጋር ሥራ፡፡

④ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይተው መኖር አደጋ ስላለ ሁልጊዜ በመጽሀፍ ቅዱስ ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ተደግፈህ መልካም ህብረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ

ዘጸ.18÷13-27፤ ሉቃ.22÷25-26፤ ሮሜ12÷8፤ 1ተሰ.5÷12-13፤ ዕብ.13÷17

5 ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

የመዝሙር ቡድን፣ የ✪ሄር መሪ፣ የሚዲያ ቡድን፣ የድራማ ቡድን፣ የክፍት ስብከት መሪ፣ ክፍል ቤተሰብ ስብከት መሪ፣ የሕፃናትና የወጣቶች አስተማሪ፣ ልምምድና የደቀ መዛሙርት ዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፣ የአምልኮ መሪ፣ የቢሮ አሰስተዳደር ወዘተ. . .

17. የመራራት ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም

በስቃይ ውስጥ ላሉት ሰዎች ርህራሄን በማሳየት ምህረትን በክርስቶስ ፍቅር የማድረግ ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሁልጊዜ አስተውለን ርዳታንና ርህራሄን እንዲናደርግ ይጠቅማል፡፡

② የሌሎች ሰዎች ሀዘን እንደራሳችን በማድረግ እንዲሰማን ይረዳል፡፡

③ በሥጋና በአዕምሮ ሕመም የሚሰቃዩትን እንዴት በርህራሄ ልብ መራራት እንደምንችል ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

④ እያንዳንዱ ሰው የሚፈልገውን ርዳታ የሚንሰጥበትን ሥራ እንዲንሠራ ያደርጋል፡፡

⑤ በንግግር፣ በሥራ በንብረት መራራት እንዲንችል ይረዳል፡፡

⑥ ስቃይ ለደረሰባቸው ሰዎች እንዲናዝን ይረዳል፡፡

⑦ ሀዘንተኞችን ብዙ ጊዜ በማየት ርህራሄ መኖራችንን ለመግለጽ ቀላል እንባ እንዲናፈስስ ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ

① ብዙ ጊዜ የሌሎች ሰዎች ችግር ሳናውቅ ርህራሄ ማሳየት እንደለብን ይገልጻል፡፡

② የተቸገሩትን አይተን ክፉ ቃልና ቁጣ እንዳናወጣ ጥንቃቄ ሊናደርግ ይገባል፡፡

③ ታላቅ ርዳታ ስናደርግ ከችግራቸው የሚላቀቁበትን መንገድ በማሳየት የርዳታ ነፃነትን ሊናነሳ ይገባል፡፡

④ ስሜታዊ ሁኔታ በፍጹም ማየት የለብንም፤ሰፊ ሀሳብ በመያዝ መራራት ያስፈልጋል፡፡

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ

ማቴ.20÷29-34፤ 25÷34-40፤ ማር.9÷41፤ ሉቃ.10÷33-37፤ ሐዋ.11÷28-30፤ ሮሜ12÷8

5 ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

ማህበረሰብን የሚረዳ ቡድን፣ የፈውስ ቡድን፣ የወንጌል ስብከት ቡድን፣ ልዩ የወንጌል ስብከት ቡድን፣ ስለ ሌሎች ሰዎች በርዕስ የሚፀልይ ቡድን፣ የማጽናናት አገልግሎት፣ የማረምያ ቤት ተልዕኮ፣ የውጭ ሚሽኔሪዎች ተልዕኮ፣ የህመምተኞች አገልግሎት፣ ድኾችን መርዳት፣ ብቸኛ የሆነውን አዛውንት መርዳት፣ መብለትንና ወላጅ አልባ ሕፃናትን መርዳት ወዘተ. . .

18. የወንጌል ስብከት ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም:- ያላመኑ ሰዎች የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑና ለውጤት እንዲበቁ ወንጌልን የመመስከር ልዩ ሥልጣን ነው፡፡ (የፀጋ ሥጦታና ሥራ ይለያያል፤ ሁሉም ክርስቲያኖች እያንዳንዳቸው የተለያየ ፀጋ ሥጦታ አላቸው፤ ነገር ግን አንድ ዓይነት አገልግሎት የሚናገልግልበት ሥራ አለ፤ ያም የወንጌል ምስክርነት ፀጋ ከሌላቸው ሰዎች ጋር በመሆን በደስታ ወንጌልን በተለያየ ሁኔታ መመስከር ነው፡፡)

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① የወንጌል ምስክርነት አገልግሎት ስንፈጽም ታላቅ ደስታ እንደምኖር እንዲንገናዘብ ይረዳል፡፡

② ለእንግዶች በቀላሉ ሁኔታ ወንጌልን በድፍረት እንዲንመስክር ይጠቅማል፡፡

③ ደህንነትን ላልተቀበሉ ሰዎች በድፍረት እንዲንናገር ይጠቅማል፡፡

④ በንግግራችን ሁሉ ስለ ወንጌል እንዲንነጋገር ይረዳል፡፡
⑤ ብዙ ሰዓት ላላመኑ ሰዎች እንዶንፀልይ ይጠቅማል፡፡
⑥ በቀላሉ ወንጌልን ለሰዎች እነዲንመስክር ሥልጣንን እንዲንቀብል ይጠቅማል፡፡
⑦ የወንጌሉን መልዕክት ገልጠን እንዲናረጋግጥ ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ
① የተሻለ ጥቅም በወንጌል ስብከት እንደሚገኝ በማሰብ ዘውትር መስበክ
② እንደ አንተ ወንጌሉን የሚመሰሩ አገልጋዮችን አትወቅሳቸው
③ አንተ ብቻህን ሆነህ የሰበክላቸውን ሰዎች በራስህ ዘንድ ሳታቆይ እነዚያን አዲስ ቤተሰቦችን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ማገናኘት መልካም ነገር ነው፤
④ ወንጌልን መመስከር ሥልጣን ሳይሆን በመንፈስቅዱስ ኃይል የሚደረግ አገልግሎት እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል፤

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ
ሐዋ.8÷5-6፤ ቁ.6-40፤ ሮሜ10÷14-15፤ ኤፌ.4÷11-14፤ 2ጢሞ.4÷5

5 ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች
በየቀኑ የወንጌል ስብከት ቡድን፣ የተለያዩ የወንጌል ምስክርነት ቡድን፣ ክፍት ስብከት ቡድን መሪ፣ ክፍት ስብከት ሰዎች፣ ማጽናናት፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጽ ቡድን፣ የውጭ ሚኔሮዎች ቡድን፣ የሕፃናት ወንጌል ምስክርነት፣የወጣቶች ወንጌል ምስክርነት፣ ወደ ጎረቤት ቀበሌያት ሄዶ ወንጌልን የሚመስክር ቡድን፣የወንጌል ማስፋፋት (ዕድጌት) ቡድን ወዘተ. . .

19. የመጋቢነት፣የወንገላዊነት (ክርስቲያኖችን የማሠለጠን) ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም:- ክርስቲጣኖችን በመንፈሳዊ ሕየወታቸው ለማሳደግ ረጅም ሥልጠና በመስጠት እንዲቆዩ ማድረግ ሥልጣን ነው፡፡ (መጋቢውና ወንጌላዊው የመጋቢነት ፀጋ ሥጦታ ሁልጊዜ ተመሳሳይ አይሆኑም፤የመጋቢነት ፀጋ ሥጦታ ለቤተ ክርሰስቲያን ጥቅም ካልሆነ መጋቢ መሆን ከክርስቲያኖች በምንም አይለይም፡፡)

2 ፀባይና ልዩ ተግባር
① የመንፈሳዊ ችግሮችን በሥልጣን ይዞ ለመቆጣጠር ይጠቅማል፡፡
② ሌሎች ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ እንዲንፀልይ ይረዳል፡፡
③ ስለሌሎች መንፈሳዊ ሕይወት ማደግ በማሰብ እንዲናገለግል ይረዳል፡፡
④ ስለሌሎች መልካም ነገርን እንዲንሞክር ያደርገናል፡፡
⑤ ለሌሎች እውነትን እንዲናረጋግጥ ይጠቅማል፡፡
⑥ ሌሎች ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመስሉ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡
⑦ ስለሌሎች መንፈሳዊ ሕይወት ዕድጌት ተልዕኮእንዲንቀበል ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ
① ነፍስን በንጽህና አንከባክበን ለማሳደግ
② የመጋቢነት ፀጋ ሥጦታ ያለው ሰው አግኝቶ ራዕይን እንዲያንጽ ማድረግ
③ ሌሎች ፀጋ ሥጦታቸውን አውቆ በሥጦታቸው እንዲያገለግሉ ማድረግ
④ የቡድን መሪ የሆነ ሰው ቡድኑ የሚያድግበት ትምህርት ማስተማር አለበት

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ
ዮሐ.10÷1-18፤ ሐዋ.20÷28-31፤ ኤፌ.4÷11-14፤ 1ጢሞ.3÷1-7፤ 1ጴጥ.5÷1-3

5 ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች
የክፍት ስብከት መሪ፣ የቡድን ቤተሰብ ስብከት መሪ፣ የፀጋ ሥጦታ ማጽናናት፣ ሕፃናትንና ወጣቶችን የሚያስተምር አስተማሪ፣ የትንሽ ቡድን መሪ፣ ወጣቶች፣ አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው ወዘተ. . .

20. እንግዶችን የመቀበል ፀጋ ሥጦታ

1 ትርጉም:- በራሳቸው ቤት ይሁን በቤተ ክርስቲያን እንግዶችን ለመቀበል በራቸውን ሆነ የቤተ ክርስቲያን በር ክፍት አድርገው ለእንግዶች ምቾትን ለመስጠት ምግብና አልጋ አዘጋጅቶ የመቀበል ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር
① እንግዶች ከሌሉበት ጊዜ ይልቅ እንግዶች ባሉበት ጊዜ ደስታን እንዲንቀበል ይጠቅማል፡፡
② ቀድሞ ለመጣው (ለመጡ) እንግዳው (እንግዶች) ምቾት እንዲንሰጥ ይረዳል፡፡
③ በራሳችን ቤት እን🅾ኳን እንግዶችን በመቀበል ደስተኞች እንዲንሆን ይጠቅማል፡፡
④ ይህንን ፀጋ አገልግሎት በፈቃደኝነት እንዲናደርግ ይረዳል፡፡
⑤ ከሌሎች ጋር ፍቅርን እንዲንከፋፈል ይጠቅማል፡፡
⑥ የሌሎች ፍላጎት ምን እንደሆነ እንዲናውቅ ይረዳል፡፡
⑦ መቼ፣ የት ሰውን አግኝተን ተዘጋጅተን የረጅም ፍቅር ልውውጥ እንዲናደርግ ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ
① እንደ አንተ ሌሎችን በፍቅርና በቸርነት የማይቀበሉ ሰዎችን በመርዳት እንግዶችን እንዲቀበል ማድረግ
② የራሱን ከፍተው እንግዶችን ስቀበል ለቤተሰቦቹ አስቀድሞ መናገር
③ እንግዶችን በመቀበል ብዙ ሰዓት ስያጠፉ ጥንቃቄ ማድረግ

④ እንግዶችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ተቀብሎ ማስተናገድ

4 <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማመሳከሪያ</u>

ዘፍ.18÷1-8፤ ማቴ.10÷11-14፤ ሉቃ.10÷38-42፤ ሮሜ12÷13፤ ዕብ.13÷1-2

5 <u>ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች</u>

አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው፣ አዲስ ቤተሰብን የሚቀበል ቡድን፣ አዲስ ቤተሰብን የሚሰብክ ቡድን፣ የተለያዩ የወንጌል ምስክርነት ቡድን፣ በጋብቻና በልቅሶ የሚያጽናና ቡድን፣ የትንሽ ቡድን ሥራ፣ የአምልኮ መሪ፣ እንግዶችን የሚቀበል ቡድን፣ ለተለያዩ ሰዎች መኝታ የሚያዘጋጁ ቡድን፣ የወጣቶች አገልግሎች፣ መኖሪያ ቤት ለሌላቸው ሰዎች መኖሪያ ቤት ሠርተው የሚሰጥ ቡድን ወዘተ. . .

<u>21. የእጅ ችሎታ (ብልኀት) ሥጦታ</u>

1 <u>ትርጉም:-</u> ለሥራ የሚያገለግሉትን ዕቃዎችን በመሳልና በመቅረጽ የመጠቀም ሥልጣን ነው፡፡

2 <u>ፀባይና ልዩ ተግባር</u>

① በብዙ ዓይነት ችሎታና ብልኀት ቤተ ክርስቲያንን እንዲንጠቅም ይረዳል፡፡

② የተለያዩ ዕቃዎችን ማሽን የሚመስሉ፣ ድምፅ ማጉያዎች፣ ኤሌትሪክና የኤሌትሪክ ዕቃዎች ሥርዓት ባለው ሁኔታ አስተካክለን በቀላሉ እንዲጠቀም ይረዳል፡፡

③ ሥፍራዎች በማስዋብ እንዲንጠቀም ይረዳል፡፡

④ በእጅ ችሎታችን እየሠራን ደስተኞች እንዲንሆን ይረዳል፡፡

⑤ በሙያችን ብዙ ሠርተን እንዲንጠቀም ይረዳል፡፡

⑥ የተለያዩ ማቴሪያሎችን ማሰባሰብ ወረቀት፣ መቀስ፣ ማሸግያ፣ መስተዋት፣ ብረታ ብረት፣ ጨርቅ ወዘተ. . . በመጠቀም ብዙ ዕቃዎችን ለማስዋብ (ለማስጌጥ) ይረዳል፡፡

⑦ ብዙ ዕቃዎችን በማበጀት ደስተኞች እንዲንሆን ይረዳል፡፡

3 <u>ጥንቃቄ</u>

① የእጅ ችሎታ የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ በመረዳት ከሌሎች ፀጋ ሥጦታዎች ጋር እኩል እንደሆነ እንዲናውቅ ያስፈልጋል፡፡

② በቤተ ክርስቲያን ይህ የእጅ ችሎታ የሚጠቅም መሆኑን መረዳት

③ የእጅ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ብዙዎች ቢሆኑም የእያንዳንዳቸው ችሎታ የተለያየ መሆኑን መገንዘብ

④ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ችሎታቸውን ለማሳደግ ሌሎች ሰዎችን ማስተማር

4 <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማመሳከሪያ</u>

ዘጸ.30÷22-31፤ 2ነገ.12÷11-13፤ 2ዜና 34÷9-13፤ ሐዋ.9÷36-39፤ 18÷3

5 <u>ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች</u>

የሕንፃ አስተዳደር ቡድን፣ የመኪና ጠጋኝ ቡድን፣ የሚድያ ቡድን፣ አታክልተኛ ፣አታክልትን የሚያስውብ ቡድን፣ ዕቃዎችን የሚያበጃጅ ቡድን፣ የውጭ ሚሽዎች ቡድን፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስውብ ቡድን፣ አዲስ ቤተሰብን የሚቀበል ቡድን፣ የመማሪያ ክፍሎችን የሚያስውብ ቡድን፣ ለአዲስ ቤተሰብ ደብዳቤን የሚጽፍ ቡድን፣ሥጦታ የሚሰጥ ቡድን፣ የልጆች የወንጌል ስርጭት ቡድን የሕፃናት አስተማሪ ወዘተ. . .

<u>22. ስለሌሎች ሰዎች በርዕስ የመፀልይ ፀጋ ሥጦታ</u>

1 <u>ትርጉም</u>

ስለሌሎች ሰዎች ለተከታታይ ፀልዮ መልስ የመቀበል ሥልጣን ነው፡፡

2 <u>ፀባይና ልዩ ተግባር</u>

① እንደተለመደው ስለሌሎች ሰዎች ብዙ ሰዓት እንዲንፀልይ ይረዳል፡፡

② የሌሎች ሰዎችን ችግር እንደራሳችን ችግር አድርገን እንዲንቆጥር ይረዳል፡፡

③ ለብዙ ጊዜ በርዕስ በሚንፀልይበት ጊዜ በኃይል እንዲንፀልይ ይጠቅማል፡፡

④ ስለሌሎች ሰዎች የፀለየነውን የጸሎት መልስ በመቀበል እንዲንፀልይ ይጠቅማል፡፡

⑤ ኃይለኛ የፀሎት መልስ እንዲናረጋግጥ ይጠቅማል፡፡

⑥ በመንፈስ ቅዱስ ምሪትአማካይነት እንዲንፀልይ ይጠቅማል፡፡

⑦ ስለወደፊት ዕቅድ በማስተዋል እያንዳንዱን ርዕስ እያነሳን እንዲንፀልይ ይረዳል፡፡

3 <u>ጥንቃቄ</u>

① በብዙ ፀሎት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሀሳብ እንደሚበልጥ ማመን

② ፀሎትንና ሥራን በፍፁም ማገናኘት የለበትም፤ በፀሎት ጊዜ መፀለይ ደግሞም በሥራ ሰዓት ሥራውን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

③ በልዩ ሁኔታ ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ መጋቢያን፣ ስለ ወንጌላዊያን፣ ስለ ሀገራችንና ስለ መንግሥታችን ሊንፀልይ ያስፈልጋል፡፡

④ በቤትና በቤተ ክርስቲያን የፀሎት ሥፍራ ማዘጋጀት

⑤ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ከሚፀልዩና ቃሉን ከሚሰሙት ጋር ለመሆን ትኩረት ማድረግ

4 <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማመሳከሪያ</u>

ሉቃ.22÷41-44፤ ሐዋ.12÷12፤ ቆላስ.1÷9-12፤ 1ጢሞ.2÷1-2፤ ያዕ.5÷14-16

5 ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

ስለሌሎች በርዕስ የሚፀልይ ቡድን፣ የፀሎት መሪ፣ ሣምንቱን በሙሉ ተራ በተራ የሚፀልይ ልዩ የፀሎት ቡድን፣ የወንጌል ሥርጭት ቡድን፣ የውጭ ሚሽኔሪዎች ቡድን ወዘተ. . .

23. የክነ ጥበብ ሥራ ሥጦታ

1 ትርጉም

በብዙ ዓይነት ክነ ጥበብ እግዚአብሔርን እንዲናመሰግንና እውነትን እንዲንሰጥ የመርዳት ሥልጣን ነው፡፡

2 ፀባይና ልዩ ተግባር

① መልዕክትንና ሀሳብን ብዙ ዓይነት ክነ ጥበብ ተጠቅመን እንዲናስተላልፍ ይረዳል፡፡

② አንድ በተለየ ክነ ጥበብ መልዕክትን እንዲናስተላልፍ ይጠቅማል፡፡

③ የሚያናድድ ብዙ ነገር ሳይኖር የሌሎችን መንፈስ ለማነሳሳትና ሀሳብን በቀላሉ ለመግለጽ ይጠቅማል፡፡

④ የማየትና የመስማት ችሎታ እንዲያድግ ይረዳል፡፡

⑤ መልካም ሀሳብ እንዲንፈጥር ይጠቅማል፡፡

⑥ በክነ ጥበቡ ባህልን እንዲናስብ ይጠቅማል፡፡

⑦ በክነ ጥበባችን ባህልን ተጠቅመን የእግዚአብሔርን እውነት በቀላሉ ለማሳየት ይጠቅማል፡፡

3 ጥንቃቄ

① በፀባይ ከሌሎች ቡድኖች ጋር ፍጹም የሆነ ግኑኝነት እንዲናደርግ

② ራሳችንን የሚናሳይበት ነገር ግብ ሳይኖር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያስመስክርና ግብ ማሳየት

③ ሌሎች በሚገስጹበት ጊዜ በፍጥነት ግሳጸአቸውን መቀበል

④ ያሁኑን ባህል ተጠቅመን በሚገባ ተንትነን ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስ ቤተ ክርስቲያን ጥቅም ነገሮችን ሁሉ ማድረግ

4 የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማመሳከሪያ

ዘጸ.31÷1-11፤ 2ሳሙ.6÷12-16፤ 1ነገ.7÷14፤ መዝ.150÷3-5፤ ማር.4÷2፣ቁ.33

5 ሥራውን የሚችሉ ሰዎችና የሥራ ዓይነቶች

ማወጅ፣ ማሳተም፣ ዕቅድ ማውጣት፣ እርማት፣ ቅርጽ ማውጣት፣ የአመልኮ እቅድ፣ ክፍት ድራማ ቡድን፣ የባህል ሥራ፣ የቅርጻ ቅርጽ ሥራ (የማስጌጥ) የመዝሙር ቡድን፣ ድራማ መኖሩን ሳያስተዋውቅ ድራማ የሚያደርግ ቡድን፣ ትንሽ የእጅ ቅርጻ ቅርጽ ቡድን፣ የውስጥ ማስዋብ ቡድን፣ የድርሰት ቡድን፣ የዜማ ቡድን፣ የቴክንክ (የሚድያ) ቡድን ወዘተ. . .

ምዕራፍ አምስት

5. ፀባይን ማግኘት

1. ፀባይ ምንድን ነው?

1) ፀባይ ማለት አንድ ሰው ሲወለድ የተቀበለው ነገር ማለትም ሁኔታን፣ ስሜትንና ዝንባሌን ሁሉ የያዘ ነገር ነው፡፡

① ዳዊት በእናቱ ማሕፀን ውስጥ እያለ እግዚአብሔር የውስጥ ፀባይን (ማንነቱን) አበጃጅቶ እንደሠራ ይናገራል፡፡

● መዝ.139÷13-16

13. አቤቱ፥ አንተ ኵላሊቴን ፈጥረሃልና፥ በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛል።

14. ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች።

15. እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፥ አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም።

16. ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።

② እግዚአብሔር የኢያንዳንዱን ሰው ፀባይ በእናት ማሕፀን ውስጥ እያሉ ልዩ አድርጎ ፈጠረ፡፡

● ኢሳ.44÷24

24. ከማኅፀን የሠራህ፥ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ሁሉን የፈጠርሁ፥ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ከእኔ ጋር ማን ነበረ?

● ገላ.1÷15

15-16 ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥

2) አንዳንዶች ብዙ ዓይነት ፀባይ የያዙ ናቸው፤ ፀባይ የአንድ ሰው ማንነት የሚገልጽ ነው፤ አንተ ከአካባቢ ሰዎች ጋር አንድ ላይ ህብረት እያደርግህ የሚትፈልገውን የሚትገልጽበት ነው፤ በፀባይህ አንተ እንዴት እንደሚታገለግል ተናገር፡፡ እግዚአብሔር ላንተ በሰጠው ፀባይ ስታገለግል ደስ የሚል ፍላጐት ታገኘዋለህ፤ ፀባይ ስል የሰውን ማንነት የሚገልጽ ነገር ነው፡፡

● 1ቆሮ.2÷11

11. በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።

● 1ቆሮ.12÷6

6. አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።

- መዝ.139÷13-16
  13. አቤቱ፥ አንተ ኵላሊቴን ፈጥረሃልና፥ በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛል።
  14. ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች።
  15. እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፥ አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም።
  16. ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።

ፀባይን የሚሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ በፀባዩ ውስጥ እውነት ወይም ውሸት የሚባል ስለሌለ አንተ እንዴት ታገለግላለህ ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል፡፡

ለምሳሌ - በመጀመሪያ ያንተን ስም በሚትጽፈው በትክክለኛ እጅ ማለትም እጅ ጽሑፍህን የሚያሳምረው ቀኝ እጅ ከሆነ በቀኝ እጅ ግራ እጅ ከሆነ በግራ እጅ ጻፍ፤

- በመቀጠልም ባልጻፍከው እጅ ስምህን ደግመህ ጻፍ፤
- በመጀመሪያ በጻፍከው እጅ ጽሑፍህ ትደሰታለህ፤ ነገር ግን በማትጽፈው እጅ ሁለተኛውን ስለ ጻፍክ ደስተኛ አይደለህም፤ ያ ደግሞ ያንተን ፀባይ በቀላሉ የሚያሳይ ነው፡፡

3) ፀባይህ የሚወድደውን ሥራ ስትሠራ በደንብ ውጤታማ መሆን ትችላለህ፡፡

① ፀባይ የሚወድደው የሥራ ዓይነት አለ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋሪያ ጴጥሮስ (ታላቅ ፍላጐት፣ ስሜት ሁልጊዜ ከሀሳብና ከንግግር ይልቅ ቶሎ ብሎ በሥራ የሚያሳይበት ፀባይ እንዳለው አይቶ ለጴጥሮስ ሀሳቡን ስተነትን ያንተ ፍላጐት በባህር ላይ በጀልባ እየሄድህ ዓሣ መያዝ ሳይሆን ከፀባይ ጋር የሚስማማ ሥራ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማምጣት ነው ብሎ ያንን እንዲሠራ ሰጠ፤ እንዲሁም ለኖህ መርከብን እንዲሠራ ከፀባዩ ጋር የሚስማማ ሥራ ሰጥ~ል፡፡

② በቀላሉ ውጤት የሚያመጣ ሥራ መለየት ይቻላል፡፤

ለምሳሌ አንድን በቀኝ እጅ በኃይል ስትወረውር ወዳሰብከው ቦታ ደርሶ ስወድቅ ደስ እንደምልህ ሁሉ በሌላው እጅ ማለትም በማትችለው እጅ በሚትወረውርበት ጊዜ በቅርብ ማለትም ወዳሰብከው ቦታ ሳይደርስ ስወርድ ያን ጊዜ ጥሩ ያልሆነ ስሜት ታሳየዋለህ፤ እንደዚሁም ከፀባይ ጋር የሚስማማውን ሥራ ስትሠራ ታላቅ ደስታ ታገኘዋለህ፤ ነገር ግን ከፀባይ ጋር የማይሰማማውን ሥራ በሚትሠራበት ጊዜ ደስታ አይሰማህም፤ ለውጤትም አትበቃም፡፡

4) ፀባይ ብርቱ ጐንና ደካማ ጐን አለው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ስለሆነው ስለሐዋሪያ ጴጥሮስ ፀባይ ብርቱና ደካማ ጐኖች ይገልጻል፡፡

① የሐዋሪያ ጴጥሮስ ብርቱ ጐን ስገልጽ በታላቅ ስሜት በፍጥነት ሥራ የሚሠራ ሰው እንደሆነ ይገልጻል፡፡

✧ ጴጥሮስ ሁሉንም ነገር ትቶ ኢየሱስ ክርስቶስን የተከተለ ሰው እንደሆነ ይገልጻል፡፡

- ማቴ.4÷20
  20. ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት።

✧ ኢየሱስ ክርስቶስ በባህሩ ላይ ተራምዶ እየመጣ ጴጥሮስን ወደ ራሱ ስጠራ በድፍረት በባህሩ ላይ ተራምዶ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሄደ ሰው ነው፡፡

- ማቴ.14÷29
  29. እርሱም፦ ና አለው። ጴጥሮስም ከታንኳይቱ ወርዶ ወደ ኢየሱስ ሊደርስ በውኃው ላይ ሄደ።

✧ በለውጥ (በፀሎት) ተራራ የኢየሱስ ልብስ መንፀባረቁን አይተው በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነውና ሦስት ዳሶችን እንሥራ በማለት ደፍሮ የጠየቀ ሰው ነው፡፡

- ማቴ.17÷4
  4. ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን። ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ።

✧ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሞቱ በሚናገርበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ለመሞት፣ ለመታሰርም ቢሆን የተዘጋጀሁ ነኝ በማለት የተናገረ ሰው ነው፡፡

- ማቴ.26÷33
  33. ጴጥሮስም መልሶ፦ ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም አለው።

✧ እስከ ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ቅጥር ግቢ ድረስ ኢየሱስ ክርስቶስን የተከተለ ሰው ነው፡፡

- ማቴ.26÷58
  58. ጴጥሮስ ግን እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ድረስ ሩቅ ሆኖ ተከተለው፥ የነገሩንም ፍጻሜ ያይ ዘንድ ወደ ውስጥ ገብቶ ከሎሌዎቹ ጋር ተቀመጠ።

✧ ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ በጥብርያዶስ ባሕር እንደገና ስገለጥ ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር ኢየሱስ መሆኑን ለጴጥሮስ ስናገር ጴጥሮስ በተረዳ ጊዜ አውልቆ የነበረውን ልብስ ታጥቆ ወደ ባሕሩ ዘሎ የገባ ሰው ነው፡፡

- ዮሐ.21÷7
  7. ኢየሱስ ይወደው የነበረውም ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን። ጌታ እኮ ነው አለው። ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ ዕራቁቱን ነበረና ልብሱን ታጥቆ ወደ ባሕር ራሱን ጣለ።

② የሐዋሪያ ጴጥሮስ ፀባይ ደካማ ጐን

በስሜት የሚሠራና በኢየሱስ ላይ ያለው እምነቱ ደካማ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

✧ በገተሰማኔ ሥፍራ የሊቀ ካህናቱ አገልጋይ የማልኮስን ጆሮ የቆረጠ ሰው ነው፡፡

● ዮሐ.18÷10

10. ስምዖን ጴጥሮስም ሰይፍ ስለ ነበረው መዘዘው፥ የሊቀ ካህናቱንም ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠ፤ የባርያውም ስም ማልኮስ ነበረ።

✧ ኢየሱስ ከመሞቱ ከአንድ ቀን በፊት ሴሊት ወደ ወህኒ ለመግባት ሆነ ለመሞት ተዘጋጅቻለው ብሎ ተናግሮ ነገር ግን ዶሮ አንዴ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ የካደ ሰው ነው፡፡

● ማቴ.26÷70

70. ጴጥሮስ ኢየሱስን ከካደ በኋላ በመጀመሪያ ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ብሎ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አስቦ መራራ ልቅሶ ያለቀሰ ሰው ነው፡፡

● ማቴ.26÷75

75. ጴጥሮስም፡- ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የኢየሱስ ቃል ትዝ አለው፤ ወደ ውጭም ወጥቶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ።

2. ፀባይን መመርመር (1)

አንዳንዴ ፀባይ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሲሆን ጥሩ ፀባይ ሆኖ ይገኛል፡፡

መግለጫ (መመሪያ)

1) የሚቀጥለውን ሠንጠረዥ ከግራ ወደ ቀኝ በማንበብ በውስጥህ ያለውን ፀባይ የሚገልጸው ቃል ስታገኝ 2 ቁጥር፣ ማሃከለኛ ከሆነ 1 ቁጥር ምንም የማይገልጽ ከሆነ 0 ቁጥር በመጻፍ አስቀምጥ፡፡

2) ሁሉንም ማለት በሠንጠረዡ ውስጥ ያሉትን አንብበህ ውጤቱን ካስቀመጥክ በኋላ ወደታች ደምረህ ውጤቱን አስቀምጥ፡፡

3) አንተ በሀሳብህ እኔ እንደዚህ ሰው እሆናለው የሚትለውን አትጻፍ፡፡ አሁን ባንተ ውስጥ ያለውን ፀባይህን የሚገልጸውን ብቻ ጻፍ፡፡

4) አንተ A,B,C,D ወደታች ከተጻፉት ጠቅላላ ድምራቸው ከፍተኛ የሆነውን ምድብ በመውሰድ 2 ቁጥሮች የተጻፉበት ቃል በጻሹ (ክፍት በሆነው ቦታ ጻፉቸው፡፡

5) አንተ (ለእኔ) (መልካም ዕድሎች ናቸው፡፡)

ከA, B, C, D ካሉት መርምረህ ከ2ና ከ3 በላይ የሆኑት ቃሎች ያንተን ፀባይን ሊያሳዩ የሚችሉ መልካም ዕድሎች እንደሆኑ በቀላሉ ትረዳለህ፡፡

A			B		C		D	
1	ቀዝቃዛ		ተወዳዳሪ		ጥሩ ፀባይ ያለው		መሃል ላይ ያለው	
2	አዲስ ነገር መፍጠር የሚችል		ብርቱ (ኃይለኛ)		አገልጋይ		ታዛዥ	
3	ታላቅ ስሜት ያለው		ደፋር		ተመርማሪ		በጥቂቱ የሚናገር	
4	ችኩል		እርግጠኛ		አስተዋይ		ጥንቁቅ	
5	በቀላሉ ከሰው ጋር የሚግባባ		ውጤታማ		በዝርዝር ነገሮችን የሚያውቅ		ግትረኛ ያልሆነ	
6	ሳቅታ (ፈገግተኛ)		የመሪነት ሥልጣን ያለው		በጥልቀት የሚያስብ		ስሜትን የሚቆጣጥር	
7	ጮበዝ (ንቁ)		ቆራጥ		የሚመሳሰል		ሁሉን የሚያጠቃልል	
8	ስሜታዊ		ብልጎተኛ		ትዕግሥተኛ		ዝምተኛ (የተረጋጋ)	
9	ሥራ የሚሞክር		ታማኝ		ታማኝ		ጸኑ	
1	ንግግርን የሚያዳምጥ		ትዕግሥተኛ		ሥራውን የሚጨርስ		በመጠን የሚኖር	
11	ድራማ ሠሪ		ችሎታ ያለው		ማደራጀት የሚችል		ፈቃደኛ	
1	ሰዎችን በቀላሉ የሚተዋወቅ		የሥራ ሰው (ጠንካራ)		ዝማሬ የሚወድ		ዝምተኛ	
1	በንግግር ከሰው ጋር የሚግባባ		ተወዳዳሪ		ተናዳጅ		ዓይን አፋር	

14	ገለጻ የሚችል		ግልጸኛ		አትኩሮት የሚሰጥ		ዝምተኛ	
15	ደስተኛ		ትዕብተኛ		በዝርዝር ነገርን የሚያስረዳ		በማሃል ያለ	
16	ሥራ የሚሞክር		ቆራጥ ሥልጣን ያለ		በቀላሉ ነገር የማይገባ		ይቅር ባይ	
17	ልታይ ባይ		ተቆጣጣሪ		ታማኝ		ማደራጀት የሚችል	
18	ቅን (ታማኝ)		ፍጭሌ		ታማኝ		በደንብ የሚሰማ	
19	ቸር		ስሜታዊ		በዕቅድ የሚሠራ		ሥራ መፍጠር የሚችል	
20	ዝነኛ		እምነቴ ጠንካራ		ትኩረት የሚያደርግ		ቸር	

3. ፀባይን መመርመር (2)

መግለጫ (መመሪያ)

1) ከሚቀጥለው ሠንጠረዥ ከግራ ወደ ቀኝ በማንበብ ያንተን ፀባይ በደንብ የሚገልጸውን 2 ቁጥር መካከለኛ የሆነውን 1 ቁጥር ምንም ያንተን ፀባይን ማይገልጸውን 0 ቁጥር በመጻፍ በሠንጠረዡ ውስጥ አስቀምጥ፡፡
2) ሁሉንም ከጻፍክ በኋላ በሠንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ቁጥሮች ጠቅላላውን ወደታች ድምራቸውን አስቀምጥ፡፡
3) ከሠንጠረዡ ውስጥ ፀባይህን የሚገልጸውንና ራስህ የተስማማኸውን ውጤት ጻፍ፡፡
4) አንተ ሁኔታ አለ፡፡ በባዶ ቦታ ላይ ከE F G H ድረስ ካሉት ከጠቅላላ ወደታች ተደምሮ ከፍተኛ ውጤት ከያዘው ምድብ 2 ቁጥር ባለው ትይዩ ያለው ያንተን ፀባይ የሚገልጽ ናቸው፡፡
5) አንተ (ለእኔ) (መልካም ዕድሎች ናቸው፡፡)

ከE, F, G, H ካሉት መርምረህ ከ2ና ከ3 በላይ የሆኑት ቃሎች ያንተን ፀባይን ሊያሳዩ የሚችሉ መልካም ዕድሎች እንደሆኑ በቀላሉ ትረዳለህ፡፡

E			F		G		H	
1	ስሜት አልባ		ተንከለኛ		ከዳተኛ		ወቃሽ	
2	ሰነፍ		ብዙ ሥራ የሚሠራ		ነጭናጫ		ቅመኛ	
3	ፈሪ		ገታራ		ውዳሴ ፈላጊ		በውስጡ ሁሉን የሚይዝ	
4	የማይጸና		የፍቅር ልብ የሌለ		ራስ ወዳድ		ፈሪ	
5	ዝግምተኛ		ችኩል		መልሶ የሚያደርግ		ተጠራጣሪ	
6	ያለ ዕቅድ የሚኖር		ተከራካሪ		የሚረሳ		ብቸኛ	
7	ህብረት የማይፈልግ		ነውረኛ (ባለጌ)		ወረኛ		ድንጉጥ	
8	መልኬ ጠፊ		ሥልጣንን መከታ አድርጎ ጫና የሚያደርግ		የማይመሳሰል		አሳፋሪ	
9	ያለ ውሳኔ የሚኖር		ንፉግ		ልታይ ባይነት		ምቀኛ	
1	አስታራቂ ሀሳብ የሌለ		ትዕብተኛ		ክሳራ የማያውቅ		ዝነኛ ያልሆነ	
11	ሰነፍ		አዛዥ		መደናፋት		ወደ ኋላ የሚያፈገፍግ	
12	ሀሳብ የሌለው		ተቆጣጣሪ		አእምሮ ማይሰራ		ክፋተኛ	
1	አሰልቺ		ግብዝ		መልካም ሀሳብ		እርግጠኛ ያልሆነ	

3					የሌለው			
14	አጉረምራሚ		ተቃዋሚ		በራስ ማይታመን		እልከኛ	
15	ሥራ ፈት		ደነዝ		በቀላሉ የሚቆጣ		ብቸኛ	
16	ህብረት የሌለ		ገታራ		ነገረኛ		ደስተኛ ያልሆነ (ሀዘንተኛ)	
17	ፈሪ		ችኩል		ሕግን የማያውቅ		ይቅርታ ማያደርግ	
18	የማይገደድ		ችኩል		ተለዋዋጭ		ተጠራጣሪ	
19	ጭንቀተኛ		ሥልጣን የሚያሳይ		የማይረዳ (የሰውን ነፃነት ማይፈልግ)		ጨለምተኛ	
20	ተጠራጣሪ		የፍቅር ዝንባሌ የሌለ		ጩኸታም (ሁከት ፈጣሪ)		ኩራተኛ (ትዕብተኛ)	

4. ፀባይን ማግኘት

1) በመጀመሪያ የመረመርከውን ፀባይ ከሠንጠረዡ ያየኸውን ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ላይ ሙላ፡፡

የፀባይ ምርመራ (1)		የፀባይ ምርመራ (2)		1+2	ጠቅላላ ድምር	ከፍተኛ ነጥብ	ፀባይ
ዓይነት	ድምር	ዓይነት	ድምር				
A		G		A+G			ማነሳሳት
B		F		B+F			መሪነት
C		H		C+H			ጥንቃቄ
D		E		D+E			መጽናት
ጠቅላላ ድምር	60	ጠቅላላ ድምር	60	120			

2) አንተ ከሠንጠረዡ በሚትጽፍበት ጊዜ ከፍተኛ ነጥብ ያመጣው ወይም በድምሩ 1ኛ የሆነው የመጀመሪያ (ትክክለኛ) ያንተ ፀባይ ነው? ጠቅላላ ድምራቸው ውስጥ ከፍተኛ ነጥብ ያመጡት ከ1ኛ እስከ 2ኛ የወጡት ያንተ ፀባዮች ናቸው?

① ከሠንጠረዡ ውስጥ ፀባይህን ስትመረምር 1ኛ ደረጃ ያመጣው ፀባይ ምንድን ነው? ከዚህ በታች ካሉት ፀባዮች መካከል ክበብ፡፡

★ ለምሳሌ

(1) ማነሳሰሳት (　　)
(2) መሪነት　(　　)
(3) ጥንቃቄ　(　　)
(4) መጽናት　(　　)

② በ2ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው ያንተ ፀባይ ምንድን ነው? ከዚህ በታች ካሉት ፀባዮች መካከል ክበብ፡፡

(1) ማነሳሳት (　　)
(2) መሪነት (　　)
(3) ጥንቃቄ (　　)
(4) መጽናት (　　)
(5) ባዶ ወይም ምንም የለም (　　)

3) የጥያቄ 2. 2 ዐረፍተ ነገር ውጤታቸው ከ15 በታች ከሆነ ለ2ኛ ፀባይ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ባዶ ወይም ምንም የለም የሚለውን ትመርጣለህ፤ ያ የመጀመሪያ ያንተ ፀባይ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች ካሉት የመጀመሪያ ያንተ ፀባይ ክበብ፡፡

(1) የመጀመሪያ ማነሳሳት ( )
(2) የመጀመሪያ መሪነት ( )
(3) የመጀመሪያ ጥንቃቄ ( )
(4) የመጀመሪያ መጽናት ( )

4) 2ኛ ፀባይ ድምራቸው ከ15 በላይ ሲሆን ያንተ ጠቅላላ ድምር ውጤት ከፍተኛ ከ1 እስከ 2 ያሉት ያንተ ፀባይን የሚገልጹ ናቸው፡፡ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መካከል ከፍተኛ ደረጃ ያመጡት ክበባቸው፡፡

★ ለምሳሌ

1ኛ ደረጃ የሆነው ከፀባዮች መካከል መጽናት የሚለው ነው፡፡ድምሩ 39 ነው፡፡
2ኛ ደረጃ የሆነው ማነሳሳት ሲሆን ድምሩ 30 ነው፡፡ ስለዚህ የእኔ ፀባይ መጽናትና ማነሳሳት ናቸው ማለት ነው፡፡

(5) ማነሳሳት መሪነት ( ) (6) ማነሳሳት ጥንቃቄ ( ) (7) ማነሳሳት መጽናት ( )	(11) ጥንቃቄ ማነሳሳት ( ) (12) ጥንቃቄ መሪነት ( ) (13) ጥንቃቄ መጽናት ( )
(8) መሪነት ማነሳሳት ( ) (9) መሪነት ጥንቃቄ ( ) (10) መሪነት መጽናት ( )	(14) መጽናት ማነሳሳት ( ) (15) መጽናት መሪነት ( ) (16) መጽናት ጥንቃቄ ( )

5) ያንተ ልዩ ፀባይ ምንድን ነው? ለምሳሌ የእኔ ልዩ ፀባይ መጽናትና ማነሳሳት ናቸው፡፡
1) ለሰው ልጆች ከ16 ፀባዮች ውስጥ አንዱ ይኖራል፡፡



2) <u>ያንተ ልዩ ፀባይ ካነበብህ በኋላ ለየው፡ ፡</u>

① <u>ማነሳሳት</u>

ዕድል	መጀመሪያ ማነሳሳት	ማነሳሳት መሪነት	ማነሳሳት ጥንቃቄ	ማነሳሳት መጽናት
መ ል ካ ም ዕ ድ ል	ታላቅ ፍላጐትና ደስታ ያለው በቀላሉ ህብረት ማድረግ የሚችልና እንቢተኛ አፍቃሪና ተወዳጅ እውነተኛና ግልጸኛ ብዙ ሥራ የሚሞክር ኃላፍነት ያለው በሥራ ደስተኛ መሆን ሠራተኛ መሆን ብዙ ጓደኛ መኖር ሰውን የሚወድድ ታማኝ (ቅን) ጥሩ ነገር መኖር ፈገግተኛ	ለሰዎች ብዙ ማሰብ የሥልጣንን ማከፋፈል ማደራጀት ከጓደኞች ጋር ህብረት ማድረግ ሰዎችን ወደ ሥራ መምራትና ከሥራ ጋር ማገናኘት ውጤታማ መሆን ሥራን አደራጅቶ የሚሠራ ከሰዎች ጋር ሲገናኝ ፈገግተኛ አመስጋኝ	ምህረት የሚያደርግ ከሰዎች ጋር የሚሠራ የራሱን ሥራ የሚያስቀጥል (የሚያስተላልፍ ከሰዎች ጋር ያለው ህብረት ወሳኝ መሆኑን የሚረዳ ተለዋዋጭ ፍላጎት ያለው	ለስላሳ ባለ ግርማ ታማኝ ፈገግተኛ ለሰዎች ርዳታ የሚሰጥ የሰዎችን ሀሳብ የሚረዳ የማይደናገር ብዙ ጓደኞች ያለው ግልጸኛና ንጽሕ የሆነ
መ ጥ ፎ ዕ ድ ል	አቅመ ቢስ (ደካማ እምነት) ለሥራ የሚሎግም (ደካማ) አትክሮት የማይሰጥ ችኩልና ቆርጦ ማይሠራ ተለዋዋጭ ስሜት ያለው ግደለየሽ በራሱ ማይታመን ተለዋዋጭ ለዘብተኛ በቀላሉ የሚቆጣ	ብዙ በመናገር የሚሳሳት ከንግግሩ ነገር የሚይዝ ብዙ ጊዜ የሚቆጣ ክፉ ተናጋሪ ሥራ የሚቃወም ሥልጣኑን የሚያጋንን	ስሜቱ ከፍና ዝቅ የሚል አንዳንድ ጊዜ ወቃሽ ራሱን የሚገዳ ከጭንቀትና ከፍርሃት የተነሣ ሥራ ማይሠራ ሰው ስቆጣ ሊበቅል የሚሞክር	እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚሆን ስለፈቃደኝነት ደካማ የሆነ መቆጣጠር የማይችል ከሥራ ይልቅ ወሬ የሚወድ ከባዱን ነገር አቅልሎ የሚያስብ
ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰው	ሐዋሪያ ጴጥሮስ	ሐዋ. ጴጥሮስ	ዳዊት	አጵሎስ

② መሪነት

ዕድል	የመጀመሪያ መሪነት	መሪነት ማነሳሳት	መሪነት ጥንቃቄ	መሪነት መጽናት
መ ል ካ ም ዕ ድ ል	የመሪነት ሥልጣን መኖር ንቁ (ጐበዝ) በእምነት ጠንካራ የማይበሳጭ ሠራተኛ መሆን ነፃነት የሚሠጥ የውሳኔ ሥልጣን መኖር ለግቡ ግልጸኛ መሆን ችግሮች ማሸነፍ ድልን ማረጋገጥ የተሻለ መንገድ መቀየስ	ውጤታማ የሆነ ሠራተኛ አስተዋይ ለግቡ ግልጸኛ የሆነ አስገራሚ ነገር የሚሠራ ከሌሎች ጋር በሠላም የሚኖር ስሜት ያለው መከራን በድል የሚያሸንፍ ከጓደኞች ጋር በቀላሉ ህብረት የሚፈጥር በፍጥነት መሪ የመሆን ፍላጐት ያለው አዲስ ነገር መፍጠር የሚችል	ግብ ያለው ዝርዝር ሃሳብ ያለው ብርቱ ተመራማሪ በፍጥነት የሚያስብ የተሻሌ ሥራ የሚሠራ ትንሹንም ሥራ አስተውሎ የሚያደርግ ዋና መሪ መሆን የሚችል ሰዎችን የሚያከብር በአንድ ሥራ ረጅም ጊዜ የሚወስድ	ፈጣኝ ብርቱ ፍላጎት ያለው የተረጋጋ የማይታወክና ደፋር የሚጠነቀቅና ጸጥተኛ ጥልቅ ዕቅድን የሚገነባ የሚያደራጅ ግልጽ ግብና ዝርዝር ሀሳብ ያለው ከሰዎች ጋር የሚሠራ የሌሎች ሰዎች ሥልጣን እንደሚበልጥ የሚያስብ
መ ጥ ፎ ዕ ድ ል	በስሜት ደካማ የሆነ ሌሎችን የማይወድ ሙያ ማጣት ዝርዝር ነገር ማይሠራ ጫና የሚያደርግ ጥቅምን መፈለግ ምቾትን መፈለግ	በአንድ ጊዜ ስሜቱ የሚገልጽ መደናፋት ቅም የሚይዝ ቁጣና ምቀኝነት ያለው የሚናደድ ኃይለኛ ቁጣ ያለ ጨካኝና የሚያፈዝ	ተቀናቃኝ ሰዎችን የሚያጣላ የራሱን ሀሳብ ብቻ የሚያሳይ በክርክር የሚደሰት ተንኮለኛ ቅመኛና ምቀኛ ሆዳም	ቅመኛና ምቀኛ ገታራ በሥራ ጫና የሚያደርግ ከሰዎች ስለ ስህተታቸው ካሣ የሚቀበል ስህተቱን በብልጎት የሚሸፍን
ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰው	ሐዋ. ጳውሎስ	ያዕቆብ	ጳውሎስ	ቲቶ

③ ጥንቃቄ

ዕድል	የመጀመሪያ ጥንቃቄ	ጥንቃቄ ማነሳሳት	ጥንቃቄ መሪነት	ጥንቃቄ መጽናት
መ ል ካ ም ዕ ድ ል	በጥልቀት ማሰብ መተንተን የሚችል ቅንነት ያለው ግብ የላቀ አዕምሮ መኖር ራሱን መስዋዕት የሚያደርግ ፍጹም ችሎታ መኖር የሚጠነቀቅ እውነተኛ በዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት ታማኝ ችግሮችን የሚመረምር ሰዎችን የሚገስጽ በታማኝነት ፍጹም የሆነ	በደንብ ያልተገለጸውን ሁኔታ እርግጡን ማወቅ የሚችል ዝርዝር ሀሳቦችን የሚጠቀም የዝርዝር ማስታወቂያዎችን አስረግጦ የሚናገር ደስተኛ የሆነ የሚያስገርም ነገር ያለው ራሱን መስዋዕት ያደረገ ሰዎችን በደንብ የሚመራ ሙያ ያለው	የሚመካበት ነገር ያለ በሥራ ኃይለኛ የሆነ ተንታኝ ፍጹም ፍላጐት ያለ የመሪነት ሥልጣን ያለ ፀባይተኛ ቅልጥፍና (ብቃት) ያለው የማይታወክ የታዘዘውን የሚፈጽም ሁልጊዜ ድል አድራጊ ማስተዳደር የሚችል	ትንተና የሚችል ማደራጀት የሚችል ምሁርና የምርመራ ችሎታ ያለው ብዙ ችሎታ ያለው ፀባይተኛ ነገሮችን በዝርዝር የሚረዳ ትክክለኛ ሰው ከልቡ የሚሰራ ፍላጎት ያለው ሐሳቡን በደንብ የሚያከናውን
መ ጥ ፎ ዕ ድ ል	ስሜቱ የሚለዋወጥ ከጓደኞቹ ጋር በቀላሉ የማይገናኝ የማያምን ተጠራጣሪ ብቸኛ አስቸጋሪ ጉልበት የሌለው አሳዛኝ አደጋ የሚሠራ በሥራ ወደ ኋላ የሚያፈገፍግ (ልግምተኛ) እንቢተኛ	ብቻውን ሠርቶ የሚደክም ተች (የሚወቅስ) ራስ ወዳድ ለሰዎች አንዳንድ ጊዜ የሚጨክን (ጨካኝ) ገታራ የማይረዳ በፍርሃትና በጭንቀት ውስጥ ያለ ከሌሎች ሙያ የማይቀበል አሳዛኝ	የማይጠግብ (ሆዳም) በቀላሉ የሚያሳዝን ራሱን የሚገዳና የሚጠላ የቁጣና የቅመኝነት ልብ ያለ አፍራሽ ሌሎችን የሚበድል የሚያሳዝን ከሌሎች ጋር የማይገናኝ	አሳዛኝ በፍርሃትና በጭንቀት ራሱን የሚያዋርድ አባካኝ የሌሎችን ሥራ ሥልጣኑን ተጠቅሞ የሚያባክን ተለዋዋጭ ችኩል ተመቻችቶ ከሰዎች ጋር የማይሠራ
ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰው	ሐዋሪያ ዮሐንስ	መጥመቁ ዮሐንስ	ሉቃስ	ሐዋሪያ ዮሐንስ

④ መጽናት

ዕድል	የመጀመሪያ መጽናት	መጽናት ማነሳሳት	መጽናት መሪነት	መጽናት ጥንቃቄ
መ ል ካ ም ዕ ድ ል	ከራሱ ጋር የመስማማት ችሎታ ያለው (ግትረኛ ያልሆነ) ዝምተኛ ስሜቱን የሚገዛ የሚቀበል ትዕግሥተኛ ከሌሎች ጋር ግንኙነት የሚፈጥር ሰዎችን የሚያስታርቅ ለጋሽ በችግር ጊዜ የማይታወክ ብዙ ጓደኞች ያለው ከሌሎች ጋር ህብረት ያለው	ማህበራዊ ነገር ያለ ደስተኛ ከሌሎች ጋር በስምምነት የሚሠራ ልባም (አስተዋይ) ስለ ሌሎች የሚያስብ ከሌሎች ጋር ህብረት ያለው እምነት የሚጣልበት ደስተኛና ተጫዋች ሰዎችን የሚወድ ጨዋ ታማኝ	ከሰዎች ጋር ህብረት ያለው የሌሎችን ሀሳብ የሚሰማ ጨዋ የማያስፈራራ እርግጠኛ (ትክክለኛ) ችሎታ ያለው በመሪነት ሰዓት ወሳኝ የሆነ አስታራቂ ዝምተኛ	ጨዋ ለጋሽ በቁጣ የማይናገር ቅምን (ጠላትነትን) የማይዝ በስምምነት የሚሠራ እምነት የሚጣልበት ትክክለኛ ህብረት የሚያደርግ ቀልጣፋና ማደራጀት የሚችል ትዕግሥተኛ
መ ጥ ፎ ዕ ድ ል	በፈቃደኝነት የማይሠራ ትዕዛዝ ብቻ የሚጠብቅ ሰነፍ ቅናተኛ ታላቅ ፍላጐት የሌለው ውሳኔ የሌለው ፈሪ ብዙ በመቆየት ሕይወቱን የሚያባክን ተመልካች ማጽደቅ የማይችል በጥርጣሬ የሚቆይ	ብቻውን የሚደሰት ሰነፍ ፈሪ እርግጠኛ ያልሆነ ታላቅ ፍላጐት የሌለ በራሱ ሥልጣን የማይሠራ የተመቻቸ ጊዜ ማይጠቀም	የራሱን ሥራ ብቻ የሚወድ ፈሪ ችኩል የሚቃወምና ከሌሎች ጋር የማይሠራ በውስጡ ያለውን ቁጣ በፍጥነት የማይገልጽ ራስ ወዳድ በፈቃደኝነት የማይሠራ አደጋ በሚያመጣ ነገር የሚዋሽ	ፈሪ ራስ ወዳድ በሒሳብ ነገር ወደ ኋላ የሚል ተቺ ጤናና የራሱ የሆነ ገንዘብ ማጣት ታላቅ ጫና የሚያደርግ ፍርድን የማይቀበል
ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰው	አብርሃም	ጢሞቴዎስ	አብርሃም	ባርናባስ

ምዕራፍ ስድስት
6. የሥራ ሰው የሕይወት ታርክ እንዴት እንደሚጻፍ

1. ባለፈው ያገኘኸው አንተን የሚያሳስብ፣ ሥጦታና ፀባይ

1) የሚያሳስብ ነገር

መልስ - ነፍስን ማዳን

2) ሥጦታ

ምሳሌ - በመጀመሪያ ያወቅኸውን ሥጦታህን ማረጋገጥ

3) ፀባይ

ምሳሌ - በመጀመሪያ ያወቅኸውን ፀባይህን ማረጋገጥ

2. ያንተ ሥራ ማግኘት

ያንተ ሥራ የሕይወት ታርክ ሦስቱን ማለትም የሚያሳስብ ነገር የተኛው እንደሆነ፣ ሥጦታህንና ፀባይህን ሁሉ የሚገልጽ የተኛው እንደሆነ ለይተህ ካወቅህ በኋላ በቤተክርስቲያን ሊትሠራ የሚትችልበት ሥፍራ ጻፍ፡፡

★ የሥራ ዝርዝር

ቀን: ወር: ዓመት: ክፍል: ስም: የስልክ ቁጥር:

ቡድን	የኮምፒዩተር ቡድን	የሥራ ዓይነት	ብዛት	ምርመራ	ቡድን	የኮምፒዩተር ቡድን	የሥራ ዓይነት	ብዛት	ምርመራ
ትልቅ ክፍል		Web design	ያልተወሰነ		ልምምድ ክፍል	ልምምድ ክፍል	የቢሮ ረዳት	M.2	
		ረዳት	ያልተወሰነ			የደቀመዛሙርት ዩንቨርሲቲ ቡድን	የወረቀት አስተዳደር	M.2	
		የምስል ፕሮግራም	M.2			ሥጋንና ነፍስን የሚፈውስ የመሪዎች ኮንፋራንስ	ኮንፋራንሱ የሚያዘጋጁና የሚያደርጉ	M.3	
		ኮምፑዩተር ማብዛት ማስተዳደር	M.2			የቢሮ ረዳት	የቢሮ ረዳት	M.2	
የቢሮ አስተዳደር	የማጽናናት ቡድን	በልቅሶ ሥፍራ ማገልገል	M.1		የመንፈስ ቅዱስ ክፍል	ስለ ሌሎች የሚፀልይና የሚያስተምር ቡድን	ፀሎትና ት/ትን የሚያዘጋጅ ቡድን	M.2	
	በበቴ/ያን በአደጋ የሚያገለግሉ ቡድን	የቤተ/ያን አባላት ቁጥር የሚቆጣጥር ቡድን	M.1			የአምልኮና የፀሎት ቡድን	የአምልኮና የፀሎት ቡድን	ያልተወሰነ	
	ሥጦታ የሚያዘጋጅ	በሥራ ሰዓት የሚረዳ	M.1			በየተራ የሚፀልይ ቡድን	በየተራ የሚፀልይ ቡድን	M.3	
	አስተማሪ የሚረዳ ቡድን	የአስተማሪ ረዳት	M.3			የሰኞ ፀሎት ቡድን	ስለ መጋቢና ስለ ወንጌላዊ የሚፀልይ ቡድን	ያልተወሰነ	
	የቢሮ አስተዳደር	የቢሮ አስተዳደሪ	M.1			የወረቀት አስተዳደር ቡድን	የቢሮ ረዳት	M.1	
	የሚያውጅ ቡድን	የቤተ/ያን ዜና የሚነግር	M.2			የአዘጋጅ ቡድን	የፀሎትና የት/ት አዘጋጅ ቡድን	M.1	
	የጋብቻ ቡድን	በጋብቻ ጊዜ የሚያገለግል	M.1			የተለያየ ፀሎት ቡድን	የአምልኮ ፀሎት ቡድን	M.2	
የወንጌል ሥርጭት ክፍል	የወንጌል ሥርጭት ቡድን	የወንጌል ሥርጭት ቡድን	ያልተወሰነ		የውጭ አገር ቡድን	የውጭ አገር ቋንቋ ት/ት	የእንግሊዘኛ የመጽ/ቅ/ት/ቤ ትና የእንግሊዘኛ ክፍት ስብከት	ያልተወሰነ	
	ክፍት ስብከት የወንጌል ሥርጭት ቡድን	የቢሮ ረዳት				በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚያመልኩ የአምልኮ ቡድን	የተጋበዙ አገልጋዮች ቡድን ለምሳሌ በየእሁዱ 10፡30 ላይ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚያመልኩ	ያልተወሰነ	
	የነጋዴዎች ቡድን	የነጋዴዎች ቡድን	ያልተወሰነ			በሌሎች ቋንቋዎች	የተጋበዙ አገልጋዮች	ያልተወሰነ	

						የሚያመል ኩ ቡድን	ቡድን ለምሳሌ በየቅዳሜ 10፡30 ላይ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚያመልኩ		
	የሒክምናና የመድኃኒት ቡድን	የሒክምናና የመድኃኒት ቤት ግለሰብ	ያልተወሰነ		የተልዕኮ ክፍል	የተልዕኮ ዕቅድ	የተልዕኮ ስትራቴጅ የተማረና ጥሪ ያለ	M.3	
	የፊት ውቤትና የፀጉር አስተካካይ ቡድን	የፊት ውቤትና የፀጉር አስተካካይ ቡድን	ያልተወሰነ			የውጭ ተልዕኮ ቡድን	የውጭ ሚሽኔሪዎች አስተዳደር	M.2	
	ፕሮፕሰር	ፕሮፕሰር	ያልተወሰነ			አንድ ለአንድ የሚደረግ ተልዕኮ ቡድን	ሚሽኔሪዎችን በፀሎትና በስብከት የሚረዳ ቡድን	ያልተወሰነ	
	ምሁር	ምሁር	ያልተወሰነ			የውጭ ቋንቋ ት/ት	እንግሊዘኛየመጽ /ቅ ት/ትና የእንግሊዘኛ ክፍት ስብከት	ያልተወሰነ	
	ሙዝቀኛ ቡድን	ሙዝቀኛ ቡድን	ያልተወሰነ						
	የሕግ ቡድን	የሕግ ቡድን	ያልተወሰነ						
	የስፖርት ቡድን	የስፖርት ቡድን	ያልተወሰነ						
	በኮሌጅና በዩንቨርሲቲ ወንጌል ሥርጭት ቡድን	በኮሌጅና በዩንቨርሲቲ ወንጌል ሥርጭት ቡድን	ተማሪዎች						
እንግዳ የሚያርፍበት ክፍል	ሰዎችን በፍላን የሚያስቀምጥ ቡድን	ሰዎችን በፍላን የሚያስቀምጥ ቡድን	M.3						
	አዲስ ቤተሰብ የሚቀበል ቡድን	አዲስ ቤተሰብ የሚያስተናግድ ጨረጴዛ	M.2						
		ሻይ ቡና የሚያስተናግዱ	M.2						
		አዲስ ቤተሰብ ፎቶ ግራፍ	M.1						

<u>መግለጫ</u>

ያልተወሰነ ማለት መጠኑ የማይታወቅ ማለት ነው፡፡

M.1 አዲስ ቤተሰብ ክፍል ት/ት ተምሮ የተመረቀና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው

M.2 የልምምድ ክፍል ተምሮ የተመረቀና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው

M.3 የደቀመዛሙርት ዩንቨርሲቲ ተምሮ የተመረቀና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው

		ማንሳት			
	አዲስ ቤተሰብ የሚያገለግል ቡድን	አከባቢው የሚፈትሽ ሰው	M.2		
	አዲስ ቤተሰብ ክፍል ቡድን	እንግዳ ሲመጣ ሻይ ቡና ማዘጋጀት	M.1		
		እንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል የሚያደርግ	M.3		-
	አዲስ ቤተሰብ የሚያስተምርና የሚያገለግል ቡድን	የቢሮ ረዳት	M.2		
	አዲስ ቤተሰብ የሚያገለግል ሴሚናር ቡድን	እንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል የሚያደርግ	M.2		

የአምልኮ ክፍል አንድ	የሆሳና መዝሙር ክፍል	የአምልኮ መዝሙር ቡድን	M.1		ድኻ ህብረተሰብን የሚረዳ ቡድን	ድኻ ህብረተሰብን ለመርዳት የሚያቅድ ቡድን	ድኻ ህብረተሰብን ለመርዳት የሚያቅድ ቡድን	M.3	
	የሃሌሉያ መዝሙር ቡድን	የአምልኮ መዝሙር ቡድን	M.1			ድኻ በሽተኞችን የሚረዳ ቡድን	በሽተኞች ወደሚኖሩበት በመሄድ የሚጎበኝ ቡድን	ያልተወሰነ	
	የጌዲዎን መዝሙር ቡድን	የወንዶች ዝማሬ ቡድን	M.1			የሚያጽናና ቡድን	የሚያጽናና ቡድን	M.2	
	የሁለት ክንፍ የመዝሙር ቡድን	የአምልኮ መዝሙር ቡድን	M.1			የቤተሰብ መጽናናት ቡድን	የቤተሰብ መጽናናት ቡድን	M.2	
	የብሄር ቡድን	የሁሉ ቤተሰብ ብሄር ቡድን	ያልተወሰነ			በሕግ የሚያጽናና ቡድን	በሕግ የሚያጽናና ቡድን	M.2	
	የፍልም ሥራ ቡድን	የፍልም ሥራ ቡድን	ያልተወሰነ			የባህል ማዕከል ቡድን	ባህልን የሚያዘጋጅ ቡድን	M.2	
	ፍልም የሚያሳዩ ቡድን	ፍልም የሚያሳዩ ቡድን	M.2			የደስታ ቦታ የሚያዘጋጅ ቡድን	ድኻ ቤተሰብን የሚረዳ ቡድን	ያልተወሰነ	

	የአምልኮ ቴክኒክ ክፍል	የአምልኮ መሣሪዎች ቴክኒክ ቡድን	M.1			አምስት ዳቦና ሁለት ዓሣ የሚያከፋፍል ቡድን	የደስታ ቦታ በስተኋላ የሚነበኝ ቡድን	ያልተወሰነ	
	የአምለኮ አዳራሽ በብርሃን የሚያደምቅ ቡድን	የአምለኮ አዳራሽ በብርሃን የሚያደምቅ ቡድን	M.2		የ ት ም ህ ር ት ቡ ድ ን	የወጣቶች ህብረት	የወጣት ክፍል አስተማሪ	M.3	
	የድራማ ቡድን	የድራማ ቡድን	M.1				የወጣት ክፍል ረዳት አስተማሪ	M.2	
	ሁሉንም የአምልኮ ሁኔታ የሚቆጣጠር ቡድን	ሁሉንም የአምልኮ ሁኔታ የሚቆጣጠር ቡድን	M.1			የልጆች ህብረት	የልጆች ክፍል አስተማሪ	M.3	
የአምልኮ ክፍል ሁለት	የአምልኮ ፕሮግራም ሁኔታ የሚያስተዋውቅ ቡድን	ደረጃ 1 የአምልኮ ቡድን	M.2				የልጆች ክፍል ረዳት አስተማሪ	M.2	
		ደረጃ 2 የአምልኮ ቡድን	M.2			ከ7 ዓመት በታች የልጆች ህብረት	ከ7 ዓመት በታች የልጆች አስተማሪ	M.3	
		ደረጃ3 የአምልኮ ቡድን	M.2				ከ7 ዓመት በታች የልጆች ረዳት አስተማሪ	M.2	
		የመዝሙር አምልኮ	M.2			ከ4 ዓመት በታች የልጆች ህብረት	ከ4 ዓመት በታች የልጆች አስተማሪ	M.3	
		የምሽት ፀሎት ቡድን	M.2				ከ4 ዓመት በታች የልጆች ረዳት አስተማሪ	M.2	
	በአምልኮ ጊዜ በመባ የሚያስተናግድ ቡድን	በአምልኮ ጊዜ በመባ የሚያስተናግድ ቡድን	M.3						
	በአምልኮ አዳራሽ መቀመጫ የሚያስተካክል ቡድን	በአምልኮ አዳራሽ መቀመጫ የሚያስተካክል ቡድን	M.1						
	በሠርግ ጊዜ የሚያስተናግድ ቡድን	በሠርግ ጊዜ የሚያገለግል አገልጋይ ቡድን	M.3						
	በየዓመቱ በዓሉ የሚያስተናግድ ቡድን	በየዓመት በዓሉ የሚያገለግል አገልጋይ	M.3						
	በአምልኮ የሚተረጉም ቡድን	በአምልኮ የሚተረጉም ቡድን	M.2						

<u>መግለጫ</u>

ያልተወሰነ ማለት መጠኑ የማይታወቅ ማለት ነው፡ ፡

M.1 አዲስ ቤተሰብ ክፍል ት/ት ተምሮ የተመረቀና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው

M.2 የልምምድ ክፍል ተምሮ የተመረቀና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው

M.3 የደቀመዛሙርት ዩንቨርሲቲ ተምሮ የተመረቀና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው

	መኪና የሚቆጣጠር ቡድን	መኪና የሚቆጣጠር ቡድን	M.2		
	የመኪና ረዳት ቡድን	የመኪና ረዳት ቡድን	M.1		
	የውቤት ቡድን	የውቤት ቡድን	ያልተወሰነ		
	የውቤት ቡድን	የውቤት ቡድን	ያልተወሰነ		

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

<u>7. በሥጦታ ማስተዳደርና ማጽናናት</u>

1. **<u>የማጽናናት ውጤት</u>**

1) ያንተ የአገልግሎት ድርሻ ከሕይወት ታርክና ማመልከቻ እንዲሁም ከሥራ ስምምነት የተረዳውን ጻፍ፡፡-

---

2) አንተ ከሕይወት ታርክ የተስማማኸውን የአገልግሎት ድርሻ ለቤተክርስቲያን አስተዋውቅ፡፡

---

3) አንተ ከሕይወት ታርክ የሚትወድደው የአገልግሎት ድርሻ፣የስራ ሰዓት፣ ዕውቀት፣ የመንፈስ ቅዱስ ዕድገት ደረጃ፣ከመጀመሪያ ሥራ ልምድ፣ከማህበራዊ ሁኔታ፣ ከዜና፣ ከተለያዩ ሥጦታ፣ከከትርፍ ጊዜ ሥራ ሁኔታና ከችሎታ የመረመርከውን በአገልግሎት (በሥራ) ሊታስተዳድር የሚትችለውን ጻፍ፡፡

---

4) አንተ መንፈሳዊ ሥጦታ እንዲያድግ የተቀበልከው ሥልጠና ተናገር፡፡

---

5) በቤተክርስቲያንና በተለያዩ ሥፍራ ያደርከኸውንና ጠይቀህ በጥልቀት የተረዳኸውን መረዳት ተናገር፡፡

---

6) በዝርዝር ያወቅኸውን የተቀበልከውን ያንተን ሥራ ጻፍ፡፡

---

7) ሥራ ለማድረግ ከቢሮ የተቀበከውን ጻፍ፡፡

---

8) ከሥራ ያስቀረበትን ምክንያት በመግለጽ በሌላ ጊዜ እንዳትቀር የሚረዳህን ተቀበል፡፡

---

2. <u>ስለ ማጽናናት አዘገጃጀት</u>

ስለ ማጽናናት አዘገጃጀት ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎችን አስቀድመህ ቢትሠራ ይጠቅማል፡፡

1) ያረጋገጥከው ነገር አለህ?

---

2) የትምህርት ዓይነት ወይም ያንተ ልዩ ፀጋ ምንድን ነው?

---

3) በማህበራዊ ሥራ ቢሮ ውስጥ ምን አደረግህ? ደግሞም ምን እያደርግህ ነህ?

---

4) በቀድሞ ቤተክርስቲያ ያደረከኸው የሥራ ልምድ ካለ ጻፍ፡፡

---

5) በጣም የተደሰትክበትና ውጤት ያስገኘኸው የቤተክርስቲያን ሥራ ምንድን ነው?

---

6) ሥራን ስንት ቀንና ስንት ሰዓት ታከናውናለህ?

<u>ለምሳሌ፡-</u> በየእሁዱ ሁልጊዜ ከ3-6 ሰዓት መስራት እችላለሁ፡፡ሌላ ጊዜ ደግሞ ቅዳሜ ከ3-8 ሰዓት እችላለሁ፡፡
እንደዚሁ አንተ ሊትሠራ የሚትችልበትን ሰዓቶችን ሁሉ ቀኖችንና ሰዓቶችን ጻፍ፡፡

7) ከሥራህ ጋር የሚታወዳድረው ነገር ካለ ጻፍ፡፡ በሚትሠራበት ጊዜ የደረሰው ችግር ሌሎቹም ካሉ ዘርዝራቸው፡፡



★ መጽሐፍ አንድ

የመፅሐፍ መውጫ

መግለጫ . . . . . ገጽ

1. ምዕራፍ አንድ - አድስ ቤተሰብ የማገልገል ሥራ ምንድን ነው? 129
2. ምዕራፍ ሁለት - ለአዲስ ቤተሰብና ለአዲስ ሰው የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ቤተክርስቲያን ማስተላለፍ133
3. ምዕራፍ ሶስት - አዲስ ሰውን የሚያገለግል የአገልግሎት ምንጭ 135
4. ምዕራፍ አራት - አዲስ ሰውን የሚያገለግል የአገልግሎት ዕቅድ 137

★ መጽሐፍ ሁለት

1. በሕይወታችን ሰይጣን የገነባውን ጠንካራ ግንብ ለመደምሰስ የሚጠቅም ዘዴ 139

★ መጽሐፍ ሶስት

1. ምዕራፍ አንድ - ልምምድ ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው? 142, 143
2. ምዕራፍ ሁለት - ልምምድ የሚያደርጉትን መጥራት 147
3. ምዕራፍ ሶስት - የልምምድ ክፍል አስተዳደር ርዕስ ማውጫ 149
4. ምዕራፍ አራት - የመምህሩ ርዕስ ማውጫ 152
5. ምዕራፍ አምስት - የክፍል መሪ ርዕስ ማውጫ 155
6. ምዕራፍ ስድስት - የልምምድ ክፍል ሥርዓተ ትምህርት 156
7. ምዕራፍ ሰባት - የእያንዳንዱ ምዕራፍ የሥራ ዘዴ 158
   (ምዕራፍ 1)- 159 / (ምዕራፍ 2)- 160 / (ምዕራፍ 3)- 161 / (ምዕራፍ 3)- 161 / (ምዕራፍ 5)- 163 / (ምዕራፍ 6)- 164 / (ምዕራፍ 7)- 165 / (ምዕራፍ 8)- 166 / (ምዕራፍ 9)- 167 / (ምዕራፍ 10)- 168
8. ምዕራፍ ስምንት - የመመስከሪያ ወረቀት ፅሁፍ ዘዴ 169

★ የምስክር ወረቀት ፎርም..... 170
★ የስልጠና ቀን 171
★ በእግዚአብሔር ፊት 172
★ የመሪዎች መግጫ (ሪፖርት) 173
★ ወደ ሥልጠና ቦታ የመጡ ሰዎች ስም መቆጣጠሪያ ወረቀት መግለጫ 174
★ ወደ ሥልጠና ክፍል የሚመጡትን መመዝገቢያ ቅጽ 175
★ የዓለም ራዕይ የደቀመዛሙርት ዩንቨርስቲ የምዝገባ ወረቀት 176
★ የምረቃ ወረቀት 177

★ መጽሐፍ አራት

1. የሥራ ማመልከቻ 178
2. በሥጦታ ማስተዳደርና ማጽናናት ሠንጠረዥ 179
3. የመረመርከው ፀጋ ሥጦታ ውጤት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ጻፍ 181
4. ፀባይን ማግኘት 182



አዲስ ቤተሰብን የማገልገል ትምህርት

መግቢያ

አዲስ ቤተሰብ የማገልገል ትምህርት ማለት ወደ ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ የመጡ አዲስ ቤተሰብን የቤተክርስቲያን አንድ ቤተሰብ ሆኖ እንዲሰፍሩት ማድረግ ነው፡፡ አዲስ ቤተሰብ የማገልገል ሥራ ወንጌልን መስበክና ደቀመዛሙር ማድረግ ነው፡፡ ወደ አዲስ ቤተሰብ የሚመጡ ሰዎች በፍጥነት ከቤተክርስቲያንና ከክርስቲያኖች ጋር እንደ አንድ ቤተሰብ ተስማምቶ እንዲኖሩ የሚረዳ ትምህርት ነው፡፡ አዲስ ሰው ሲፃፍ አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው በየሳምንቱ አንድ ጊዜ ከቤተሰብ ጋር አንድ ላይ ተገናኝቶ ምግብ በመብላትና ሻይ ቡና እያሉ ህብረት ማድረግ አለበት፡፡ በየዕሁዱ ለቤተክርስቲያን አባላት ገለፃ (ማስተዋወቅ) ያስፈልጋል፡፡ አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል አገልጋይ የሥራ ነጥብ ማስፈር፡፡ በዚህ ሥራ ጊዜ አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግልበት ሥራ ሲጨርሱ ከ80% በላይ ሰዎች በቤተክርስቲያን ይኖራሉ፡፡

★ እንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ማድረግ

አዲስ ቤተሰብ የማገልገል ትምህርት ቤት እንኳን ደህና መጣችሁ!

አዲስ ቤተሰብ የማገልገል ትምህርት ማለት ወደ ቤተክርስቲያን የመጡ አዲስ ሰዎችን በደንብ እንድትተክሉ (እንዲኖሩ) መርዳት ማለት ነው፡ የሐዋሪያትን ሥራ በርናባስና ጳውሎስ አዲስ ሰውን በደንብ እንድጸኑ ወንጌል ታላቅ ተጨማሪ ነገር እንደሆነ አምነዋል፡፡ ደግሞም እኔ ሳገለግል አዲስ ሰውን ለማስፈር ዋና የጌታ ሥራ በማድረግ እንደ ጳውሎስ ሊሠራ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ሥራ በኩል ቤተክርስቲያን ዕድገት ታገኛለች፤ ደግሞም አዲስ ሰዎችን የምትተክል ቤተክርስቲያን በፍፁም ታድጋለች፡፡ እግዚአብሔር የሰጠው ዋና ሥራ አዲስ ቤተሰብን በቤተክርስቲያን ውስጥ የማጽናጽ ሥራ (አገልግሎት) ነው፡፡ ወደዚህ በረከት ቦታ እንኳን ደህና መጣችሁ!! ቤተክርስቲያን ሁሉም እኩል ነው፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሥራ የሚትሠራ ቤተክርስቲያን ጌታ ልዩ ያደርጋል፡፡ በጌታ ዘንድ 12 ደቀመዛሙርት ነበሩ፡፡ ነገር ግን ወሳኝ በሆኑ ሥራ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን፤ያዕቆብንና ዮሐንስን ከ12ቱ ደቀመዛሙርት ውስጥ ለይቶ መርጦዋል፡፡

ለመጋቢ ለወንጌላዊ ደቀመዛሙርት የማድረግ ራዕይ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ጳውሎስ እኔ ክርስቶስን እንደ ምመስል እናንተ እኔን ምሰሉ አለ፡፡ ሰዎችን ማስተማር ብቻ ሳይሆን ሕይወቱንም ጭምር አስተምረዋል፡፡ መሪ ከሕይወቱ ጌታን ማገልገል ያስፈልጋል፡፡ ደቀመዛሙርት ከሆንኩ በኃላ ደቀመዛሙርት ማድረግ እችላለሁ፡፡

★ ቤተክርስቲያን የምታድግበት 3 መሠረታዊ ነገሮች

① ወንጌልን መስበክ፡- ቤተክርስቲያን ለአዲስ ሰው ወንጌልን ሰብካ ማምጣት አለባት፤

② አዲስ ሰዎችን መንከባከብ አለባት፡፡ (ጥንቃቄ ማድረግ)

- በዚህ ጊዜ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት አይደለም
- አዲስ ሰዎች ስለ መፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ ምንነት አያውቁም፤
- ለመጀመሪያ ጊዜ ከአዲስ ሰዎች ጋር ህብረት በመፍጠር ወደ መዝናኛ ቦታዎች በመውሰድ ምግብና ሻይ ቡና ማለት ህይወታቸውን ለማረጋጋት ይጠቅማል፡፡
- ለአንድ ወር ያህል አዲስ ሰውን እያዝናኑ ከቆዩ በኃላ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ መቀበሉን ለቤተክርስቲያን መግለጽ
- መሪ ገንዘብን በአግባቡ የሚሰጥ ሰው መሆን ያስፈልጋል፡፡

- በተለይም አዲስ ሰውን የሚያገለግል ሰው ገንዘብ ያለው ሰው ቢሆን የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም በየሳምንቱ ከአዲስ ሰው ጋር የሻይ ቡና ፕሮግራም ስለሚካሄድ ይህ ደግሞ ገንዘብ ስለሚጠይቅ ነው፡፡

③ ደቀ መዛሙርን ማሠልጠን (ደቀመዝሙር ማድረግ)

ማውጫ **ገፅ**

1. ምዕራፍ አንድ - አድስ ቤተሰብ የማገልገል ሥራ ምንድን ነው? ……..
2. ምዕራፍ ሁለት - ለአዲስ ቤተሰብና ለአዲስ ሰው የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ቤተክርስቲያን ማስተላለፍ..
3. ምዕራፍ ሶስት - አዲስ ሰውን የሚያገለግል የአገልግሎት ምንጭ ……
4. ምዕራፍ አራት - አዲስ ሰውን የሚያገለግል የአገልግሎት ዕቅድ ……

ምዕራፍ አንድ
1. አዲስ ቤተሰብን የማገልገል ሥራ ምንድን ነው?

1. ቤተክርስቲያንን የሚጠቅም ሥራ በክብር የሚሠራ ሰው አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው (ኤፌ.4÷11-16)

1) የእያንዳንዳችን ሥጋ የክርስቶስ አካል ነው፡፡
2) እያንዳንዳችን የሥጋው ክፍሎች መሆናችንን በማወቅ በየክፍላችን ስንሠራ የክርስቶስን አካል ፍፁም እናደርጋለን፡፡
3) አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው ስንል ቤተክርስቲያንን ፍፁም ለማድረግና ለመትከል የሚሠራ ማለት ነው፡፡
4) አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው አዲስ ሰውን በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ቤተሰብ እንዲሆን የሚሰፍር (የሚተክል) ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ከ3 ሰው በላይ ያሉትን ለቤተክርስቲያን ማስተዋወቅ።
5) አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው ወንጌልን የሚሰብክና ደቀመዝሙርት የሚያደርግ ሰው ነው፡፡

● ኤፌ.4÷11-16

11. እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤
12-13 ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።
14. እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም፥
15. ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤
16. ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።

2. አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው የሚመች ነው

1) በመንፈስ ህፃናት የሆኑትን የሚረዳ ነው
2) በአገልግሎት መንፈስ የሚያሳድግ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን በታላቅ በረከት መንፈስ ማደግ አለባት፤ አዲስ መፅሐፍ ከማንበብ አዲስ ሰውን መማኘት ታላቅ ውጤት ነው፡፡ በአገልግሎት ማደግ ያስፈልጋል፡፡
3) አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው አዲስ ሰውን እንደ ቤተሰብ የሚያደርግ ታላቅ ወሳኝነት አለው፡፡ ለቤተክርስቲያን አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው የመጀመሪያ ዋና ሰው ነው፡፡
4) አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው እንደ ተማሪ ብዙ የመፅሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ለማግኘት ኮሌጅ ገብቶ መማር አያስፈልግም፡፡ ደረጃ 3 ደቀመዛሙርት ማሠልጠን (ደቀመዛሙርት የማድረግ) ትምህርት የተማረ ይህንን ሥራ ሊሠራ ይችላል፡፡

★ አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው ሥራ ምንድን ነው?

① አዲስ ሰውን ማስፈር (መትከል)
② መጸለይ ለምሳሌ፡- እንደ ባርናባስ
③ ሰዎችን እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ምጻአት ድረስ ማዘጋጀት ምሳሌ፡- እንደ መጥምቁ ዮሐንስ አዲስ ሰው ከመገናኘት በፊት እኔ፣ አንተ፣ አንቺ እንደ ባርናባስ መቀየር ያስፈልጋል፡፡
④ አስቀድሞ ራሱ መቀየር

⑤ አዲስ ቤተሰብን ማገልገል ስንል አዲስ ሰውን ትምህርት ማስተማር ሳይሆን አዲስ ሰውን ወደ ቤተክርስቲያን አምጥቶ በአጭር ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ አንድ ቤተሰብ ግንኙነት መፍጠር ማለት ነው፡፡ ማስተማር ብቻ እምነትን አያሳድግም፡፡ ብቻ አዲስ ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ እንድንጸና ያደርጋል፡፡

⑥ ባርናባስ የሐዋ. ጳውሎስ አስተማሪ ሳይሆን የክርስቶስ አስተዋዋቂ ሰው ነው፡፡

⑦ የቤተሰብ ሥራ የዕድገት ሥራ ነው፡፡ የቤተሰብ ሥራና የቤተክርስቲያን ሥራ ዕድገት ያለው ሥራ ነው፡፡

3. አዲስ ቤተሰብን ያገለገለ ሰው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥሩ ምሳሌ፡- የሆነው ባርናባስ

1) የማፅናናት ሰው

ባርናባስ የመፅናናት ጥሩ ቃል የሚናገር ሰው ነው፡፡

- ሐዋ.4÷36

36. የሚያጭድ ደመወዙን ይቀበላል፣ ለዘለዓለም ሕይወት የሚሆን ፍሬም ይሰበስባል፣ ስለዚህ የሚዘራውም፣ የሚያጭደውም አብረው ይደሰታሉ፡፡

2) መልካም ሰው

ባርናባስ መልካም ሰው፤ መንፈስ ቅዱስና እምነት የበዛ ሰው ነው፡፡

- ሐዋ.11÷24

24. ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትም የሞላበት ነበረና። ብዙ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመሩ።

★ መልካም ሰው ማለት

① መልካም ልብ ያለው ሰው ማለት ነው፡፡

② በልቡ ውስጥ መልካም ነገር ያስቀመጠ

③ መልካም ሥራ የሚሠራ

3) ለሐዋሪያ ጳውሎስ የሚፀልይ ሰው

- ሐዋ.9÷27

27. በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት አገባውና ጌታን በመንገድ እንዴት እንዳየውና እንደ ተናገረው በደማስቆም በኢየሱስ ስም ደፍሮ እንዴት እንደ ነገረ ተረከላቸው።

4) በፍርድ የሚሳሳት ሰው ሳይሆን የሚስማማ ሰው ነው፡፡

ፍፁም እምነት እኩል ይሆናል ፍፁም መስማማት

- ሐዋ.9÷26-27

26. ሳውልም ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ከደቀ መዛሙርት ጋር ይተባበር ዘንድ ሞከረ፤ ሁሉም ደቀ መዝሙር እንደ ሆነ ስላላመኑ ፈሩት።

27. በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት አገባውና ጌታን በመንገድ እንዴት እንዳየውና እንደ ተናገረው በደማስቆም በኢየሱስ ስም ደፍሮ እንዴት እንደ ነገረ ተረከላቸው።

5) ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው፡፡

በልብ የተሰማውን ሲያደርግ ፍሬን የሚወስድ ሰው ነው፡፡

- ሐዋ.9÷27

27. በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት አገባውና ጌታን በመንገድ እንዴት እንዳየውና እንደ ተናገረው በደማስቆም በኢየሱስ ስም ደፍሮ እንዴት እንደ ነገረ ተረከላቸው።

6) ዕውቀትን የሚቀበል ሰው ነው፡፡

ከሌሎች ሰዎች ከዘመዶች ከመጋቢዎች ከወንጌላውያን ከቤተክርስቲያን ዕውቀትን የሚቀበል ሰው ነው፡፡

- ሐዋ.4÷36

36. ትውልዱም የቆጵሮስ ሰው የነበረ አንድ ሌዋዊ ዮሴፍ የሚሉት ነበረ፥ እርሱም በሐዋርያት በርናባስ ተባለ ትርጓሜውም የመጽናናት ልጅ ነው፤

7) ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው

- ሐዋ.11÷25-26

25. በርናባስም ሳውልን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ መጣ፤

26. ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፥ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ፤ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።

★ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚሠራ ሰው ማለት

① መልካም ሰውን የሚያይ ዐይን ያለው
② ጊዜን የሚያውቅ ሰው
③ ራሱን መስዋዕት ያደርገ ሰው፤ ሥራ የሚከፋፈል ሰው
④ ሰዎችን የሚወድ (የሚቀበል)

4. አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው፤ ለእያንዳንዱ ሰው ታማኝ መሆን አለበት፡፡

1) ከእያንዳንዱ ቤተሰቡ ጋር በታማኝነት መኖር
2) ከእያንዳንዱ ሰው ጋር በተገናኘ ጊዜ ዕውቀትን የሚቀበል መሆን
3) አዲስ ሰውን የሚተክል መሆን
4) ለታማኝነቱ መስዋዕት የሚሆን ያስፈልጋል፡፡ ለሰዓት፣ለገንዘብ፣ታማኝ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ሁሉንም ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር ጥቂቱን ነገር በታማኝነት እንዲትሠጥ ይፈልጋል፡፡
5) ለታማኝነት መስዋዕት ከሆነ እያደገ ይመጣል፡፡

★ በሥራ ላይ የምታውለው ነገር፡- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸውን ነገር ውጤትህንና ልታደርገው ያሰብከውን ለጓደኞችህ በፅሁፍ አቅርበህ ከእነርሱ ጋር ተወያዩ፡፡

መልስ፡- አዲስ ቤተሰብ የሚያገለግል ሰው

1. በመጀመሪያ የተለወጠ ሰውና ግብ ያለው መሆን አለበት

2. እንደ አስተማሪ ሳይሆን ለቤተክርስቲያን የሚያስተዋውቅ
ከ3 ሰዎች በላይ ክርስቲያኖችን ደቀመዛሙር አድርጎ ለቤተክርስቲያን የሚያስተዋውቅ መሪ ነው፡፡

ፀሎት፡- ቤተክርስቲያን እንድትተከል በክብር አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው በደንብ መፀለይ አለበት፡፡

ምዕራፍ ሁለት

2. ለአዲስ ቤተሰብና ለአዲስ ሰው እንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ቤተክርስቲያን ማስተላለፍ

★ ቤተክርስቲያን አዲስ ቤተሰብ የሚባረክበት አገልግሎት የምትሰጥ ናት፡፡
የሚጎበኝ ሰው ደግሞ ወደ ቤተክርስቲያን የመምጣት ፍላጎት ያለው ሰው መሆን አለበት፡፡

1. የመስማት ልብና ጤናማ ክብር ያላቸው ክርስቲያኖች የቤተክርስቲያን ታላቅ ክብር ናቸው፡፡ የእኛ ቤተክርስቲያናችንን በተሻለ ሁኔታ ልንወድድ ያስፈልጋል፡፡ ልዩ ክብር ለመጋቢና ለወንጌል ስንሰጣቸው አዲስ ክርስቲያኖች በቀላሉ የሚተከሉበት ይሆናል፡፡
2. ቤተክርስቲያን ከክርስቲያኖች ጋር በህብረትና በስምምነት የምትሠራ ቤተክርስቲያን ሊትሆን ይገባታል፡፡
3. መጋቢንና ወንጌላዊውን በታላቅ ፍላጎት የሚወዱ ቤተክርስቲያን ሊሆን ይገባታል፡፡

   <u>የሚያከናውን ሰው ፀባይ</u>

   1) ግብ ያለው ሰው መሆን አለበት
   2) ፍላጎትና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የበዛ ሰው መሆን
4. ስለ አካባቢው ሥራ የበዛበት ቤተክርስቲያን ሊሆን ይገባታል፤ የአካባቢ ፅዳት፣ ድልድይ በተበላሸበት ቦታዎችን ከሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር የምትሠራ ቤተክርስቲያን ልትሆን ይገባታል፡፡
5. በትንሽ ቡድን ታታሪ (ጎበዝ) የሆኑት ቤተክርስቲያን

   በቤተክርስቲያን ውስጥ የክፍል ስብከት፣ ክፍት ስብከትና የመዝናኛ ክበባት ሁሉ የሚኖሩበት ሥፍራ ነው፡፡

<u>★ በቤተክርስቲያን ሊኖሩ የሚገቡ የስፖርት ዓይነቶች</u>

1. የእግር ኳስ ጨዋታ በክለብ
2. የመረብ ኳስ ጨዋታ በክለብ
3. የጠረጴዛ ተንስ ጨዋታ በግልና በቡድን

1. <u>አዲስ ቤተሰብ ስለመስፈር (ስለመትከል) የተሳሳተ አመለካከት</u>

1) አዲስ ቤተሰብ ከሸመገለ በኋላ እኔ ለቤተክርስቲያን መሰፈር አልጠቅም ማለት የተሳሳተ አመለካከት ነው፡፡ አዲስ ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ ከክርስቲያኖች ጋር ህብረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ እነርሱንም የሚያካትት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡
2) አዲስ ቤተሰብን ስለ መስፈር የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ መጋቢ፣ ወንጌላዊ ታማኝነት አለመስጠት፤ (ይህ ማለት አዲስ ቤተሰብ በቤተክርስቲያን አባልነት ውስጥ እስከሚገቡ በማለት ስፍራ አለመስጠት) አዲስ ሰውን ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጣ ክርስቲያኖች ቸልተኛ፣ ግብዞችና ትምክተኞች መሆን የለባቸውም፡፡ እነዚህን ነገሮች ክርስቲያኖች ከሕይወታቸው ማስወገድ አለባቸው፡፡ መጋቢና ወንጌላዊ በቂ መንፈሳዊ ምግብ በመስጠት ክርስቲያኖች አዲስ ሰዎችን በህብረትና በፍቅር እንዲያሰፍሩ (እንዲተክሉ) ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

   - የቤተክርስቲያን ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል መጋቢና ወንጌላዊ ከክርስቲያኖች ጋር በፍቅር ማድረግ አለባቸው፡፡
3) አዲስ ቤተሰብ ለተከላ ያለመግባቱ ምክንያት እነርሱ አዲስ ቤተሰብ ብቻ ናቸው ብሎ ማሰብ የተሳሳተ አመለካከት ነው፤ ክርስቲያኖች ታማኝ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቤተክርስቲያን በአዲስ ቤተሰብ ላይ ትኩረት ልትሰጥ ይገባታል፡፡
4) አዲስ ቤተሰብ በሳምንት ዕሁድ በአምልኮ ጊዜ ብቻ መምጣት ይበቃቸዋል ማለት የተሳሳተ አመለካከት ነው፡፡ ዕሁድ በአምልኮ ፕሮግራም ብቻ ሳይሆን በሳምንታት ውስጥ በሚደረጉ ፕሮግራሞች ላይም አዲስ የተተከሉ ቤተሰቦች እንዲመጡ መናገር ያስፈልጋል፡፡

   - ወደ ክፍት ስብከት ትምህርት ክፍል ቡድን የሚደረጉ ትምህርቶች ደቀመዛሙር ትምህርት ወዘተ . . . እንደሚመቻቸው በዕድሜ፣ በትምህርት ደረጃ አዲስ ያመኑትን (የሰፈሩትን) ቤተሰብን መጋበዝ ያስፈልጋል፡፡

2. <u>አዲስ ቤተሰብን ከመረዳት አስቀድሞ የሰዎችን ፀባይ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡</u>

1) አዲስ ቤተሰብ የቀድሞና የአሁኑ የተሳሳተ አመለካከት ብዙ ሊኖራቸው ስለሚችል
2) በስህተት መንፈስ ተይዞ ሊኖሩ ስለሚችሉ
   ጣአት መምለክ፣ ወደ ጣአት ቤት መሄድና አሸንክታብ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡
3) ከሰዎች መካከል እኔ ብቸኛ ነኝ የማለት ስሜት ውስጥ ሊኖሩ ስለሚችሉ፡፡
4) የተሰወረ (የተሸሸገ) ቁስልና ሐዘን ሊኖር ስለሚችል
5) ሰውን ሳያምኑ ለምኞት ባሪያዎችም ሆነው ራስ ወዳዶች ሆነው በገዛ ፈቃዳቸው የሚሰሩ ሊሆኑ ስለሚችሉ፡፡
6) ስለ ቤተክርስቲያን ጥላቻ አስተሳሰብ ሊኖር ስለሚችል፡፡
   ምሳሌ፡- አንዳንድ ጊዜ ከቤተክርስቲያን መልካም ያልሆነውን ዜና ሲሰሙ ቤተክርስቲያንን የመጥላት አስተሳሰብ ውስጥ ይገባሉ፡፡
7) ስለ ወደፊት እርግጠኛ ያልሆኑና በቤተክርስቲያን የማይመኩ ሊኖሩ ስለሚችሉ፡፡
8) በራሳቸው ሥልጣንና ፍፁም መውጫ በር የማያገኙ ስለሚኖሩ
9) በቤተክርስቲያን አማካኝነት እውነተኛ መፍተሔ ወንጌል ብቻ ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የሚገኝ መሆኑን ላያውቁ ስለሚችሉ፡፡ ኢየሱስ ብቻውን የሕይወት መፍትሄ የሚሰጥ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚናገኝበት ቦታ ነው፤ እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን በኩል በረከትን ይሰጣል፡፡

3. <u>አዲስ ቤተሰብን የምሰብክበት ይሰጣል፡፡</u>

1) አዲስ ቤተሰብ ብቻቸው ከኖሩ አይታገሱም ደግሞም ተስማሚነት የላቸውም፡፡
2) ቤተክርስቲያን ስፍራ አዘጋጅታ በደንብ አዲስ ቤተሰብን መምራት አለበት፡፡

3) አዲስ የመጡትን ሰዎች ቤተክርስቲያን ለክርስቲያኖች ማስተዋወቅ አለበት፡፡ በአንድ ሳምንት 3 ሰዎችን ለክርስቲያኖች ማስተዋወቅ በክፍት ስብከትና ክፍል ስብከት አማካይነት የተመሠረቱ ወይም የሰፈሩ ቤተሰብ ናቸው ብሎ ማስተዋወቅ፡፡
4) በየሳምንቱ አንድ ጊዜ ምግብና ሻይ ቡና በህብረት ማድረግ
5) ክፍት ስብከት የሚማሩትንና በቤተሰብ ስብከት የሚማሩትን አንድ ላይ ጠርቶ ህብረት ማድረግ፡፡
ይህ ሥራ በጥሩ ሁኔታ ከተሠራ 100% በቤተክርስቲያን ውስጥ ቤተሰብ ያጸናል፡፡ አንዴ በዚህ ሁኔታ ወደ ጌታ የመጡ ሰዎች ቶሎ ብለው ወደ ዓለም አይመለሱም፡፡ የመፅናት ዕድላቸው 100% ይሆናል ማለት ነው፡፡
6) የፀሎት ሰው ሁን፡፡
- በየቀኑ ፀልይ፡፡
7) በየ6ኛ ወር ተገናኝቶ አንድ ላይ በመሆን የእግዚአብሔርን ቃል የሚማሩበት ዕድል ማመቻቸት፡፡
8) በአባታዊ ልብ እስከ መጨረሻ ማገልገል፡፡ (በፍቅር ማገልገል)

4. <u>አትኩሮት መስጠትና ፍቅር ለቤተክርስቲያን መትከል ቁልፍ ናቸው</u>

1) ደብዳቤ በመፃፃፍ ተገናኝቶ ማመስገን
ምሳሌ፡- ድህረ ገፅ
2) የፀሎት ዝርዝር መጠየቅ መፀለይ፡፡ የፀሎት ዝርዝር መጠየቅ ማለት የፍቅር አትኩሮት መስጠትን ነው፡፡ በፍፁም በፀሎት የተገኘ መፍትሄ አለህ? በማለት ስለተፀለየላቸው ሰዎች መልስ አግኝተሃል? በማለት መጠየቅ ነው፡፡
3) አዲስ ቤተሰብ የሚያገለግል ሰው በመጀመሪያ የራሱን ልብ በማዘጋጀት ከሚያገለግለው ቤተሰብ ጋር መነጋገር
4) ከአዲስ ቤተሰብ ጋር ወደ ምግብ ቤት በመሄድ በመጠራራት የፍቅር ግብዣ ማድረግ፡፡
5) አዲስ ቤተሰብ ወደ ሚኖሩበት ሰፈር በመሄድ ህብረት መድረግ፡፡
6) በልደት፣ በጋብቻ፣ በሀዘን፣ በደስታ አንድ ላይ በመሆን ደስተኞች እንዲሆኑ ማፅናናት
7) አትኩሮት ያለመስጠት ኃጢአት ነው፡፡ ሰዎች ያለ ኢየሱስ ከኖሩ በሚሞቱበት ጊዜ ወደ ሲኦል ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህ አሁን ኢየሱስ እንደሚያስፈልጋቸው ልንሰብክ ያስፈልጋል፡፡
8) የጌታ ልብና የእግዚአብሔር የፍቅር ቅባት እንዲኖር አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው ሊፀልይ ያስፈልጋል፡፡

<u>★ በሥራ ላይ የምናውል፡- ከዚህ ምዕራፍ አዲስ ነገር ያወቅከውንና በሥራ ላይ የምታውለውን ነገር ከምዕራፍ ፅፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተካፈል፡፡ አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው አትኩሮት መስጠት ያስፈልጋል፡፡</u>

<u>★ ፀሎት፡- የጌታ ፍቅር እንዲበዛ አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው በደንብ መፀለይ ያስፈልጋል፡፡</u>

<u>ምዕራፍ 3</u>
<u>3. አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው የሥራ ምንጭ</u>

1. <u>አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው ልብ</u>

1) የመጋቢነት ልብ
እግዚአብሔር የሚሰጠውን ማንኛውንም ነገር እንጂ የራሱን ስልጣን ሳይገለጥ በትህትና ማስተዳደር
2) የመስዋዕትነት ልብ
እንደ ባርናባስ፣ ሐናንያና ሳጲራ (ሐዋ.4÷3 34-5÷11) ባርናባስ ንብረቶች፣ ገንዘቡን፣ ሰዓቱን (ጊዜውን) ለጌታ የሰጠው ሰው ነው፤ ነገር ግን እንደሌሎች ሐዋሪያት ሐናኒያና ሳጲራ መሬታቸውን ሸጦ ግማሽ እቤት በመሸሸግ ሁለቱም ለሞት ተዳረጉ፡፡
3) የታዛዥነት ልብ
ለመንፈስ ቅዱስ የሚታዘዝ ልብ፣ ለቤተክርስቲያን፣ ለመጋቢ፣ ለወንጌላዊ፣ ለመሪዎች የመታዘዝ ልብ ያለው ሰው ነው፡፡
4) የጠባቅነት ልብ
አዲስ ቤተሰብን ለማገልገል እንደ ሐዋ.ጳውሎስ ጠንቃቃ መሆን ያስፈልጋል፡፡
5) የጌታ ልብ ያለው

የአባቱን ልብ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ እኛ በቤተክርስቲያን አዲስ ቤተሰብ 100% እንዲሰፍር ማድረግ እንችላለን፡፡

2. <u>አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው አስተሳሰብ</u>

1) የሚያስተምር ሳይሆን የሚያገለግል አስተሳሰብ ያለው፡፡
2) በፀባይ የሚያገለግል
   ① ጥሩ ልብ ለብሶ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት አቀባበል ማድረግ
   ② በደስታና በሳቅ በትህትና ቃል መነጋገር
3) ለአዲስ ሰው የእምነት መጠን የሚናገር፡፡ (1ቆሮ.3÷2)
4) በፍፁም ተስፋውን የሚጠብቅ
   በተስፋ የሚያደርግና የማይመካ ይወድቃሉ፡፡
5) ሚስጢርን የሚጠብቅ (ወደ መንግስተ ሰማይ እስከሚሄድ ድረስ ምስጢርን የሚጠብቅ መሆን)

★ <u>ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚናገር ሰው ጥንቃቄ</u>

1. አዲስ ቤተሰብ የራሳቸውን ምስጢር ሲናገሩ አገልጋዩ እስከ መጨረሻ ድረስ ምስጢራቸውን የሚጠበቅ መሆን አለበት፡፡
2. በቤተክርስቲያን ስለ ቃል ጥንቃቄ ማድረግ ፈተና አይደለም፡፡
   <u>ለምሳሌ</u>፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ መልካም የማይናገሩ ሁል ጊዜ ክፉ ቃል የሚናገሩ ምስጢርንም የማይጠብቁ ሰዎች አፋቸውን በመርፌ መስፋት ይሻላቸዋል፡፡

★ <u>ሰውን ለመስበክ 3 መንገዶች</u>

1. ሰውን መቀበል
2. ከሰው ጋር መስማማት
3. ወሳኝ በሆኑ አስተሳሰብ መቅረብ

<u>3. እንደገና ደጋግመህ ሰምተህ የምታገለግል ሰው መሆን</u>

1) በምትናገርበት ጊዜ ፊቱን (የግለሰቡን ዓይን) በማየት መናገር በአትኩሮት መኖሩን መግለፅ
2) አትኩሮት ባለው ሁኔታ መስማማትህን በሚገልፅ ሁኔታ ምላሽ መስጠት፡፡
3) በምትናገርበት ጊዜ አማካይ የሆነ ጥያቄ መጠየቅ፡፡ በአትኩሮት መስማቱን የሚገልፅ ማለት ነው፡፡
4) ንግግርህን ከጨረስክ በኃላ ቃሉን መስማታቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄ መጠየቅ፡፡ ሰውን አስተማሪ ማድረግ ሳይሆን በስምምነት ሰምቶ ምላሽ እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡
5) በራሱ አስተያየት ለአዲስ ቤተሰብ ሁላችንም እኩል መሆናችን መናገር
6) አዲስ ቤተሰብ መልካም ቃል ባይናገሩም አትቃወማቸው
7) የመስማማት ቃል ካለን በማንቀሳቀስ መግለፅ እሽታ መስጠት ወሳኝ ነው፡፡
   <u>ውጤት</u>፡- 55% የእግዚአብሔር ቃል በምትናገርበት ጊዜ የራሳቸው ቋንቋ መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡ የአካል እንቅስቃሴ 38% በቃል መግለፅ፡፡ 70% የእግዚአብሔር ቃል አውድ ጠብቆ መናገር
   <u>ለምሳሌ</u>፡- የመዝሙር መሪ፡- በመጀመሪያ በህዝቡ ፊት ሲቀርብ ደስተኛ፣ በሳቅ በተሞላ ፈገግታ እንቅስቃሴ እያደረገ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መጠበቅ

<u>4. ስለ አዲስ ቤተሰብ ፀሎት ማድረግ</u>

1) በየቀኑ ስለ እነርሱ ፀልይ፡፡ በፀሎት ጊዜ አንተ ስለ እነርሱ መፀለያቸውን እነርሱ በመንፈሳቸው ያውቃሉ፡፡
2) በክፍት ስብከትና በክፍል ስብከት ጊዜ አንድ ላይ መፀለይ አዲስ ቤተሰብ በደንብ እንድተከሉ ያደርጋል፡፡
3) የአዲስ ቤተሰብ ችግሮችና የፀሎት ርዕሶች ወስደህ ወደ እግዚ/ር ፀልይ፡፡ ፀሎት ማለት የፈውስ አጭር መንገድ ነው፡፡ ምግብ ከመብላታችን በፊት ወደ እግዚ/ር መፀለይ ወሳኝ ነው፡፡
4) ስለ አዲስ ቤተሰብ የእግዚ/ር ድምፅ መስማት አለብን፡፡ ስንፀልይ የአዲስ ቤተሰብ ችግሮችና የፀሎት ርዕሶች መላሽ መንፈስ ቅዱስ አውቆ ይሰጣል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ዲዳ አይደለም፤ ሁል ጊዜ ቃል ይሰጣል፡፡
5) አዲስ ቤተሰብ በሰፈሩበት ቦታ ችግሮች ሲኖሩ መፆምና መፀለይ ጥሩ ነው፡፡

<u>5. አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው የሥራ ምንጭ</u>

1) ገንዘብን መስጠትና መቀበል ጥሩ አይደለም፡፡ ገንዘብ ስለሚጠፋ ሰዎች ወደ ኃላ ስለሚሉ በእግዚአብሔር እውነትና ፍቅር ገንዘብን ሳያዩ ማገላገል መልካም ነው፡፡
2) ስለችግሮቻቸው መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ችግሮቻቸውን ራሳቸው የሚፈቱበትን ዕውቀትንና ጥበብን ማካፈል፡፡
3) አዲስ ቤተሰብ ቶሎ ቶሎ መቀባበል መልካም አይደለም፡፡ ምክንያቱም አዲስ ቤተሰብ ከእግዚ/ር አስበልጦ የሚያገለግለውን ሰው ስለምያምኑ ቶሎ ቶሎ መቀበል መልካም አይሆንም፡፡
4) ራስህና አትግለፅ፡፡ ስለ ራስህ ታሪክ አትናገር በመጋቢ ላይ፣በወንጌላዊ ላይ፣በቤተ/ያን ላይ አትኩሮት እንዲያደርግ አድርግ፡፡ ሁል ጊዜ በመልካም ቃል ምላሽ ስጥ
5) በቤተክርስቲያን ውስጥ መልካም ሥራ እንዲሠሩ የምታነሳሳ ሰው ሁን፡፡

6) በቤተክርስቲያን ውስጥ ለመጋቢ፣ለወንጌላዊ ጥሩ ክብር እንዲሰጡ መናገር
7) ዘወትር በምታገለግልበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፡ ፡

★ በሥራ ላይ የምታውለው ነገር፡ - ከዚህ ምዕራፍ አዲስ የተረዳኸው ነገር ጽፈህ ከጓደኞችህ ጋር ተነጋገር፡ ፡

★ ፀሎት፡ - የአባት ልብ በመያዝ አዲስ ቤተሰብ የሚያገለግል ሰው እንዲሆን በደንብ መፀለይ፡ ፡

ምዕራፍ አራት
4. አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው የሥራ ዕቅድ

1. አዲስ ቤተሰብ የማስፈር ኮርስ





2. <u>አዲስ ቤተሰብን የሚያገለግል ሰው የሳምንቱ ሥራ አገባብ</u>

<u>1) 1ኛ ሳምንት</u>

① እንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ማድረግ
② ለአዲስ ቤተሰብ 1ኛ ምዕራፍ ማካፈል
③ ለክርስቲያኖች 3ቱን ቤተሰብ የሆኑትን ማስተዋወቅ
④ የሳምንቱን ሪፖርት ለቤተክርስቲያን መሪዎችና ለመጋቢ መስጠት
⑤ ደብዳቤ መፃፍ
⑥ በሳምንቱ በሚመቸው ቀን ተገናኝቶ ምግብ መብላትና ሻይ ቡና መጠጣት

<u>2) 2ኛ ሳምንት</u>

① ዕሁድ ጠዋት አዲስ ቤተሰብ የሚኖሩበት ቦታ ሄዶ እነርሱን ወደ ቤተክርስቲያን ማምጣት
② ለአዲስ ቤተሰብ ምዕራፍ 2ኛ ማካፈል
③ ለቤተክርስቲያን ሶስት ሰዎችን ማስተዋወቅ
④ ለቤተክርስቲያን መሪዎችና መጋቢ የሳምንቱን ሪፖርት ማቅረብ
⑤ በሳምንቱ በሚመቸው ቀን ተገናኝቶ ምግብ መብላትና ሻይ ቡና መጠጣት

<u>3) 3ኛ ሳምንት</u>

① ዕሁድ ጠዋት አዲስ ቤተሰብ የሚኖሩበት ቦታ ሄዶ እነርሱን ወደ ቤተክርስቲያን ማምጣት
② ለአዲስ ቤተሰብ ምዕራፍ 3ኛ ማካፈል
③ ለቤተክርስቲያን ሶስትን ሰዎች ማስተዋወቅ
④ ለቤተክርስቲያን መሪዎችና መጋቢ የሳምንቱን ሪፖርት ማቅረብ
⑤ በሳምንቱ በሚመቸው ቀን ተገናኝቶ ምግብ መብላትና ሻይ ቡና መጠጣት

<u>4) 4ኛ ሳምንት</u>

ከአሥር ደቂቃ በፊት በአምልኮ ሥፍራ መገናኘት
① ዕሁድ ጠዋት አዲስ ቤተሰብ ወደሚኖሩበት ሰፈር በመሄድ እነርሱን ለአምልኮ ማምጣት
② አዲስ ቤተሰብ ደረጃ ትምህርት ወደሚማሩበት ክፍል መምራት አቅጣጫውን መጠቆም
③ አዲስ ቤተሰብ ምዕራፍ አራት ትምህርት መጋቢና ወንጌላዊ ጋር አንድ ላይ በመሆን መከፋፈል፡፡
④ በምረቃ ጊዜ ምረቃ ማካሄድና ስጦታ መሰጠት፡፡

⑤ አዲስ ቤተሰብ የሚያገለግል ሰው የሥራ ውጤት ለቤተክርስቲያን መስጠት

★ መጽሐፍ መግለጫ ሁለት

ሥጋንና መንፈስን የሚፈውስ ህብረት
★ በሕይወታችን ሰይጣን የገነባውን ጠንካራ ግንብ ለመደምሰስ የሚጠቅም ዘዴ

በዚህ ጥያቄ ላይ በአንተ ሕይወት ውስጥ የሚገኙ ስህተቶችን በመርመር ፃፍ፡፡ ይህ ጥያቄ ወረቀት በአንተና በጌታ ፊት አስቀምጥ! የትኛውን ዓለም አየኸው? የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ስትጨርስ በዚህ ወረቀት ላይ የዘረዘርካቸውን ኃጢአቶችን አቃጥል፡፡

★ የግል ጥያቄዎች

ጥያቄዎችን በምትፅፍበት ጊዜ በእውነት ልትመልስ ይገባሃል፡፡ የምትመልሳቸው መልሶችም ብዙ ናቸው፡፡

1. ከሚቀጥሉት ልምድ ያንተን ድካም (ችግሮች) የሚያሳይ የትኞቹ ናቸው?

①ፀሎት ( ) ②ፆም ( ) ③የጥሞና ጊዜ ( ) ④መጠን (ልከኛ) ( )

⑤እምነት ( ) ⑥ባለስልጣንን መታዘዝ ( ) ⑦ሕብረት ( ) ⑧አስራት መስጠት ( )

⑨ደቀመዝሙር ማድረግና ማሰልጠን ( ) ⑩የመንፈስ ቅዱስ ታምራት ስራ ( )

2. ከሚቀጥለው ጥያቄዎች ውስጥ በየትኛው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ውስጥ አለህ?

①ሴሰኛ መሆን ( ) ②ዝሙት (አመንዝራ)( ) ③ግብረ ሰዶም መፈፀም ( )

④ከዘመድ ጋር ግንኙነት ማድረግ ( ) ⑤ራስ በራስ ግንኙነት ማድረግ ( ) ⑥ፍትወት ( )

⑦ከእንስሳት ጋር ዝሙት መፈፀም ( ) ⑧በስልክ በኢንተርኔት ግንኙነት መፈፀም ( )

⑨ራቆት የመሄድ ኃጢአት ( ) ⑩በሃሳብ ዝሙትን መፈፀም ( )

⑪ሌሎች ሰዎች ራቆታቸውን ዝሙት የሚያደርጉትን በዓይን በማየት ኃጢአት ( )

⑫የግንኙነት ፊልም ማየት ( )

3. ሕይወትህን እንደገና የሚመርዝ (የሚጎዳ) ልምድ የተኛው ነው?

①የማያቋርጥ እንቅልፍ ( ) ②የሌላ ሀብት መስረቅ ( ) ③መርሳት ( )

④ብዙ መጠጥ መጠጣት ( ) ⑤ጫት መቃም ( ) ⑥ግፈኛ መሆን ( ) ⑦ማጨስ ( )

⑧ቅንዓት ( ) ⑨አደንዛዥ እፅዎችን መጠቀም ( ) ⑩መዋሸት ( ) ⑪ሆዳምነት ( )

⑫ስንፍና ( ) ⑬ብዙ የኮምፒተር ውጤቶች ጌሞችን መጫወት ( ) ⑭ስንፍና ( )

⑮ትችት ( ) (16)ተስፋ መቁረጥ ( ) (17)ቁማርተኛ ( ) (18)ምኞት ( )

(19)ጥላቻ ( ) (20)የቪዲዮ ጨዋታ እየተጫወቱ ጊዜ ማባከን ( )

(21)የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያሳይ ፊልም ማየት ( ) (22)የቴሌቭዥን ሱስ መያዝ ( )

(23)ክፉ መሳደብ(ስምፍና ቃል መናገር ( ) (24)መፈተን(ክፉ ስራ ለመስራት ( )

4. ከሚቀጥለው አንተ የተለማመድከው የስሜት ኃጢአት የትኞቹ ናቸው?

①መጨነቅና ፍርሃት ( ) ②የልብ ክፋት ( ) ③ቁጣ ( ) ④መደናገር ( )

⑤ራስ ወዳድነት ( ) ⑥መወዳደር ( ) ⑦ቸልተኛ ( )

⑧ሁል ጊዜ ልክ ነኝ ማለት ( ) ⑨ትዕቢተኛ (ትምክህተኛ)( ) ⑩ሀዘን (ማዘን) ( )

⑪ምክር መፈለግ ( ) ⑫ልዩነት ማምጣት(ሰውን መለየት) ( )

⑬ሌሎች ሰዎችን ሁል ጊዜ መተቸት ( ) ⑭ሌሎች መጥላትና ቂም መያዝ ( )

⑮አለመታገስ (ትዕግስት ማጣት) ( )

5. አንተ በሕይወትህ የተለማመድካቸው መንፈሳዊ ኃጢአቶች የትኞቹ ናቸው?

①ክፉ ህልም ( ) ②በእንቅልፍ መሰቃየት (ቅዠት) ( )

③ፍርሀትና ክፉ ሀሳብ ( ) ④ሰይጣንና ጭፍራዎችን ማየት ( )

6. አንተ በሰውነትህ ጤና እንዳይኖር ያወኩ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

①ብዙ ህልም ( ) ②የሆድ ህመም ( ) ③የአካል ህመም ( )

④ድካም (አቅም ማጣት) ( ) ⑤የሥራ ብዛት ሕመም ( )

★ የቤተሰብ ጥያቄዎች

7. በአንተ ቤተሰብ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምን ማን ነው?

8. በቤተሰቦችህ መካከል ከሚቀጥለው ጋር ሕብረት የሚያደርግ አለ?

①ከኃጢያን ሐይማኖት ጋር ( ) ②ከእስልምና ሐይማኖት ጋር ( )

③ሙታን ከሚያምኑ ጋር ( ) ④የይሐዋ ምስክሮች ጋር ( )

⑤ከቡዲዝም ሐይማኖት ጋር ( ) ⑥ከሞርሞን ጋር ( ) ⑦ጣኦትን ከሚያመልኩ ጋር ( )

⑧ሌሎችን ከሚጠራጠሩ ጋር ( ) ⑨ከክርስቲያኖች ጋር ( )

9. በአንተ ቤተሰብ መካከል ከሚቀጥለው ጋር ህብረት የሚያደርግ ሰው አለህ?

①ጥንቆላ ከሚያደርግ ጋር ( ) ②ከዕድል ነጋሪዎች ጋር ( )

③የሰውን ፊት አይቶ ከሚናገሩት ጋር ( ) ④የጣኦት መስመማን በማየት ከሚናገሩት ጋር ( )

⑤የዕድሜና የልደት ወረቀት በማየት ሰውን ከሚያነሳሳው ሰው ጋር ( )

⑥ከሚጠራጠሩት ጋር ( ) ⑦ከቡዲዝም መሪዎች ጋር ( )

⑧የወደፊቱን ህይወት ከሚናገሩት ጋር ( ) ⑨ጥሞና ከሚያደርጉ ጋር ( )

⑩ክታብ ከሚከትቡ ጋር ( ) ⑪አስማትና መተት ከሚያደርጉ ጋር ( )

⑫ከዮጋ (ከሰይጣን) ጋር ህብረት ከሚያደርግ ሰው ጋር ( )

⑬የቀን መቁጠሪያ በማየት ዕድል በወረቀት ከሚያይ ሰው ጋር ( )

4. የአንተ ቤተሰብ በዳግመኛ ሐዘን ውስጥ አሉ?

①በህመም ( ) ②መግደል ( ) ③በእሳት ቃጠሎ ( ) ④ፍቺ ( )

⑤ገንዘብ ማጣት ( ) ⑥ድህነት ( ) ⑦መቅሰፍት ( ) ⑧አስገድዶ መስፈር ( )

⑨ጥላቻ ( ) ⑩የመጠጥ ሱስ ( ) ⑪የአዕምሮ ህመም ( )

⑫ከዘመድ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ( ) ⑬አደንዛዥ ዕፆችን መጠቀምና ጫት መቃም ( )

5. አንተ የምታውቀው የአያት ኃጢአት የትኞቹ ናቸው?

①ግፍ መስራት ( ) ②ማመንዘር ( ) ③የመጠጥ ሱስ ( )

④ቁማርተኛ ( ) ⑤ድህነት ( ) ⑥ነቀርሳ ( ) ⑦ስቃይ ( )

⑧የአዕምሮ ህመም ( ) ⑨ዝሙት መፈፀም ( ) ⑩መቅሰፍት (በደል)( )

⑪ ጫት መቃም አደንዛዥ ነገሮችን መጠቀም ( ) ⑫ፍቺ (ትዳር መፍታት) ( )

6. አንተ ከቤተሰቦችህና ከሌሎች ሰዎች ጋር በህፃንነት ስትኖር ከሚቀጥለው ሀሳቦች የተጎዳኸው በየተኛው ነው?

①በየጊዜው ማስፈራራት ( ) ②በዝሙት ግፍ መስራት ( )

③በስድብ ግፍ መስራት ( ) ④መጣል ( )

⑤መደብደብ (መመታት)( ) ⑥መቃወም ( )

★ የህብረት ጥያቄ

ለጥያቄው እውነተኛ መልስ ፃፍ፡፡ መልሶቹም ብዙ ናቸው፡፡

13. ከአባትህ ጋር ህብረት አለህ?

14. ከእናትህ ጋር ህብረት አለህ?

15. ከሚስትህ ጋር ህብረት አለህ?

16. ከልጆችህ ጋር ህብረት አለህ?

17. ከምትወደው ከወዳጅህ (ከቅርብ ሰው) ጋር ህብረት አለህ?

18. ከማህበረሰብህ ጋር ህብረት አለህ?

19. ከዚህ ጥያቄ ወረቀት በጣም ያልተረዳኸው ጥያቄ ምንድን ነው?

20. ቀድሞና አሁን የአንተን ሕይወት የያዘው የእርግማን ቃል አለህ?
<u>ለምሳሌ</u>፡- የአንተ ቤተሰብ ሁልጊዜ የሚረግሙት ርግማን ቃል

21. ቀድሞና አሁን በሕይወትህ ውስጥ የያዝከው መሀላና ተስፋ ቃል አለህ?

22. በለፈው ዓመታትና ዘንድሮ በህይወትህ ውስጥ የሰማከው የፍርድ ቃል አለህ?
<u>ለምሳሌ</u>፡- አንተ ሰነፍ ነህ! ፉንጋ ነህ! የማትረባ ነህ ተባለህ የተሰደብከው ቃላት በውስጥህ አሉህ?



<u>የልምምድ እርካታ የሚሰጥ መመሪያ</u>

<u>ማውጫ</u> **<u>ገፅ</u>**

1. ምዕራፍ አንድ - ልምምድ ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው? ……..
2. ምዕራፍ ሁለት - ልምምድ የሚያደርጉትን መጥራት ……
3. ምዕራፍ ሶስት - የልምምድ ክፍል አስተዳደር ርዕስ ማውጫ …….
4. ምዕራፍ አራት - የመምህሩ ርዕስ ማውጫ ……
5. ምዕራፍ አምስት - የክፍል መሪ ርዕስ ማውጫ ……..
6. ምዕራፍ ስድስት - የልምምድ ክፍል ሥርዓተ ትምህርት …….
7. ምዕራፍ ሰባት - የእያንዳንዱ ምዕራፍ የሥራ ዘዴ ……..
8. ምዕራፍ ስምንት - የመመስከሪያ ወረቀት ፅሁፍ ዘዴ ……

<u>★ ተጨማሪ (አባሪ)</u>
የጌታ ኢየሱስ ልብ በመያዝ መማር ብቻ ሳይሆን በሥራ ላይ ለማዋል ልምምድ አድርግ፡፡
ልምምድ ማድረግ ማለት እንክብካቤና መርዳት ማለት ነው፡፡
ልምምድ ስናደርግ መቀየር ይቻላል፡፡

<u>መግቢያ</u>

በሕይወት ያለ ነገር ፍፁም ያድጋል፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት ደግሞ ማደግ ያስፈልጋል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምኑ ሰዎች ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወት ዳግመኛ ተወልዶ በፍፁም ማደግ ያስፈልጋል፡፡ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሕይወት ልምምድና እንክብካቤ ሲያደርግ የተስተካከለ ዕድገት ስለሚኖር ይህንን ተለማመድ፡፡ እናት ልጅዋን እንደምታንከባክብና አባትም ልጆቹን እንደሚያንከባክብ የተዘረዘሩት እንክብካቤዎች በክርስቲያኖች ላይ ቢኖር ክርስቲያኖች በፍጥነት ያድጋሉ፡፡

ይህ መፅሐፍ የክርስቶስ ልጆችን እንዴት ማንከባከብ እንዳለበትና ውጤትስ እንዴት ማግኘት እንዳለበት የሚረዳ መፅሐፍ ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ህፃናት የሆኑ ክርስቲያኖች እንክብካቤ የሚፈልጉ ስላሉ የክርስቶስ አካል የሆኑትን ለማነፅ ይጠቅማልና መሪዎች ይህ መፅሐፍንን በዝርዝር ቢረዱ ብዙ ፍሬ እንደሚሰበስቡ ተስፋ አለኝ፡፡

ከጻሐፊው

ምዕራፍ አንድ

1. ልምምድ ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው?

የወንጌል ምስክርነት በሰይጣን መንፈስ የተያዙትን ከግዞት ነፃ የማውጣት ሥራ ማለት ነው፡፡ በመንፈሳዊ ህፃናት የሆኑትን ክርስቲያኖች በማንከባከብ ማሳደግ ማለት ነው፡፡ ሕፃን ካልተንከባከበ በሥልጣን ምንም ማደግ አይችልም፡፡ አዲስ የተወለደ ሕፃን፤ (ዳግም የተወለደ ክርስቲያን) እንክብካቤ ይፈልጋሉ፡፡ ይህንን ልምምድ ማድረግ አለብን፡፡ የአባት ልብ ልጆች (ሕፃናት) ለሆኑ ክርስቲያኖችን በቃል በፀሎት በፍቅር ማንከባከብ ነው፡፡ ደግሞም ሌሎች ሰዎች እንዲያገለግሉ ማነፅ ነው፡፡

1. መፅሐፍ ቅዱስ የሚገልፀውን ልምምድ የማድረግ (ማሠልጠን) ትርጉም ፈልገህ አግኝ፡፡

1) እናት የራስዋ ልጆቿን እንደምታሳድግ አዲስ የተወለዱ ገና በክርስትና ልጅ የሆኑ ሰዎችን ማንከባከብ ማለት ነው፡፡

- 1ተሰ.2÷6-12

6. የክርስቶስም ሐዋርያት እንደ መሆናችን ልንከብድባችሁ ስንችል÷ ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም።
7. ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትከባከብ÷ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን፤
8. እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ÷ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና።
9. ወንድሞች ሆይ÷ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን÷ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን።
10. በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለ ቅድስናና ጽድቅ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድን÷ እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ፤
11-12 ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጸናን እየመሰከርንላችሁም÷ አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደ ሆንን ታውቃላችሁና።

2) አስተማሪ ከተማሪዎች ጋር ህብረት እንደሚያደርጉ ሳይሆን ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ወስደው የራሳቸው ልጅ አድርገው እንደሚያሳድጉ ነው፡፡

- ቆሮ.4÷14

14. እንደምወዳችሁ ልጆቼ አድርጌ ልገሥጻችሁ እንጂ ላሳፍራችሁ ይህን አልጽፍም።
ወላጅ አልባ ሕፃናትን በማንከባከብ ህብረት ልናደርግ ያስፈልጋል፤

ምሳሌ፡- ሐዋ.ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በእምነት ወልዶ አሳድጓል፤ ቀድሞ የተለወጠ ሰው ሌሎችን መለወጥ ይችላል፡፡ በፍቅር ልብ ልምምድ ያደረገ ሰው የፍቅር ስሜት ይገባዋል፡፡ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልብ በየአንድ ሰዓት ከፀለየክ በኋላ ወደ መማሪያ ክፍል መግባት አለብህ፡፡

ልምምድ የሚያደርጉ ተማሪዎችን አስተማሪው ከራሱ ትከሻ ላይ ማውረድ የለበትም፤ ይህ ማለት ገና በትምህርት ላይ ተማሪዎች ስላሉ የመምህሩን ፈለግ ከተከተሉ የመምህሩን ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ፡፡ በሌላ ቋንቋ ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እዳስተማራቸው በሕይወቱ መጨረሻ የጌታ የኢየሱስ ሥራ ደቀመዛሙርቱ እንደተረከቡ ማለት ነው፡፡

ለዓሣማ ምግብ የሚሰጠውን ሰው ዓሣማው ያውቃል፡፡ እንደዚሁም ለሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ዕውቀት ስናስተምራቸው የሚቀበሉና የሚያውቁ ሰዎች ልክ እንደ ዓሣማ ያውቃሉ ማለት ነው፡፡ በአባታዊ ልብና ፍቅር ተማሪዎችን ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ልምምድን የተቀበለ ሰው ሌሎችን ማለማመድ ይችላል፤ ፍቅርን የተቀበለ ሰው ሌሎችን መውደድ ይችላል፡፡

2. ልምምድ ለሚያደርገው ሰው የሚያስፈልግ ነገር ምን እንደሆነ ፈልገህ አግኝ፡፡

1) በክርስትና ህፃናት የሆኑትን ለማነፅ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

ሁሉንም ሰዎች ለማሠልጠን (ለማለማመድ) መዘጋጀት፡፡ ልምምድ ለማድረግ የሚፈልጉትን ጠንቋይንም ቢሆን ማስተማር አለብን፡፡ በቃልና በመንፈስ ቅዱስ (በፀሎት) ሚዛናዊ በማድረግ ልምምድ ማድረግ (ማሰልጠን) ያስፈልጋል፡፡

- ቆላ.1÷28

28. እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው።

2) ሐዋ.ጳውሎስ የተሰሎንቄን ቤተክርስቲያን እንዴት አሠለጠነ?

የተሰሎንቄን ቤተክርስቲያን በሚያሠለጥንበት ጊዜ (ልምምድ በሚያደርግበት ጊዜ) እርሱን

- በማፅናናት

- በማበረታታትና
- እነርሱን በመለመን በፍቅር አደረገ፡፡
  - 1ተሰ.2÷11

    11-12 ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጸናን እየመሰከርንላችሁም፥ አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደ ሆንን ታውቃላችሁና።

3) ሐዋሪያ ጳውሎስ እንዲያሠለጥን ያደረገበት ምክንያት ምንድን ነው? (1ቆሮ.4÷14-16) እንደ መንፈሳዊ አባት በወንጌል እነርሱን ስለ ወለደላቸው፡፡ እንደ አባት ስለሆነ የእርሱን ምሳሌ ተከተሉ፡፡

4) እግዚአብሔር ሙሴን ከእስራኤላዊያን መካከል የራሱን ሥራ እንዲሠራ የመረጠበት ምክንያት ምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ሥራ ወደፊት የሚረከቡ ሰዎችን እንዲያንከባክብ ፈልጎ ነው፡፡

- ዘኁ.11÷11-15

11. ሙሴም እግዚአብሔርን አለው። ለምን በባሪያህ ላይ ክፉ አደረግህ? ለምንስ በፊትህ ሞገስ አላገኘሁም? ለምንስ የዚህን ሕዝብ ሁሉ ሸክም በእኔ ላይ አደረግህ?
12. አንተ ለአባቶቻቸው ወደ ማልህላቸው ምድር አደርሳቸው ዘንድ። ሞግዚት የሚጠባውን ልጅ እንድታቀፍ በብብትህ እቀፋቸው የምትለኝ፥ በውኑ ይህን ሕዝብ ሁሉ እኔ ፀነስሁትን? ወለድሁትንስ?
13. በፊቴ ያለቅሳሉና። የምንበላውን ሥጋ ስጠን ይላሉና ለዚህ ሕዝብ ሁሉ የምሰጠው ሥጋ ከወዴት እወስዳለሁ?
14. እጅግ ከብዶኛልና ይህን ሁሉ ሕዝብ ልሸከም አልችልም።
15. እንዲህስ ከምታደርግብኝ፥ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፥ በእኔ ላይ የሚሆነውን መከራ እንዳላይ፥ እባክህ፥ ፈጽሞ ግደለኝ።

5) ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ያዘዘው ነገር ምንድን ነው? ወደ ሁሉም ወገን ሄደው ደቀመዛሙርት እንዲያደርጉ እንዲያስተምሩና እንዲጠብቁ ነው፡፡

- ማቴ.28÷18-20

18. ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።
19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

3. ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ደቀመዛሙርት ያደረገበት ዘዴን ተወያዩ

1) አንድ ላይ በመኖር፡፡

- ማር.3÷13-15

